# ለምጽአቱ ተዘጋጅ

1ኛ እና 2ኛ ተሰሎንቄ

ዳግም ምጽአት የመወያያ ንድፈ-አሳብ

ሳይሆን፥ ልንኖርበት የሚገባ እውነት ነው!

ጸሐፊ፡ ዋረን ደብልዩ ዌርዝቢ

ትርጉም፡ በግርማዊ

እርማት፡ ዓቢይ ደምሴ

Copyright © 1995 by SIM, Addis Ababa, Ethiopia. Originally published in English under the title of BE READY. Copyright © 1979 by SP Publications, Inc., Wheaton, Illinois, U.S.A. All rights reserved.

# መግቢያ

በ1ኛ እና 2ኛ ተሰሎንቄ ውስጥ የሚገኙ ሁለት ዓበይት አሳቦች ልቤን በሐሤት ይሞሉታል። እነርሱም፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአትና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ናቸው።

በእነዚህ ሁለት መልእክቶች፥ ጳውሎስ ትንቢታዊውን መልእክት ከተግባራዊ ሕይወት ጋር ያወዳድረዋል። ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስን መመለስ የሚያንጸባርቀው መሠረታዊ ትምህርት (ዶክትሪን)፥ ከትምህርትነት ደረጃም ልቆ፥ የሕይወታችንና የአብያተ ክርስቲያናት አገልግሎታችን አንቀሳቃሽ ኃይል ስለመሆኑ አጥብቆ ያምናል።

ክርስቶስ በቶሎ ይመጣል። አንተም ለምጽአቱ ተዘጋጅ!

ዋረን ደብልዩ ዌርዝቢ።

# ማውጫ

መግቢያ

1. የቤተ ክርስቲያን ልደት (1ኛ ተሰሎንቄ 1፡1) ............... 1

2. ቤተ ክርስቲያን እንዴት ልትሆን ይገባል?
(1ኛ ተሰሎንቄ 1፡1-10) ........................... 14

3. ሕፃኑን በእንክብካቤ እንዲያድግ መርዳት
(1ኛ ተሰሎንቄ 2፡1-12)............................ 25

4. አዲስ አማኞች በማደግ ላይ እያሉ የሚያጋጥማቸው ጫና
(1ኛ ተሰሎንቄ 2፡13-20) ......................... 36

5. ጸንተህ ቁም! (1ኛ ተሰሎንቄ 3፡1-13) ............... 47

6. አባትህን እንዴት ደስ ታሰኘዋለህ? (1ኛ ተሰሎንቄ 4፡1-12) ... 59

7. የምጽአቱ መጽናኛ (1ኛ ተሰሎንቄ 4፡13-18).............. 70

8. አታንቀላፉ! (1ኛ ተሰሎንቄ 5፡1-11).................. 81

9. ምእመናን ሁሉ እንደ አንድ ቤተሰብ አባላት
(1ኛ ተሰሎንቄ 5፡12-28).......................... 93

10. ክፉዎች ዕረፍት የላቸውም (2ኛ ተሰሎንቄ 1፡1-12) ...... 106

11. የእግዚአብሔር የጊዜ ሰሌዳ (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡1-12)...... 119

12. እውነት ብቻ (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡13-3፡5) ............. 132

13. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ሥርዓት
(2ኛ ተሰሎንቄ 3፡6-18)........................... 143

# የሐዋርያት ሥራ 17፡1-15

«በአንፊጶልና በአጶሎንያም ካለፉ በኋላ ወደ ተሰሎንቄ መጡ፥ በዚያም የአይሁድ ምኲራብ ነበረ። ጳውሎስም እንደ ልማዱ ወደ እነርሱ ገባ፥ ሦስት ሰንበትም ያህል ከእነርሱ ጋር ከመጻሕፍት እየጠቀሰ ይነጋገር ነበር ሲተረጕምም ክርስቶስ መከራ እንዲቀበልና ከሙታን እንዲነሣ ይገባው ዘንድ እያስረዳ፡- ይህ እኔ የምሰብክላችሁ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው ይል ነበር። ከእነርሱም አንዳንዶቹ ተረድተው፥ ከሚያመልኩም ከግሪክ ሰዎች ብዙ ከከበሩትም ሴቶች ጥቂቶች ያይደሉ፥ ከጳውሎስና ከሲላስ ጋር ተባበሩ። አይሁድ ግን ቀንተው ከሥራ ፈቶች ክፉ ሰዎችን አመጡ ሕዝብንም ሰብስበው ከተማውን አወኩ፥ ወደ ሕዝብም ያወጡአቸው ዘንድ ፈልገው ወደ ኢያሶን ቤት ቀረቡ ባላገኙአቸውም ጊዜ ኢያሶንንና ከወንድሞች አንዳንዶችን ወደ ከተማው አለቆች ጐተተው፡- ዓለምን ያወኩ እነዚህ ወደዚህ ደግሞ መጥተዋል፥ ኢያሶንም ተቀብሎአቸዋል እነዚህም ሁሉ፡- ኢየሱስ የሚሉት ሌላ ንጉሥ አለ እያሉ የቄሣርን ትእዛዝ ይቃወማሉ ብለው ጮኹ። ሕዝቡና የከተማውም አለቆች ይህን ነገር በሰሙ ጊዜ ታወኩ፥ ከኢያሶንና ከሌሎቹም ዋስ ተቀብለው ለቀቁአቸው።

«ወዲያውም ወንድሞች ጳውሎስንና ሲላስን በሌሊት ወደ ቤርያ ሰደዱአቸው፥ በደረሱም ጊዜ ወደ አይሁድ ምኲራብ ገቡ እነዚህም በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና፥ ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ። ስለዚህም ከእነርሱ ብዙ፥ ከግሪኮችም የከበሩት ሴቶችና ወንዶች ጥቂት ያይደሉ፥ አመኑ። በተሰሎንቄ ያሉት አይሁድ ግን ጳውሎስ በቤርያ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ሰበከ ባወቁ ጊዜ፥ ወደዚያው ደግሞ መጡና ሕዝቡን አወኩ። በዚያን ጊዜም ወንድሞቹ ወዲያው ጳውሎስን እስከ ባሕር ድረስ ይሄድ ዘንድ ሰደዱት ሲላስና ጢሞቴዎስም በዚያው ቀሩ። ጳውሎስን የሸኙት ግን እስከ አቴና አደረሱት፥ እንደሚቻላቸውም በፍጥነት ወደ እርሱ ይመጡ ዘንድ ወደ ሲላስና ወደ ጢሞቴዎስ ትእዛዝ ተቀብለው ሄዱ።»

# 1ኛ ተሰሎንቄ 1፥1

«ጳውሎስና ስልዋኖስ ጢሞቴዎስም፥ በእግዚአብሔር አብ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም ወደምትሆን ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን፤ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስም ጸጋ ሰላምም ለእናንተ ይሁን።

# - 1 -

# የቤተ ክርስቲያን ልደት

አንድ አባት ልጁን ለማዝናናት በመሻት፥ በከተማዬቱ ውስጥ ወደሚገኘው ታላቅ ቤተ-መዘክር ወሰደው። ልጁ ግን ለሁለት ሰዓታት ያህል «አፍ ...» እያለ ከማጉረምረም በስተቀር አንዳችም የአድናቆት ቃል አልተነፈሰም። በመጨረሻም በጭንቀት ተውጦ፥ «አባባ፥ እስኪ እውነተኛ ነገሮች ወዳሉበት ስፍራ እንሂድ!» አለው።

አንዳንድ ሰዎችም መጽሐፍ ቅዱስን በሚያነቡበት ወቅት የዚህ ዓይነት ስሜት ያድርባቸዋል። የሳይንስ ምጥቀት ለገነነበት ለዛሬው ሕይወት ትርጉም የማይሰጡ ጥንታዊ ዕቃዎች በተሰባሰቡበት ሃይማኖታዊ ቤተ-መዘክር ውስጥ የተቀመጡ ይመስላቸዋል። ይሁንና በእጅጉ ተሳስተዋል። እስከ ዛሬ ከታተሙት መጻሕፍት፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ ለሕይወታችን ትርጉም የሚሰጥና ከሕይወታችን ጋር የሚዛመድ አይገኝም። ይህንን ስንገነዘበው ደግሞ፥ ለዓመታት «እጅግ አነቃቂ ፕሮፌሰር» የሚል መጠሪያ የተሰጣቸው ዊልየም ሊዮን ፌልፕስ፥ «የኮሌጅ ትምህርት ያልታከለበት የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከሌለበት የኮሌጅ ትምህርት እንደሚበልጥ አምናለሁ» ማለታቸው የሚያስደንቀን አይሆንም።

በመቀጠልም እጅግ ቀደምት የሆኑትን ሁለቱን የጳውሎስ መልእክቶች፥ ማለትም 1ኛ እና 2ኛ ተሰሎንቄ ልናጠና ነው። (የገላትያ ሰዎች መልእክት ከእነዚህ በፊት ተጽፎአል ተብሎ ይገመታል)። እነዚህ ሁለት መልእክቶች የተጻፉት፥ ከክርስትና እምነታቸው ጋር ከማይስማማ ዓለም ጋር፥ የሕይወት ግብግብ ገጥመው ለነበሩ እውነተኛ ሰዎች ነበር። አንተና እኔም ከእነዚህ ሰዎች ጋር በቀላሉ ልንተባበር እንችላለን፤ ምክንያቱም በተመሳሳይ ዓለም ውስጥ ስለምንኖርና በርካታ ተመሳሳይ ችግሮችን ስለምንጋራ ነው። እነዚህ ሁለት ደብዳቤዎች የተጻፉበትን ዳራ (የኋላ ታሪክ)፥ የጊዜውን አስከፊነትና ያስገኙትን በረከት ከልብ ካጤንከው ከዘመኑ የክርስትና ሕይወት ጋር የሚዛመዱ ተግባራዊ መልእክቶች መሆናቸውን በቀላሉ ትረዳለህ።

## ዳራው (የኋላ ታሪክ)

ተሰሎንቄን መጐብኘት ይቻላል፤ የጉዞ ወኪሎችም ተሰሎኒቂ ይሏታል። (ሰሎንቃ ተብላም ትታወቅ ነበር።) ይህች ከተማ በዘመናዊቷ ግሪክ ውስጥ የምትገኝ፥ የኢንዱስትሪና የንግድ እንቅስቃሴ የሚጧጧፍባት ስትሆን፥ በሕዝብ ብዛትም ከአቴንስ ቀጥሎ ሁለተኛውን ማዕረግ ጨብጣለች። በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት፥ ለኅብረት መንግሥታቱ የጦር ሰፈር ሆና ያገለገለች ሲሆን፥ በሁለተኛው የዓለም ጦርነትም በጀርመን ወታደሮች በመወረሯ በውስጧ የሚገኙት ስልሳ ሺህ የሚሆኑ አይሁዶች ለስደትና ለጭፍጨፋ ተጋልጠዋል።

ተሰሎንቄ ጥንታዊት ከተማ ስትሆን፥ የመጀመሪያ ስያሜዋም «ተርማ» የሚል ነበር። ይህም በአቅራቢያዋ ከሚገኙ በርካታ የፍል ውኃ ምንጮች አንጻር የተሰጣት ስም ነበር። በ315 ዓ.ዓ. ደግሞ ተሰሎንቄ ተብላ ተሰየመች፤ ይህም ከታላቁ እስክንድር እህት የተወሰደ ስም ነበር። በ168 ዓ.ዓ. ሮም መቄዶንያን ስትወር፥ ከተማዪቱ የጠቅላይ ግዛቱ ርዕሰ-ከተማ ለመሆን በቃች። በጳውሎስ ዘመን ሁለት መቶ ሺህ ሰዎች የሚኖሩባት ሲሆን፥ አብዛኛዎቹ ግሪኮች ነበሩ፤ በርካታ ሮማውያንና አነስተኛ ቁጥር የነበራቸው ጠንካራ የአይሁድ ማኅበረሰቦችም ነበሩ። ዛሬ ሦስት መቶ ሺህ ሕዝብ የሚኖርባት ሲሆን፥ በአዲስ ኪዳን የሐዋርያት የአገልግሎት ዘመን ከነበሩትና እስካሁንም ካልጠፉት ጥቂት ከተሞች አንደኛዋ ነች።

ሐኪሙ ሉቃስ ጳውሎስ እንዴት ወደ ተሰሎንቄ እንደመጣና ቤተ ክርስቲያኗም እንዴት እንደተመሠረተች ገልጾአል (የሐዋ. 17፡1-15)። ጳውሎስ ወደ መቄዶንያ የሄደው፥ «ወደ መቄዶንያ ተሻገርና እርዳን» ይል የነበረውን የአንድ ሰው «ጥሪ» ተከትሎ ነበር (የሐዋ. 16፡9)። ጳውሎስ፥ ሲላስ፥ ሉቃስና ጢሞቴዎስ በመጀመሪያ ወደ ፊልጵስዩስ ደርሰው ሊድያንና ቤተሰቦችዋን ወደ ክርስቶስ መሩ፤ በዚያም ቤተ ክርስቲያን መሠረቱ። ጳውሎስና ሲላስ በውሸት ክስ ታሰሩ፤ ግርፋትም ደረሰባቸው። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ነፃ አወጣቸውና የወኅኒ ቤቱን ጠባቂና ቤተሰቡን በክርስቶስ ወደሚገኝ እምነት መሩአቸው።

አዳዲሶቹን አማኞች ካበረታቱአቸው በኋላ፥ ጳውሎስና ጓደኞቹ ፊልጵስዩስን ለቀው (ሉቃስ ለጥቂት ጊዜ ሊቆይ ቢችልም) ዒላማቸው ወደነበረችው ወደ ተሰሎንቄ ገሰገሱ። አንፊጶልንና አጶሎንያንን አልፈው ወደ ተሰሎንቄ ሄዱ (የሐዋ. 17፡1)። ይህንንም ያደረጉት በእነዚህ ከተሞች

ውስጥ ለነበሩት ሰዎች ስላልገደዳቸው ሳይሆን፥ የጳውሎስ ዕቅድ በታላላቅ ከተሞች ውስጥ ለማገልገል ሆኖ፥ አማኞች ደግሞ በአቅራቢያቸው የሚገኙትን ትናንሽ ከተሞች በተራቸው እንዲደርሱ በመፈለጉ ነው። ከፊልጵስዩስ እስከ ተሰሎንቄ የመቶ ስልሳ ኪሎ ሜትር ማይሎች ርቀት ነው።

የጳውሎስ ተልዕኮ ወንጌልን ወደ አሕዛብ ማድረስ ቢሆንም (የሐዋ. 9፡15፤ ኤፌ. 3፡1-12)፥ ሁልጊዜም አገልግሎቱን በአይሁዶች መካከል ይጀምር ነበር። የመጀመሪያ አጥቢያው ምኩራብ ሲሆን፥ ይህም የብሉይ ኪዳን ሕግ የሚታወቅበትና የሚከበርበት ስፍራ ነበር። ቢያንስ ስደት እስከሚደርስበት ድረስ፥ በምኩራብ ውስጥ የሚሰባሰቡ አይሁዶች በሚገባ ይሰሙት ነበር። በተጨማሪም፥ ሁልጊዜም «እግዚአብሔርን የሚፈሩ» አሕዛብ በምኩራብ ውስጥ ስለሚገኙ፥ በእነርሱ አማካኝነት አረማዊ ለነበሩት አሕዛብ ምስክርነት ሊጀምር ይችል ነበር። ከዚህም በተጨማሪ፥ ጳውሎስ ለአይሁዶች ይሰማው የነበረው ልዩ መጨነቅ (ሮሜ 9፡1-3 እና 10፡1)፥ እንደዚሁም «በመጀመሪያ ለአይሁዶች» የሚለው ታሪካዊ መመሪያ (ሮሜ 1፡16) አንድ ላይ ተዳምሮ፥ እርሱና ተባባሪዎቹ የሚሰጡትን አገልግሎት በምኩራብ ውስጥ እንዲጀምሩ አድርጓቸዋል።

ጳውሎስ በምኩራብ ውስጥ ያካሂድ የነበረውን ይፋዊ አገልግሎት ለመግለጽ ሉቃስ የተጠቀመባቸውን ቃላት ማጥናት አስፈላጊ ነው (የሐዋ. 17፡2-3)። «መነጋገር» ማለት «ጥያቄና መልስ እየተለዋወጡ መወያየት» ማለት ነው። ምናልባትም «ምልልስ» የሚለው ቃል ሊተካው ይችላል። «እያስረዳ» ማለት «እየገለጸ» ማለት ነው። ጳውሎስ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ አንድ ክፍል ያነብና ከኢየሱስ ክርስቶስና ከወንጌሉ ጋር በማዛመድ ትርጉሙን ይገልጽ ነበር። «እየጠቀሰ» የሚለው ደግሞ ጳውሎስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ቅደም ተከተሉን በጠበቀ ሁኔታ፥እንዴት እንደሚገጣጠሙ ለማሳየት የተጠቀመበትን ዘዴ የሚያመልክት ነው። እንደዚሁም፥ «መስበክ» ማለት «ማወጅ፥ ማስታወቅ» ማለት ነው። ጳውሎስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማስተማር ብቻ ሳይሆን፥ ክርስቶስን በማወጅ፥ አድማጮቹ በእምነት እንዲከተሉት ይገፋፋቸው ነበር።

እኛም ከጳውሎስ የወንጌል አቀራረብ በርካታ ቁም-ነገሮች ልንገበይ እንችላለን። የእግዚአብሔርን ቃል በመጠቀም፥ ስለ እግዚአብሔር ልጅ ያውጅ ነበር። ሕዝቡ ከነበረበት ተጨባጭ ሁኔታ በመነሣት፥ ወደ ወንጌሉ እውነት መራቸው። (ጳውሎስ ለአሕዛብ በሰበከ ጊዜ፥ ስለ ብሉይ ኪዳን

መጻሕፍት የሚያውቁት አልነበራቸውምና የእግዚአብሔርን የፍጥረት ታሪክ አቀረበላቸው። የሐዋ. 14፡8-18 እና 17 ከቁጥር 16 ጀምሮ ተመልከት።)

በምኩራብ ውስጥ ለሦስት ሰንበቶች ሲያገለግል፥ ጌታም በኃይል ይሠራ ጀመር። ጥቂት ከፍተኛ ማዕረግ ያላቸውን ሴቶች ጨምሮ፥ በርካታ ሰዎች በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ዳኑ። ይሁንና የማያምኑ አይሁዶች አገልግሎቱን መቃወም በመጀመራቸው፥ ጳውሎስና አጋሮቹ ከተማዪቱን ለመልቀቅ ተገደዱ። ሰባ ኪሎ ሜትር ርቃ ወደምትገኘው ቤርያ ተጓዙና መልካም አገልግሎት ለመስጠት ቻሉ፤ ዳሩ ግን በተሰሎንቄ የነበሩ አይሁዶች ተከትለዋቸው መጡና አወኩአቸው። በዚህ ጊዜ ነበር ጳውሎስ ወደ አቴና፥ ከዚያም ወደ ቆሮንቶስ ያመራው።

ለመሆኑ ጳውሎስ በተሰሎንቄ ለምን ያህል ጊዜ አገለገለ? ደግሞስ «ሦስት ሰንበት» (የሐዋ. 17፡2) የሚለው አገላለጽ የሚያመለክተው በጠቅላላው ሦስት ሳምንታት ብቻ ማገልገሉን ነው፥ ወይስ በምኩራብ ውስጥ ብቻ ለሦስት ሳምንታት ካገለገለ በኋላ በሌላ ስፍራ ማገልገል መቀጠሉን ነው? ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ከምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ሁለት ጊዜ ስጦታ እስኪላክለት ድረስ (ፊልጵ. 4፡16)፥ በተሰሎንቄ እንደነበረ እናውቃለን። በተጨማሪም፥ ጳውሎስ ራሱን ለመርዳት ድንኳን የመሥራቱን ሙያ ያከናውን ነበር (1ኛ ተሰ. 2፡9 እና 2ኛ ተሰ. 3፡6-15)።

ጳውሎስ በተሰሎንቄ ውስጥ የቆየው ለሦስት ሳምንታት ብቻ ከሆነ፥ ለአዳዲስ ክርስቲያኖች ከፍተኛ መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አስጨብጧል ማለት ነው። እነዚህን ሁለት መልእክት ስናጠና፥ ጠቅላላው ዐቢይ የክርስትና እምነት ትምህርት ከሞላ ጐደል እንደተጠቀሰ እንረዳለን።

ጳውሎስ በተሰሎንቄ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ባያገለግልም ቅሉ፥ ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት የሚያበቃ ጽኑ መልእክት ትቶላቸው ነበር። ጳውሎስ ወደ አቴንስ በሚሄድበት ጊዜ፥ ጢሞቴዎስና ሲላስ በዚያ ቀርተው አዲሲቱን ቤተ ክርስቲያን እንዲረዱና ከዚያ በኋላ እንዲደርሱበት ነገራቸው። ዳግም በተገናኙ ጊዜም፥ ክርስቲያኖቹን እንዲያጽናናና ለእነርሱ ያለውን ፍቅርና ሸክም እንዲያረጋግጥላቸው፥ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን መልሶ ወደ ተሰሎንቄ ላከው (ጳውሎስ ሁለት ጊዜ ወደዚያ ለመመለስ ሞክሮ ሳይሳካለት ቀርቷል - 1ኛ ተሰ. 2፡17-18)። ጢሞቴዎስ ከጳውሎስ ጋር በቆሮንቶስ ከተማ ዳግም በተገናኘና ስለአዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን ዘገባ ባቀረበ ጊዜ ነበር ጳውሎስ 1ኛ ተሰሎንቄን የጻፈው። ትንሽ ቆየት ብሎ ደግሞ 2ኛ ተሰሎንቄን ጻፈ።

ይህ ሁሉ ሥረ መሠረት በርካታ ጠቃሚ ትምህርቶችን ያስተምራል። ያለጥርጥር እግዚአብሔር በሰዎች ይጠቀማል። እግዚአብሔር የተሰሎንቄን ሰዎች በወንጌል ለመድረስ መልእክተኞቹ ያደረገው፥ የተለወጠውን አይሁዳዊ የሃይማኖት መምህር (ራቢ) እና ጓደኞቹን፥ እንደዚሁም ከፊል አይሁዳዊና ከፊል አሕዛባዊ የነበረውን ወጣት እንጂ፥ መላእክትን አልነበረም። ዛሬም እግዚአብሔር በሰዎች ይጠቀማል ምሪቱን የሚታዘዙና መልእክቱን የሚጋሩትን ሰዎች አብዝቶ ይጠቀምባቸዋል።

ሁለተኛው ትምህርት፡- ዛሬም ቢሆን ወንጌሉ «የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን» መሆኑን (ሮሜ 1፡16) ማሳየት ነው። በተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት በዓመታት የሚቆጠር ጊዜ አልወሰደም። የእግዚአብሔር ኃይል ሕይወትን በመለወጡ ረገድ ብርቱ ነበርና ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተ። ጳውሎስ ወንጌሉ ወደ እነርሱ የደረሰው፥ «በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ . . . እንጂ በቃል ብቻ» እንዳልሆነ ያስታውሳቸዋል (1ኛ ተሰ. 1፡5)።

በመጨረሻም፥ ዛሬም ሰይጣን ወንጌሉን እንደሚቃወምና የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደሚያሳድድ ልብ ልንል ይገባል፤ ይሁንና ስደት ወደ ዕድገት የሚያደርስ አንደኛው መንገድ ሊሆን ይችላል። እነዚህን መልእክቶች በምናጠናበት ወቅት፥ መከራን የሚቀበሉ ቅዱሳን በክርስትና ሕይወትና ምስክርነት አበሳዎች ውስጥ እያለፉ ሲጓዙ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚያበረታታቸውና እንደሚያጽናናቸው እንመለከታለን።

## ሽከሙ

ጳውሎስ እነዚህን ሁለት መልእክቶች ለምን ጻፈ? በመጀመሪያ፥ ለወዳጆቹ ፍቅሩንና ሸክሙን ለመግለጽ ይፈልጋል። ከተማዪቱን ለቆ የወጣው ሌሊቱን በጥድፍያ ስለነበር፥ እንደተዋቸው አድርገው እንዳያስቡ አልፈለገም ነበር። በተጨማሪም፥ የጳውሎስ ጠላቶች ባሕርዩን የማንቋሸሽና ስሙን የማጥፋት ዘመቻ በማካሄድ፥ በተለይ ለአዳዲሶቹ አማኞች መሪያቸው ሃይማኖትን የገንዘብ ማግኛ ምንጭ በማድረግ የሚሰብክ ስግብግብና አስመሳይ ሰው እንደሆነ ለማሳመን ይጥሩ ነበር (1ኛ ተሰ. 2)። በግሪክ ውስጥ እንዲህ ያሉ ከቦታ ወደ ቦታ በመዘዋወርና በመስበክ ገንዘብ የመዝረፍ ክፉ ባሕርይ የተጠናወታቸው ሰዎች ስለነበሩ፥ ጳውሎስም ከእነዚህ እንደ አንዱ እንደሆነ ያስወሩ ነበር። በዚህ መልእክት፥ ጳውሎስ ለአንባብያኑ የነበረውን ፍቅርና እነርሱን በማገልገሉ በኩል ያለውን ታማኝነት ያረጋግጥላቸዋል።

ሁለተኛም ዓላማ ነበረው:- በክርስትና እምነት ትምህርቶች፥ በተለይም የክርስቶስን ምጽአት በተመለከተ ጽኑ መሠረት ሊጥልላቸው ፈልጐ ነበር። በወቅቱ ቤተ ክርስቲያን በከፋ ስደት ውስጥ የምትገኝ ስትሆን፥ ይህም ሁልጊዜም ከአሳዳጆችዋ ጋር መስሎ ለመኖር የሚገፋፋና ተስፋ ወደመቁረጡ የሚያደርስ የፈተና ወቅት ነበር። ስለሆነም ጳውሎስ የክርስትናን እምነት እውነቶችና እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ያደረገላቸውን ነገር በማስታወስ፥ ጸንተው እንዲቆሙና ጠንካራ ምስክርነታቸን እንዲጠብቁ ያበረታታቸዋል።

በተቀደሰ አኗኗር እንዲመላለሱም ያደፋፍራቸዋል። በዚያን ጊዜ በከተሞች አካባቢ የሥነ-ምግባር ግድፈቶች የተለመዱ መሆናቸውንና የወሲብ ኃጢአቶችም በብዙዎቹ ዘንድ እንደማይኮነኑ ልብ ልንል ይገባል። እነዚህ መልእክቶች በሕይወት ንጽሕና ላይ ያተኩራሉ ይህ በአብያተ ክርስቲያናታችንም ደግሞ ሊተኮርበት የሚገባው አሳብ ነው።

አዳዲሶቹ አማኞች የኢየሱስ ክርስቶስን ምጽአት በተመለከተ ግራ ተጋብተው ነበር። ጳውሎስ ጌታ በአየር ላይ እንደሚገለጽና እንደሚወስዳቸው ነግሮአቸው ነበር በመሀሉ ግን ከአባሎቻቸው አንዳንዶቹ ሞቱ። በመሆኑም በሐዘን ላይ የነበሩት ሰዎች፥ እነዚህ ክርስቲያን ሆነው የሞቱት ዘመዶቻቸው በቤተ ክርስቲያን «ንጥቀት» ውስጥ የሚወሰዱ ስለመሆን አለመሆናቸው በማሰብ ይደነቁ ነበር። ጳውሎስም ይህንኑ ጉዳይ በ1ኛ ተሰሎንቄ 4፡3-18 ውስጥ ያብራራዋል።

እንደዚሁም ሁለተኛ ውዝግብ ተነሥቶ ነበር። ስደቱ እጅግ ከፍቶ ነበርና አንዳንድ አማኞች «የጌታ ቀን» የደረሰ ስለመሆኑ ያስወሩ ጀመር። (ለዚህ ውዝግብ መንስዔው የአንድ ሐሰተኛ መልእክት መሠራጨት ሳይሆን አይቀርም 2ኛ ተሰ. 2፡1-2 ተመልከት)። ጳውሎስ 2ኛ ተሰሎንቄን የጻፈው ይህንኑ ትምህርት ግልጽ ለማድረግና የጌታ ቀን ገና እንዳልደረሰ ለማረጋገጥ ነበር።

በመጨረሻም፥ ጳውሎስ በዚህ መልእክት አማካኝነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩትን አንዳንድ ድክመቶች ለማረም ይፈልጋል። አንዳንድ ምእመናን እንደሚገባቸው መጠን መንፈሳዊ መሪዎቻቸውን አያከብሩም ነበር (1ኛ ተሰ. 5፡12-13)። ሌሎች ደግሞ የጌታ ምጽአት መቃረቡን ማመካኛ በማድረግ ከሥራ ተገልለው ነበር (2ኛ ተሰ. 3 ከቁጥር 6 ጀምሮ)።

እንዲሁም በጉባኤ አገልግሎቶቻቸው ሳቢያ አንዳንድ ዕርማት የሚያሻው ውዝግብ ተፈጥሮ ነበር (1ኛ ተሰ. 5፡19-21)።

ዛሬም የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢትን በተመለከተ የሚነሣው ውዝግብ፥ የሬድዮና የቴሌቭዥን ሰባኪዎችን እርስ በርስ (እና ከመጽሐፍ ቅዱስም ጋር) እያጋጨና የቅዱሳንን ልብ እያሳዘነ ይገኛል። የጌታ ምጽአት በእርግጥ ተቃርቧልን? ከመመለሱስ በፊት መታየት ያለባቸው ምልክቶች ሊኖሩ ያስፈልጋልን? የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆነውስ ወገን ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት በጌታ ቀን (በታላቁ መከራ) ውስጥ ያልፍ ይሆን? ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በተጻፉት ሁለቱ መልእክቶች አማካይነት እነዚህን አስፈላጊ ጥያቄዎች መልሶአል።

ስለተግባራዊ ቅድስናስ ጉዳይ? ለክርስቲያኖች ከዓለም ብልሽት ርቆ መኖር ቀላል አይደለም። የወሲብ አስፋፊዎች ከሞላ ጎደል በሁሉም ጋዜጦችና የመድኃኒት መደብሮች ሳይቀር የቅስቀሳ ጽሑፎቻቸውን ለሽያጭ ያቀርባሉ። ምግባረ ብልሹነትና በአንድ የወሲብ ጓደኛ አለመርካት፥ እንደዚሁም ዘመን አመጣሽ ሙዚቃዎች የሬድዮና የቴሌቭዥን ተዘውታሪ ርዕሶች ናቸው። ከዝነኛ ሰዎች አጓጉል ምሳሌነት የተነሣ፥ ወጣቶቹ «ሁሉም የሚያደርገው ነውና ምናለበት!» እያሉ የብክለትን ጎዳና ይያያዙታል።

በዕለታዊ ሕይወታችን ውስጥ ጥንቁቅ ከመሆንም በተጨማሪ፥ በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናታችንም የበለጠ ሥርዓት ልንይዝና ሌሎችን ልናከብር ይገባል። በበኩሌ፥ ለመንፈሳዊ መሪዎች አክብሮትን አለማሳየት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚነሡ ጠቦችና ክፍፍሎች ዋንኛ ምክንያት መሆኑን ተረድቻለሁ። ጳውሎስ በ1ኛ ተሰሎንቄ 5፡12-13 እና 2ኛ ተሰሎንቄ 3፡6-15 ውስጥ ያሰፈረው ቁም ነገር ለዛሬው ሕይወታችን እጅግ አስፈላጊ ነው።

ያለምንም አድልዎ እስከተናገርን፥ ምሳሌነታቸውን ልንከተለው የማይገባ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች ስለመኖራቸው ተገንዝቤአለሁ። መንፈሳዊነት አይታይባቸውም፤ አይጸልዩም፤ ለሚጠፉት ነፍሳትም አይጨነቁም። አገልግሎታቸውን የተመቻቸ ሕይወት ለመምራት ጥሩ አጋጣሚ አድርገው ይጠቀሙበታል። አንድ መጋቢ እንደ ጳውሎስ ፍጹም በተሰጠ ሕይወቱና መሥዋዕትነትን በሚጠይቅ አገልግሎቱ ሊታወቅ እንጂ፥ አክብሮትን ሊጠብቅ አይገባውም።

1ኛ ተሰሎንቄ ከአንድ መንፈሳዊ አባት ለልጆቹ የተጻፈ ደብዳቤ ነው። ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ አንድ ቤተሰብ የገለጸ ሲሆን («ወንድሞች» ወይም «ወንድም» የሚለው ቃል፥ በመጀመሪያው መልእክት ውስጥ 19 ጊዜ ሲጠቀስ፥ በ2ኛው መልእክት ውስጥ 9 ጊዜ ተጠቅሶአል)፥ እግዚአብሔር በእርሱ አገልግሎት አማካኝነት ያደረገላቸውንም ነገር አስታውሶአቸዋል። ከዚህም አንጻር ስንመለከተው፥ የ1ኛ ተሰሎንቄ አስተዋጽኦ የሚከተለውን ይመስላል፡-

ሀ. የጳውሎስ ትውስታዎች - ምዕራፍ 1-3

1. ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደተወለደች - ምዕራፍ 1
2. ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደ አደገች - ምዕራፍ 2
3. ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደ ተጠናከረች - ምዕራፍ 3

ለ. የጳውሎስ ምክሮች - ምዕራፍ 4-5

(ቤተ ክርስቲያን እንዴት መመላለስ እንዳለባት)

1. በቅድስና - 4፡1-8
2. በአንድነት - 4፡9-10
3. በታማኝነት - 4፡11-12
4. በተስፋ - 4፡13-5፡11
5. በርዳታ - 5፡12-28

ሁለተኛው መልእክት የተጻፈው የጌታን ምጽአት በተመለከተ፥ አንዳንድ የተሳሳቱ አስተሳሰቦችንና ልምምዶችን ለማረም ነበር። የዚህን መልእክት ዝርዝር አሳብ ወደ በኋላ የምናቀርብ ቢሆንም፥ ለጊዜው የ2ኛ ተሰሎንቄ አስተዋጽኦ ቀጥሎ የተመለከተውን ይመስላል፡-

ሀ. በመከራ ውስጥ ለሚገኙ ወገኖች የቀረበ መጽናኛ - ምዕራፍ 1

1. ምስጋና - 1፡1-4
2. የተስፋ ቃል - 1፡5-10
3. ጸሎት - 1፡11-12

ለ. በትምህርት ማንቃት - ምዕራፍ 2

1. የዓመፅ ሰው እንዴት እንደሚገለጽ - 2፡1-7

2. የእግዚአብሔር ልጅ እንዴት እንደሚገለጽ - 2፡8-12

3. የእግዚአብሔር ልጅ እንዴት መኖር እንዳለበት - 2፡13-17

ሐ. የአኗኗር ብቃት - ምዕራፍ 3

1. ቃሉን ታዘዙ - 3፡1-6

2. ምሳሌአችንን ተከተሉ - 3፡7-9

3. ሥርዓተ - አልበኞችን ቅጡ - 3፡10-15

4. የመጨረሻ ቡራኬ 3፡16-18

እስካሁን ድረስ የመልእክቶቹን ሥረ-መሠረትና ጳውሎስ መልእክቶቹን ለመጻፍ የገፋፋውን ከባድ ሸክም ተመልክተናል። አሁን ደግሞ የእነዚህን መልእክቶች በረከቶች በመመልከት በየግል ሕይወታችን ውስጥ የሚኖራቸውን ተዛምዶ ለመረዳት እንሞክር።

## በረከቱ

እያንዳንዱ የአዲስ ኪዳን መልእክት ፍጹም የራሱ የሆነ ልዩ መልእክት ወይም በረከት አለው። ለምሳሌ፥ የሮሜ መልእክት በእግዚአብሔር ጽድቅ ላይ በማተኮር፥ እግዚአብሔር ከኃጢአተኞችም ሆነ ከአማኞች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ጻድቅ መሆኑን ያሳያል። 1ኛ ቆሮንቶስ በእግዚአብሔር ጥበብ ላይ፥ 2ኛ ቆሮንቶስ ደግሞ በእግዚአብሔር ማጽናናት ላይ ያተኩራል። ገላትያ አርነትን፥ ፊልጵስዩስ ደስታን ሲያሳየን፥ ኤፌሶን ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ የምናገኘውን ብልጽግና ያቀርብልናል።

በ1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ ውስጥ የሚገኘው ልዩ በረከትስ ምንድን ነው? መልእክቱ የኢየሱስ ክርስቶስን መመለስ ከማብሠሩም፥ ይህም ዋንኛ ትምህርት (ዶክትሪን) በሕይወታችንና በአብያተ ክርስቲያናታችን ላይ ለውጥ በማስከተል፥ እንዴት በበለጠ መንፈሳውያን ሊያደርገን እንደሚችል ያሳየናል። በ1ኛ ተሰሎንቄ ውስጥ እያንዳንዱ ምዕራፍ የሚጠቃለለው የኢየሱስ ክርስቶስን ምጽአት በማመልከት ሲሆን፥ እያንዳንዱም ማጣቀሻ ትምህርቱን ከተግባራዊ የክርስቲያን የአኗኗር ገጽታ ጋር ያዛምደዋል። ማጠቃለያውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

1፡10 - ደኅንነትና የደኅንነት ዋስትና

2፡19-20 - ነፍሳትን መማረክና አገልግሎት

3፡11-13 - ፌር የያዘ የክርስትና አኗኗር

4፡ 13-18 - በኃዘን ምትክ ብርታት

5፡ 23-24 - የሕይወት ቅድስና

በሌላ አባባል፥ ጳውሎስ ይህን ትምህርት የሚመለከተው እንደመወያያ ንድፈ-አሳብ በመቁጠር ሳይሆን፥ ሕይወትን የሚመሩበት እውነታ አድርጎ ነው። ኢየሱስ በማንኛውም ጊዜ ሊመጣ ስለሚችል፥ እነዚህ መልእክቶች ወደፊት አርቀን በመመልከት እንድንኖር ያደርጉናል።

ስለዚህ በኑሮ ዘይቤአችን ውስጥ፥ የእርሱን የዳግም ምጽአት ተስፋ ማሳየት አለብን። ወደ 2ኛ ተሰሎንቄ ስንሸጋገር ደግሞ፥ ወደፊት ስለሚፈጸሙ ክስተቶችና ስለ ቤተ ክርስቲያን ተጨማሪ እውነታዎችን እናገኛለን። ሁለተኛው ደብዳቤ የተጻፈው የጌታችንን መመለስ በተመለከተ የተነሣውን ውዝግብ ለማረም እንደነበር ልብ በል። አንዳንድ አማኞች የጌታ ቀን (ታላቁ መከራ) እንደተከሰተ በማሰብ፥ ጌታ መቼ ይሆን በግልጥ የሚታየው? እያሉ ይደነቁ ነበር። ምናልባት የሁለቱን ደብዳቤዎች ዐበይት መልእክቶች ለመረዳት ከሁሉም የሚሻለው በንጽጽር መመልከቱ ይሆናል፡-

| 1ኛ ተሰሎንቄ | 2ኛ ተሰሎንቄ |
|---|---|
| - ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ በአየር ላይ ይገለጻል (4፡ 13-18) | - ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር ወደ ምድር ይመለሳል (1፡ 10) |
| - በማንኛውም ጊዜ ሊፈጸም የሚችል ቅጽበታዊ ስውር ንጥቀት | - የተተነበየው መርሐ-ግብር አካል የሆነ ቀውጢ ሁኔታ |
| - ዛሬ ሊፈጸም ይችላል | - የተወሰኑ ክስተቶች ከተፈጸሙ በኋላ ብቻ የሚደርስ ነው |
| - የክርስቶስ ቀን | - የጌታ ቀን |

መንፈሳውያን ሰዎች ትንቢትን፥ በተለይም የቤተ ክርስቲያንን መነጠቅ ወይም ወደ ታላቁ መከራ ውስጥ የመግባቱን ሁኔታ በተመለከተ በሚያቀርቡት አተረጓጎም እንደሚለያዩ በበኩሌም ቢሆን የምረዳው ነው። እኔ ግን ቤተ ክርስቲያን ከታላቁ መከራ በፊት ወደ ሰማይ ትነጠቅና መከራው ከተፈጸመ በኋላ ከጌታ ጋር ተመልሳ ትመጣለች ብዬ አምናለሁ (ራእይ 19 ከቁጥር 11 ጀምሮ)። አንደኛ ተሰሎንቄ በቤተ ክርስቲያን ንጥቀት ላይ

ሲያተኩር፥ ሁለተኛ ተሰሎንቄ በዓለም ላይ ለመፍረድ ጌታ ከቤተ ክርስቲያን ጋር በሚገለጽበት ሁኔታ ላይ እንደሚያተኩር ተመልክቻለሁ።

ይሁንና የእነዚህ እውነቶች ተጨባጭ የሆኑት መንፈሳዊ ትምህርቶች በአተረጓጎም ሙግቶች መካከል ተድበስብሰው ወይም ተውጠው ሊቀሩ አይገባም። ዶክተር ሊዮን ሞሪስ «ዘ ኒው ኢንተርናሽናል ኮሜንቴሪ» በተባለው መጽሐፋቸው ውስጥ በተሰሎንቄ መልእክት ላይ ያሰፈሩትን ግሩም ማብራሪያ ማንበቡ ያስደስተኛል።

ዶክተር ሞሪስ አንደኛ ተሰሎንቄ 5፡1-3ን በተመለከተ ባቀረቡት ማብራሪያ ውስጥ፥ አማኞች ከታላቁ መከራ በፊት ስለመነጠቃቸው ወይም በዚያ አስጨናቂ ክስተት ውስጥ ለማለፍ በምድር ላይ የሚቆዩ ስለመሆናቸው ሲናገሩ፥ «የዚህ ምዕራፍ ቋንቋ በሁለቱም መንገድ ሊታይ ይችላል» ይላሉ። ከዚያም ቤተ ክርስቲያን በታላቁ መከራ ውስጥ ታልፋለች የሚለውን የግል አቋማቸውን ያጠናክራሉ። አክለውም፥ «ይሁንና ሌሎችም አተረጓገሞች ሊያስኬዱ እንደሚችሉ በመገንዘብ፥ እንደዚህ ዓይነቶቹን ምንባቦች በተለየ መንገድ የሚመለከቱትን ወገኖች መኮነኑ አስተዋይነት አይደለም» ይላሉ።

በሌላ አባባል፥የአሳብ አለመግባባት ቢኖረንም በጥል መለያየት አያስፈልገንም። ለምሳሌ እኔ በግሌ የማምነው «ከሚመጣው ቁጣ» እንደምንድን ነው (1ኛ ተሰ. 1፡10፤ 5፡9-10)። ጌታችን ባለማቋረጥ ምጽአቱን እየተጠባበቅን እንድንኖር እንደሚፈልግ አምናለሁ። ሌላውን አቋም የሚይዙትን ወገኖች ግሩም የማሳመኛ ነጥቦችንም በጥንቃቄ አጥንቻለሁ፤ እናም ለእነዚህ ሰዎች አክብሮት አለኝ። ይሁንና ፍቅር ባልተለየው ሁኔታ በነጥቦቻቸው አልስማማም።

ጳውሎስ እነዚህን መልእክቶች የጻፈው ክርክር ለማስነሣት አልነበረም። የእርሱ ፍላጐት እነዚህ መልእክቶች ሕይወታችንንና አብያተ ክርስቲያናችንን እንዲባርኩልን ነበር። የጌታችን መመለስ ትምህርት የመጫወቻ አሻንጉሊት፥ ወይም ደግሞ የመዋጊያ መሣሪያ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን እኛን ለማነፅ የሚረዳ መሣሪያ ነው። አማኞች በአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ላይ ላይስማሙ ቢችሉም፥ ኢየሱስ ክርስቶስ አማኞችን ለመሸልመና በኃጢአተኞች ላይ ለመፍረድ ዳግም እንደሚመለስ ሁላችንም እናምናለን። ሁላችንም ምጽአቱን እያሰብን ልንኖር ይገባል።

እነዚህን መልእክቶች ማጥናትህ ወደፊት ስለሚሆነው ነገር ዋስትና ሊሰጥህና በምስክርነትህና ከጌታ ጋር በምታደርገው የሕይወት ጉዞ

ሊያበረታታህ ይገባል። እንደዚሁም በክርስቶስ አምነው ስለሞቱት ሰዎች መጽናናት ሊሆንህና ስለራስዋ እንኳ ርግጠኛ ባልሆነችው ዓለም ውስጥ ሳትናወጥ ጸንተህ እንድትኖር ሊረዳህ ይችላል። ጳውሎስ በእነዚህ ሁለት መልእክቶች ውስጥ ያሰፈራቸውን መመሪያዎች በተግባር ላይ ማዋል ለወደፊቱ ዝግጅትህ ይረዳሃል።

## 1ኛ ተሰሎንቄ 1፡ 1-10

«ጳውሎስና ስልዋኖስ ጢሞቴዎስም፥ በእግዚአብሔር አብ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም ወደምትሆን ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን፤

ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስም ጸጋ ሰላምም ለእናንተ ይሁን።

በጸሎታችን ጊዜ ስለእናንተ ስናሳስብ፥ የእምነታችሁን ሥራ የፍቅራችሁንም ድካም በጌታችንም በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን የተስፋችሁን መጽናት በአምላካችንና በአባታችን ፊት ሳናቋርጥ እያሰብን፥ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ በሁላችሁ ምክንያት እናመሰግናለን፤ በእግዚአብሔር የምትወደዱ ወንድሞች ሆይ፥ እንደ ተመረጣችሁ አውቀናልና። ወንጌላችን በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ በቃል ብቻ ወደ እናንተ አልመጣምና፤ በእናንተ ዘንድ ስለ እናንተ እንዴት እንደነበርን ታውቃላችሁ። ደግሞ እናንተ ቃሉን በብዙ መከራ ከመንፈስ ቅዱስ ደስታ ጋር ተቀብላችሁ፥ እኛንና ጌታን የምትመስሉ ሆናችሁ፤ ስለዚህም በመቄዶንያና በአካይያ ላሉት ምእመናን ሁሉ ምሳሌ ሆናችሁላቸው። ከእናንተ ወጥቶ የጌታ ቃል በመቄዶንያና በአካይያ ብቻ አልተሰማምና፥ ነገር ግን ምንም እንድንናገር እስከማያስፈልግ ድረስ፥ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚሆን እምነታችሁ በሁሉ ስፍራ ተወርቶአል። እነርሱ ራሳቸው ወደ እናንተ መግባታችን እንዴት እንደ ነበረ ስለ እኛ ይናገራሉና፤ ለሕያውና ለእውነተኛ አምላክም ታገለግሉ ዘንድ፥ ከሙታንም ያስነሣውን ልጁን እርሱንም ኢየሱስን ከሚመጣው ቁጣ የሚያድነንን ከሰማይ ትጠብቁ ዘንድ፥ ከጣዖቶች ወደ እግዚአብሔር እንዴት ዘወር እንዳላችሁ ይናገራሉ።»

# - 2 -

# ቤተ ክርስቲያን እንዴት ልትሆን ይገባል?

ያለጥርጥር አንዳንድ ሰባኪያን «እንከን የሌለባት ቤተ ክርስቲያን ለምናልባቱ ብታገኙ እንኳን፥ አደራችሁን አባል እንዳትሆኑ። አባል ከሆናችሁባት ፍጹምነቷን ታጣለችና!» ሲሉ መናገራቸውን ሳትሰሙ አትቀሩም።

አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በእግዚአብሔር ጸጋ በዳኑ ሰብአዊ ሰዎች የተገነቡ በመሆናቸው፥ ፍጹም የሆነች ቤተ ክርስቲያን የለችም፤ ዳሩ ግን አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ከሌሎቹ ይልቅ የአዲስ ኪዳኗን ቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ለማሟላት የተሻሉ ናቸው። የተሰሎንቄዋም ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ምድብ የምትገባ ነች። ጳውሎስ በዚህ መልእክት ውስጥ፥ ቢያንስ አራት ጊዜ ለቤተ ክርስቲያኒቱ እና ለአገልግሎቱ ስለሰጠችው ምላሽ ምስጋናውን ያቀርባል (1:2፤ 2:13፤ 3:9፤ 5:18)። ነገር ግን በዚህ ዘመን ያሉ አንዳንድ መጋቢዎች ለተደረገላቸው ነገር እንደ ጳውሎስ አመስጋኞች መሆን ያስቸግራቸዋል።

ለመሆኑ ይህችን ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ወደ ፍጹምነት የሳቧትና ለጳውሎስም ያን ያህል ልባዊ ደስታ ሊያሳድሩበት የቻሉት ባሕርያት የትኞቹ ነበሩ?

## የተመረጡ ሕዝብ (1:1-4)

በቁጥር 1 «ቤተ ክርስቲያን» የሚለው ቃል «ተጠርተው የወጡ ሰዎች» የሚል ትርጉም ይሰጣል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ጥሪ» የሚል ቃል በምታነብበት ጊዜ፥ መለኮታዊ ምርጫን እንደሚያመለክት ልብ በል። እግዚአብሔር ሰዎችን ከዚህ ዓለም ይጠራቸዋል (የሐዋ. 5:13-18)። በዮሐንስ 17 ውስጥ ጌታችን አማኞችን እግዚአብሔር ከዓለም አውጥቶ ለእርሱ እንደሰጣቸው በመጥቀስ ሰባት ጊዜ ተናግሯል (2፥ 6፥ 9፥ 11፥ 12፥ 24)። ጳውሎስም የተሰሎንቄ ሰዎች በእግዚአብሔር እንደተመረጡ አውቃለሁ ይላል (1:4)።

የመለኮታዊ ምርጫ ትምህርት አንዳንዶችን ሲያደናግር፥ ሌሎችን ደግሞ ያስፈራል። ይሁንና መደናገሩም መፍራቱም አግባብነት የለውም። አንድ ጊዜ አንድ የሰሚናሪ (የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ) ፕሮፌሰር፥ «ስለ

መለኮታዊ ምርጫ ለመግለጽ ስትሞክር አእምሮህን ልታጣ ትችላለህ፤ ዳሩ ግን መሠረተ አሳቡን ከለቀቅህ፥ ነፍስህን ታጣለህ» ብሎኝ ነበር።

በዚህ ዓለም ሳለን የእግዚአብሔርን ምርጫ ፅንሰ-አሳብ ሙሉ ለሙሉ ልንረዳ አንችልም። ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዳር እስከ ዳር ጐልቶ የሚታየውን ይህንን አስፈላጊ ትምህርት ችላ ልንለው አይገባም። እስኪ ስለመለኮታዊ ምርጫ አንዳንድ ግልጽ ነጥቦች እንመልከት፡-

1. ደኅንነት የሚጀመረው በእግዚአብሔር ነው። «እግዚአብሔር ... ለመዳን እንደበኩራት መርጦአችኋልና» (2ኛ ተሰ. 2፡13)። «እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም» (ዮሐ. 15፡16)። «ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ [እግዚአብሔር] በክርስቶስ መረጠን» (ኤፌ. 1፡4)። ሰው ሳይፈጠር ወይም አጽናፈ-ዓለሙ ሳይመሠረት በፊት፥ ጠቅላላው የደኅንነት ዕቅድ በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ተፀንሶ ነበር።

2. በደኅንነት ውስጥ የእግዚአብሔር ፍቅር ይታያል። ጳውሎስ እነዚህን ቅዱሳን «የተወደዳችሁ ወንድሞች» ብሏል፤ በጳውሎስ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔርም የተወደዱ ናቸው (2፡17 ተመልከት)። የእግዚአብሔር ፍቅር የጎልጐታን ጣር ከተግባር ላይ ስላዋለው (ሮሜ 5፡8)፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሊሞትልን ችሏል። ይሁንና ኃጢአተኛውን የሚያድነው የእግዚአብሔር ፍቅር ብቻ ሳይሆን ጸጋውም ነው። እግዚአብሔር በጸጋው የማይገባንን ችሎታ ይሰጠናል። በምሕረቱ ደግሞ የሚገባንን ቅጣት እንኳ አይሰጠንም። ይህም ጳውሎስ በአመዛኙ መልእክቶች፥ «ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስም ጸጋ ሰላምም ለእናንተ ይሁን» (1፡1) ብሎ ለምን እንደሚጀምር ያስረዳናል።

3. በደኅንነት ውስጥ እምነትም አለ። «ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና» (ኤፌ. 2፡8)። ጳውሎስ፥ ሲላስ (በሮማውያን አጠራር ስልዋኖስ) እና ጢሞቴዎስ ወንጌሉን ወደ ተሰሎንቄ በማድረስ፥ በእግዚአብሔር ኃይል ሰበኩ (1፡5)። አንዳንዶችም ወንጌሉን ሰምተው ከከንቱ የጣዖት አምልኮአቸው ወደ እውነተኛውና ሕያው አምላክ ተመለሱ (1፡9)። የእግዚአብሔር መንፈስ እምነትን ለማምጣት በእግዚአብሔር ቃል ተጠቀመ (ሮሜ 10፡17)። ጳውሎስ ይህንን «በመንፈስ ቅዱስ እውነትንም በማመን ለመዳን» ይለዋል (2ኛ ተሰ. 2፡13)።

4. ደኅንነት የሥላሴን የሥራ ድርሻ ያካትታል። ይህንን ደብዳቤ በምታነብበት ጊዜ፥ የሥላሴን ትምህርት ልትመለከት ትችላለህ። ክርስቲያኖች በሦስት አካላት ሕልውና በሚኖር አንድ አምላክ ያምናሉ፡- እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ። እነዚህ ሦስቱም አካላት በደኅንነታችን ውስጥ እንደተሳተፉ ልብ በል። ይህም አንድም ሰብአዊ ኃላፊነትን ከሚክዱ አሊያም መለኮታዊ ሉዓላዊነትን ከሚያቃልሉ አደገኛ አክራሪዎች እንድትጠበቅ ይረዳሃል። ሁለቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጠቀሳቸውንም አትርሳ።

በበኩሌም ቢሆን የሚከተለውን የምስክርነት ቃል እሰጣለሁ። እግዚአብሔር አብን በተመለከተ፥ ዓለም ከመፈጠሯ በፊት በክርስቶስ በመረጠኝ ጊዜ ድኛለሁ። እግዚአብሔር ወልድን በተመለከተ፥ በመስቀል ላይ በሞተልኝ ጊዜ ድኛለሁ። መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ፥ በመጋቢት ወር 1945 አንድ ቅዳሜ ምሽት ቃሉን በመስማት በኢየሱስ ክርስቶስ ባመንሁ ጊዜ ድኛለሁ። በዚያች ቅጽበት ጠቅላላው ዕቅድ መታና የእግዚአብሔር ልጅ ሆንሁ። በዚያች ምሽት፥ «የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ወይ?» የሚል መጠይቅ ብታቀርብልኝ ኖሮ የምለው አይኖረኝም ነበር። ያኔ ስለምርጫ የማውቀው አልነበረኝም። ይሁንና መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኔን በልቤ ውስጥ መስክሮልኛል።

5. ደኅንነት ሕይወትን ይለውጣል። ጳውሎስ እነዚህ የተሰሎንቄ ሰዎች በእግዚአብሔር መመረጣቸውን እንዴት አወቀ? በሕይወታቸው ውስጥ የደረሰውን ለውጥ በመመልከት ነው። 1፡3 ን ከ 1፡9-10 ቀጥለህ ብታስቀምጥ፥ ሥዕሉ ጎልቶ ሊታይህ ይችላል፡-

- የእምነታችሁ ሥራ – ከጣዖቶች ወደ እግዚአብሔር ተመለሳችሁ
- የፍቅራችሁ ድካም– ለሕያውና ለእውነተኛ አምላክ ታገለግሉ ዘንድ
- የተስፋችሁ መጽናት–ልጁን ከሰማይ ትጠብቁ ዘንድ

ራሱን ከእግዚአብሔር ምርጦች መካከል የሚመድብና ዳሩ ግን የሕይወት ለውጥ ያላገኘ ሰው ራሱን እያታለለ ነው። እግዚአብሔር የሚመርጣቸውን ሰዎች ይለውጣቸዋል፤ ይህም ፍጹማን ይሆናሉ ማለት ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ሊሰወር የማይችል አዲስ ሕይወት ይኖራቸዋል ማለት ነው።

እምነት፥ ተስፋና ፍቅር እነዚህ ሦስቱ የክርስትና ሕይወት መሠረታዊ ምግባሮች ሲሆኑ፥ የአንድን ሰው መዳን የሚያመለክቱ ከሁሉም የላቁ መረጃዎች ናቸው። እምነት ሁልጊዜም ወደ ተግባር ማምራት አለበት (ያዕ. 2፡14-26)። «የዳንነው በእምነት ላይ መልካም ሥራ በማከል ሳይሆን፥ ወደ መልካም ተግባር በሚመራ እምነት ነው» ተብሏል። የተሰሎንቄ ሰዎች በሕያው አምላክ እናምናለን እያሉ የጣዖት አምልኮአቸውን ቢቀጥሉ ኖሮ፥ ተግባራቸው ከእግዚአብሔር ምርጦች መካከል እንዳልሆኑ ባረጋገጥባቸውም ነበር።

ፍቅር የደኅንነትን መኖር የሚያሳይ መረጃ ነው፡- «በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለፈሰሰ ...» (ሮሜ 5፡5)። «እናንተ ራሳችሁ እርስ በርሳችሁ ልትዋደዱ በእግዚአብሔር ተምራችኋልና» (1ኛ ተሰ. 4፡9)። ክርስቶስን የምናገለግለው ስለምንወደው ነው፤ ጳውሎስም «የፍቅራችሁ ድካም» በማለት የተጠቀሰው ይህንኑ ነው። «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» (ዮሐ. 14-15)።

ሦስተኛው የደኅንነት መረጃ የኢየሱስ ክርስቶስን መመለስ የመጠባበቅ ተስፋ ነው (1፡10)። የኢየሱስ ክርስቶስ መመለስ የአንደኛና ሁለተኛ ተሰሎንቄ መልእክት ዐቢይ አሳብ ነው። ያልዳኑ ሰዎች የጌታን መመለስ በናፍቆት አይጠባበቁም። ጌታችን ቤተ ክርስቲያኑን ወደ አየር በሚነጥቅበት ጊዜ፥ ያልዳኑ ሰዎች ሙሉ ለሙሉ በግርምት ይዋጣሉ (5፡1-11)።

እምነት፥ ተስፋና ፍቅር የምርጫ መረጃዎች ናቸው። እነዚህ መንፈሳዊ ብቃቶች በአንድ ላይ የተጣመሩ ሲሆኑ፥ የሚመጡትም ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ ነው። ለተጨማሪ መረጃ የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብ፡- 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡13፤ ሮሜ 5፡2-5፤ ገላትያ 5፡5-6፤ ቈላስይስ 1፡4-5፤ ዕብራውያን 6፡10-12፤ 10፡22-24፤ 1ኛ ጴጥሮስ 1፡21-22።

አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ጸጋ የተመረጡ ሰዎች የሚገኙባት ልትሆን ይገባል። ዛሬ የሚያውከን አንዱ ችግር ስማቸው በቤተ ክርስቲያን መዝገብ ላይ ሰፍሮ ቢገኝም በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ያልተመዘገቡና ከደኅንነት የራቁ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖራቸው ነው። እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል በርግጥ ዳግም ተወልዶ ከእግዚአብሔር ምርጦች ውስጥ እንደተደባለቀ ለማወቅ ልቡን መመርመር አለበት።

## ለሌሎች ምሳሌ የሚሆኑ ሰዎች (1፡5-7)

ጳውሎስ ገና ይህች ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴዋን ስትጀምር፥ በውስጧ የሚገኙ ክርስቲያኖች የሚጠሩበትን ስም የሚያስከብሩ መሆናቸውን በመረዳቱ በደስታና በምስጋና ተመለከታቸው። በበርካታ ዕለታዊ ሕይወታቸው ለሌሎች የሕይወት ምሳሌዎች የሚሆኑ ነበሩ።

1. *ቃሉን ተቀብለዋል* (1፡5)። ወንጌሉ ወደ እነርሱ የደረሰው በጳውሎስና በተባባሪዎቹ አማካኝነት ነበር። በዚያን ዘመን የነበሩት በርካታ ተዘዋዋሪ ሰባኪያንና ፈላስፋዎች ዓላማ ከመሐይሙ ሕዝብ ገንዘብ መሰብሰቡ ብቻ ነበር። ዳሩ ግን መንፈስ ቅዱስ በታላቅ ኃይሉ ቃሉን ስለተጠቀመ፥ የተሰሎንቄ ሰዎች መልእክቱንና መልእክተኞቹን በመቀበል አዎንታዊ ምላሽ ሰጡ። በፊልጵስዩስ ከነበረው ስደት ባሻገር፥ ጳውሎስና ሲላስ ወንጌሉን በድፍረት በመመስከራቸው (2፡2)፥ ሰዎች አምነው ዳኑ። ያም ለቃሉ የነበራቸው ጉጉት አንድም ጊዜ አልቀነሰም ነበር (2፡13)።

2. *መንፈሳዊ መሪዎቻቸውን ተከትለዋል* (1፡6)። በመሠረቱ «ተከታዮች» የሚለው ቃል «መሪዎቻቸውን የሚመስሉ» ማለት ነው። እነዚህ አዳዲስ አማኞች መልእክቱንና መልእክተኞቹን መቀበል ብቻ ሳይሆን፥ የሕይወት ምሳሌነታቸውንም ይከተሉ ነበር። ይህም ወደ ከፋ ስደት መራቸው። በተመሳሳይ ሁኔታም የወጣት ክርስቲያኖች መንፈሳዊ መሪዎችን ማክበርና ከበሳል አማኞችም የሕይወት ልምድ ትምህርት መቅሰም በጣም አስፈላጊ ነው። ለአንድ አዲስ ለተወለደ ሕፃን ቤተሰብ እንደሚያስፈልገው ሁሉ፥ አዲስ ለተወለደውም ክርስቲያን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና በዚያ የሚገኙ መሪዎች ያስፈልጉታል። «ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ ... ስለነፍሳችሁ ይተጋሉና» (ዕብ. 13፡17)። እኛም እንደ በሳል አማኞች ነፍሳትን መማረክ ብቻ ሳይሆን፥ ነፍሳትን ልንንከባከብና አዳዲስ አማኞች የእግዚአብሔርን ቃል ይታዘዙ ዘንድ ልናበረታታቸው ይገባል።

3. *ለክርስቶስ ተሠቃይተዋል* (1፡6)። እነዚህ አማኞች ሰዎችን ከጣዖታት አምልኮ እግዚአብሔርን ወደ ማምለክ በመመለሳቸው፥ የወዳጆቻቸውንና የዘመዶቻቸውን ቁጣ ቀሰቀሱ–ቁጣውም ለከፋ ስደት አጋለጣቸው። አንዳንዶቻቸው ከአዲሱ እምነታቸው የተነሣ ከሥራቸው እንደ ተፈናቀሉ አይጠረጠርም። የማያምኑ አይሁዶች በይሁዳ ውስጥ አማኞችን እንዳሳደዱ ሁሉ፥ የማያምኑ አሕዛቦችም የተሰሎንቄን አማኞች አሳደዱ

(2፡14-16)። እምነት ሁልጊዜም ይፈተናል፤ ከሚፈተንባቸው መንገዶች አንዱ ደግሞ ስደት ነው (ማቴ. 13፡21፤ 2ኛ ጢሞ. 3፡12)።

4. ሌሎችን አብያተ-ክርስቲያናት አበረታትተዋል (1፡7)። ክርስቲያኖች አንድም እርስ በርሳቸው ይበረታታሉ አሊያም እርስ በርሳቸው በመተያየት ተስፋ ይቆርጣሉ። ይህ መመሪያ ለቤተ ክርስቲያንም ይሠራል። ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት ለኢየሩሳሌም አማኞች በሚሰበስበው ርዳታ ውስጥ ይሳተፉ ዘንድ ለማነሣሣት የተጠቀመው በመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት ምሳሌነት ነው (2ኛ ቆሮ. 8፡1-8)። ምንም እንኳ አዲስ አማኞች ቢሆኑም፥ የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች በአቅራቢያቸው የሚገኙትን ማኅበረ-ምእመናን የሚያበረታታ መልካም ምሳሌነትን አሳይተዋል። አብያተ ክርስቲያናት «ለፍቅርና ለመልካም ሥራ» ሊነቃቁ እንጂ (ዕብ. 10፡24)፥ እንደ ዓለማውያን እርስ በርሳቸው ፉክክር ሊገጥሙ አይገባም።

የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን በሁሉም በኩል የጐላ ምሳሌነት ነበራት። የዚህም ምሥጢሩ እምነታቸው፥ ተስፋቸውና ፍቅራቸው ነበር፤ እነዚህ ሦስቱ ባሕሪያት የክርስትና ሕይወት መንፈሳዊ አንቀሳቃሾች ናቸውና!

## ንቁ ሕዝቦች (1፡8)

«የእምነታቸው ሥራና የፍቅራቸው ድካም»፥ ወንጌልን ለሌሎች በማጋራታቸው ራሱን በገሃድ ሊያሳይ በቅቷል። ተሰሎንቄዎች «ተቀባዮችም» (ቃሉ ወደ እነርሱ መጣ - 1፡5) «አስተላላፊዎችም» (ቃሉን ወደ ሌሎች ያስተላለፉ - 1፡8) ነበሩ። እያንዳንዱ አማኝና እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቃሉን መቀበልና ማስተላለፍ ነበረባቸው።

«መሰማት» የሚለው ቃል «እንደ መለከት ድምፅ ተሰማ» ማለት ነው። ይሁንና ተሰሎንቄዎች እንደ ፈሪሳውያን፥ «መለከት እያስነፉ» ሳይሆን (ማቴ. 6፡1-4)፥ የደኅንነትን መልካም የምሥራች ያሰሙ ነበር፤ መልእክታቸውም ግልጽና ርግጠኛ ድምፀት ነበረው (1ኛ ቆሮ. 14፡8)። በመሆኑም ጳውሎስ በሚደርስበት ስፍራ ሁሉ ሰዎች ስለ ተሰሎንቄ አማኞች እምነት እያነሡ ይነግሩት ነበር።

የደኅንነትን መልእክት ለጠፋው ዓለም ማካፈል የእያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊነትና ዕድል ነው። በአራቱ ወንጌላት መደምደሚያና በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ አብያተ ክርስቲያናት

ሊከተሉአቸው የሚገቡ ተልዕኮዎች አሉ (ማቴ. 28፡18-20፤ ማር. 16፡15-16፤ ሉቃ. 24፡46-49፤ ዮሐ. 20፡21፤ የሐዋ. 1፡8)። ዛሬ በርካታ ማኅበረ-ምእመናን የምስክርነትና የነፍስ ማዳን ተግባር ለመፈጸም ደመወዝተኛ ወንጌላዊያንን እስከቀጠሩ በዚያው ይረካሉ። በአዲስ ኪዳን አብያተ ክርስቲያናት ግን መልካሙን የምሥራች በማሰራጨቱ በኩል ጠቅላላው ምእመን ይሳተፍ ነበር (የሐዋ. 2፡44-47 እና 5፡42)።

አንድ የቤተ ክርስቲያን ዕድገት ጥናት እንዳመለከተው፥ ከ70 እስከ 80 እጅ (ፐርሰንት) የሚሆነው የቤተ ክርስቲያን ዕድገት የተገኘው ወዳጆች ለወዳጆቻቸው፥ ዘመዶች ለዘመዶቻቸው ካሳሙት ምስክርነት ነው። የጉብኝት የወንጌል ስርጭትና ሌሎችም ዘዴዎች እገዛ ቢያደርጉም፥ አንድ ሰው ለሌላው ሰው በግል የሚሰጠው ምስክርነት ከፍተኛውን ስፍራ ይይዛል።

ይሁንና የእግዚአብሔር ምርጫና የወንጌል ስርጭት አብረው የሚጓዙ ናቸው። «እግዚአብሔር ለማዳን የሚፈልጋቸውን ሰዎች ራሱ ስለሚያድናቸው፥ የእኔ እገዛ አያስፈልገውም» የሚል ሰው፥ ስለምርጫም ሆነ የወንጌል ስርጭት የሚያውቀው ነገር እንደሌለ ያሳያል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፥ ሁልጊዜም የእግዚአብሔር ምርጫ ኃላፊነትን ያካትታል። እግዚአብሔር እስራኤልን በመምረጥ ለአሕዛብ ትመሰክር ዘንድ የተለየ ሕዝብ አደረጋት።

እንደዚሁም፥ ዛሬ ምስክሮቹ እንሆን ዘንድ ቤተ ክርስቲያንን መርጦአል። የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ የመሆናችን እውነታ ከወንጌሉ ሥራ የምናፈነግጥበትን ቀዳዳ አይሰጠንም። በተቃራኒው፥ የምርጫ ትምህርት ለወንጌል ስርጭት እጅግ ታላቅ ማበረታቻ ከሚሆኑት ነገሮች አንዱ ነው።

ጳውሎስ በቆሮንቶስ የገጠመው ነገር ለዚህ ፍጹም ተዛማጅነት ያለው ማብራርያ ነው (የሐዋ. 18፡1-11)። ቆሮንቶስ በኃጢአት የተበከለች ከተማ በመሆኗ፥ በዚያ ቤተ ክርስቲያን መመሥረት ቀላል አልነበረም። ሕዝቡ ከፈሪሃ-እግዚአብሔር ርቀው ኃጢአተኞች ቢሆኑም (1ኛ ቆሮ. 6፡9-11)፥ ጳውሎስ በእምነት ቃሉን ሰበከ። የማያምኑ አይሁዶች ስደት በቀሰቀሱበት ጊዜ፥ ጳውሎስ ከምኩራብ ወደ ኢዮስጦስ ቤት አመራ። ከዚያም ጌታ፥ «እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፥ ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሣብህ የለምና አትፍራ፥ ነገር ግን ተናገር ዝምም አትበል፤ በዚህ ከተማ ብዙ ሕዝብ አሉኝና» በማለት አበረታታው (የሐዋ. 18፡9-10)። እግዚአብሔር በቆሮንቶስ ምርጦች

እንደነበሩት ጳውሎስ በመረዳቱ፥ ብርታት ተሰምቶት ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል በዚያ ቆየ።

ደኅንነት የሰው ሥራ ቢሆን ኖሮ፥ ተስፋ ቆርጠን ሁሉን ለመተው ምክንያት ነበረን፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ሥራ በመሆኑ፥ ምርጦቹን ለመጥራት በሕዝቡ ይጠቀማል። «... በወንጌላችን ጠራችሁ» (2ኛ ተሰ. 2፡14)። ፍጻሜውን (የጠፉትን ሰዎች መዳን) የሚወስነው እግዚአብሔር ራሱ፥ ለፍጻሜ የሚያደርሰውንም መንገድ (የወንጌሉን ስብከት) ያዘጋጃል። ምንም እንኳ ሁለቱም በአሳባችን ባይስማሙም፥ በመለኮታዊ ሉዓላዊነትና በሰብዓዊ ኃላፊነት መካከል ምንም ዓይነት ግጭት የለም።

ዛሬ ምእመናን የደኅንነትን መልእክት ለሌሎች ለማካፈል ነቅተው የሚሠሩባቸው በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ያስፈልጉናል። ይህን በምጽፍበት ወቅት፥ በዓለማችን ውስጥ 2.4 ቢሊዮን ሕዝብ የተሳካ የወንጌል ምስክርነት አልደረሰውም፤ ቤተ ክርስቲያንም አልተመሠረተለትም። በሬድዮ፥ በቴሌቭዥንና በአሳታሚ ድርጅቶች አማካይነት ከምናሰራጨው ትምህርት ባሻገር፥ ወደጠፉት በመድረሱ ረገድ እየተዳከምን ነው። ታዲያ አንተ ንቁ ክርስቲያን ነህን? ቤተ ክርስቲያንህስ በምስክርነት አገልግሎት ንቁ ነችን?

## በተስፋ የሚጠባበቁ ሰዎች (1፡9-10)

ተሰሎንቄዎች ከጣዖት አምልኮአቸው ወደ እግዚአብሔር ዞር ብለው በኢየሱስ ክርስቶስ ስላመኑ፥ የእምነታቸው ሥራ ምርጥ ሕዝብ አድርጎአቸዋል። በእግዚአብሔር ቃል ሲኖሩና ወንጌሉን ለሌሎች ሲያካፍሉ፥ የፍቅራቸው ድካም ለአርአያነት የሚበቁና ንቁ ክርስቲያኖች አድርጓቸዋል። የተስፋቸው መጽናት ደግሞ የአዳኛቸውን መመለስ የሚጠባበቁ ሰዎች ለመሆን አስችሏቸዋል።

በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ፥ ጳውሎስ የጌታን ዳግም ምጽአት ከደኅንነታቸው ጋር ያዛምደዋል። በክርስቶስ ስለታመኑ፥ «ከሚመጣው ቁጣ» እንደሚድኑ ያውቁ ነበርና (1፡10)፥ ምጽአቱን በደስታ ይጠባበቁ ነበር። ጳውሎስ ይህንን እውነት በ5፡9-10 ውስጥ ደጋግሞ የጠቀሰ ሲሆን፥ በ2ኛ ተሰሎንቄ 1፡5-10 ውስጥም አብራርቶታል።

የተሰሎንቄ ሰዎች ጣዖታትን በሚያመልኩበት ወቅት፥ ተስፋ አልነበራቸውም፤ ዳሩ ግን «ሕያውን አምላክ» ባመለኩ ጊዜ፥ ሕያው ተስፋ ነበራቸው (1ኛ ጴጥ. 1፡2-3 ተመልከት)። በክርስትና ትምህርት ውስጥ

ያደግን ሰዎች ስለ አረማዊው የጣዖት አምልኮ እስራት ልንረዳ አንችልም። ጳውሎስ ወንጌሉን ይዞላቸው ከመምጣቱ በፊት፥ እነዚህ ሰዎች ያለተስፋና ያለ እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ ይንከራተቱ ነበር (ኤፌ. 2፡12)። ጣዖትን ማምለክ ምን እንደሚመስል በግልጽ የሚያስረዳውን መዝሙር [115] አንብብ።

ክርስቲያኖች «የሕያው እግዚአብሔር ልጆች» ናቸው (ሮሜ 9፡26)። ሰውነታቸውም «የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ» ነው (2ኛ ቆሮ. 6፡16)—«የሕያው እግዚአብሔር መንፈስ» የሚያድርበት (2ኛ ቆሮ. 3፡3)። ቤተ ክርስቲያን «የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን» ስትሆን (1ኛ ጢሞ. 3፡15)፥ እግዚአብሔርም ለቤተ ክርስቲያኑ የ«ሕያው እግዚአብሔር ከተማ» እያዘጋጀላት ነው (ዕብ. 12፡22)። ሕያው እግዚአብሔር ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን በማስነሣት ሕያው ተስፋ ሰጥቶናል።

የጌታ ምጽአት ገጽታዎችን ለይተን መረዳት አለብን። በመጀመሪያ፥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ በአየር ላይ ይገለጻል (1ኛ ተሰ. 4፡13-18)። ይህም በምድር ላይ ከሚመጣው ከታላቁ የመከራ ጊዜ ቀደም ብሎ የሚፈጸም ይሆናል (1ኛ ተሰ. 5፡1-3)። በዚህ ዘመን መጨረሻ ላይ ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር ወደ ምድር በመመለስ (2ኛ ተሰ. 1፡5-10፤ ራእይ 19፡11-21)፥ ጠላቶቹን ይደመስስና መንግሥቱን ይመሠርታል (ራእይ 20፡1-6)።

በ1፡10 ላይ «ትጠብቁ ዘንድ» የሚለው ቃል «አንድን ሰው በትዕግሥትና በመተማመን መጠባበቅ» ማለት ነው። መጠበቅ መጽናትንና መሥራትን ይጠይቃል። አንዳንድ የተሰሎንቄ አማኞች ሥራቸውን በማቆምና ጌታ በቅርቡ ይመጣል እያሉ በመሟገት ሥራ-ፈትና ጣልቃ-ገቦች ሆነው ነበር። ዳሩ ግን እየመጣ እንዳለ በትክክል ካመንን፥ አብዝተን በማገልገልና ቃሉን በመታዘዝ እምነታችንን ማረጋገጥ ይኖርብናል። የጌታችን የመክሊት ምሳሌ (ሉቃስ 19፡11-27) የሚያስተምረን እስኪመለስ ድረስ የሰጠንን አደራ ተወጥተን መገኘት እንዳለብን ነው።

ክርስቲያኖች የኢየሱስ ክርስቶስን መመለስ በመጠባበቅ ላይ ናቸው፤ እርሱም በማንኛውም ጊዜ ሊመለስ ይችላል። የምንጠብቀው አዳኙን እንጂ፥ ማንኛውንም «ምልክት» አይደለም። የሰውነታችንን ቤዛነት (ሮሜ 8፡23-25) እና የጽድቅን ተስፋ (ገላ. 5፡5) በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን። ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ አዲስ አካል ለብሰን (ፊልጵ.

3፡20-21)፥ እርሱን እንመስላለን (1ኛ ዮሐ. 3፡1-2)። ወዳዘጋጀልን ስፍራም በመውሰድ (ዮሐ. 14፡1-6)፥ በስሙ ላበረከትነው አገልግሎት ሽልማት ይሰጠናል (ሮሜ 14፡10-12)።

ኢየሱስ ክርስቶስን በማንኛውም ጊዜ ለማየት የምትጠባበቅ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፥ ንቁና በድል-ነሺነት የሚመላለሱ አባላት ይኖሩአታል። የጌታን ምጽአት መጠባበቅ፥ ነፍሳትን ለመማረክ (2፡19-20) እና በክርስትና ጸንቶ ለመኖር (3፡11-13) ትልቅ ማነቃቂያ ነው። የጌታ ምጽአት በኃዘን ውስጥ የሚኖሩ የመጠቀ ሐሤት (4፡13-18) የሚያላብስና ፈሪሃ-እግዚአብሔር ለሰፈነበት ሕይወት የላቀ ማበረታቻ ነው (5፡23-24)። አብያተ-ክርስቲያናት ይህንን አስደናቂ መሠረታዊ ትምህርት መዘንጋታቸው በእጅጉ አሳዛኝ ነው። እንዲሁም አብያተ-ክርስቲያናት በጉዳዩ እያመኑበትና እየሰበኩት ዳሩ ግን በሕይወታቸው ውስጥ አለመለማመዳቸው የባሰ አሳዛኝ ጉዳይ ነው።

ጳውሎስ ይህች ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደተወለደች በማስታወስ (1፡3)፥ ምእመናኗም ስለነበራቸው መንፈሳዊ ባሕርያት እግዚአብሔርን ያመሰግናል። ተሰሎንቄዎች የተመረጡ፥ መልካም ምሳሌነትን ያተረፉ፥ የላቀ መሻት ያላቸው፥ ብሎም ምጽአቱን የሚጠባበቁ ነበሩ። መረሳት የሌለበት ፍሬ ነገር ደግሞ አብያተ ክርስቲያናት የግለሰቦች ጥርቅሞች መሆናቸው ነው። እኔና አንተ ስለ ቤተ ክርስቲያን ስንናገር፥ ከቶውንም «እነርሱ» ማለት የለብንም ፤«እኛ» ነው እንጂ። እኛ ቤተ ክርስቲያን ነን። ይህም ማለት እኔና አንተ እነዚህን መንፈሳዊ ባሕርያት ብንጐናጸፍ፥ ቤተ ክርስቲያናችን እግዚአብሔር እንድትሆን የሚፈልገውን ዓይነት ሆና ትገኛለች። የዚህም ውጤት ከደኅንነት ርቀው የጠፉትን ወደ ጌታ ቤት መማረክና ጌታን ማስከበር ይሆናል።

እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን መሆን ያለበት እያንዳንዱ ክርስቲያን መሆን ያለበትን ነው፡- ምርጥ (በዳግም ልደት)፥ መልካም ምሳሌነት ያለው (ትክክለኛ ባሕርይ ያላቸውን ሰዎች በመምሰል)፥ የላቀ መሻት ያለውና (ወንጌሉን ለሌሎች በማካፈል)፥ እንዲሁም በተስፋ የሚጠባበቅ (በየዕለቱ የጌታን ምጽአት በመናፈቅ)።

ምናልባት ራስን የመመርመሪያው ጊዜው አሁን ይሆናል።

## 1ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 1-12

«ወንድሞች ሆይ፥ ራሳችሁ ወደ እናንተ መግባታችን ከንቱ እንዳልሆነ ታውቃላችሁና። ነገር ግን እንደምታውቁት በፊልጵስዩስ አስቀድመን መከራ ተቀብለን ተንገላትተንም፥ በብዙ ገድል የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ እንናገር ዘንድ በአምላካችን ደፈርን። ልመናችን ከስሕተት ወይም ከርኩሰት ወይም ከተንኰል አልነበረምና፤ ነገር ግን ወንጌልን አደራ ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔር የታመንን ሆነን እንዳገኘን መጠን፥ እንዲሁ እንናገራለን፥ ልባችንን የሚመረምር እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ደስ እንደምናሰኝ አይደለም። እንደምታውቁ፥ እያቈላመጥን ከቶ አልተናገርንም፥ እግዚአብሔርም እንደሚመሰክር እያመካኘን በመጐምጀት አልሠራንም፤ የክርስቶስም ሐዋርያት እንደመሆናችን ልንከብድባችሁ ስንችል፥ ከእናንተ ቢሆን ወይም ከሌሎች ክብርን ከሰው አልፈለግንም። ነገር ግን ሞግዚት የራስዋን ልጆች እንደምትከባከብ፥ በመካከላችሁ የዋሆች ሆንን፤ እንዲሁም እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን ነበረ፥ ለእኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና።

«ወንድሞች ሆይ፥ ድካማችንና ጥረታችን ትዝ ይላችኋልና፤ ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሠራን፥ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበክን። በእናንተ በምታምኑ ዘንድ በእንዴት ያለ ቅድስናና ጽድቅ ነቀፋም በሌለበት ኑሮ እንደ ሄድን፥ እናንተና እግዚአብሔር ምስክሮች ናችሁ፤ ወደ መንግሥቱ ወደ ክብሩም ለጠራችሁ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እየመከርንና እያጸናን እይመሰከርንላችሁም፥ አባት ለልጆቹ እንደሚሆን ለእያንዳንዳችሁ እንደሆንን ታውቃላችሁና።»

# ሕፃኑን በእንክብካቤ እንዲያድግ መርዳት

አንደኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ አንድ ከወንጌላዊው ጳውሎስ ጋር አስተዋውቆናል። ይኸኛው ምዕራፍ ደግሞ ታላቁ ሐዋርያ እራሱ በመሠረታቸው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ለሚገኙ አዳዲስ አማኞች እንዴት እንደሚጠነቀቅ ስለሚያብራራ፥ ከመጋቢው ጳውሎስ ጋር ያስተዋውቀናል። ጳውሎስ «የአብያተ ክርስቲያናትን አሳብ» (2ኛ ቆሮ. 11፡28) በአገልግሎቱ ውስጥ ከተጋፈጣቸው መከራዎች ሁሉ በላይ የላቀ ሸክም አድርጎ ይቆጥራል (2ኛ ቆሮ. 11 ከቁጥር 23 ጀምሮ)።

እግዚአብሔር ወንጌልን ከደኅንነት ርቀው ለጠፉት ሰዎች ለማድረስ በሰዎች እንደሚጠቀም ሁሉ፥ በክርስቶስ ሕፃናት የሆኑትን ለመንከባከብና ወደ ብስለት ይደርሱ ዘንድ ለመምራትም እንደዚሁ በሰዎች ይጠቀማል። የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያውና በረዳቶቹ አማካኝነት የተወለደች ስትሆን፥ ለሕፃኒቱ ቤተ ክርስቲያን እንክብካቤ ይደረግላት የነበረውም ጳውሎስና የአገልግሎት አጋሮቹ ባቀረቡላት ታማኝነት በጎላበት መጋቢነት አማካኝነት ነበር። ይህም በመከራ ማዕበል መሀል ጸንተው እንዲቆሙ ረዳቸው።

በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ፥ ጳውሎስ ለለጋዋ ቤተ ክርስቲያን ሲያስተምርና ሲጠነቀቅ ሳለ የሰጠውን የአገልግሎት ዓይነት ያስታውሳቸዋል። ከዚህም ውስጥ የአገልግሎቱን ሦስት ሥዕሎች እንመለከታለን።

## ታማኝ አገልጋይ (2፡1-6)

ጳውሎስ «የወንጌል አደራ» ተሰጥቶት ነበር (2፡4)። ይኸውም እርሱ ራሱ ያቀነባበረው ወይም ከሰዎች የተቀበለው መልእክት አልነበረም (ገላ. 1፡11-12)። ጳውሎስ ራሱን የእግዚአብሔርን መልእክት ለማስተላለፍ አደራ እንደተሰጠው ሰው አድርጎ ይቆጥራል።

አንድ ባለአደራ የጌታውን ንብረት በሙሉ ከመያዝና ከመጠቀም በስተቀር፥ የራሱ የሆነ ነገር የለውም። ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤት ውስጥ በባለአደራነት ተሹሞ ነበር (ዘፍ. 39፡1-6)። በመሆኑም የጌታውን ጉዳዮች በመከታተልና ንብረቶቹን በሙሉ በመቆጣጠር ለጌታው በሚበጅ መልኩ

ይጠቀምባቸዋል። አንድ ቀን እያንዳንዱ ባለአደራ ስለአገልግሎቱ ምላሽ ይሰጣል (ሉቃ. 16፡1-2)። ታማኝነቱን ካጐደለም፥ መከራ ይደርስበታል።

የወንጌሉ መልእክት እግዚአብሔር በአደራ የሰጠን ንብረት ነው። በመሆኑም ለእግዚአብሔር ክብር «መንፈሳዊ ትርፍ» እንዲያመጣ መነገድ እንጂ፥ መቅበር የለብንም። አንዳንድ ክርስቲያኖች የቤተ ክርስቲያን ብቸኛው ኃላፊነት ወንጌሉን ከሚለውጡ ሰዎች መጠበቅ እንደሆነ አድርገው ያስባሉ (ገላ. 1፡6-9)። እውነታው ግን ወንጌሉን ለሌሎች ማካፈል አለብን፤ ይህ ካልሆነ በከንቱ እየጠበቅነው ነው።

ታማኝነት ለአንድ ባለአደራ ሊኖረው የሚገባው እጅግ አስፈላጊ ብቃት ነው (1ኛ ቆሮ. 4፡1-2)። በሰዎች ዓይን ሲታይ ተወዳጅነትን ላያተርፍ ቢችልም፥ በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ግን ታማኝ ሆኖ መገኘት አለበት። «ልባችንን የሚመረምር እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ደስ እንደምናሰኝ አይደለም» (2፡4)። የሰዎችን ሙገሳ የሚፈልግ ክርስቲያን፥ የእግዚአብሔርን ምስጋና የማግኘት ብቃት ያጣል። ጳውሎስ በባለአደራነት ያከናወነውን የአገልግሎት ባሕርይ ስንመለከት፥ ታማኝነት ምን እንደሆነ እንረዳለን።

1. የአገልግሎቱ ሁኔታ (2፡1-2)፡- ጳውሎስና ሲላስ በፊልጵስዩስ ድብደባና ውርደት ቢደርስባቸውም፥ ወደ ተሰሎንቄ ተጉዘው በዚያ ሰበኩ። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ቢያጋጥመን ብዙዎቻችን የዕረፍት ፈቃድ በወሰድንም ነበር፤ አለበለዚያም በዚህ ሰበብ ከአገልግሎቱ ለመለየት ማመኻኛ ባገኘንም ነበር። ጳውሎስ ግን እንዲህ ዓይነት ሰው አልነበረም። ተስፋ ቆርጦ ወደኋላ የሚያፈገፍግ ሳይሆን፥ በቆራጥነት የሚገሰግስ የእምነት ጀግና ነበር። ለእግዚአብሔር ራስን አሳልፎ ከመስጠት የመነጨ «ቅዱስ ድፍረት» ነበረው። ከእርሱ በፊት እንደነበሩት ሐዋርያት፥ ጳውሎስ በድፍረት የምሥራቹን ቃል አውጇል (የሐዋ. 4፡13፥ 29፥ 31)።

የስብከት አገልግሎቱን የሚያካሄደው «በብዙ ገድል» ነበር። ይህም ተወዳዳሪ አትሌትን የሚያመለክት ሲሆን፥ ትርጉሙም «ውድድር፥ ትግል» ማለት ነው። የግሪኩ ዓለም ከአትሌቲክስ ውድድሮች ጋር የጠበቀ ዝምድና ስለነበረው፥ ጳውሎስ ብዙውን ጊዜ መንፈሳዊ እውነቶችን ለማብራራት በዚሁ አሳብ ይጠቀማል (1ኛ ቆሮ. 9፡24-27፤ ፊልጵ. 3፡13-14፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡7)። የክርስትናን ሕይወት ራስን ሙሉ በሙሉ በመስጠት ከፍተኛ ልምምድ ማድረግን እንደሚጠይቅ ለማሳየት፥ በአትሌቲክስ ውድድር

ምሳሌነት በፊልጵስዩስ 1፡30 ላይ ተጠቅሞበታል። በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን መመሥረት ቀላል አልነበረም—በተሰሎንቄም ቢሆን።

2. የአገልግሎቱ መልእክት (2፡3)፡- «ልመናችን ከስሕተት ... አልነበረም።» በዚህ ስፍራ የመልእክቱን እውነተኛነት አረጋግጦላቸዋል። እንደዚሁም በዚሁ ደብዳቤ ውስጥ ወንጌል የሚለውን ቃል ስድስት ጊዜ ጠቅሶታል። ይህ ስለ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የሚናገረው መልእክት እውነተኛ መልእክትና በእውነተኛነቱም ብቸኛ የሆነ ወንጌል ነው (1ኛ ቆሮ. 15፡1-6፤ ገላ. 1፡6-12)። ጳውሎስ ይህንን ወንጌል ያገኘው ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰው አልነበረም። ከደኅንነት ርቆ የጠፋውን ሰው የሚያድነው ብቸኛው መልካሙ የምሥራች ወንጌል ብቻ ነው።

3. የአገልግሎቱ አነሣሽ ምክንያት (2፡3)፡-አነሣሽ ምክንያቶቹ ንጹሓን ስለነበሩ፥ የ«ርኩሰት» ጥፋት አልነበረበትም። ትክክለኛውን መልእክት በተሳሳቱ አነሣሽ ምክንያቶች በመገፋፋት መስበክ ይቻላል (ፊልጵ. 1፡14-19)። የሚያሳዝነው ደግሞ፥ በጳውሎስ ዘመን አንዳንድ ሰዎች ሃይማኖትን የገንዘብ ማግኛ መንገድ አድርገው ይጠቀሙበት ነበር። ጳውሎስ ወንጌሉን ጉምጅቱን የመሸፈኛ ሽማ አድርጎ አልተጠቀመበትም (2፡5)። በአካሄዱ ሁሉ ግልጽና ታማኝ ሲሆን፥ ለኑሮው መደጎሚያ ለማግኘት ሲል በሥራ ላይ ተሰማርቶ ነበር (2ኛ ተሰ. 3፡8-10)።

ጳውሎስ በገንዘብ ጉዳይ ላይ በጣም ጥንቁቅ ሰው ነበር። ማንም የሃይማኖት ሽቃጭ አድርጎ እንዲቆጥረው ቀዳዳ ለመክፈት አልፈለገም ነበር (1ኛ ቆሮ. 9፡1-18)። ሐዋርያ እንደመሆኑ፥ ከቤተ ክርስቲያን ድጋፍ የማግኘት ዕድል ቢኖረውም፥ ዳሩ ግን አገልግሎቱን ሊያስነቅፍ ከሚችል ከማንኛውም ሐሜት ነፃ ለመሆን ሲል መብቱን እርግፍ አድርጎ ትቷል።

4. የአገልግሎቱ መንገድ (2፡3)፡- ጳውሎስ ሰዎችን ለማሳመን በማታለያ ዘዴ ወይም በተንኰል መንገድ አልተጠቀመም። «ተንኰል» ተብሎ የተተረጐመው ቃል «ከመንጠቆ ላይ ምግብ መጨመር» የሚል አሳብ አለው። በሌላ አባባል ጳውሎስ፥ አንድ ብልጣብልጥ ነጋዴ ሰዎች ዕቃውን እንዲገዙለት በሚያጠምድበት መንገድ፥ ሰዎች ወደ ደኅንነት እንዲደርሱ አላጠመደም ነበር። መንፈሳዊ ምስክርነትና «የክርስትና ንግድ» የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ደኅንነት የእግዚአብሔር ቃልና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ውጤት እንጂ (1፡5)፥ የቀልጣፋ ሙግት ወይም ነገሮችን በተራቀቀ ዘዴ የማቅረብ ፍጻሜ አይደለም።

ብዙውን ጊዜ፥ «መልእክትህ ትክክል እስከሆነ ድረስ፥ ዘዴህ የትኛውም ዓይነት ቢሆን ግድየለኝም» የሚል አባባል እንሰማለን። ይሁንና ወንጌሉ የእግዚአብሔርን አንድያ ልጅ መሥዋዕትነት የጠየቀ ውድ ነገር ሆኖ ሳለ፥ አንዳንድ ዘዴዎች አስጸያፊ በመሆናቸው ለወንጌሉ ደረጃ የማይመጥኑ ናቸው። ወንጌሉ በእግዚአብሔር ክብር ማዕከልነት ላይ ያረፈ ሲሆን፥ እነዚህ ዘዴዎች ግን ዓለማዊና በሰው ማዕከላዊነት ላይ ያተኮሩ ናቸው።

በተሰሎንቄ የሚገኙ የጳውሎስ ጠላቶች የዚሁ አዲስ መልእክት ሽቃጭ እንደሆነ አድርገው ወቀሱት። ብቸኛውና አነሣሽ ምክንያቱም ገንዘብ ማግኘት እንደሆነ በማስመሰል ተናገሩ። በመሆኑም ራሱን ታማኝ ባለአደራ አድርጎ በማቅረብ፥ ጳውሎስ ለእነዚህ ተቺዎች ምላሽ ይሰጣል፤ አንባቢዎቹም እውነቱን እንደተናገራቸው ያውቁ ነበር። (በ 1፡5፤ 2፡1፥ 5፥ 11፤ 3፡3-4፤ 4፡2፤ 5፡2 «ታውቃላችሁ» የሚለውን ቃል ተመልከት።) ጳውሎስ የእግዚአብሔርንና የአማኞቹን ምስክርነት ፈለገ። እርሱ «በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ሁልጊዜ ነውር የሌለባት ሕሊና» ነበረው (የሐዋ. 24፡16)።

ጳውሎስ ማቈላመጥን (ሽንገላን) ይጠላ ነበር (2፡5)። ዳዊትም ይህንን ኃጢአት ይጠላ ነበር። «እርስ በርሳቸው ከንቱ ነገርን ይናገራሉ፤ በሽንገላ [በቁልምጫ] ከንፈር ሁለት ልብ ሆነው ይናገራሉ» (መዝ. [12]፡2)።

በአንድ ወቅት፥ ሌሎችን በማቈላመጥ የሚያነጋግር ሰው ተግባቢ ሳይሆን፥ ሰዎችን ወደፈለገበት አቅጣጫ ለመምራት የሚሞክር መሠሪ እንደሆነ የሚናገር ታሪክ አንብቤ ነበር። ይኸው ማቈላመጥን የሚወድ ሽንጋይ ሰው እውነትን ወይንም ውሸትን በማውራት፥ የሰዎችን ውሳኔዎች ለራሱ ጥቅም ለማዋል ለሚወጥነው ያልተቀደሰ ዓላማ ማሳኪያ ይጠቀምበታል።

አንዳንድ ሰዎች ራሳቸውን ሳይቀር ይሸነግላሉ። «በአንደበቱ ሸንግሎአልና» (መዝ. [36]፡2)። ይህ በመጽሐፈ አስቴር ውስጥ የሚገኘው የዚያ ክፉ ሰው የሐማ ኃጢአት ነበር። ራሱን የማቈላመጡ ጉዳይ እጅግ ስላሳሰበው፥ ይህንኑ ዓላማ ከግብ ለማድረስ አይሁዶችን ሁሉ ለመጨፍጨፍ ሤራ ወጥኖ ነበር።

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርን ለመሸንገል ይጣጣራሉ። «[እስራኤላውያን] በአፋቸው ብቻ ወደዱት፤ በአንደበታቸውም዗ዋሹበት» [መዝ. (78)፡36]። መሸንገል ወይም ማቈላመጥ ሌላው የውሸት ዓይነት

ነው። ልባችን ከእርሱ ርቆ ሳለ፥ በአፋችን ለእግዚአብሔር አንድ ነገር መናገር ማለት ነው (ማር. 7፡6)።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ወዳጆች ለማፍራትም ሆነ ሰዎችን ለመማረክ በተለያዩ የመደለያ ዘዴዎች ይጠቀማሉ። እውነተኛ የወንጌል አገልግሎት ግን በሐቀኝነት (ማለትም በፍቅር) ኃጢአትንና ፍርድን በመዳኘት፥ የማያምነውን ሰው በራስ ከመመካት ከንቱ አዝማሚያ ያድነዋል። የጳውሎስ ዘዴ እንደ አነሣሽ ምክንያቱ ሁሉ ንጹሕ ነበር፤ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የእግዚአብሔርን ቃል አቅርቦ፥ እግዚአብሔር እንደሚሠራ ተማመነ።

## አፍቃሪ እናት (2፡7-8)

የባለአደራ አትኩሮት ታማኝነት ሲሆን፥ የእናት አትኩሮት ደግሞ ገርነት ነው። ሐዋርያ እንደመሆኑ፥ ጳውሎስ ሥልጣን ያለው ሰው ነበር፤ ዳሩ ግን ሁልጊዜም ሥልጣኑን በፍቅር ይጠቀምበት ነበር። በክርስቶስ ሕፃናት ለሆኑት ሰዎች አስፈላጊውን እንክብካቤ ያደርግላቸው ስለነበር፥ የፍቅር መስተንግዶውን ተረድተውት ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ ጳውሎስ ለልጆችዋ እንደምትጠነቀቅ አፍቃሪ እናት ነበር።

ለልጆች እንክብካቤ ለማድረግ ጊዜና ጉልበትን ይጠይቃል። ለአዳዲሶቹ አማኞች ጳውሎስ ራሱ መሥዋዕት ከፍሎ እንክብካቤ አደረገላቸው እንጂ፥ ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች ለሕፃናት ማሳደጊያ በማስረከብ አልረሳቸውም ነበር። ወይም በራሱ የግል አገልግሎት ምትክ «መጽሐፍ እንዲያነቡ» አልነገራቸውም። እርግጥ ጥሩ ክርስቲያናዊ ሥነ-ጽሑፍ አዳዲስ ክርስቲያኖች እንዲያድጉ እገዛ ያደርጋል።

ጳውሎስ አዳዲስ ክርስቲያኖችን በትዕግሥት ያስተናግድ ነበር። የእኔና የባለቤቴ አራቱ ልጆቻችን በአሁኑ ጊዜ አድገው ትላልቅ ሰዎች ሆነዋል፤ ዳሩ ግን እዚህ ከመድረሳቸው በፊት የቱን ያህል ባለቤቴና እኔ በእጅጉ እንደታገሥን ልነግርህ እወዳለሁ። (ይህንን በማካካሱ በኩል እኛንም፥ ወላጆቻችን በጣም ታግሠውናል!) ልጆች ወዲያውኑ አድገው ራሳቸውን አይችሉም። በመሆኑም፥ ልጆች ሁሉ በዕድሜ እየገፉ ሲሄዱ በአንዳንድ በማያስደስቱ ልምዶች ውስጥ ያልፋሉ፤ እየበሰሉ ሲሄዱም የተለያዩ ችግሮችን ይጋፈጣሉ። ፍቅር ስለሚታገሥና ቸርነትንም ስለሚያደርግ (1ኛ ቆሮ. 13፡4)፥ ጳውሎስም ለእነርሱ ከነበረው ፍቅር የተነሣ ታጋሽ ሆነ።

በተጨማሪም ጳውሎስ መግቦአቸዋል። ቁጥር 7፥ «ጡት የምታጠባ እናት የራስዋን ልጆች እንደምትንከባከብ» ተብሎ ሊነበብ ይችላል። ከዚህ

የምንማረው ምንድን ነው? ጡት የምታጠባ እናት የራስዋን ሕይወት ለልጇ ታካፍላለች። ጳውሎስ በቁጥር 8 ላይ የሚለው ይህንኑ ነው። አንዲት ጡት የምታጠባ እናት ልጇን ለሌላ ሞግዚት አሳልፋ ልትሰጥ አትችልም። ሕፃኑ ልጅ ከልቧ አጠገብ፥ በእቅፎችዋ ውስጥ መሆን አለበት።

ጡት የምታጠባ እናት ለእራሷ ምግብ ትመገብና ለልጇ ወደሚስማማ ወተት ትለውጠዋለች። የበሰለው ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል ይመገብና ለወጣት አማኞች ያካፍላል። እነርሱም በዚህ ዓይነት ያድጋሉ (1ኛ ጴጥ. 2፡1-3)። ሕፃን ልጅ እናቱ ከተመገበችው የተበከለ ምግብ የተነሣ ሊታመም ይችላል። ሌሎችን የሚመግብ ክርስቲያንም እንዲሁ ለራሱ ትክክል ያልሆነ ነገር እንዳይመገብ መጠንቀቅ አለበት።

መሥዋዕትነትን ከመክፈል፥ ከመታገሥና ከመመገብ በተጨማሪም፥ እናት ልጇን ትጠብቃለች። ንጉሥ ሰሎሞን በሕይወት የነበረው ልጅ እናት ማን እንደሆነች ለማወቅ የቻለው በዚህ ሐቅ አማካኝነት ነበር (1ኛ ነገሥ. 3፡16-18)። ጳውሎስ ወንጌሉን ብቻ ሳይሆን፥ የገዛ ሕይወቱን ጭምር ለመስጠት ተዘጋጅቶ ነበር። ለተሰሎንቄዎች የነበረው ፍቅር እጅግ የገዘፈ በመሆኑ፥ ቢያስፈልግ ለእነርሱ ለመሞት እንኳ ፈቃደኛ ነበር።

ይሁንና «ጡት የምታጠባ እናት» መሆን ቀላል አይደለም። ለሙሴም ቢሆን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የመንከባከቡ ሸክም ከብዶት ነበር። «አንተ ለአባቶቻቸው ወደማልህላቸው ምድር አደርሳቸው ዘንድ፡- ሞግዚት የሚጠባውን ልጅ እንድታቅፍ በብብትህ እቀፋቸው የምትለኝ፥ በውኑ ይህን ሕዝብ ሁሉ እኔ ፀንስሁትን? ወለድሁትንስ?» (ዘኁ. 11፡12)። ይሁንና ለአዳዲስ ክርስቲያኖች የቃሉን ወተት በማቅረብ ካልተንከባከብናቸው፥ የቃሉን ሥጋ ለማኘክና ለማጣጣም ወደሚችሉበት ከፍተኛ የብስልት ደረጃ ሊደርሱ አይችሉም (ዕብ. 5፡10-14)።

## አሳቢ አባት (2፡9-12)

ጳውሎስ በቆሮንቶስ ለነበሩት ቅዱሳን እንዳደረገው ሁሉ፥ ለተሰሎንቄ አማኞችም «መንፈሳዊ አባት» እንደሆነ ይናገራል። «በክርስቶስ አእላፍ ሞግዚቶች ቢኖሩአችሁ ብዙ አባቶች የሉአችሁም፤ እኔ በክርስቶስ ኢየሱስ በወንጌል ወልጄአችኋለሁና» (1ኛ ቆሮ. 4፡15)። በጳውሎስ አገልግሎት ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ በእግዚአብሔር ቃል ስለተጠቀመ፥ በተሰሎንቄ ብዙ ሰዎች በእግዚአብሔር ቤተሰብነት ዳግም ተወልደው ነበር።

ይሁንና አባት መውለድ ብቻ ሳይሆን፥ ለልጆቹ እንክብካቤም ያደርጋል። የራሱን ሥራ ከሐሰተኛ ክሶች ከመከላከሉ ጐን ለጐን፥ ጳውሎስ በተሰሎንቄዎች መንፈሳዊ አባትነቱ ከሚያከናውናቸው ተግባራት ሦስቱን ይጠቅሳል።

1. *ሥራው* (2፡9)፡- አባት ቤተሰቡን ለማስተዳደር ሲል ይሠራል። ምንም እንኳ የፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች የገንዘብ ድጐማ ቢያደርጉለትም (ፊልጵ. 4፡15-16)፥ ጳውሎስ አሁንም እንኳን ድንኳን በመስፋት ወጪውን ይሸፍንነበር። በመሆኑም፥ ማንም ሰው አገልግሎቱን ለገዛ ጥቅሙ እንደሚያውል አድርጐ ሊወቅሰው አይችልም ነበር። በኋላ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩትን ሰነፍ ክርስቲያኖች ስለ ሥራ ክቡርነት ለማሳመን ይህንኑ እውነታ ተጠቅሞበታል (2ኛ ተሰ. 3 ከቁጥር 6 ጀምሮ)።

ጳውሎስ «ድካም» እና «ጥረት» በሚሉ ቃላት ይጠቀማል። ጄ.ቢ. ፊሊፕስ እነዚህን ቃላት፥ «ትግሎቻችንና ብርቱ ተግባራችን» በማለት ተርጉመዋል። «መማሰንና መከራን መጋፈጥ» የሚለው ሌላው ትርጉም ሊሆን ይችላል። በአንድ ጊዜ ድንኳንን መስፋትና በሌላ ጊዜ ቃሉን ማገልገል ቀላል አይደለም። ጳውሎስ «ቀንና ሌሊት» ተግቶ መሥራቱ የሚያስደንቅ አይሆንም (የሐዋ. 20፡31)። ይህንን ያደረገው አማኞችን ስለወደደና በተቻለ ዓቅም ሊረዳቸው ስለፈለገ ነበር። «እናንተን እንጂ ያላችሁን አልፈልግምና። ወላጆች ለልጆች እንጂ ልጆች ለወላጆች ገንዘብ ሊያከማቹ አይገባቸውምና» (2ኛ ቆሮ. 12፡14)።

2. ኑሮው (2፡10)፡- አባቶች ለልጆቻቸው መልካም ምሳሌዎች በሚሆኑበት ሁኔታ መኖር አለባቸው። እንደዚሁ ሁሉ ጳውሎስ ሕይወቱ በማንኛውም መንገድ መልካም ምሳሌነት እንደነበረው የተሰሎንቄን አማኞች በእማኝነት ሊያቀርብ ይችል ነበር። ከምእመናኑ ውስጥ ጳውሎስን መልካም ምሳሌነት እንዳላሳየ አድርጐ የሚኮንን ማንም ሰው አልነበረም። በተጨማሪም እግዚአብሔር የጳውሎስን ሕይወት አይቷል፤ በመሆኑም፥ ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ በመጠንቀቅ የተሰጠ ሕይወት ስለመኖሩ፥ እግዚአብሔርን በምስክርነት ለማቅረብ አልሠጋም ነበር።

ሕይወቱ ቅዱስ ነበር። ይህ ቃል በግሪክኛ «እግዚአብሔር የሰጠውን ኃላፊነት በጥንቃቄ መፈጸም» ማለት ነው። በመሆኑም የጠለቀ እምነት እንደ

ነበረውና እምነቱም ከአኗኗሩ ይታይ እንደ ነበር፥ ከዚሁ ቃል እንረዳለን። ይኸው ተመሳሳይ ቃል በራእይ 15፡4 እና 16፡5 ላይ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ለመግለጽ ተጠቅሶአል።

እንዲሁም ሕይወቱ ጽድቅ የሚታይበት ነበር። ይህም የባሕርይንና የጸባይን ታማኝነትና ቀጥተኛነት (ቀናነት) ያመለክታል። ይህ «የሕግ ጽድቅ» ሳይሆን፥ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ራሳችንን ለእርሱ በምናስረክብበት ጊዜ በሕይወታችን ውስጥ የሚፈጽመው ነው (ፊልጵ. 3፡4-10)።

በተጨማሪም የጳውሎስ ሕይወት ነቀፋ የሌለበት ነበር። ጠላቶቹ ይከሱት ይሆናል፤ ዳሩ ግን ማንም ሰው ከጳውሎስ ላይ በደል አገኘሁ ብሎ በመረጃ ሊያስረግጥ አይችልም ነበር። ክርስቲያኖች በዓለም ውስጥ ሲኖሩ «ነቀፋና ጉድፍ ባሕርይ የሌላቸው» ሊሆኑ ይገባል (ፊልጵ. 2፡15)።

3. ቃሎቹ (2፡11-12)፡- አባት ተግቶ በመሥራት በሚያገኘው ገንዘብ ቤተሰቡን መደገፍ ብቻ ሳይሆን፥ መልካም ምስሌነትን በማሳየትም ቤተሰቡን ሊያስተምር ይገባል። ከቤተሰቡ አባላት ጋር ለመጫወት ጊዜ መውሰድ አለበት። ጳውሎስ ለእነዚህ አዳዲስ አማኞች በጌታ እንዲያድጉ የሚረዱዋቸውን እውነቶች የማስተማርን አስፈላጊነት ያውቅ ነበር።

ጳውሎስ ከያንዳንዱ አማኝ ጋር በግል የመግባባት ጥበብ ነበረው። «አባት ለልጆቹ እንደሚሆን ለእያንዳንዳችሁ እንደ ሆንን ታውቃላችሁና» (2፡11)። ያንን ያህል ሥራ ቢበዛበትም፥ ጳውሎስ አሁንም ከማኅበረ-ምእመናን አባላት ጋር በግል ለምክር አገልግሎት የሚገናኝበት ጊዜ ነበረው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በርካታ አባላት የሚሳተፉበትን ትልቅ ቡድን ማገልገላቸው መልካም ቢሆንም፥ ከሕዝቡ ጋር አንድ - ለአንድ ተገናኝቶ መወያየቱም አስፈላጊ ነው። ጌታችን ምንም እንኳ እጅግ ለሚበዛ ሕዝብ የስብከት አገልግሎት ቢሰጥም፥ ከግለሰቦች ጋር የሚገናኝበትን ጊዜ አላጣም ነበር። በመሠረቱ፥ ይህ አስቸጋሪ ቢሆንም፥ ዳሩ ግን በትጋት የሚሠራ ሥራ ነው። ይሁንና እግዚአብሔርን የሚያስከብርና ሽልማትም የሚያስገኝ ተግባር ነው።

ጳውሎስ አዳዲስ አማኞችን አበረታቷል። ልጆቹ ቶሎ ብለው ተስፋ እንዳይቆርጡበት የሚፈልገው አባትም ለልጆቹ የሚያደርገው ይህንኑ መሰል ማበረታታት ነው። አዳዲስ ክርስቲያኖች በጌታ የሚያበረታታቸውን ሰው ይሻሉ። «መገሠጽ» የሚለው «አንድን ሰው ማቅረብ፥ ማበረታታት» የሚል

ትርጉም አለው። ይህም ማለት ጳውሎስ ዘልፎአቸዋል ማለት ሳይሆን፥ ይልቁንም ከጌታ ጋር ወደ ፊት እንዲራመዱ አበረታቷቸዋል ማለት ነው።

አንዲት የሬዲዮ አድማጭ ከዝግጅታችን ላገኘችው አበረታች መልእክት የምስጋና ቃላት ያዘለ ደብዳቤ ጽፋልኝ ነበር። እርስዋም፥ «ወደ ቤተ ክርስቲያን በምንሄድበት ጊዜ መጋቢያችን የሚያደርገው ነገር ቢኖር እኛን መዝለፍና በቃላት ጅራፍ ማቆሳሰል ብቻ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ የዚህ ዓይነቱ ስብከት ሰልችቶናል። አንዳንድ የማበረታቻ ቃላት ማድመጡ መንፈስን ያድሳል» ብላ ነበር።

ጳውሎስ ከዚህም በተጨማሪ አማኞችን አጽናንቶአቸዋል። ይህ ቃል ከፍ ብሎ ከቀረበው «ማበረታቻ» ጋር የሚመሳሰል አሳብ ያዘለ ተግባር ላይ የሚያተኩር ነው። ጳውሎስ ያደረገው የተሻለ ስሜት እንዲሰማቸው ብቻ ሳይሆን፥ የተሻለ ነገር ለማድረግ እንዲፈልጉም ጭምር ማነቃቃት ነበር። አባት ልጁን ስሕተቱን ለማረም እንዲጣጣር ማበረታታት እንጂ፥ ማሞላቀቅ የለበትም። የክርስቲያን ማበረታቻ እንቅልፍ የሚያስወስድ ክኒን ሊሆነን አይገባም። ይልቁንም የተሻለ ነገር ለማከናወን የሚያነቃቃን ሊሆን ይገባል።

በመጨረሻም፥ ጳውሎስ አደፋፍሮአቸዋል። ይህም ማለት ጳውሎስ ራሱ ከጌታ ጋር ካሳለፈው የሕይወት ልምምድ በመነሣት መስክሮላቸዋል ማለት ነው። የግል ምስክርነት የመስጠትን አሳብ ያንጸባርቃል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ያደረገልንን ነገር ለአዳዲስ ክርስቲያኖች እንመሰክር ዘንድ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እናልፋለን። «እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል፥ ስለዚህም እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት በመከራ ሁሉ ያሉትን ለማጽናናት እንችላለን» (2ኛ ቆሮ. 1፡4)።

ወላጆች የሆንን ሰዎች ልጆቻችን (በተለይም ወጣቶች) «ድሮ ልጅ ሳለሁ ...» ብለን የምናቀርብላቸውን ታሪክ ለመስማት እንደማይፈልጉ እናውቃለን። ይሁንና ይህ ቤተሰብን ለማሠልጠን ከሚረዱ አስፈላጊ ክፍሎች አንዱ ነው። አንድ «መንፈሳዊ አባት» ከጌታ ጋር ከነበረው ልምምዱ በመነሣት «ልጆቹን» ለማጽናናትና ለመርዳት መቻሉ ግሩም ነው። «ልጆቼ ኑ፥ ስሙኝ፤ እግዚአብሔርን መፍራት አስተምራችኋለሁ» (መዝ. [34]፡11)።

የዚህ ለአማኞች የሚሰጥ አባታዊ አገልግሎት ዓላማ ምን ነበር? ዓላማው ልጆቹ «ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ይመላለሱ ዘንድ» ነው (2፡12)። አንድ

አባት በልጆቹ ለመኩራት እንደሚፈልግ ሁሉ፥ ጌታም በልጆቹ ሕይወት ክብር ሊያገኝ ይሻል። «ከልጆችሽ በእውነት የሚሄዱ አንዳንዶችን ስለአገኘኋቸው እጅግ ደስ ብሎኛል» (2ኛ ዮሐ. 4)። ጳውሎስ በዚህ ሁኔታ በግል ያገለገላቸው እንዴት እንደሚመላለሱ ለማስተማር ከመፈለጉ የተነሣ ነው።

እያንዳንዱ ልጅ እንዴት እንደሚራመድ መማር አለበት። መልካም አርአያ ሊሆኑትና ሊከተላቸው የሚገቡ ምሳሌዎች ያስፈልጉታል። ጳውሎስ «ለእግዚአብሔር እንደሚገባ» ይመላለሱ ዘንድ መክሮአቸዋል (ቈላ. 1፡10 እና ፊልጵ. 1፡27 ተመልከት)። በክርስቶስ ኢየሱስ ላለን ጥሪ እንደሚገባ መመላለስ አለብን (ኤፌ. 4፡1)። እግዚአብሔር ስለጠራን፥ በጸጋው ድነናል፤ የመንግሥቱና የክብሩም አካላት ነን። ይህ ዋስትና ሕይወታችንን ሊገዛውና ጌታን ለማስደሰት እንድንሻ ሊያበረታታን ይገባል።

በቁጥር 12 ላይ የሚገኘው አንቀጽ አገባብ በአሁን ጊዜ የተነገረ ነው፤ «ባለማቋረጥ ለሚጠራችሁ» የሚል አሳብ ይሰጣል። እግዚአብሔር ለደኅንነት የጠራን ሲሆን (2ኛ ተሰ. 2፡13-14)፥ ቅድስናና ታዛዥነት የሰፈነበት ሕይወት እንድንመራ አሁንም ባለማቋረጥ እየጠራን ነው። «ዳሩ ግን፡- እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ» (1ኛ ጴጥ. 1፡15-16)።

ይህ ምንባብ የአዲስ ኪዳንን የተሟላ ትምህርት አስተላላፊነት የሚያመለክት ውብ ምሳሌ ነው። ጳውሎስ ሕፃናትን እንዴት ማሳደግ እንዳለብን አሳይቶናል። በመሆኑም፥ ታማኝ ባለአደራዎች፥ አፍቃሪ እናቶችና አሳቢ አባቶች መሆን አለብን። ለእግዚአብሔር ታማኞች ካልሆንን በስተቀር፥ ልጆቻችንን አንጉል የምናሞላቅቅ ወላጆች ልንሆን እንችላለን። ለልጆች ፍቅርም ቅጣትም አስፈላጊ ነው። እንዲያውም፥ መቅጣት ማፍቀራችንን አጉልቶ ያሳያል።

የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ከከፋ ስደት ባሻገር፥ የተሳካ አገልግሎት ልትሰጥና በብዙ ኪሎ ሜትር ርቀው ለሚገኙ ወገኖች ወንጌልን ለማዳረስ መቻሏ የሚያስደንቅ አይሆንም። ለምን ቢባል፥ በትክክል በመወለዳቸው (ምዕራፍ 1) እና በትክክለኛም እንክብካቤ በማደጋቸው (ምዕራፍ 2) ነው። ይህን እኛም ልንከተለው የሚገባን መልካም ምሳሌ ነው።

## 1ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 13-20

«ስለዚህም የመልእክትን ቃል እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ከእኛ በተቀበላችሁ ጊዜ፥ በእውነት እንዳለ በእናንተ በምታምኑ ደግሞ እንደሚሠራ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል አድርጋችሁ ስላልተቀበላችሁት፥ እኛ ደግሞ እግዚአብሔርን ሳናቋርጥ እናመሰግናለን። እናንተ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በይሁዳ የሚኖሩትን በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉትን የእግዚአብሔርን ማኅበሮች የምትመስሉ ሆናችኋልና፤ እነርሱ ከአይሁድ መከራ እንደ ተቀበሉ፥ እናንተ ደግሞ ያንን መከራ ከአገራችሁ ሰዎች ተቀብላችኋልና። እነዚያም ጌታን ኢየሱስን ደግሞ ገደሉ ነቢያትንም እኛንም አሳደዱ፥ እግዚአብሔርንም ደስ አያሰኙም፥ ሰዎችንም ሁሉ ይቃወማሉ፥ ሁልጊዜ ኃጢአታቸውን ይፈጽሙ ዘንድ አሕዛብ እንዲድኑ እንዳንነግራቸው ይከለክሉናልና። ነገር ግን ቁጣው ወደ እነርሱ ፈጽሞ ደርሶአል።

«እኛ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ በልብ ያይደለ ፊት ለፊት ለጥቂት ጊዜ አጥተናችሁ፥ በብዙ ናፍቆት ፊታችሁን ለማየት እጅግ ሞከርን፤ ወደ እናንተ ልንመጣ ወደን ነበርና፥ እኔ ጳውሎስም አንድና ሁለት ጊዜ፥ ሰይጣን ግን አዘገየን። ተስፋችን ወይስ ደስታችን ወይስ የትምክህታችን አክሊል ማን ነው? በጌታችን በኢየሱስ ፊት በመምጣቱ እናንተ አይደላችሁምን? እናንተ ክብራችን ደስታችንም ናችሁና።»

## - 4 -

# አዲስ አማኞች በማደግ ላይ እያሉ የሚያጋጥማቸው ጫና

አማኞች በስደትና በመከራ አሳርና ፍዳ በሚያዩባት በተሰሎንቄ ውስጥ፥ ክርስቲያን ሆኖ መኖር ቀላል ነገር አልነበረም። በመሆኑም የነበሩበትን ሁኔታ ከጳውሎስ የቃላት አጠቃቀም ልንረዳ እንችላለን፤ ከእነዚህ መካከል «ፍዳ» (1፡6፤ 3፡3) ማለትም «ከሁኔታዎች የሚመጣ ጫና»፥ የጌታችንን ሥቃይ ለመግለጽ ያገለገለው ሥቃይ (መከራ) (2፡14)፥ «ስደት» (2፡15) ማለትም «ከሚኖሩበት ስፍራ መፈናቀል ወይም መገለል»፥ «ተቃውሞ» (2፡15) በኃይል እየነፈሰ አላስኬድ የሚል ነፋስ ለመግለጽ የሚያገለግል ቃል፥ እንዲሁም «መሰናክል» (2፡18) ከመቦርቦሩ የተነሣ ለጉዞ የማይመቸውን መንገድ ለመግለጽ የሚያገለግለው ቃል አንዳንዶቹ ናቸው።

ይሁንና በመከራ መሀል ሳሉ፥ የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ከፍተኛ ደስታ ነበራቸው። የጳውሎስን የቃሉን አገልግሎት «በብዙ መከራ ከመንፈስ ቅዱስ ደስታ ጋር» ተቀበሉት (1፡6)። ጳውሎስ በመከራ ማዕበል ውስጥ ለሚፍገመገሙ ወንድሞቹ ይጨነቅላቸው ነበር፤ ይሁንና ደስታም ይሰማው ነበር (2፡19-20)። ይኸውም የጌታችን የተስፋ ቃል ተፈጻሚነት በማግኘቱ ነው፤ «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ» (ዮሐ. 16፡33)።

አብያተ-ክርስቲያናት ከደኅንነት ርቀው የጠፉትን ለመመለስና ጌታን ለማስከበር በሚፈልጉበት ጊዜ «አዳዲስ አማኞች በማደግ ላይ እያሉ የሚያጋጥማቸው ጫና» ይደርስባቸዋል። ምናልባት (ምንም እንኳ ዛሬም በአንዳንድ የዓለም ክፍሎች የስደቱ መጠን እንደያኔው የቀጠለ ሊሆን ቢችልም፥) የጥንቱ ዘመን ክርስቲያኖች በተንገላቱባቸው ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ መከራዎች ውስጥ ላናልፍ እንችላለን። ይሁንና፥ «በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰልን የምንኖር» ከሆነ፥ ስለስሙ መከራ መቀበላችን አይቀሬ ነው (2ኛ ጢሞ. 3፡12)። ጳውሎስ በዚህ አንቀጽ ውስጥ በመከራና በስደት ጊዜ የምንጠቀምባቸውን መለኮታዊ ምንጮች እንደሚከተለው አብራርቷል።

## በውስጣችን ያለው የእግዚአብሔር ቃል (2፡13)

ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው የኢየሱስ ክርስቶስ የወንጌሉ መልእክት በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ነበር (1፡6)። ደኅንነትን ያስገኝልን ያው ቃል ደግሞ ለክርስቶስ እንድንኖርና ለስሙም መከራን እንድንታገሥ ያስችለናል። የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ቃል ላይ ትክክለኛ መንፈሳዊ አመለካከት ስለነበራቸው፥ ጳውሎስ ያመሰግናቸዋል። ይህም በመከራው ስደት በትዕግሥት እንዲቆሙ ረድቶአቸዋል።

1. ቃሉን በአድናቆት ተቀበሉ፡- ቃሉን እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ፥ እንደ ሰው ቃል አልተቀበሉትም ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ በምንጩ፥ በባሕርዩ፥ በይዘቱና በዋጋው የተለየ ስለሆነ፥ ከቶውንም እንደ ማንኛውም ተራ መጽሐፍ ልንመለከተው አይገባም። መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት (2ኛ ጢሞ. 3፡16)፥ መንፈሱ በተጠቀመባቸው ሰዎች የተጻፈ (2ኛ ጴጥ. 1፡20-21) የእግዚአብሔር ቃል ነው። የእግዚአብሔር ቃል ቅዱስ፥ ንጹሕና ፍጹም ነው [መዝ. (19)፡7-9]። መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በከፍተኛ ድካም ነበር፤ ይህም ድካምና መሥዋዕትነት በጸሐፊዎቹ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ቃል በእርሱ በኩል ይደርሰን ዘንድ ሰው በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስም ላይ የደረሰ ነው።

አንድ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን የሚያይበት ሁኔታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን አመለካከት ያሳየናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው ቃል ሲሆን (ዮሐ. 1፡1፥ 14)፥ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ የተጻፈ ቃል ነው። ይዘታቸው ግን አንድ ዓይነት ነው። ሁለቱም እንጀራ (ዮሐ. 6፡48፤ ማቴ. 4፡4)፥ ብርሃን [ዮሐ. 8፡12፤ መዝ. (119)፡105]፥ እንዲሁም እውነት ናቸው (ዮሐ. 14፡6፤ 17፡17)። መንፈስ ቅዱስ በቅድስት ሴት አማካኝነት ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲወለድ አድርጓል (ሉቃስ 1፡35)፤ እንዲሁም ይኸው መንፈስ በእግዚአብሔር ቅዱሳን ሰዎች አማካኝነት መጽሐፍ ቅዱስ እንዲጻፍ አድርጓል (2ኛ ጴጥ. 1፡20-21)፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘላለም የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ ሲሆን (ሮሜ 1፡25)፥ የእግዚአብሔርም ቃል ለዘላለም ይኖራል (መዝ. [119]፡89፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡23፥ 25]።

ምንም እንኳን ግላዊ የሆነ ስሜቱ ሊሆን ቢችልም፥ ዳሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስን ከወለል ላይ ተጥሎ ወይም ከሌሎች መጻሕፍት ክምር ሥር ተቀምጦ

ለማየት አልወድም። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በርካታ መጻሕፍት ቢኖሩ፥ መጽሐፍ ቅዱስን ከላይ ለማስቀመጥ እጥራለሁ። መጽሐፍ ቅዱስን በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት እንደ ተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል አድርገን ከወሰድን፥ ይህንኑ ግንዛቤአችንንና አድናቆታችንን መጽሐፍ ቅዱሳችንን በምንይዝበት ሁኔታ ጭምር እናሳያለን።

አንተስ ከምግብ ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስ ቢኖርህ ትመርጣለህ? ኢዮብ፥ «ከከንፈሩ ትእዛዝ አልተመለስሁም የአፉን ቃል በልቤ ሰውሬአለሁ» (ኢዮብ 23፡12) ይላል። የእግዚአብሔር ቃል እንጀራ (ማቴ. 4፡4)፥ ወተትና ሥጋ (ዕብ. 5፡11-14)፥ እንዲሁም ማር ነው [መዝ. (119)፡103]። ማርያም ቃሉን ማዳመጡን ስትመርጥ፥ እህቷ ማርታ ግን ምግብ ለማዘጋጀት ሽር-ጉድ አለች (ሉቃ. 10፡38-42)። በመሆኑም ማርያም በረከቱን ስትቀበል፥ ማርታ ድሉን አጣች።

ከገንዘብ ይልቅ የእግዚአብሔር ቃል ቢኖርህ ትመርጣለህ? መዝሙር [119]ን የጻፈው አማኝ የእግዚአብሔር ቃል ከ«ብልጽግና ሁሉ» (ቁ. 14)፥ «ከአእላፋት ወርቅና ብር» (ቁ. 72)፥ «ከወርቅና ከዕንቁ» (ቁ. 127)፥ እንዲሁም ከ«ብዙ ምርኮ» (ቁ. 162) ሁሉ እንደሚበልጥበት ተናግሯል።

በአንድ ወቅት ከአብያተ-ክርስቲያናታችን በአንደኛው ውስጥ አባል የነበሩና በተለይም ልረዳቸው እፈልግ የነበሩ ወጣት ባለትዳሮች ትዝ ይሉኛል። እነዚህ ሰዎች አንድ ቆንጅዬ ትንሽ ልጅ ሲኖራቸው፥ የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ፕሮግራም ለመሳተፍም ሆነ የሰንበት ትምህርት ለመከታተል እምብዛም ፍላጐት አልነበራቸውም። ትንሹ ልጅ የሚያስፈልገውን ክርስቲያናዊ ሥልጠና ለማግኘት አልቻለም። ቤታቸውን በጐበኘሁ ጊዜ ምክንያቱ ምን እንደነበር ተረዳሁ። አባት ብዙ ገንዘብ ለማግኘት ስለፈለገ፥ እጥፍ ክፍያ ለማግኘት በዕለተ-ሰንበት ይሠራ ነበር። በጌታ ቀን መሥራት ባይኖርበትም፥ ከእግዚአብሔር ቃል በላይ ገንዘብን ይወድ ነበር። በመሆኑም፥ ብዙ ገንዘብ ለማግኘት ቢችልም፥ ከቶውንም ገንዘቡን ለማከማቸት አልተሳካለትም ነበር። ይባስ ብሎ ትንሹ ልጅ በመታመሙ ምክንያት ተጨማሪውን ገንዘብ ለሕክምና ለማውጣት ተገደዱ።

ከእንቅልፍ ይልቅ የእግዚአብሔር ቃል ቢኖርህ ትመርጣለህ? «ቃልህን አስብ ዘንድ ዓይኖቼ ለመማለድ ቀደሙ» ([119]፡148)። አይሁዶች ሦስት የሌሊት የመማለጃ ሰዓታት ነበሯቸው፤ ከፀሐይ መጥለቂያ እስከ ምሽቱ 4 ሰዓት፥ ከ4 ሰዓት እስከ 8፥ ከ8 እስከ ንጋት። መዝሙረኛው ከቃሉ ጋር

ለመቆየት በየምሽቱ ሦስት ጊዜ ይነቃና የእንቅልፍ ሰዓቱን ይሠዋ ነበር። ይሁንና እሑድ እንኳ በማለዳ ነቅተው ቃሉን የማያጠኑ አንዳንድ ክርስቲያኖች አሉ።

በመከራችን ድል ለመንሣት ከፈለግን፥ ቃሉን በአድናቆት ማጥናት አለብን። በዚያው መጠን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሊኖረን የሚገባ ሁለተኛ አመለካከት ደግሞ የሚከተለው ነው፡-

2. ቃሉን ከሕይወታቸው ጋር አዛመዱ፡- ጳውሎስ «ተቀበላችሁ» የሚለውን ቃል ለሁለት የተለያዩ ገለጻዎች ይጠቀምበታል። የመጀመሪያው፥ «ከሌላው ሰው መቀበል» ለማለት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ፥ ለእንግዶች «አቀባበል ማድረግ» ለማለት ነው። አንዱ «በጆሮ መስማት» ሲሆን፥ ሌላው «ከልብ መስማት» ማለት ነው። በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞች ቃሉን መስማት ብቻ ሳይሆን፥ ወደ ውስጣቸው በማስገባት ከሕይወታቸው ጋር አዛምደውት ነበር።

ጌታ ኢየሱስ ሰዎችን በተደጋጋሚ ትክክል ስላልሆነው የመስማት ሁኔታ ያስጠነቅቅ ነበር። ዛሬም ቢሆን እነኛ ማስጠንቀቂያዎቹ ለእኛ ያስፈልጉናል፡- «የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ» (ማቴ. 13፡9)። በሌላ አባባል፥ «የምትሰማውን አስተውለህ ስማ» ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ባለህ ዕድል ሁሉ ተጠቀምበት።

ከዚህ በተጨማሪም በማርቆስ 4፡24ም ላይ ሌላ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶናል፡- «ምን እንድትሰሙ ተጠበቁ።» በሰንበት ትምህርት ቤትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አማኞች የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው ሲያበቁ፥ ወዲያውኑ ወደ ቤታቸው ውስጥ ገብተው ከቃሉ ያገኙዋቸውን ገንቢ እውነቶች የሚያስወግዱባቸውን ፕሮግራሞች ከሬድዮናቸው የሚከታተሉበት አጋጣሚ ምንኛ የበዛ ነው! እኔና ባለቤቴ በታላቋ ብሪታንያ ውስጥ የሚገኙትን የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች በጐበኘንበት ወቅት፥ ከቡራኬው በኋላ ምእመናኑ ጸጥ ብለው ተቀምጠው የሚታይባቸውን የመረጋጋት መንፈስ በማጤን በእጅጉ ተደንቀናል። ቃሉን በማሰላሰል መንፈስ ቅዱስ ከሕይወታቸው ጋር እንዲዋሃድ ጊዜ ይወስዳሉ። ይህም በጥድፍያ የቤተ ክርስቲያንን በር ለቆ ከመውጣትና ከጓደኛ ጋር ከመቀላለድ ይልቅ የተሻለና የሰመረ ውጤት ያስገኛል።

የጌታችን ሦስተኛ ማስጠንቀቂያ የሚገኘው በሉቃስ 8፡18 ላይ ነው፡- «እንዴት እንድትሰሙ ተጠበቁ።» ብዙ ሰዎች ግድየለሽ አድማጮች

ስለሆኑ፥ የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረውን እውነት አስተውለው ከሕይወታቸው ጋር አያዛምዱም። እነዚህ ሰዎች «የሚያሳክክ ጆሮ» ስላላቸው፥ ሃይማኖታዊ መዝናኛን ይሻሉ (2ኛ ጢሞ. 4፡3)። አንዳንዶቻቸውም «ጆሮአቸው ስለ ፈዘዙ» (ዕብ. 5፡11) ቃሉን መስማትና በሕይወታቸው ለመተግበር አይፈለጉም። በአንድ ወቅት አብያተ ክርስቲያናት «የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት» የሚራቡና የሚጠሙበት ጊዜ ይመጣል (አሞ. 8፡11)። እጅግ በርካታ አብያተ ክርስቲያናት የእግዚአብሔርን ቃል ስብከት በመዝናኛ ፕሮግራም ስለለወጡት፥ ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለመቀበል የተዘጋጁ አይደሉም።

ቃሉን እንዴት ከሕይወታችን ጋር ልናዛምደው እንችላለን? ቃሉን በመረዳትና ወደ ልባችን በማስገባት፥ የውስጣዊ እኛነታችንም አካል እንዲሆን ተመስጠን በማሰላሰል ነው። ማድቀቅ ለሥጋዊ ሕይወት ሲሆን፥ ማሰላሰል ደግሞ ለመንፈሳዊ ሕይወት የሚሠራ ነው። የምትበላውን ምግብ አድቅቀህ ባትውጥ ትሞታለህ። ቃሉን ለማሰላሰል ጊዜ ይወስዳል፤ ዳሩ ግን ቃሉን ከሕይወት ጋር ለማዛመድና ለማደግ ብቸኛው መንገድ ይኸው ነው።

3. ቃሉን ከሥራ ላይ አዋሉት፡- ቃሉን በእምነት ስለታዘዙ፥ ቃሉ በሕይወታቸው ውስጥ ይሠራ ጀመር። መጽሐፍ ቅዱስን ማድነቅ፥ ወይም ከራስ ሕይወት ጋር ማዛመድ ብቻ በቂ አይደለም። ቃሉን ከተግባር ላይ በማዋል፥ ሰሚዎችና አድራጊዎች ልንሆን ይገባል (ያዕ. 1፡19-25)።

የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔርን ፈቃድ የመፈጸምን ኃይል በውስጡ አቅፎ ይዞአል። «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና» (ሉቃ. 1፡37)። «የእግዚአብሔር ትእዛዛት የእግዚአብሔር የማስቻል ብቃቶች ናቸው» የሚለው አባባል እውነትነት ያለው ነው። ኢየሱስ ሽባውን ሰውዬ እጁን እንዲዘረጋ አዘዘው፤ ይህንንም ድርጊት ሰውዬው በራሱ ጥረት ጨርሶ ሊያደርገው የማይሞክረው ዓይነተኛ ነገር ነበር። ይሁንና ያ ትእዛዝ የሚታዘዝበትን ኃይል አስከተለ። በመሆኑም ቃሉን በመተማመንና በመታዘዝ፥ ፈውስን አገኘ (ማር. 3፡1-5)። የእግዚአብሔርን ቃል አምነን በምንታዘዝበት ወቅት፥ ቃሉ በሕይወታችን ውስጥ ዓላማዎቹን ለማሳካት የሚሠራውን ኃይል ወይንም መለኮታዊ ጉልበት ይልክልናል።

በውስጣችን ያለው የእግዚአብሔር ቃል በፈተናና በመከራ ጊዜያት ታላቅ የኃይል ምንጭ ነው። ቃሉን በልባችን ብናደንቀው፥ ከሕይወታችን ጋር አእምሮአችንን ብናዛምደውና ከተግባር ላይ ፈቃዳችንን ብናውለው፥

ሙሉ ስብእናችን በእግዚአብሔር ቃል ቁጥጥር ሥር ይውልና ከእርሱም ዘንድ ድልን እናገኛለን።

## በዙርያችን የሚገኘው የእግዚአብሔር ሕዝብ (2፡14-16)

በመጋቢነት አገልግሎቴ ውስጥ፥ መከራና ችግር የሚደርስባቸው ሰዎች፥ ብዙውን ጊዜ ወደራስ ወዳድነት ሲያዘንብሉና በመከራ እቶን ውስጥ የሚገኙትም እነርሱ ብቻ እንደሆኑ አድርገው ራሳቸውን ወደመቁጠሩ መቃረባቸውን ተመልክቻለሁ። ሁሉም ሰው እንደ በሽታ፥ ስቃይና የጓደኛ ወይም የዘመድ ሞት በመሳሰሉ ተለምዶአዊና ሰብአዊ መከራዎች ውስጥ ያልፋል። ሆኖም እኔ አሁን፥ እንድንወያይበት የምፈልገው ክርስቲያኖች በመሆናችን የተነሣ ሊያጋጥሙን ስለሚችሉት ችግሮች ብቻ ነው።

ምናልባት ከእምነትህ የተነሣ ቤተሰቦችህ አግልለውህ ይሆናል፤ ወይም ደግሞ ክርስቲያን በመሆንህ ምክንያት የመሥሪያ ቤት እድገት አልፎህ ይሆናል። ምንም እንኳ እነዚህ ሁኔታዎች የሚጐዱን ቢሆኑም፥ በዚህ ዓይነት ሕይወት የምናልፈው እኛ ብቻ አይደለንም። ሌሎችም ክርስቲያኖች በእንደዚህ ዓይነት መከራዎች ውስጥ እያለፉ ሲሆን፥ በሌሎቹ የዓለም ክፍሎች ደግሞ ከዚህ የባሰም መከራ የሚታገሡ አሉ።

የተሰሎንቄ ቅዱሳን ጌታንና ጳውሎስን ብቻ ሳይሆን (1፡6)፥ መከራ በመቀበላቸው የአይሁድ አማኞችንም መስለው ነበር። በይሁዳ የነበሩ ቅዱሳን በአይሁዶች መከራ ሲቀበሉ፥ በተሰሎንቄ የሚገኙ ቅዱሳን ከአሕዛብ መከራ ደርሶባቸው ነበር። ይሁንና ይህ የአሕዛቦች ስደት እንኳ በማያምኑ አይሁዶች የተቀሰቀሰ መሆኑን ልብ በል (የሐዋ. 17፡5፥ 13)። ኢየሱስ ይህ እንደሚሆን ተንብዮ ነበር (ዮሐ. 15፡18-27)።

ምናልባት ጳውሎስ አይሁዶችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመግደላቸውና ክርስቲያኖችን በማሳደዳቸው መውቀሱ፥ አግባብ ያልሆነ «ሃይማኖት አጥባቂነት»ን ማሳየቱ ይሆንን? አይደለም! ይልቁኑስ የታሪኩን ሐቅ እየጠቀሰ ነው። ክርስቶስ በተሰቀለበትና ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተችበት ጊዜ፥ በኢየሩሳሌምና በይሁዳ የሚገኙ ጥቂት አይሁዳውያን የፈጸሙትን ግፍና በደል መነሻ በማድረግ መጽሐፍ ቅዱስ መላ አይሁዳውያንን ጥፋተኛ በማድረግ አንድም ጊዜ አይኮንንም። ሮማውያንም በክርስቶስ መከራና ሞት ላይ ተሳታፊዎች ነበሩ፤ እንደ እውነቱማ ኢየሱስን ለመስቀል ሞት ያደረሰው የእኛው ኃጢአት ነበር (ኢሳ. 53፡6)። በመሆኑም የክርስትና እምነት

ለፀረ-አይሁዳዊነት ስፍራ የለውም። ጳውሎስ ራሱ የገዛ ወገኖቹን ይወድና ለመርዳትም ይፈልግ ነበር (የሐዋ. 24፡17፤ ሮሜ 9፡15)።

እግዚአብሔር እስራኤል ለዓለም ሁሉ በረከት እንድትሆን ጠርቶአት ነበር (ዘፍጥ. 12፡1-3፤ 22፡18)። እግዚአብሔር የተስፋ ቃሎችንና ቃል ኪዳኖችን ከሰው ልጅ ጋር የተጋባው በእስራኤል በኩል ነበር፤ የዓለም አዳኝ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስም የመጣው በእስራኤል በኩል ነበር። «መዳን ከአይሁድ» ነው (ዮሐ. 4፡22)። ታላቁ ክርስቲያን ወንጌላዊ ጳውሎስ እንደ ነበረ ሁሉ፥ የመጀመሪያዎቹም ክርስቲያኖች አይሁዶች ነበሩ።

እንግዲህ የእስራኤል መሪዎች ኢየሱስ ክርስቶስን በአደባባይ የተቃወሙትና ተከታዮቹንም ያሳደዱት ለምን ይሆን? እነዚህ ሰዎች የአባቶቻቸውን ኃጢአቶች ከመድገም በስተቀር ያደረጉት ነገር አልነበረም። የቀደሙ አባቶቻቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ከመምጣቱ ከብዙ ጊዜ በፊት ነቢያትን ያሳድዱ ነበር (ማቴ. 5፡10-12)። ሕጉ ለእግዚአብሔር አዲሱ የጸጋ ኪዳን ጊዜያዊ ዝግጅት ብቻ እንደ ነበር አላስተዋሉም ነበር። የእግዚአብሔርን እውነት በማግለል፥ ሰው-ሠራሽ ወጐቻቸውን ይጠብቁ ነበር (ማር. 7፡1-8)። ጌታችን በሉቃስ 20፡9-19 ያቀረበው ምሳሌ በኃጢአት የተሞላ አመለካከታቸውን ይገልጻል።

የሚያሳዝነው እስራኤል ኃጢአቷን እየፈጸመችና (2፡16) ለፍርድ ቀን ቁጣን እያከማቸች መሆኗ ነው። ይህ አሳብ በዘፍጥረት 15፡16 ላይ የተጠቀሰ ከመሆኑም፥ ኢየሱስ ፈሪሳዊያንን በተቃወመበት በስብከቱ ውስጥ ተጠቅሞበታል (ማቴ. 23፡32)። እግዚአብሔር ኃጢአተኞች ቢያምፁበትም የኃጢአትና የፍርድ ጽዋቸው እስኪሞላ ድረስ በትዕግሥት ይመለከታል። ጊዜው ሲደርስ ግን፥ የእግዚአብሔር ትዕግሥት ያልቅና ፍርዱ ይገለጻል።

በአንድ በኩል፥ እስራኤላውያን ስለተበተኑና በፍልስጤምም ምድር የሚገኘው የተቀረው ወገናቸው በሮም አገዛዝ ሥር ስለሚቀቀ (ዘዳግ. 28 ከቁጥር 15 ጀምሮ ተመልከት)፥ ፍርዱ ቀደም ብሎ ደርሶባቸዋል። ይሁንና ወደ ፊት ከዚህ የባሰ ፍርድ ይጠበቃቸው ነበር። ይህ የሆነው በ70 ዓ.ም. የሮም ሠራዊት ኢየሩሳሌምን በመክበብ፥ ከተማዪቱንና ቤተ መቅደሱን በመደምሰሱ፥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የነበረው ትዕግሥት መሟጠጡን በሐዋርያት የአገልግሎት ዘመን ውስጥ አሳይቷል (ማቴ. 22፡1-11)። በክፉዎች ኃጢአት የተነሣ የጻድቃን መሠቃየት ምንኛ አሳዛኝ እውነታ ነው!

ጳውሎስ በመከራ መሀል የነበሩትን ክርስቲያኖች ያጋጠሟቸው ነገሮች አዲስ ወይም የተለዩ እንዳልሆኑ በመግለጽ ያበረታታቸዋል። ከእነርሱ በፊት ብዙዎች ተመሳሳይ መከራ ተቀብለዋል፤ በዚያን ጊዜም እንኳ ቢሆን እንደእነርሱ የሚሠቃዩ ነበሩ። በይሁዳ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት በመከራው ምክንያት አልጠፉም ነበር፤ ምንም ይሁን ምን፥ በጥራትና በቁጥርም በርክተው ሊጸኑ በቅተዋል። አሳዳጆቹ ግን የቁጣ ጽዋቸውን በላያቸው ላይ እየሞሉና እያፈሰሱባቸው ነበር። ቅዱሳን በፍጹም መዳን ድነዋል (ዕብ. 7፡25)፤ ኃጢአተኞች ግን ፍጹም የከፋ ቁጣ ይጠብቃቸዋል (2፡16)።

ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ታላላቅ እሴቶች አንዱ ይህ ነው፤ በችግር ጊዜ ተደጋግፈን በመቆም እርስ በርሳችን እንበረታታለን። ኤልያስ ተስፋ የቆረጠውና ለመሞት የፈለገው ከሌሎች ታማኝ እስራኤላውያን በተነጠለ ጊዜ ነበር። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ወደ ተሰሎንቄ ከሰደደባቸው ምክንያቶች አንዱ አማኞችን እንዲያጽናና ነበር (1ኛ ተሰ. 3፡1-4)። ብቻውን የቆመ ቅዱስ ሰው ለሰይጣን ጥቃት ይበልጥ የተጋለጠ ነው። በሕይወት ሰልፍ ላይ አንዳችን የሌላችንን ድጋፍ እንሻለን።

## የእግዚአብሔር ክብር በፊታችን (2፡17-20)

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች የነበረውን ፍቅሩን ለመግለጽ አላፈረም ነበር። መንፈሳዊ እናታቸውም አባታቸውም ስለነበር (2፡7፥ 11) «ልጅነታቸውን ያጣው» መስሎ ተሰማው (2፡17) ጳውሎስ በእምነታቸው ሥር ይሰዱና ይጠናከሩ ዘንድ ለመርዳት በዚያ ለመቆየት ፈልጎ ነበር፤ ጠላት ግን ከእዚያ አስወጣው። ይሁንና ልቡ ሁልጊዜም ከእነርሱ ጋር ስለነበር (ፊልጵ. 1፡7 ተመልከት) ከእነርሱ የተለየው በአካል ብቻ ነበር።

ምንም እንኳ ሰይጣን «መንገዱን ቢያፈራርስና መሰናክሎችን ቢያስቀምጥ» (በ2፡18 «አዘገየ» የሚለው ቃል ቀጥተኛ ትርጉም)፥ ጳውሎስ ወደ እነርሱ ለመመለስ የተቻለውን ጥረት ሁሉ ያደርግ ነበር። ጳውሎስ ከእነርሱ ጋር ለመቆየት የነበረው ጥልቅ መሻት፥ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ለመቆየት ከነበረው ብርቱ ፍላጐት ጋር ተመሳሳይ ነበር (ሉቃ. 22፡15)።

ይህም ቢሆን ጳውሎስ ወደ ኋላ ተመልሶ ለመጸጸት አልፈለገም ነበር። ይልቁንም የፊት ፊቱን እያየ ይደሰት ነበር። ለክርስቲያን ከሁሉም የሚልቀው

ነገር ወደ ፊት የሚመጣው ነው። ጳውሎስ በእምነት ወደ ፊት አሻግሮ ተመለከተና ወዳጆቹ የነበሩትን ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ባለበት በክብር ስፍራ ተቀምጠው አየ።

መከራና ፈተና በሚጋረጥብን ወቅት፥ ነገሮችን ሰፋ አድርጎ መመልከቱ ጠቃሚ ነው። ጳውሎስ ባለውም በሚመጣውም የጊዜ ክልል ይኖር ነበር። እንቅስቃሴዎቹን ሁሉ እግዚአብሔር ወደ ፊት በሚያደርገው በጎነት በመተማመን አስገዝቷቸው ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚመለስና ለታማኝነት አገልግሎቱ እንደሚሸልመው ያውቅ ነበር፤ በዚያም ጊዜ፥ የተሰሎንቄ አማኞች ለእግዚአብሔር ክብርን፥ ለጳውሎስ ልብ ደግሞ ደስታን እንደሚያመጡ ያውቅ ነበር። በእንግሊዝኛ ተናጋሪው ኅብረተሰብ ዘንድ ተወዳጅ የሆነ አንድ መዝሙር እንደሚጠቁመን፥ «ኢየሱስን ስናየው፥ ሁሉም የሰመረ ይሆናል።»

አንድ ቀን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት የመቆማችን እውነታ፥ ከችግሮች ሁሉ ባሻገር በታማኝነት እንድናገለግል ሊያነሣሣን ይገባል። ታማኝነት አስፈላጊ ነገር መሆኑን መዘንጋት የለብንም (1ኛ ቆሮ. 4፡2)። በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት በሥራዎቻችን ላይ ፍርድ ይሰጥና ሽልማቶች ይታደላሉ (1ኛ ቆሮ. 4፡1-5፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡9-10፤ ሮሜ 14፡10-12)። ጳውሎስ በመልእክቶቹ፥ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ሽልማቶች እንደ አክሊሎች አድርጎ ይጠቅሳል። ቃሉ የሚያመለክተው፥ የንጉሥን ዘውድ ሳይሆን፥ በውድድሮች አሸናፊ የሆነውን ሰው «የድል አክሊል» ነው። እስጢፋኖስ የሚለው ስም የድል አክሊል ማለት ነው።

ሆኖም ጳውሎስ ምንም እንኳ ይህን ፍንጭ ቢሰጠንም፥ አክሊል እንደሚቀበል ግን አልተናገረም። ይልቁንም በፍርዱ ወንበር ፊት ቅዱሳኑን በሚገናኛቸው ጊዜ፥ እነርሱ ራሳቸው አክሊሎቹ እንደሚሆኑለት ተናግሯል። እርግጥ አንዳንዶች አማኞች እንደሚገባቸው አይኖሩም ነበርና ለጳውሎስ ሸክም ሆነውበት ነበር። ይሁንና የወደፊቱን በተመለከተ ጊዜ የክብር ስፍራ ይዘው እንደተቀመጡ በማየቱ ልቡ በደስታ ተሞላ።

ይህ በመንግሥተ ሰማይ አማኞችን የማግኘቱ ደስታ የጠበቀም ማስጠንቀቂያ ያስተላልፍልናል፤ ይኸውም ባዶ እጃችንን ወደ መንግሥተ ሰማይ ብንሄድ ደስታችንን የምናጣ መሆኑን ነው። ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት በታማኝነት ያልጣረ ክርስቲያን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ የዚህ ደስታና ክብር ተካፋይ ሊሆን አይችልም። «ልጁን መጠባበቁ» ለብቻው በቂ አይደለም (1፡10)። ወደ መንግሥተ ሰማይ በምንደርስበት

ጊዜ ለክብሩ የምናቀርባቸው ሽልማቶች እንዲኖሩን፥ ለእግዚአብሔር ልንመሰክርና ለልጆም ልንሠራ ይገባል። ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ ለሚያመጡ ሰዎች የተዘጋጀ ልዩ ደስታና ሽልማት አለ (ዳን. 12፡3)።

እንዲሁም ደግሞ ሰውነቱን ለእግዚአብሔር ክብር ሲል ለሚገዛና ለሚቆጣጠር አማኝም አክሊል ተዘጋጅቶለታል (1ኛ ቆሮ. 9፡24-27)። ራስን መግዛት የመንፈስ ፍሬ ነው (ገላ. 5፡23)። ሰውነታችን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ስለሆነ እንዳናረክሰው ልንጠነቀቅ ይገባል። ሰውነታችንን በፍጹም መስጠት ማለት ለእርሱ ስም መሥዋዕት እስከመሆን ፈቃደኛ መሆን ማለት ሲሆን፥ ለዚህም አክሊል አለው (ራእይ 2፡10)። የክርስቶስን መገለጽ በናፍቆት የሚጠባበቁ ሰዎች «የጽድቅን አክሊል» ይቀበላሉ (2ኛ ጢሞ. 4፡8)። ታማኙ መጋቢም «የክብርን አክሊል» ሊጠብቅ ይችላል (1ኛ ጴጥ. 5፡4)።

ሆኖም ወደ ፊት የምንቀበላቸውን አክሊሎች በሌሎች ቅዱሳን ላይ መመጻደቂያ አድርገን ልንጠቀምባቸው አይገባም። በራእይ 4፡4 እንደተገለጹት ሽማግሌዎች (የከበረች ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ)፥ አክሊላችንን ከእግሩ ሥር አኑረን ጌታችንን እናመልከዋለን (ራእይ 4፡10)። ሥራችንም ከፍጻሜ የደረሰው በኃይሉና ለክብሩ ስለሆነ፥ ምስጋና ሁሉ ለእርሱ ሊሆን ይገባዋል።

እግዚአብሔር ለእኛ ሽልማቶችን ለመስጠት ቃል መግባቱ ሌላው ጸጋውን የሚያሳየን መረጃ ነው። እግዚአብሔር ካደረገልን ቸርነት የተነሣ አገልግሎታችንን በነፃ የመጠየቅ መብት አለው። እርሱን ለማገልገል የሚያነሣሣን ፍቅር ነው። በምላሽም የምንሰጠው ነገር ይኖረን ዘንድ፥በጸጋው ሽልማቶችን ይሰጠናል።

የተሰሎንቄ አማኞች ይህንን ሲያነቡ፥ እጅግ ሳይበረታቱ አልቀረም። በከፋ ስደትና መከራ ውስጥ እያለፉ ነበርና ምናልባትም አንዳንዶቻቸው እምነታቸውን እስከመተውም ተፈትነዋል።

ጳውሎስ «እምንታችሁን አትተዉ!» በማለት አበረታታቸው። «በኢየሱስ ክርስቶስ ያሉአችሁን መንፈሳዊ ሀብቶች ተጠቀሙባቸው። በውስጣችሁ የእግዚአብሔር ቃል አለ፥ በዙሪያችሁ ደግሞ የእግዚአብሔር ሰዎች፥ በፊታችሁም የእግዚአብሔር ክብር አለ። ተስፋ የምትቆርጡበት ምክንያት የለም።»

## 1ኛ ተሰሎንቄ 3፡ 1-13

«ስለዚህ ወደ ፊት እንታገሥ ዘንድ ባልተቻለን ጊዜ፥ በአቴና ብቻችንን ልንቀር በጎ ፈቃዳችን ሆነ። ስለ እምነታችሁም እንዲያጸናችሁና እንዲመክራችሁ ወንድማችንን የእግዚአብሔርንም አገልጋይ ከእኛ ጋርም አብሮ በክርስቶስ ወንጌል የሚሠራውን ጢሞቴዎስን ላክነው፤ በዚህ መከራ ማንም እንዳይናወጥ፥ ለዚህ እንደተመረጥን ራሳችሁ ታውቃላችሁና። በእውነት ከእናንተ ጋር ሳለን፥ መከራ እንቀበል ዘንድ እንዳለን አስቀድመን እንነግራችሁ ነበር፤ እንዲሁም ደግሞ ሆነ፥ ይህንም ታውቃላችሁ። ስለዚህ እኔ ደግሞ ወደ ፊት እታገሥ ዘንድ ባልተቻለኝ ጊዜ፡- ፈታኝ ምናልባት ፈትኖአችዋል ድካማችንም ከንቱ ሆኖአል ብዬ እምነታችሁን ለማወቅ ላክሁ።

«አሁን ግን ጢሞቴዎስ ከእናንተ ዘንድ ወደ እኛ መጥቶ ስለ እምነታችሁና ስለ ፍቅራችሁ የምስራች ብሎ በነገረን ጊዜ፥ እኛም እናያችሁ ዘንድ እንደምንናፍቅ ታዩን ዘንድ እየናፈቃችሁ ሁልጊዜ በመልካም እንደምታስቡን በነገረን ጊዜ፥ ስለዚህ ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በእምነታችሁ በኩል በችግራችንና በመከራችን ሁሉ ስለእናንተ ተጽናናን፤ እናንተ በጌታ ጸንታችሁ ብትቆሙ፥ አሁን በሕይወት እንኖራለንና። ፊታችሁን ልናይ በእምነታችሁም የጐደለውን ልንሞላበት ሌሊትና ቀን ከመጠን ይልቅ እየጸለይን፥ በአምላካችን ፊት ከእናንተ የተነሣ ስለምንደሰተው ደስታ ሁሉ፥ ለእግዚአብሔር በእናንተ ምክንያት ምን ያህል ምስጋና እናስረክብ ዘንድ እንችላለን?

«አምላካችንና አባታችን ራሱ ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እናንተ መንገዳችንን ያቅና፤ ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ሲመጣ፥ በአምላካችንና በአባታችን ፊት በቅድስና ነቀፋ የሌለበት አድርጐ ልባችሁን ያጸና ዘንድ፥ እኛ ደግሞ ለእናንተ እንደምንሆን ጌታ እርስ በርሳችሁ ያላችሁን ለሁሉም የሚሆን ፍቅራችሁን ያብዛ ይጨምርም።»

## 1ኛ ተሰሎንቄ 3፡ 1-13

«ስለዚህ ወደ ፊት እንታገሥ ዘንድ ባልተቻለን ጊዜ፥ በአቴና ብቻችንን ልንቀር በጎ ፈቃዳችን ሆነ። ስለ እምነታችሁም እንዲያጸናችሁና እንዲመክራችሁ ወንድማችንን የእግዚአብሔርንም አገልጋይ ከእኛ ጋርም አብሮ በክርስቶስ ወንጌል የሚሠራውን ጢሞቴዎስን ላክነው፤ በዚህ መከራ ማንም እንዳይናወጥ፥ ለዚህ እንደተመረጥን ራሳችሁ ታውቃላችሁና። በእውነት ከእናንተ ጋር ሳለን፥ መከራ እንቀበል ዘንድ እንዳለን አስቀድመን እንነግራችሁ ነበር፤ እንዲሁም ደግሞ ሆነ፥ ይህንም ታውቃላችሁ። ስለዚህ እኔ ደግሞ ወደ ፊት እታገሥ ዘንድ ባልተቻለኝ ጊዜ፡- ፈታኝ ምናልባት ፈትኖአችዋል ድካማችንም ከንቱ ሆኖአል ብዬ እምነታችሁን ለማወቅ ላክሁ።

«አሁን ግን ጢሞቴዎስ ከእናንተ ዘንድ ወደ እኛ መጥቶ ስለ እምነታችሁና ስለ ፍቅራችሁ የምስራች ብሎ በነገረን ጊዜ፥ እኛም እናያችሁ ዘንድ እንደምንናፍቅ ታዩን ዘንድ እየናፈቃችሁ ሁልጊዜ በመልካም እንደምታስቡን በነገረን ጊዜ፥ ስለዚህ ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በእምነታችሁ በኩል በችግራችንና በመከራችን ሁሉ ስለእናንተ ተጽናናን፤ እናንተ በጌታ ጸንታችሁ ብትቆሙ፥ አሁን በሕይወት እንኖራለንና። ፊታችሁን ልናይ በእምነታችሁም የጐደለውን ልንሞላበት ሌሊትና ቀን ከመጠን ይልቅ እየጸለይን፥ በአምላካችን ፊት ከእናንተ የተነሣ ስለምንደሰተው ደስታ ሁሉ፥ ለእግዚአብሔር በእናንተ ምክንያት ምን ያህል ምስጋና እናስረክብ ዘንድ እንችላለን?

«አምላካችንና አባታችን ራሱ ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እናንተ መንገዳችንን ያቅና፤ ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ሲመጣ፥ በአምላካችንና በአባታችን ፊት በቅድስና ነቀፋ የሌለበት አድርጐ ልባችሁን ያጸና ዘንድ፥ እኛ ደግሞ ለእናንተ እንደምንሆን ጌታ እርስ በርሳችሁ ያላችሁን ለሁሉም የሚሆን ፍቅራችሁን ያብዛ ይጨምርም።»

## - 5 -

# ጸንተህ ቁም!

አንድ ልጅ ለመራመድ ከመቻሉ በፊት፥ ለመቆም መማር አለበት። ብዙውን ጊዜ አባትና እናት ልጁ እንዲቆምና ከዚያም እንዲራመድ ያስተምሩታል። ጳውሎስ የአማኞቹ «መንፈሳዊ ወላጅ» ቢሆንም፥ ከተሰሎንቄ እንዲወጣ ተገዶአል። እንግዲህ፥ እነዚህን አዳዲስ ክርስቲያኖች በሕይወታቸው በሚገጥማቸው መከራ ውስጥ ጸንተው እንዲቆሙ ሊረዳቸው የሚችለው እንዴት ነው?

ጳውሎስ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች ውስጥ፥ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደ ተወለደችና እንክብካቤ እንደ ተደረገላት አብራርቶአል። አሁን በብስለት ጉዳና ላይ ቀጥሎ ስለሚመጣው ነገር ይናገራል፤ ይህም ቤተ ክርስቲያን እንዴት ጸንታ እንደምትቆም ነው። የዚህ ምዕራፍ ቁልፍ ቃል «መጽናት» የሚል ሲሆን (3፡2፥ 13)፥ ዋናው አሳብ በቁጥር 8 ላይ ተገልጾአል:-«እናንተ በጌታ ጸንታችሁ ብትቆሙ፥ አሁን በሕይወት እንኖራለንና።»

ጳውሎስ እነዚህ አዳዲስ ክርስቲያኖች ጸንተው ይቆሙ ዘንድ፥ የፈጸማቸውን ሦስት አገልግሎቶች ገልጾአል።

## ረዳት ላከላቸው (3፡1-5)

ጳውሎስና አጋሮቹ ከተሰሎንቄ ሲወጡ፥ ወደ ቤርያ በመሄድ በዚያ ቃሉን በማካፈል አገለገሉ። ይሁንና ረብሻ ፈጣሪዎቹ ከተሰሎንቄ ተከትለዋቸው በመሄድ፥ አሁንም ተቃውሞ አስነሡባቸው። ሲላስና ጢሞቴዎስ በቤርያ ሲቀሩ፥ ጳውሎስ ወደ አቴና ዘለቀ (የሐዋ. 17፡10-15 ተመልከት)። ከዚያም ጢሞቴዎስ ከጳውሎስ ጋር በአቴና የተገናኘ ይመስላል (በ1ኛ ተሰ. 3፡1-2 «እንታገሥ ዘንድ» የሚለው ከአንድ የሚበዛ ሰው እንዳለ ያሳያል)፤ ይሁንና ጳውሎስ በመከራ የምትፍገመገመውን አዲስ የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን ይረዳ ዘንድ ጢሞቴዎስን ወደ ተሰሎንቄ መልሶ ላከው። በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ በርካታ አስፈላጊ ነገሮች ተካተዋል:-

1. የጳውሎስ ሸክም (3፡1):- «ስለዚህ» የሚለው የዚህ ምዕራፍ መክፈቻ፥ ጳውሎስ ለአማኞች ያለውን ፍቅር የገለጸበትን 2፡17-20 ያመለክታል። መንፈሳዊ ርዳታ በፈለጉ ጊዜ ችላ ሊላቸው ያልቻለው፥ በዚህ ፍቅር

ምክንያት ነበር። ጳውሎስ ወንጌላዊ ብቻ ሳይሆን፥ መጋቢም ጭምር ነበር። ነፍሳትን ወደ ጌታ ማምጣት፥ እግዚአብሔር ከሰጠው ተልዕኮ አንዱ አካል ብቻ እንደሆነ ያውቅ ነበር። እነዚህ አዳዲስ አማኞች ሊማሩና በእምነትም የጸና መሠረት ሊኖራቸው ይገባ ነበር።

በመሆኑም ጢሞቴዎስ ወደ ተሰሎንቄ ተመልሶ ቅዱሳንን ያጸና ዘንድ በመመረጡ፥ ጳውሎስ በአቴንስ ብቻውን መቅረት ነበረበት። በቁጥር አንድ ላይ «ልንቀር» ተብሎ የተተረጐመው ቃል፥ «ከሚወዱት ሰው በሞት ተለይቶ መቅረትን» ያመለክታል። በ1ኛ ተሰሎንቄ 2፡17 ላይ በተሰሎንቄ የነበሩትን ወዳጆቹን «ወላጅ እንደሌለው» ሆኖ እንደ ተሰማው ገልጾአል፤ ይህም ቃል በግሪኩ «በሞት በመለየት ያለውን ኀዘን» ሊያመለክት ይችላል። ጳውሎስ አደጋ ሲመጣ ተመልክቶ እንደሚፈረጥጥ «ቅጥር የበጐች እረኛ» አልነበረም (ዮሐ. 10፡12-13)። አዳዲስ አማኞችን ትቶ መለየቱ የሞትን ያህል የከበደ ነገር ሆኖበት ነበር።

ይህ ለዛሬዎቹ ክርስቲያን አገልጋዮች ጠቃሚ ትምህርት ነው። ጳውሎስ የተሰሎንቄን አማኞች በጣም ስለወደዳቸው፥ ወደ እነርሱ ለመመለስ ሲል ሕይወቱን በአደገኛ ሁኔታ ላይ ጥሎ ነበር። በፊልጵስዩስ የነበሩትንም አማኞች እጅግ ከመውደዱ የተነሣ ያበረታታቸው ዘንድ፥ ወደ መንግሥተ ሰማይ ከመሄድ ሊቆይ ፈቃደኛ ነበር (ፊልጵ. 1፡22-26)። ወላጆች ለሚወዱአቸው ልጆቻቸው እንደሚያደርጉ ሁሉ፥ ራሱንና ሀብቱን ሊሰጣቸው ፈለገ። «እኔ ግን ስለ ነፍሳችሁ በብዙ ደስታ ገንዘቤን እከፍላለሁ፥ ራሴን እንኳ እከፍላለሁ» (2ኛ ቆሮ. 12፡15)።

2. የጢሞቴዎስ ባሕርይ (3፡2)፡- ሁሉም ክርስቲያን ሌሎችን ክርስቲያኖች በእምነት ለማጽናት የታጠቀ አይደለም። ቢቻል ኖሮ ሁሉም ክርስቲያን ሌሎች ክርስቲያኖች በጌታ እንዲያድጉና በራሳቸው ሁለት እግሮች ጸንተው እንዲቆሙ ለመርዳት የሚያስችል በቂ ብስለት ቢኖረው በተመረጠ ነበር። የሚያሳዝነው ግን፥ አንዳንድ ክርስቲያኖች እንደ እነዚያ በዕብራውያን 5፡11-14 እንደተጠቀሱ ሰዎች ይኖራሉ። በመንፈሳዊ እርምጃቸው የኋሊት ተጉዘው፥ የቃሉን መሠረታዊ እውነቶች ዘንግተዋል። ሌሎችን ከማስተማር ይልቅ፥ እነርሱው ራሳቸው ከሌሎች ዳግመኛ ሊማሩ ያስፈልጋቸዋል። በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ለሁለተኛ ጊዜ በልጅነት ደረጃ ውስጥ ያልፉሉ።

ስለዚህ እነኝህን ጸንተው እንዲቆሙ ለመርዳት ሊላክ የሚገባው ትክክለኛው ሰው ጢሞቴዎስ ነበር። ምን ጊዜም አብያተ ክርስቲያናት በችግር

ውስጥ በሚያልፉበት ጊዜ ጳውሎስ እንደ ሽምጋይ የሚጠቀምባቸው «ልዩ ወኪሎቹ» ጢሞቴዎስና ቲቶ ነበሩ። ጳውሎስ በዚያ የነበሩትን ችግሮች እንዲያቀና ጢሞቴዎስን ወደ ቆሮንቶስ ልኮት ነበር (1ኛ ቆሮ. 16፡10-11)። እንዲሁም ደግሞ በፊልጵስዩስ የነበሩትን ቅዱሳን ይረዳ ዘንድ ይህንኑ ጢሞቴዎስን ለመላክ ዐቅዶ ነበር (ፊልጵ. 2፡19-23)።

አዳዲስ አማኞች በጌታ እንዲያድጉ ሊረዳ የሚችለው ምን ዓይነት ሰው ነው? በቅድሚያ ሰውየው ራሱ ክርስቲያን መሆን አለበት፤ «ወንድማችን ... ጢሞቴዎስ» (3፡2)። እኛ እራሳችን ወዳልነበርንበት ስፍራ ሌላውን ሰው ልንመራ አንችልም፤ የሌለንንም ነገር ለሌላው ልናካፍል አይቻለንም። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በክርስቶስ ወዳለው እምነት መርቶት ስለነበር (1ኛ ጢሞ. 1፡2)፥ በእርግጥም ወንድም ነበር።

በተጨማሪም ጢሞቴዎስ አገልጋይ (ዲያቆኖስ) ነበር። ይህም አገልጋይነትን የሚያመለክት የግሪክ ቃል ሲሆን፥ ዲያቆን የሚለው የአማርኛ ቃል የተገኘው ከ«ዲያቆኖስ» ነው። ጢሞቴዎስ ለማገልገል ወደ ኋላ አላለም ነበር። ከጳውሎስ ጋር በታማኝነት አገልግሎ ስለነበር (ፊልጵ. 2፡22)፥ አብያተ ክርስቲያናትን እንዴት ማገልገል እንደሚቻል ያውቅ ነበር። አዳዲስ ክርስቲያኖችን ማነፅ አስፈላጊ ነገር ነው። እነርሱም በርካታ ችግሮች ያሉባቸው ሲሆን፥ በአመዛኙ በምናስበው ፍጥነት አያድጉም። በመሆኑም፥ እነዚህን ሰዎች ለማስተማር ፍቅርና ትዕግሥት አስፈላጊ ሲሆን፥ ጢሞቴዎስ ደግሞ እነዚህ ብቃቶች ነበሩት።

ጢሞቴዎስ ተባብሮ ለመሥራት የሚመች ሰው በመሆኑ «አብሮአቸው ይሠራ» ነበር። ብቻውን ፊት ፊት እየቀደመ ሌሎች እንዲከተሉት የሚፈልግ ሰው አልነበረም። ሆኖም ከእግዚአብሔር ጋር የሚሠራ ሰው ነበር። በጢሞቴዎስ ውስጥና በጢሞቴዎስ በኩል ሥራውን ከፍጻሜ ለማድረስ የሠራው እግዚአብሔር ነበር (ፊልጵ. 2፡13 እና 1ኛ ቆሮ. 3፡9 ተመልከት)።

ይሁንና ጢሞቴዎስ ከሌሎችም አማኞች ጋር አብሮ ይሠራ ነበር። ጳውሎስን በመታዘዝ ከአቴና ወደ ተሰሎንቄ ተጉዞአል። ከዚያም የተሰሎንቄን ቤተ ክርስቲያን ዜና ይዞ ቆሮንቶስ ወደነበረው ወደ ጳውሎስ ተመልሶአል። ስለዚህ ጳውሎስ ስለእርሱ፥ ሲናገር «እንደ እርሱ ያለ፥ ስለ ኑሮአችሁ በቅንነት የሚጨነቅ፥ ማንም የለኝም» ማለቱ የሚያስደንቅ አይደለም (ፊልጵ. 2፡20)።

3. የቤተ ክርስቲያን ግጭት (3፡3-5)፡- ክርስቲያኖች እንደመሆናችን ወደ ሕይወታችን የሚመጡ መከራዎችና ፈተናዎች በአጋጣሚ የሚከሰቱ አይደሉም፤ በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚመጡ እንጂ! ስለዚህ «ስለ ስሙ» መከራ ለመቀበል ተዘጋጅተን መጠባበቅ አለብን (ፊልጵ. 1፡29)። ለክርስቲያን መከራ የክርስትናው ሕይወት ተለምዶአዊ አካል እንጂ፥ እንግዳ ነገር አይደለም (1ኛ ጴጥ. 4 ከቁጥር 12 ጀምሮ)። ጳውሎስ ከእነርሱ ጋር ሳለ በተደጋጋሚ ይህንኑ እውነት አስገንዝቦአቸዋል። እኛም አዳዲስ አማኞች ለክርስቶስ ለመኖር በሚፈልጉበት ጊዜ መንገዱ ስጋጃ የተነጠፈበት ወላንሳ እንደማይሆንላቸው በመግለጽ ማስጠንቀቅ አለብን። አለዚያ ግን መከራዎች ከተታቸውን ጭነው ሲመጡባቸው ተስፋ ቆርጠው ለሽንፈት ይዳረጋሉ።

በመሠረቱ፥ ከእነዚህ ስደቶች በስተጀርባ የክርስቲያኑ ባላንጣ የሆነው ሰይጣን እንዳለም አንስትም (3፡5)። ሰይጣን ፈታኝ ስለሆነ፥ እምነታችንን ለማናጋት ይሻል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በእምነት ላይ የተደረገውን አጽንኦት ልብ በል (ቁ. 5፥ 6፥ 7፥ 10)። እንደሚያገሣ አንበሳ ሰይጣን አማኞችን ስለሚያውክ፥ «በእምነት ጸንተን» ልንቃወመው ይገባል (1ኛ ጴጥ. 5፡8-9)። ሰይጣን ሔዋንን በፈተናት ጊዜ፥ የተንኮል ሥራውን የጀመረው በእግዚአብሔር ላይ የነበራትን እምነት በማዳከም ነበር፤ «በውኑ እግዚአብሔር ... አዝዞአልን?» (ዘፍ. 3፡1)። ሰይጣን እንደ እባብ ያታልላል (2ኛ ቆሮ. 11፡3)፤ እንደ አንበሳ ያገሣል (1ኛ ጴጥ. 5፡8)። ክርስቲያኑን ለማጥቃትና በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነቱን ለማዳከም ማንኛውንም መንገድ ከመጠቀም አይመለስም።

በቁጥር 3 ላይ «መናወጥ» ተብሎ የተተረጐመው ቃል አስገራሚ ነው። ቀጥተኛ ትርጉሙ «[እንደ ውሻ] ጅራትን በማወዛወዝ፥ ወዳጅነትን መግለጽ» ማለት ነው። የአባባሉም ፍሬ አሳብ ሰይጣን በአመዛኙ አማኙን ወደ ጥፋት ለመምራት በሽንገላና በማታለል (በማቆላመጥ) እንደሚጠቀም ለማመልከት ነው። ሰይጣን ሔዋንን ከተከለከለው ዛፍ ፍሬ ወስዳ ከበላች እንደ እግዚአብሔር እንደምትሆን ነገራት፤እርስዋም በሽንገላው ተታልላ ወደቀች። ሰይጣን አደገኛ ጥቃት የሚያደርሰው በቁልምጫ እንጂ በግልምጫ አይደለም።

የጢሞቴዎስ ተግባር እንግዲህ፥ እነዚህን አማኞች በእምነታቸው ማበረታታት (ማጽናናት) ነበር። በጠላት በምንጠቃበት ጊዜ እግራችን ጸንቶ

እንዲቆም የሚረዳው በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነታችን ነው። በእግዚአብሔር ላይ እምነት ከሌለን፥ ለሽንፈት እንዳረጋለን፤ «ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው» (1ኛ ዮሐ. 5፡4)።

## መልእክት ጻፈላቸው (3፡6-8)

ጢሞቴዎስ ከጳውሎስ ጋር በቆሮንቶስ ተገናኝቶ (የሐዋ. 18፡5)፥ በተሰሎንቄ ነገሮች ሁሉ በመልካም ሁኔታ እየተከናወኑ የመሆናቸውን አስደሳች ዜና አበሰረው። «የምሥራች ብሎ በነገረን ጊዜ» የሚለው ሐረግ፥ «የወንጌሉን የምሥራች መስበክ» ከሚለው ጋር አንድ ዓይነት ነው። ጢሞቴዎስ ያቀረበለት ይህ ዘገባ ለጳውሎስ ወንጌሉን የመስማት ያህል አስደሳች ዜና ነበር።

ጢሞቴዎስ አዳዲሶቹ አማኞች ከመከራው ባሻገር ጸንተው ስለመቆማቸው አስታወቀ። ጠላት ስለ ጳውሎስ ያስወራበትን የሐሰት ዜና ወደ ጐን በመተው፥ አሁንም በከፍተኛ የፍቅር ደረጃ ከጳውሎስ ጋር እንደተሳሰሩ ነበር።

ለዚህም ምላሽ ይሆን ዘንድ ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ መጻፍ ነበረበት። ጳውሎስ የአዲስ ኪዳን አካል ያልሆኑ አንዳንድ መልእክቶችን ጽፎ ነበር (1ኛ ቆሮ. 5፡9)፤ ዳሩ ግን ለተሰሎንቄ አማኞች የተጻፉት ሁለቱ መልእክቶች የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ያለው የእግዚአብሔር ቃል አካላት ናቸው።

ይህም የእግዚአብሔር ቃል አዳዲስ ክርስቲያኖችን በእምነት ለማጽናት ከሚረዱ እጅግ አስፈላጊ መሣሪያዎች አንዱ እንደሆነ ያመለክታል። «እንግዲያስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ጸንታችሁ ቁሙ፥ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ» (2ኛ ተሰ. 2፡15)። ኢየሱስ በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ፥ ሰይጣንን ለማሸነፍ የተጠቀመው በእግዚአብሔር ቃል ነበር (ማቴ. 4፡1-11)። ጳውሎስ የኤፌሶን አማኞች ከሰይጣንና ከአጋንንታዊ ግብረ-አበሮቹ ጋር ሲዋጉ ሳለ፥ «የመንፈስን ሰይፍ» ማለትም «የእግዚአብሔርን ቃል» እንዲይዙ መከሮአቸዋል (ኤፌ. 6፡17)።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያረፈበት በመሆኑ፥ ሊያጸናን ይችላል (2ኛ ጢሞ. 3፡16)። መጽሐፍ ቅዱስ ዓይነተኛው የእግዚአብሔር ቃል እንጂ፥ ሃይማኖታዊ አሳቦች ወይም መልካም የሥነ-ምግባር ምክሮች የተጠራቀሙበት መጽሐፍ አይደለም። በመሆኑም፥ «ለትምህርትና ለተግሣጽ፥ ልብንም ለማቅናት፥ በጽድቅም ላለው ምክር

ደግሞ ይጠቅማል።» «ትምህርት ትክክለኛውን ነገር ሲነግረን፥ ተግሣጽ ደግሞ ትክክል ያልሆነውን ነገር ያሳውቀናል፤ ልብን ለማቅናት የሚሰነዘረው እርማት ትክክል ለመሆን የሚቻልበትን መንገድ ሲጠቁመን፥ ምክር ደግሞ እንዴት በትክክል መኖር እንደሚቻል ያመለክተናል» የሚለው አባባል ማለፍያ ነው።

አንደኛ ተሰሎንቄ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ትምህርቶች የበለጸገ ነው። በእነዚህ አጫጭር ምዕራፎች ውስጥ የእምነቱ ዐበይት ትምህርቶች በሙሉ ተዳስሰዋል። ስለ እግዚአብሔር አብና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገሩ ከአሥር በላይ የሚቆጠሩ ማጣቀሻዎች ሲኖሩ፥ መንፈስ ቅዱስም ቢያንስ አራት ጊዜ ያህል ተጠቅሶአል (1፡5-6፤ 4፡8፤ 5፡19)። በዚህ መልእክት፥ ጳውሎስ ስለ ኃጢአትና ደኅንነት፥ ስለ ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ትምህርት፥ ስለ አገልግሎት ሥራና በተለይም ስለ መጨረሻው ዘመን ሁኔታዎች ገልጾአል። ጳውሎስ በተሰሎንቄ ብዙ ጊዜ ካለማሳለፉም፥ ለአዲስ አማኞቹ ይህን ያህል በርካታ ቁም ነገር ማስጨበጡ አስደናቂ ነው።

ዶክተር አር. ደብልዩ ዴይል ለ50 ዓመታት ያህል፥ በእንግሊዝ አገር ውስጥ የምትገኘውን የካር ሌይን ማኅበረ-ምእመናን ቤተ ክርስቲያን በመጋቢነት አገልግለው ነበር። ምእመኖቻቸው ያመኑትን ነገር ወይም የሚያምኑበትን ምክንያት ካላወቁ በስተቀር፥ በእምነታቸው ጸንተው እንደማይቆሙ በመረዳት፥ በመሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ላይ ተከታታይ ስብከቶችን ማቅረብ ጀምሩ። በዚህም ጊዜ አብሮአቸው የሚያገለግል ሌላ መጋቢ፥ «ምእመናኑ ይህንን ትምህርት በፍጹም መረዳት ስለማይችሉ አይቀበሉትም» በማለት ተናገረ። ዶክተር ዴይልም፥ «መረዳትና መቀበል አለባቸው!» በማለት መለሱ። እንዳሉትም ሆነና፥ ምእመናኑ ትምህርቱን አምነውበት ከመቀበላቸውም ባሻገር ለቤተ ክርስቲያኒቱ ጥንካሬ አጥብቀው የሚያስቡ ሆኑ።

እኔ ክርስቲያን በሆንሁ ጊዜ፥ አብያተ ክርስቲያናት ዛሬ ያለን ዓይነት ለአዲስ አማኞች የሚሰጥ ተከታታይ ትምህርት አልነበራቸውም። እኔ «ለተከታታይ ትምህርት» የተጠቀምሁበት አንድ በግል ጥረቱ የተማረና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ያለው ተራ ሰው ባቀረበው የዕብራውያን መጽሐፍ ጥናት ነበር። አዲስ አማኝ እንደመሆኔ፥ ከተማርኋቸው ነገሮች ብዙዎቹ ከዓቅሜ በላይ ነበሩ። ይሁንና ከዚህ ትምህርት ያገኘሁት እውነት፥ በቃሉ ላይ ሊመሠርተኝና በእምነትም ሊያጸናኝ ችሏል።

ለመንፈሳዊ ዕድገትና ጽናት ተግባራዊ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት በእጅጉ አስፈላጊ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ለግንባታችን የሚረዳ ምግብ (ማቴ. 4፡4)፥ በመንገዳችን የሚመራን ብርሃን [መዝ. (119)፡ 105]፥ እንዲሁም ከጠላት ጥቃት የሚታደግ መጣሪያችን ነው (ኤፌ. 6፡17)። አስተማማኙ መሠረታችን፥ «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል!» የሚለው ነው። እግዚአብሔር አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን ከመሠረተባቸው ምክንያቶች አንዱ አማኞች በቃሉ እንዲያድጉና ከዚያም ለሌሎችም ያድጉ ዘንድ እንዲረዱ ነው (2ኛ ጢሞ. 2፡2፤ ኤፌ. 4፡11-16)።

ጳውሎስ በቃሉ የሚያጸናቸውን ሰው ልኮላቸዋል። የሰውየውም ተልዕኮ የተሳካ ነበር። ሆኖም ጳውሎስ ተሰሎንቄዎችን ያገለገለበት ሦስተኛም መንገድ ነበር፡-

## ጸለየላቸው (3፡9-13)

የእግዚአብሔር ቃልና ጸሎት አብረው ሊሄዱ ይገባል። ነቢዩ ሳሙኤል ለእስራኤል ሕዝብ፥ «ደግሞ መልካሙንና ቅኑን መንገድ አስተምራችኋለሁ እንጂ ስለ እናንተ መጸለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ» ብሏል (1ኛ ሳሙ. 12፡23)። ጴጥሮስም፥ «እኛ [ሐዋርያት] ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን» ብሏል (የሐዋ. 6፡4)። ጳውሎስም ይኸው ተመሳሳይ አጽንኦት ነበረው፤ «አሁንም ለእግዚአብሔርና ያንጻችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ» (የሐዋ. 20፡32)።

ልክ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች እንደ ጸለየው ሁሉ፥ ኢየሱስም እምነታቸው እንዳይጠፋ ለደቀ መዛሙርቱ ጸልዮአል (ሉቃ. 22፡31-32)። ለበርካታ ሳምንታት በኬንያና በዛየር አገልግዬ ነበርና፥ ወደ አገር ቤት በተመለስሁ ጊዜ፥ ከሁሉም በላይ ለወንጌላውያንና ለብሔራዊ አብያተ ክርስቲያናት ጸሎት እንደሚያስፈልግ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ተገነዘብሁ። እዚህ በአገራችን ለሚገኙ አዳዲስ ክርስቲያኖችም ደግሞ መጸለይ አለብን። የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ማስተማር ብቻ በቂ ስለማይሆን፥ በጸሎትም ልንደግፋቸው ይገባል።

ጳውሎስ ለሦስት ግልጽ ጥያቄዎች ጸልዮአል። በመጀመሪያ፥ እምነታቸው ወደ በሳልነት ደረጃ እንዲደርስ ጸልዮአል (3፡10)። ጳውሎስ በመካከላቸው በመገኘት፥ እራሱ የሚያገለግልበትን ሁኔታ ያመቻችለት ዘንድ፥ እግዚአብሔርን ጠይቆታል፤እግዚአብሔር ግን ይህንን ጸሎት

አልመለሰለትም። ጳውሎስ እነርሱን ዳግም ለማየት፥ ሊያገለግላቸውና እምነታቸውን ወደ ብስለት ደረጃ ለማድረስ ይናፍቅ ነበር። «የጐደለውን ልንሞላበት» ተብሎ የተተረጐመው ሐረግ «ማስተካከል፥ ማስታጠቅ፥ ማሰማመር» የሚል አሳብ አለው። ይህ ሐረግ በማርቆስ 1፡19 ላይ መረብን ስለማበጀትም ሳይቀር ጥቅም ላይ ውሏል። እምነታችን ከቶውንም ወደ ፍጹምነት ስለማይደርስ፥ ሁልጊዜም ማስተካከልንና ማሳደግን ይሻል። «ከእምነት ወደ እምነት» እንሻገራለን (ሮሜ 1፡17)።

አብርሃም ለዚህ መመሪያ መልካም ምሳሌ ነው። እግዚአብሔር ወደ ከነዓን ምድር እንዲሄድ ጠርቶት ነበርና እዚያ በደረሰ ጊዜ ረሃብ አጋጠመው። የአብርሃም እምነት ይፈተን ዘንድ፥ እግዚአብሔር ረሃቡ እንዲመጣ ፈቀደ። የሚያሳዝነው ግን አብርሃም በፈተናው ወደቀና ለርዳታ ወደ ግብፅ ወረደ።

እግዚአብሔር በአብርሃም ሕይወት ላይ ያደረሳቸው እያንዳንዳቸው ሁኔታዎች ደረጃ በደረጃ፥ በእግዚአብሔር እንዲታመንና በእምነቱ እንዲያድግ አስችለውታል። እምነት ልክ እንደ ጡንቻ ነው፤ እየተጠቀሙበት በሄዱ መጠን እየፈረጠመና እየጠነከረ ይሄዳል። አብርሃም ከሥጋዊ ወንድሙ ልጅ ከሎጥ የተነሣ ችግር ነበረበት። ከባለቤቱ ከሣራና ከቤት ሠራተኛዋ አጋር የተነሣም እንዲሁ ችግሮች ነበሩበት። ከሁሉም የላቀ የእምነት ፈተና የገጠመው ግን እግዚአብሔር የሚወደውን ልጁን ይስሐቅን እንዲሠዋለት በጠየቀው ጊዜ ነበር።

ሊፈተን የማይችል እምነት ሊታመንበት አይችልም። እግዚአብሔር እምነታችንን የሚፈትነው ሊያጠፋው ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ሊያሳድገው ነው። አብርሃም በረሃቡ እግዚአብሔርን ለመታመን ባይማር ኖሮ፥ ከቶውንም በሌሎች ችግሮች ውስጥ ሊታመነው ባልቻለም ነበር። ጳውሎስ በተሰሎንቄ በመከራ ውስጥ የሚገኙ ክርስቲያኖች በእምነታቸው ያድጉ ዘንድ ጸለየ፤ እግዚአብሔርም ጸሎቱን አደመጠ። ጳውሎስ በሁለተኛው መልእክቱ፥ «ወንድሞች ሆይ፥ እምነታችሁ እጅግ ስለሚያድግ . . . ሁልጊዜ ስለእናንተ እግዚአብሔርን እንደሚገባ ልናመሰግን ግድ አለብን» በማለት ጽፎአል (2ኛ ተሰ. 1፡3)።

የጳውሎስ ሁለተኛ ጥያቄ ፍቅራቸው እንዲበዛ ነበር (3፡12)። የመከራ ጊዜያት የራስ-ወዳድነት ጊዜያት ሊሆኑ ይችላሉ። በአመዛኙ በስደት ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ከፍተኛ ራስ-ወዳድነት ስለሚያጠቃቸው «ስጡኝ» የሚሉ ዓይነቶች ይሆናሉ። ሕይወት ለእኛ የምትቸረን ነገር ሕይወት ከእኛ

በምታገኘው ነገር ላይ ስለሚወሰን፥ የመከራን እቶን ያህል የሰውን ውስጣዊ እውነተኛ ገጽታ የሚያሳይ ምንም ፈተና የለም። በመከራ ጊዜያት አንዳንድ ሰዎች የመለየትን ግድግዳ አበጅተው ራሳቸውን ሲያገሉ፥ ሌሎች ግን ድልድይ በመሥራት ወደ እግዚአብሔርና ወደ ሕዝቡ ይቀርባሉ። ጳውሎስ ለእነኚህ አማኞች የጸለየው ይህንኑ ነበርና እግዚአብሔርም ምላሽ አልነፈገውም፤ «የሁላችሁም የእያንዳንዳችሁ ፍቅር እርስ በርሳችሁ ስለሚበዛ» (2ኛ ተሰ. 1፡3)።

በእግዚአብሔር ላይ የሚኖረን አዳጊ ፍቅር ለሌሎችም እያደገ የሚሄድ ፍቅር ማስከተል አለበት። «እርስ በርሳችሁ ልትዋደዱ በእግዚአብሔር ተምራችኋልና» (1ኛ ተሰ. 4፡9) እንደተባለው ሁሉ፥ ከእነዚህ ትምህርቶች አንዳንዶቹን በበለጠ ሁኔታ ለመማር የሚቻለው በመከራ ውስጥ በማለፍ ነው።

ዮሴፍ ከወንድሞቹ ቀናተኛነትና አሳዳጅነት የተነሣ ለ13 ዓመታት ቢንገላታም፥ ከጥላቻቸው ባሻገር በፍቅር ሊያቅፋቸው ችሏል። የአይሁድ ሕግ አጥባቂዎች ጳውሎስን ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላው እያሳደዱ አሣር ቢያሳዩትም፥ ጳውሎስ ሕዝቡን እጅግ ስለወደደ፥ በፈንታቸው ለመሞት ፈቃደኛ ነበር (ሮሜ 9፡1-3)።

ለጋብቻ የሚዘጋጁትን ወጣቶች በማማክርበት ጊዜ በአመዛኙ ወንዱን፥ «ከተጋባችሁ ከሦስት ሳምንታት በኋላ ባለቤትህ ሽባ ብትሆን፥ ከእርሷ ጋር ለመኖርና ለመንከባከብ የሚያስችል ፍቅር ይኖርሃልን?» ብዬ እጠይቀዋለሁ። እውነተኛ ፍቅር በመከራ ጊዜያት ሥር እየሰደደ ሲሄድ፥ መሠረት የሌለው ፍቅር ግን በመከራ ጊዜ በኖ ይጠፋል።

ይሁንና እውነተኛውን የክርስትና ፍቅር የምናሳየው ለአማኞች ብቻ ሳይሆን፥ «ለሁሉም» ሰው ነው (3፡12)። እርስ በርሳችን ከመዋደዳችን በተጨማሪ፥ ከደኅንነት ርቀው የጠፉትንና ጠላቶቻችንንም ሳይቀር እንወዳቸዋለን። ከልብ የመነጨ ፍቅር ለመስፋፋትና ወደ ሰዎች ሁሉ ለመድረስ የሚችል እንጂ፥ በተወሰኑ ቡድኖች መካከል ብቻ የታጠረ መሆን የለበትም።

የጳውሎስ ሦስተኛ ጥያቄ የሕይወት ቅድስና ነበር (3፡13)። አሁንም አማኙን ለተቀደሰ ሕይወት የሚያነሣሣው የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ነው። የጌታችን መመለስ በክርስትና ሕይወት እንድንጸናም ይረዳናል። ጽናት

ባለበት በዚያ ቅድስና ሊኖር ይችላል፤ ቅድስናም ባለበት በዚያ ዋስትና አለ። በመሆኑም ሁለቱ ጐን ለጐን ይሄዳሉ።

ጳውሎስ ለወዳጆቹ የሚያቀርባቸው ጸሎቶች የግዴለሽነት ወይም ወቅታዊ ክስተቶች ብቻ እንዳልነበሩ ልብ በል። ጸሎቱ «ሌሊትና ቀን» «በሚገባ» የሚከናወን ነበር። ይህ «በሚገባ» የሚለው ቃል በኤፌሶን 3:20 ላይ «እጅግ አብልጦ» ተብሎ ከተተረጐመው ጋር አንድ ዓይነት ነው። እውነተኛ ጸሎት ከባድ ሥራ ነው። ኤጳፍራ ለሰዎች እንዴት መጸለይ እንደሚቻል ከጳውሎስ ሳይማር አይቀርም፤ «በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉ ተረድታችሁና ፍጹማን ሆናችሁ እንድትቆሙ፥ ሁልጊዜ ስለእናንተ በጸሎቱ ይጋደላል» (ቈላ. 4:12)።

በዚህ ጸሎት ውስጥ የሥላሴን ትስስር እንመለከታለን። ጳውሎስ በቁጥር 11 ላይ አብንና ወልድን ጠቅሶአል። በ1ኛ ተሰሎንቄ 3:12-13 ላይ «ጌታችን» የሚለው ቃል በግልጽ ኢየሱስ ክርስቶስን ስለሚያመለክት፥በመጨረሻ ላይ «ጌታ» የሚለው መንፈስ ቅዱስን የሚገልጽ ሊሆን ይችላል። ይህም ከሆነ፥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለመንፈስ ቅዱስ ሲቀርብ ያየሁት ጸሎት ይኸው ብቻ ነው። የተለመደው የመጽሐፍ ቅዱስ የጸሎት አቀራረብ፥ ለአብ፥ በወልድ በኩል፥ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው። መንፈስ ቅዱስ አማኙን ስለሚቀድስና ይህም ጸሎት ለተቀደሰ አኗኗር ተገቢ በመሆኑ፥ አቀራረቡ ትክክል ነው።

ጳውሎስ ምዕራፍ ሁለትን የደመደመው ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ቅዱሳን የሚኖራቸውን ስፍራ በማመልከት ሲሆን፥ ይህንንም ምዕራፍ የፈጸመው በተመሳሳይ መንገድ ነው። በእርሱ በኩል ወደ አዲስ ሕይወት የመጡት ሰዎች፥ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ በቅድስናና ያለነውር በእግዚአብሔር ፊት ይቆሙ ዘንድ ይጸልያል። ጌታ በሚመለስበት ጊዜ አማኞች ሁሉ ክርስቶስን ለመምሰል ስለሚለወጡ (1ኛ ዮሐ. 3:2)፥ የጳውሎስ ልመና በሰማይ ስለሚኖረው የግል ሁኔታችን አይደለም። ሕይወታችን በዚሁ በምድር ላይ እያለ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት የተቀደሰ እንዲሆን መጥቀሱ ነበር። ኃጢአታችንም በዚሁ በምድራዊው ሕይወታችን ይቅር የተባለልን ስለሆነ፥ ዳግመኛ በመንግሥተ ሰማይ ለፈተና አይጋለጥም (ሮሜ 8:1፤ ዕብ. 10:14-18)። ይሁንና ጸባይን ከባሕርይ ለመለየት ስለማይቻል፥ ሥራዎቻችን ለፍርድ ይቀርባሉ።

የጳውሎስ ጸሎት ለጥቂቶች ብቻ ሳይሆን፥ ለአማኞች ሁሉ እንዴት መጸለይ እንደሚቻል ያስተምረናል። እምነታቸው ወደ በሳልነት ደረጃ

እንዲደርስ፥ ፍቅራቸው እንዲጐለብት፥ ብሎም ባሕርያቸውና ጸባያቸው በእግዚአብሔር ፊት የተቀደሰና ነውር የሌለው እንዲሆን መጸለይ አለብን። «በእርሱም ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደሆነ ራሱን ያነጻል» (1ኛ ዮሐ. 3፡3)።

ይህን ምዕራፍ ስንከልስ ሳለ፥ ለአዳዲስ ክርስቲያኖች እንክብካቤ ማድረግ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እንመለከታለን። አንድን ሰው በክርስቶስ ወዳለው እምነት መምራቱ ብቻ አይበቃም። በክርስትና ሕይወቱም ልንመራውና እንዲጸናም ልንረዳው ይገባል። ካልጸና በቀር፥ የስደት ነፋሳት መንፈስ ሲጀምሩ ለመውደቅ ይንገዳገዳል፤ ለውድቀት ይዳረጋል፤ጸንቶ ካልቆመም፥ ከቶውንም እንዴት መራመድ እንደሚቻል ሊማር አይችልም።

ስለዚህ እንዴት ልንረዳው እንችላለን? ልናበረታታውና እያደገም ሳለ ከጐኑ ልንቆምለት እንችላለን። የእግዚአብሔርን ቃል ልናካፍለውና ልንጸልይለት እንችላለን። ጳውሎስስ ያደረገው ይህንኑ አይደል? ጥረቱም ደግሞ ለፍሬ በቅቷል።

## 1ኛ ተሰሎንቄ 4፡ 1-12

«እንግዲህ በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ልትመላለሱ እግዚአብሔርንም ደስ ልታሰኙ እንዴት እንደሚገባችሁ ከእኛ ዘንድ እንደተቀበላችሁ፥ እናንተ ደግሞ እንደምትመላለሱ፥ ከፊት ይልቅ ትበዙ ዘንድ በጌታ በኢየሱስ እንለምናችኋለን እንመክራችሁማለን። በጌታ በኢየሱስ የትኛውን ትእዛዝ እንደሰጠናችሁ ታውቃላችሁና። ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና፤ ከዝሙት እንድትርቁ፥ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አሕዛብ በፍትወት ምኞት አይደለም እንጂ፥ ከእናንተ እያንዳንዱ የራሱን ዕቃ በቅድስናና በክብር ያገኝ ዘንድ እንዲያውቅ አስቀድመን ደግሞ እንዳልናችሁና እንደ መሰከርንላችሁ፥ ጌታ ስለዚህ ነገር ሁሉ የሚበቀል ነውና ማንም በዚህ ነገር አይተላለፍ ወንድሙንም አያታልል። ለርኩሰት ሳይሆን እግዚአብሔር በቅድስና ጠርቶናልና። እንግዲህ የሚጥል ሰውን የጣለ አይደለም፥ መንፈስ ቅዱስን በእናንተ እንዲኖር የሰጠውን እግዚአብሔርን ነው እንጂ።

«እናንተ ራሳችሁ እርስ በርሳችሁ ልትዋደዱ በእግዚአብሔር ተምራችኋልና ስለ ወንድማማች መዋደድ ማንም ይጽፍላችሁ ዘንድ አያስፈልጋችሁም፤ እንዲሁ በመቄዶንያ ሁሉ ላሉት ወንድሞች ሁሉ ታደርጋላችሁና። ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ከፊት ይልቅ ልትበዙ፥ በጸጥታም ትኖሩ ዘንድ ልትቀኑ፥ የራሳችሁንም ጉዳይ ልትጠነቀቁ፥ እንዳዘዝናችሁም፥ በውጭ ባሉት ዘንድ በአገባብ እንድትመላለሱ፥ አንዳችም እንዳያስፈልጋችሁ በእጃችሁ ልትሠሩ እንለምናችኋለን።»

# - 6 -

## አባትህን እንዴት ደስ ታሰኘዋለህ?

በአሁኑ ጊዜ፥ ከሶምሶማ ሩጫ ልምምድ ጐን ለጐን የሽርሽር ጉዞ ማድረግ በየጐዳናዎቹ ላይ የሚዘወተር ተወዳጅ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ እየሆነ መጥቷል። በቺካጐ ከተማ ውስጥ ሳልፍ፥ ብዙውን ጊዜ ግለሰቦችና ጠቅላላው ቤተሰብ በመናፈሻዎች ወይም በዛፎች መሀል እየተንሸራሸረ ሲደሰት እመለከታለሁ። አንዳንድ ጊዜ በዋና ዋና ጐዳናዎች ላይ በማሽከረከርበት ወቅት፥ ራቅ ወዳሉ የቀጠሮ ቦታዎች በእግራቸው ለሚጓዙ «የሽርሽር ጉዞ ጓደኞቼ» እጆቼን በማወዛወዝ ሰላምታ እሰጣለሁ።

የክርስትና ሕይወት ከጉዞ (ከመመላለስ) ጋር ሊወዳደር ይችላል። እንዲያውም፥ ይህ ከጳውሎስ ተወዳጅ የማብራርያ ምሳሌዎች አንዱ ነው፡- «በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ» (ኤፌ. 4፡1)፤ «አሕዛብ ደግሞ በአእምሮአቸው ከንቱነት እንደሚመላለሱ ከእንግዲህ ወዲህ እንዳትመላለሱ እላለሁ» (ኤፌ. 4፡17)፤ «በፍቅር ተመላለሱ» (ኤፌ. 5፡2)፤ «እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ» (ኤፌ. 5፡8)።

የክርስትና ሕይወት የሚጀምረው በእምነት እርምጃ ሲሆን፥ ያ እርምጃ በእምነት ወደ መመላለስ ይመራል፤ «በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና» (2ኛ ቆሮ. 5፡7)። መመላለስ እድገትን ስለሚያመለክት፥ በክርስትና ሕይወታችን ማደግ አለብን (ዕብ. 6፡1፤ ፊልጵ. 3፡13-16)። በተጨማሪም ጉዞ ጥንካሬን ስለሚጠይቅ፥ እግዚአብሔር «እንደ ዕድሜህ እንዲሁ ኃይልህ ይሆናል» በማለት የተስፋ ቃል ሰጥቶአል (ዘዳግ. 33፡25)።

ዳሩ ግን ጠላት ወጥመድን ስለሚዘረጋና ሊያጠምደንም ስለሚፈልግ፥ «በብርሃን ስለመመላለሳችን» እርግጠኞች ልንሆን ይገባል (1ኛ ዮሐ. 1፡5-7)። በመሠረቱ፥ የሕይወትን ጉዞ ስናጠናቅቅ፥ ጌታ ወዳለበት ስፍራ እንሻገራለን። «ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም፥ እግዚአብሔር ወስዶታልና» (ዘፍ. 5፡24)።

ጳውሎስ ክርስቲያኑ ሊመላለስበት የሚገባ ሦስት ገጽታ ያለው ጉዞ (መመላለስ) አስፍሯል፡-

## በቅድስና ተመላለሱ (4፡ 1-8)

በሮም ግዛት ውስጥ ሥነ-ምግባራዊው ሁኔታ ጤነኛ አልነበረም። ምግባረ-ብልሹነት ተለምዶአዊ የአኗኗር ስልት ሲሆን፥ በባሪያዎች ጉልበት መገልገሉ የተለመደ ነበረና፥ ሕዝቡ በምኞት ተንደላቅቀው ለመኖር አመቺ ሆኖላቸው ነበር። የተቀደሰ አኗኗርን የሚሰብከው ክርስቲያናዊ መልእክት ለባህሉ እንግዳ ከመሆኑም፥ ለእነዚህ አዳዲስ ክርስቲያኖች በዙሪያቸው የሚስተዋለውን ፈተና መቋቋም የዋዛ አልነበረም። ጳውሎስ ለምን ከወሲብ ምኞቶች ርቀው የተቀደሰ ሕይወት መኖር እንዳለባቸው አራት ምክንያቶችን ይሰጣል፡-

1. እግዚአብሔርን ለማስደሰት (4፡1)፡- ሁሉም ሰው ሌላውን ሰው ለማስደሰት በሚያስችል መልኩ ሕይወቱን ይመራል። ብዙዎች ግን የሚያስደስቱት ራሳቸውን ሆኖ ይገኛል። በመሆኑም እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች ለሌሎች ሰዎች ግድ የላቸውም። ዊልያም ሐዝሊት፥ «የአንድ ጉዞ ሕይወት ነፃነት ሆኖ፥ ይኸውም ለማሰብ፥ ስሜትን ለመግለጽ፥ ሰው እንዳሻው ለመሆን የሚችልበት ፍጹም ነፃነት ነው» በማለት ጽፎአል። ያ ምክር ምናልባት በመዝናናት ላይ ለሚገኝ ሰው ሊሠራ ይችል ይሆናል፤ በዕለት-ተዕለት የሕይወት ጉዳዮች ውስጥ ግን ከቶውንም ስፍራ ሊኖረው አይችልም። ክርስቲያኖች ራሳቸውን ብቻ እያስደሰቱ የሕይወትን ጉዞ ሊቀጥሉ አይችሉም (ሮሜ 15፡10)።

ሌሎችን በማስደሰቱም ጉዳይ ላይ ልንጠነቀቅ ይገባል። ሌሎችን እያስደሰቱ እግዚአብሔርንም ማስከበር ይቻላል፤ዳሩ ግን እግዚአብሔርን አለማስከበርም ሊከተል ይቻላል። «አሁንም ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም» (ገላ. 1፡10)። ጳውሎስ በተሰሎንቄ ሲያገለግል ሳለ ዝንባሌው ይኸው ነበር። «ልባችንን የሚመረምር እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ደስ እንደምናሰኝ አይደለም» (1ኛ ተሰ. 2፡4)።

እግዚአብሔርን ማስደሰት የክርስትና ሕይወት ዐቢይ ዓላማ ሊሆን ይገባል። ልጆች አባታቸውን በሚያስከብር መልኩ መኖር አለባቸው። መንፈስ ቅዱስ «ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም» በእኛ ውስጥ ይሠራል (ፊልጵ. 2፡13)። ሄኖክ ከእግዚአብሔር ጋር ስለተመላለሰ፥ እግዚአብሔር ወደ መንግሥተ ሰማይ ሳይጠራው በፊት፥ «እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመስክሮለታል» (ዕብ. 11፡5)። ኢየሱስ፥ «እኔ ደስ የሚያሰኘውን ዘወትር አደርጋለሁና» ብሏል (ዮሐ. 8፡29)።

እግዚአብሔርን ማስደሰት፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከማድረግ የላቀ ትርጉም አለው። እግዚአብሔርን መታዘዝና ዳሩ ግን አለማስደሰት ይቻላል። ለዚህ ዮናስ ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል። እግዚአብሔርን ቢታዘዝና የታዘዘውን ቢፈጽምም፥ ልቡን ግን በትእዛዙ ላይ አላሳረፈም ነበር። በዚህም ጊዜ እግዚአብሔር ቃሉን ባርኮታል፤ ዳሩ ግን ባሪያውን ሊባርክ አይችልም ነበር። በመሆኑም፥ ዮናስ እግዚአብሔርን ጨምሮ ከሰው ሁሉ ጋር በመቀያየም ከነነዌ ከተማ ደጃፍ ላይ ተቀመጠ። መታዘዛችን «የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርጉ እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ አትሁኑ» የሚለውን ምክር ያገናዘበ ሊሆን ይገባል (ኤፌ. 6፡6)።

እግዚአብሔርን የሚያስደስተው ምን እንደሆነ እንዴት እናውቃለን? ምድራዊ አባታችንን የሚያስደስተው ነገር እንዴት እንደሆነ በምን እናውቃለን? እርሱን በመስማትና ከእርሱ ጋር በመኖር ነው። ቃሉን ስናነብና በአምልኮና በአገልግሎት ከእርሱ ጋር ኅብረት ስናደርግ፥ የእግዚአብሔርን ልብ እያወቅን እንሄዳለን፤ ይህም ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይመራናል።

2. እግዚአብሔርን ለመታዘዝ (4፡2-3)፡- ጳውሎስ በተሰሎንቄ ሲያገለግል ሳለ፥ የግል ንጽሕናን በተመለከተ ለአማኞች የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሰጥቷል። «ትእዛዝ» የሚለው ወታደራዊ ቃል ሲሆን፥ ከበላይ አካላት የሚመጡትን መመሪያዎች ያመለክታል። እኛ በእግዚእብሔር የጦር ሠራዊት ውስጥ የምንገኝ አገልጋዮች ስለሆንን፥ ትእዛዛትን መቀበል አለብን። «የሚዘምትው ሁሉ ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም» (2ኛ ጢሞ. 2፡4)።

በቁጥር 3 ላይ፥ ጳውሎስ ለእነዚህ አዳዲስ አማኞች ወሲባዊ ምኞትና ዝቅጠት እግዚአብሔርን እንደማያስከብር አስታውሶአቸዋል። እግዚአብሔር ወሲብን ስለፈጠረ፥ አጠቃቀሙንም የማዘዝ ሥልጣን አለው። ከጅማሬው፥ ጋብቻን በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚፈጸም የተቀደሰ ጥምረት አድርጎ መሥርቷል። እግዚአብሔር ወሲብን የፈጠረው ዘርን ለመቀጠልና ለተጋቢዎቹ ምቾት በማሰብ ነበር። «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር፥ መኝታውም ንጹሕ ይሁን» (ዕብ. 13፡4)። ወሲብን በተመለከተ የቀረቡት የእግዚአብሔር ትእዛዛት የሕዝቡን ደስታ ለመንጠቅ የታለሙ ሳይሆኑ፥ ደስታቸው እንዳይጠፋባቸው ለመጠበቅ የተሰጡ ናቸው። «አታመንዝር» የሚለው ትእዛዝ ጋብቻን እስር ቤት ሳይሆን ይልቁንም ጤነኛና ውብ የሚያደርገው የአትክልት አጥር ነው።

ይህን በተመለከተ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን ይሆን ስንል ለማወቅ መሻት የለብንም፤ ስለምን በግልጽ ነግሮናልና። ትእዛዙ «ከዝሙት ሽሹ» የሚል ሲሆን፥ የትኛውም ዓይነት ዘመን አመጣሽ ሥነ-መለኮት ወይም ፍልስፍና ይህንን የመለወጥ ብቃት አይኖረውም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዳር እስከ ዳር እግዚአብሔር የወሲብ ኃጢአትን በተመለከተ ጥብቅ ማስጠንቀቂያዎችን ይሰጣል፤እነዚህንም ማስጠንቀቂያዎች ልብ ማለት ያሻል። የእግዚአብሔር ዓላማ ቅዱሳን እንሆን ዘንድ ነው። ይኸውም በአእምሮአችንና በልባችን ተቀድሰን በተለየ አኗኗር እንመላለስ ዘንድ ነው።

3. እግዚአብሔርን ለማስከበር (4፡4-5)፡- ይህ የእግዚአብሔር ትእዛዝ አዎንታዊ ገጽታ ነው። ክርስቲያኖች ካልዳኑ ሰዎች እንዲለዩ ተነግሮአቸዋል። አሕዛብ (ያልዳኑ ሰዎች) እግዚአብሔርን ስለማያውቁ፥ፈሪሃ-እግዚአብሔር የሌለበትን ሕይወት ይመራሉ። ይሁንና እኛ እግዚአብሔርን ስለምናውቅ፥በዚህ ዓለም ውስጥ እርሱን እንድናስከብር ታዘናል። «ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና ከዝሙት እንድትርቁ» (1ኛ ተሰ. 4፡3)።

በቁጥር 4 ላይ «የራሱን ዕቃ ያገኝ ዘንድ» የሚለው ምናልባት «ሰውነቱን እንዲቆጣጠር» ለማለት ይሆን ይሆናል፤ ሰውነታችን የእግዚአብሔር ዕቃ ነውና (2ኛ ቆሮ. 4፡7፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡20-21 ተመልከት)። እንዲሁም ሚስት «ደካማ ፍጥረት [ዕቃ]» ስለተባለች (1ኛ ጴጥ. 3፡7)፥ «ከራሱ ሚስት ጋር ለመኖር እንዲማር» የሚል ትርጉም ሊኖረው ይችላል። ጳውሎስ የጻፈው ለተጋቡት ብቻ ሳይሆን፥ ለሁሉም ክርስቲያኖች ነውና በበኩሌ ሁለተኛውን አተረጓጎም እመርጣለሁ። የወሲብን ኃጢአት የሚፈጽም ክርስቲያን በሥጋው ላይ ኃጢአት ከመፈጸሙም በላይ (1ኛ ቆሮ. 6፡19-20)፥ ለእግዚአብሔርም ከአማኙ የሕይወት ምስክርነት ሊቀበል የሚገባውን ክብር የሚነፍገው ይሆናል።

ይህም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚገኙ መንፈሳዊ መሪዎች እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነት መመሪያ የሰጠበትን ምክንያት ያስረዳናል (1ኛ ጢሞ. 3)። መንፈሳዊ መሪዎች በቤታቸው ውስጥ ለማስተዳደር እስካልቻሉ፥ እንዴትስ ቤተ ክርስቲያንን ሊመሯት ይችላሉ? እግዚአብሔርን በአካላችን (በሥጋችን) ውስጥ ለማስከበር ከቻልን፥ አካሉ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥም ልናስከብረው እንችላለን።

4. ከእግዚአብሔር ፍርድ ለማምለጥ (4:6-8):- እግዚአብሔር ለሰብአዊ ክብር የሚያጐበድድ አምላክ አይደለም፤ ልጆቹ ኃጢአት በሚፈጽሙበት ጊዜ ይቀጣቸዋል (ቈላ. 3:23-25)። አንዲት ምእመን የቤተ ክርስቲያኗ መጋቢ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ የሚፈጸመውን ኃጢአት በመቃወም ስለ ሰበከ ትተቸው ጀመር። ይህችው ሴት «በአማኝ ሕይወት ውስጥ የሚፈጸም ኃጢአት ባልዳኑ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ከሚፈጸመው የተለየ ነው» ስትል ተሟገተች። መጋቢውም፥ «አዎን፥ የአማኙ የከፋ ነው» በማለት መለሰላት።

ክርስቲያን ኩነኔ እንደሌለበት የታወቀ ቢሆንም (ዮሐ. 5:24፤ ሮሜ 8:1)፥ የሥጋን ሥራ በሚዘራበት ጊዜ ከሚከተለው የኃዘን አዝመራም ነፃ እንዳልሆነ ትክክል ነው (ገላ. 6:7-8)። ንጉሥ ዳዊት ዝሙት በፈጸመ ጊዜ ኃጢአቱን ለመሸሸግ ቢሞክርም፥ ዳሩ ግን እግዚአብሔር በከፋ ሁኔታ ቀጥቶታል (በእነዚህ ወራት ውስጥ ያጣውን ሰላም ለማጤን፥ መዝሙር [32]ንና መዝሙር [51]ን አንብብ)። ዳዊት ኃጢአቱን በተናዘዘ ጊዜ እግዚአብሔር ይቅር ቢለውም፥ዳሩ ግን እግዚአብሔር የኃጢአቱን ውጤቶች ለመለወጥ አልቻለም። ዳዊት የዘራውን አጭዶአል፤ ይህም መፈፍ ኃዘንን አስከትሎበታል።

ይሁንና አንድ ክርስቲያን «እኔ ከእግዚአብሔር ምርጦች አንዱ ነኝ» በማለት ሊሟገት ይችላል። «እኔ የእርሱ ነኝና ከቶውንም ወደ ውጭ ሊጥለኝ አይችልም» ሊልም ይችላል። መረዳት ያለብን ምርጫ በቅድስና እንድናድግ የሚያበረታታን እንጂ፥ የኃጢአት ማመካኛ እንዳልሆነ ነው። «ለርኩሰት ሳይሆን እግዚአብሔር ለጽድቅ ጠርቶናልና» (4:7)። «የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ» (1ኛ ጴጥ. 1:15)። የምርጫ ዕድል በተጨማሪም የመታዘዝን ኃላፊነቶች ያካትታል (ዘዳግ. 7:6፥ 11)።

የቅድስና ሕይወት (ከጠራን) ከእግዚአብሔር አብ፥ (ከሞተልን) ከእግዚአብሔር ወልድና (በውስጣችን ከሚኖረው) ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ማድረግን ያጠቃልላል። ሰውነታችንን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሚያደርገው የመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መኖር ነው። በተጨማሪም፥ በሥጋ ምኞት ላይ ድልን የምንቀዳጀው በመንፈስ በመመላለስ ነው (ገላ. 5 ከቁጥር 16 ጀምሮ)። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ማናናቅ ማለት የእግዚአብሔር ፍርድ በእኛ ላይ እንዲደርስ ማድረግና የእግዚአብሔርን መንፈስ ማሳዘን ማለት ነው።

የእግዚአብሔር መንፈስ ከወሲብ ዝቅጠት የጠራ ንጹሕ ሕይወት እንድንኖር የሚረዳን እንዴት ነው? በመጀመሪያ ደረጃ፥ በውስጣችን የተቀደሱ መሻቶችን ስለሚፈጥር፥ ለተበከለው የሥጋ ግሳንግስ ሳይሆን (ሮሜ 13፡12-14)፥ ለእግዚአብሔር ንጹሕ ቃል ጥማት ይኖረናል (1ኛ ጴጥ. 2፡1-3)። በተጨማሪም፥ ቃሉን በማስተማር በፈተና ጊዜ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች እንድናስታውስ ይረዳናል (ዮሐ. 14፡26፤ ኤፌ. 6፡17)። ራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ አሳልፈን በምንሰጥበት ጊዜ፥ በዓለምና በሥጋ ምኞቶች ሳንጠመድ በቅድስና እንድንመላለስ ኃይልን ያለብሰናል። በመሆኑም የመንፈስ ፍሬ የሥጋን ሥራዎች ድል ይነሣል (ገላ. 5፡16-26)።

የወሲብ ንጽሕና ጉዳይ በወቅቱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዐቢይ ችግር ስለነበር፥ ጳውሎስ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በስፋት ጽፎበታል። ዛሬም ቢሆን የወሲብ ንጽሕና ጉዳይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዐቢይ ችግር ነው። ለበርካታ ሰዎች፥ የጋብቻ ቃል ኪዳኖች እንደ ቅዱስ ነገር ካለመቆጠራቸውም በላይ፥ ፍች (በአማኞች መካከል ሳይቀር) ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ መፈጸሙን እንመለከታለን። ወንዶች-ከወንዶችና ሴቶች-ከሴቶች ጋር የወሲብ ግንኙነት እየፈጸሙ፥ ዳሩ ግን ክርስቲያኖች ነን የሚሉባቸው አካባቢዎችም አሉ። በብዙ ስፍራዎች በሚገኙ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ውስጥ ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የወሲብ ግንኙነትና «ለወሲባዊ ክንዋኔ የሚገፋፉ ክርስቲያናዊ ሥነ-ጽሑፎች (ፖርኖግራፊ)» ተቀባይነት የተሰጣቸው ናቸው። ይሁንና እግዚአብሔር «በቅድስና ተመላለሱ» ብሎናል።

## በመተባበር ተመላለሱ (4፡9-10)

ከቅድስና ወደ ፍቅር የሚደረገው ሽግግር አስቸጋሪ አይደለም። ጳውሎስ ይህንኑ ሽግግር በ1ኛ ተሰሎንቄ 3፡11-13 ባቀረበው ጸሎቱ ውስጥ አሳይቷል። የእግዚአብሔር ፍቅር ቅዱስ ፍቅር እንደሆነ ሁሉ፥ እኛም ለእግዚአብሔርና ለሌሎች የምናሳየው ፍቅር ለተቀደሰ አኗኗር ሊያነቃቃን ይገባል። ይበልጥ እግዚአብሔርን እየመሰልን ስንኖር፥ ይበልጥ እርስ በርሳችን እየተዋደድን እንሄዳለን። አንድ ክርስቲያን በትክክል ወንድሙን የሚወድ ከሆነ፥ በእርሱ ላይ በደል ሊፈጽም አይችልም (1ኛ ተሰ. 4፡6)።

በግሪክ ቋንቋ ለፍቅር የተሰጡ አራት መሠረታዊ ቃላት አሉ። «ኤሮስ» የሚለው ሥጋዊ ፍቅርን የሚገልጽ ሲሆን፥ የወሲብ መሳሳብን

የሚያመለክተው የእንግሊዝኛ ቃል «ኤሮቲክ» ከዚህ ቃል የመነጨ ነው። የኤሮስ ፍቅር ኃጢአት መሆን የለበትም፤ ይሁንና በጳውሎስ ዘመን የነበረው ዝንባሌ ስሜታዊነት ነበር። ሌላው «ስቶር-ጌይ» የሚለው የቤተሰብን ፍቅር ያመለክታል፤ ወላጆች ለልጆቻቸው የሚኖራቸው ፍቅር ማለት ነው። ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ የለም። ምንም እንኳ ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያለው ቃል በሮሜ 10፡12 ላይ «በወንድማማች መዋደድ» ተብሎ ቢተረጐምም፥ ይህም ቃል ቢሆን በአዲስ ኪዳናችን ውስጥ አልተጠቀሰም።

ፍቅርን ለመግለጽ አዘውትረው ያገለገሉት ግን «ፊልያ» እና «አጋፔ» ናቸው። የፊልያ ፍቅር በጓደኝነት ወይም በጋብቻ ውስጥ የሚታይ ጥልቅ የመውደድ ዓይነት ነው። የአጋፔ ፍቅር ግን እግዚአብሔር ለእኛ የሚያሳየው ፍቅር ነው። ይህም በስሜት ላይ ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን፥ በፈቃዳችን የሚገለጽ ነው። የአጋፔ ፍቅር ከስሜት ወይም ከግል ምርጫ ባሻገር፥ እግዚአብሔር ሰዎችን በሚቀርብበት መልኩ የሚገለጽ ነው።

«ፊላደልፊያስ» የሚለው የግሪክ ቃል «የወንድማማች መዋደድ» ተብሎ ተተርጉሞአል። ክርስቲያኖች የአንድ ቤተሰብ አባላት ስለሆኑና አንድ አባት ስላላቸው፥ እርስ በርሳቸው ሊዋደዱ ይገባል። እንዲያውም፥ «እርስ በርሳችን ልንዋደድ ከእግዚአብሔር ተምረናል።» እግዚአብሔር አብ ስለ እኛ በመስቀል ላይ እንዲሞት ክርስቶስን በሰጠ ጊዜ፥ እርስ በርሳችን እንድንዋደድ አስተምሮናል። «እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን» (1ኛ ዮሐ. 4፡19)። እግዚአብሔር ወልድ፥ «እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ» ባለ ጊዜ (ዮሐ. 13፡34)፥ እርስ በርሳችን እንድንዋደድ አስተምሮናል። እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን በተቀበልን ጊዜ የእግዚአብሔርን ፍቅር ከልባችን ላይ በማፍሰሱ (ሮሜ 5፡5)፥ እርስ በርሳችን እንድንዋደድ አስተምሮናል።

እንስሳት በሕይወት ለመቆየትና በጤንነት ለመሰንበት የሚያስፈልጋቸውን ነገር በተለምዶ እንደሚያደርጉ ልብ ብለህ ታውቅ ይሆን? ዓሦች በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥም እንኳ በሚገኙ የውኃ ገንዳዎች ለመዋኘት ቢችሉም፥ እንዴት ለመዋኘት እንደሚችሉ በክፍል ውስጥ ገብተው አይማሩም፤ ወፎችም ለመብረር ይችሉ ዘንድ በተፈጥሮአቸው ክንፎቻቸውን ዘርግተው ያርገበግባሉ። በመሆኑም ተግባርን የሚወስነው ተፈጥሮ ነው ማለት ነው። ዓሣ የዓሣ ባሕርይ ስላለው ይዋኛል፤ ወፍም የወፍ ባሕርይ ስላለው ይበራል። ክርስቲያንም የእግዚአብሔር ባሕርይ በውስጡ

ስላለ (2ኛ ጴጥ. 1፡4)፥ ለሌሎች የሚያስተላልፈው ፍቅር አለው፤ «እግዚአብሔር ፍቅር ነውና» (1ኛ ዮሐ. 4፡8)።

እምነት፥ ተስፋና ፍቅር የመጀመሪያዎቹ የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ልዩ መለያ ባሕርያት ነበሩ (1ኛ ተሰ. 1፡3)። ጢሞቴዎስ የፍቅራቸውን መልካም የምሥራች ስለተናገረ (1ኛ ጢሞ. 3፡6)፥ ጳውሎስ የሌላቸውን ባሕርይ እንዲያገኙ እየመከራቸው አልነበረም። ይልቁንም ቀደም ብሎ ይደሰቱበት የነበረው ነገር በተጨማሪ እንዲኖራቸው እያበረታታቸው ነበር። መቼም ቢሆን ከመጠን ያለፈ ክርስቲያናዊ ፍቅር ሊኖርህ አይችልም። ጳውሎስ እግዚአብሔር ፍቅራቸውን እንዲያበዛና እንዲጨምር ጸልዮ ነበርና (1ኛ ተሰ. 3፡12)፥ እግዚአብሔርም ያንን ጸሎት መልሶለታል (2ኛ ተሰ. 1፡3 ተመልከት)።

እግዚአብሔር ፍቅራችን በይበልጥ እንዲጨምር የሚያደርገው እንዴት ነው? ክርስቲያናዊ ፍቅር እንድንለማመድ ወደሚያስገድዱን ሁኔታዎች ውስጥ በማስገባት ነው። ፍቅር የክርስቶስ አካል «የደም ዝውውር» ነው፤ ለምሳሌ ያህል የሰውነታችንን ጡንቻ ከተጠቀምንበት ደም በሰውነታችን ውስጥ እንደ ልብ ሊዘዋወር ይችላል፤ ነገር ግን የሰውነታችንን ጡንቻ ካልተጠቀምንበት ደም እንደ ልብ መዘዋወር ስለማይችል ብርታታችን እየከዳን ይሄዳል። እንዲሁ ሁሉ እኛ አማኞች እርስ በርሳችን የምንጋራቸው ችግሮች በፍቅራችን የምናድግባቸው አጋጣሚዎች ናቸው። ይህም እርስ በርሳቸው እጅግ የከበዱ ችግሮች የነበሩባቸው ክርስቲያኖች በመጨረሻ ላይ ጥልቅ ፍቅር የሚያዳብሩበትን ምክንያት ያስረዳል፤ ዓለም እጅግ እስክትደነቅ ድረስ መዋደዳቸውን ያሳያሉ።

## በታማኝነት ተመላለሱ (4፡11-12)

በቁጥር 12 ላይ «በአገባብ» የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፥ «ታማኝነት» ተብሎ የተተረጐመ ሲሆን፥ «ተስማሚ» የሚል ፍች ይሰጣል። ይኸው ቃል በ1ኛ ቆሮንቶስ 14፡40 ላይም ተጠቅሶ እናገኘዋለን፤ «ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን።» አጽንኦቱ ከክርስቲያን ኅብረት ውጭ ለሚገኙ ሰዎች በሚሰጠው የአማኞች ምስክርነት ላይ ነው። «በውጭ ባሉት» የሚለው የማያምኑትን ወገኖች ለመጥቀስ የሚያገለግል የተለመደ አገላለጽ ነው።

ክርስቲያኖች እርስ በርስ መዋደድ ብቻ ሳይሆን፥ ለማያምኑ የዓለም ሰዎችም መልካም ምስክሮች የመሆን ግዴታ አለባቸው። የጳውሎስ ትልቁ

ሸክም የተሰሎንቄ አማኞች ራሳቸውን እንዲችሉና በማያምኑ ሰዎች ላይ ጥገኛ ሆኖ ከመኖር እንዲታቀቡ ነበር። «በጸጥታም ትኖሩ ዘንድ ልትቀኑ» (ቁ. 11) የሚለው አሳብና ምናልባት ለዓለማዊ ነገሮች የሚኖረን ዝንባሌና ጉጉት ሊጋጩ ስለሚችሉ፥ ጸጥታ የሰፈነበት ሕይወት ላይኖረን ይችላል። ይሁንና በዚህ ስፍራ አጽንኦት የተሰጠው ሰው በክርስቶስ አማካኝነት ሊያገኘው በሚችለው ውስጣዊ ሰላም፥ በልብና በአእምሮ ጸጥታ ላይ ነው። ጳውሎስ ቅዱሳን ለዕለታዊ እንጀራቸው ወዲያና ወዲህ እየሮጡ ችግር ፈጣሪዎች እንዲሆኑ አልፈለገም ነበር።

ግሪኮቹ ብዙ ጊዜ የጉልበት ሥራን ስለሚንቁ፥ አብዛኛው ሥራ የሚሠራው በባሪያዎች ነበር። በመሠረቱ ጳውሎስ ድንኳን ሠሪ ሲሆን፥ በተሰሎንቄ ጠንክሮ የመሥራትን አርአያነት ለማሳየት ይጥር ነበር (1ኛ ተሰ. 2፡6 እና 2ኛ ተሰ. 3 ከቁጥር 6 ጀምሮ ተመልከት)። የሚያሳዝነው ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳንድ አዳዲስ አማኞች የክርቶስን ምጽአት የሚስተምረውን እውነት በተሳሳተ አቅጣጫ ስለወሰዱ፥ ምጽአቱን ለመጠባበቅ በማሰብ ሥራቸውን አቁመው ነበር። ይህም ማለት በሌሎች ክርስቲያኖች ከመደገፋቸውም፥ ይብስ ብሎ ደግሞ ከመካከላቸው አንዳንዶቹ ለቤተሰቦቻቸው የሚበቃ ንብረት አልነበራቸውም ማለት ነው። እንዲሁም ደግሞ እነዚህ አጥባቂዎች ዕዳቸውን የማይከፍሉና ከዚህም የተነሣ ደኅንነትን ባላገኙ ነጋዴዎች ዘንድ ምስክርነታቸውን አጥተው ነበር ማለት ነው።

በዚህ ሁኔታ የማያስፈልጉንን ነገሮች ለመሸመት የምንከፍለው የገንዘብ እጥረት ማጋጠሙ ብቻ ሳይሆን፥ መልካሙን ክርስቲያናዊ ምስክርነታችንን ማጣት ምንኛ ቀላል ነው! «እንግዲያስ በዓመፃ ገንዘብ ካልታመናችሁ፥ እውነተኛውን ገንዘብ ማን አደራ ይሰጣችኋል?» (ሉቃስ 16፡11)። የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና አባሎቻቸው ያላቸው ዶክትሪን ትክክለኛ እንደሆነ አድርገው ቢከራከሩም፥ ያለባቸውን ዕዳ ባይከፍሉ ከዚህ በፊት የተከራከሩለት ዶክትሪናቸው ትክክል ያለመሆኑን ያሳያል።

ጳውሎስ «የራሳችሁን ጉዳይ ልትጠነቀቁ፥ ... በእጃችሁ ልትሠሩ» በማለት አዞአቸዋል (ቁ. 11)። ሥራ-ፈት ሰዎች በሌሎች ጉዳዮች ውስጥ ዘለው ጣልቃ በመግባትና ራሳቸውንና ሌሎችን በችግር ውስጥ በመክተት ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ። «ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፥ በሰው ነገር እየገቡ፥ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና» (2ኛ ተሰ. 3፡11)። «ከእናንተ ማንም ... በሌሎች ጉዳይ እንደሚገባ ሆኖ መከራን አይቀበል» (1ኛ ጴጥ. 4፡15)።

በሰማያዊ አባታቸው ሥራ ላይ የተሰማሩ አማኞች በሌሎች ጉዳይ ጣልቃ የሚገቡበት ጊዜውም፥ ፍላጐቱም የላቸውም (ሉቃስ 2፡49)። የሚያሳዝነው ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሳቢያ በግል መኖሪያ ቤት የሚሰበሰቡበት ጊዜ እንኳ («ከልብህ እንድትጸልይ በሚል ሰበብ») ለሐሜት ኃጢአት አመቺ የሚሆንበትና እውነተኛውን ክርስቲያናዊ አገልግሎት ሊተካ የሚችልበት አጋጣሚ መኖሩ ነው።

አማኞች እንደመሆናችን፥ «በውጭ ካሉት» ጋር በምናደርገው ግንኙነት ጥንቁቆች ልንሆን ይገባል። ነገር ሳያዛምቱ መልካም ግንኙነት ለማድረግና ፈራጅና ኩሩ ሳይሆኑ ልዩ ሆኖ ለመኖር፥ መንፈሳዊ ጸጋንና ጥበብን ይጠይቃል። «በውጭ ባሉት ዘንድ በጥበብ ተመላለሱ» (ቈላ. 4፡5)። ይህንን መንፈሳዊ ጥበብ ካጣን፥ ከምናለማው ይልቅ የምናጠፋው ሚዛን ይደፋል።

ክርስቲያኖች ለቤተሰባቸው ከሚበቃው በታች ለምን መሥራት እንደሌለባቸው የሚያስረዱን በርካታ ጥሩ ጥሩ ምክንያቶች አሉ (1ኛ ጢሞ. 5፡8)። ደኅንነትን ያላገኙ ሰዎች ዕዳቸውን ለመክፈል መሥራት ካለባቸው፥ ክርስቲያኖችስ ለምን ይህንን ሐቅ ያቃልሉታል? በተጨማሪም ችግር ላለባቸው ሰዎች ለመርዳት እንድንችል እንሠራለን (ኤፌ. 4፡28)፤ ደግሞም «ሊሠራ የማይወድ አይብላ» (2ኛ ተሰ. 3፡10) ተብሏል። ሥራ እርግማን ሳይሆን፥ በረከት ነው። እግዚአብሔር ለአዳም የሚያከናውነውን ሥራ በገነት ሰጥቶታል። በመሆኑም ርግማኑ ጣሩና ላቡ እንጂ፥ ሥራው በራሱ አይደለም (ዘፍ. 2፡15 እና 3 ከቁጥር 17 ጀምሮ)።

ይህን ክፍል በምንከልስበት ጊዜ፥ የክርስትና ጉዞ በእርግጥ ምን ያህል ተግባራዊ እንደሆነ እንመለከታለን። ታዛዥ ክርስቲያን ከወሲብ ኃጢአት በመራቅ የተቀደሰ ሕይወት ይመራል። እንደዚሁም የወንድማማችን መዋደድ በመለማመድ ከሌሎች ጋር በመግባባት ይኖራል። በተጨማሪም፥ በራሱ እጅ በመሥራት በሌሎች ጉዳይ ጣልቃ ባለመግባት አግባብ ያለው ሕይወት ይኖረዋል። ሆኖም ደኅንነትን ያላገኙ ሰዎች በዚህ ዓይነት ሕይወት ውስጥ ክርስቶስ ከብሮ ሲመለከቱ፥ አንድም በቅንዓት ተቃውሞ ያሰማሉ። አለበለዚያም ለራሳቸው የዚህኑ ዓይነት ሕይወት ለማግኘት ይነሣሣሉ። ይሁን እንጂ፥ በዚህም ሆነ በዚያ እግዚአብሔር ከበረ ማለት ነው።

## 1ኛ ተሰሎንቄ 4፡ 13-18

«ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፥ አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን። ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና። በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉቱን አንቀድምም። ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክት አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን። ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ።»

## - 7 -

# የምጽአቱ መጽናኛ

በጳውሎስ ዘመን ለነበረው አረማዊ ዓለም ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት የሚተማመንበት ምንም ዓይነት ተስፋ አልነበረውም። በአንድ በመቃብር ሐውልት ላይ የተቀረጸው የሚከተለው ጽሑፍ ይህንን ሐቅ ያረጋግጥልናል፡-

ከዚህ በፊት አልነበርሁም
በአንድ ወቅት በሕይወት ብኖርም
አሁን ግን የለሁም
ለወደፊቱ ግድ የለኝም

እንደ ሶቅራጥስ ያሉ አንዳንድ ፈላስፋዎች ከሞት በኋላ ደስታ እንዳለ ለማረጋገጥ ቢጣጣሩም፥ አረማዊው ዓለም ያንን የዋስትና ቃል አድርጎ አልተቀበለውም።

በተሰሎንቄ የሚገኙ አማኞች ስለሞቱት ወዳጆቻቸው ተጨንቀው ነበር። ጌታ ቢመጣስ? በቅርቡ በሞት የተለዩአቸው ወዳጆቻቸው በሕይወት ከነበሩት ጋር አብሮ የመገኘት ዕድል አይገጥማቸውም ይሆን? ጌታ ሲመጣ በሕይወት የሚቆዩ ሰዎች ከሞቱት የተሻለ ጠቀሜታ ያገኙ ይሆን? በዚህ አንቀጽ፥ ጳውሎስ ጥያቄዎቻቸውን መልሶአል። ማበረታቻውንና ማጽናኛውንም በአምስት መሠረታዊ ሐቆች ላይ አሳርፎአል።

## መገለጥ፡- የእግዚአብሔር እውነት አለን (4፡13፥15)

ሟች የሆነው ሰው መቃብርን ፈንቅሎ፥ ከባሻገሩ ዋስትናና ሰላምን እንዴት ወደ ልቡ ሊያስገባ ይችላል? ከብሉይ ኪዳን ዘመን እስከ ዛሬ ድረስ፥ የሰው ልጅ የሞትንና ከሞት በኋላ ያለውን ሕይወት እንቆቅልሽ ለመፍታት ሲፍጨረጨር ኖሯል። ፈላስፋዎች ከሕያውነት ጥያቄ ጋር ትግል ገጥመዋል። የመናፍስት ዓለም አስተማሪዎች አስቀድመው ከሞቱት ጋር ለመነጋገር ሞክረዋል።

በዘመናዊውም ዓለም፥ ሳይንቲስቶች «ሞቼ ተነሣሁ» የሚሉትን ሰዎች ገጠመኞች ለማጣራት ጥረት አድርገዋል። እንዲሁም ከሞት በኋላ ስለሚኖረው ሕይወት ፍንጭ እናገኝ ይሆናል በሚል አስማታዊ ክስተቶችንም አጥንተዋል።

ጳውሎስ፥ «በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና» በማለት ችግሩን አቃሏል (4፡15)። እኛ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር የተሰጠ መገለጥ በቃሉ ውስጥ ስላለን፥ ስለ ሕይወት ወይም ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት መደነቅ የለብንም። ታዲያ በመለኮታዊ መገለጥ ምትክ ለምን ሰብአዊ የሆኑ መላ-ምቶችን እንተካለን?

ስለ ሞትና ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት የሚያስረዳው መገለጥ ሁሉ በአንድ ጊዜ እንዳልተሰጠ መረዳቱ አስፈላጊ ነው። በርካታ ኑፋቄዎች የሐሰት ትምህርታቸውን «እውነተኛነት ለማረጋገጥ» ከመዝሙረ ዳዊትና ከመክብብ ውስጥ ጥቅሶችን በመረጃነት ያቀርባሉ። እነዚህ ጥቅሶች መቃብር የሕይወት ፍጻሜ እንደሆነ፥ ወይም ነፍስ እስከ ዕለተ-ትንሣኤ «እንደምታንቀላፋ» የሚያስተምሩ ይመስላሉ። እግዚአብሔር እውነቱን የገለጠው ቀስ በቀስ፥ደረጃ በደረጃ እያደገ እንደመጣና «ሞትን በሻረውና በወንጌል ሕይወትንና ሕያውነትን ወደ ብርሃን ባወጣው» በክርስቶስ መምጣት የመጨረሻው ደረጃ ላይ እንደደረሰ ልብ ልንል ያሻል (2ኛ ጢሞ. 1፡10)። ሞትን በተመለከተ ስለ ተፈጸመው መገለጥ ወደ ክርስቶስና አዲስ ኪዳን እንመለከታለን።

እግዚአብሔር ትንሣኤንና የክርስቶስን መመለስ በተመለከተ ለጳውሎስ ልዩ መገለጥ ሰጥቶታል (1ኛ ቆሮ. 15፡51-54 ተመልከት)። ጳውሎስ ያስተማረው ኢየሱስ ካስተማረው ጋር ይስማማል (ዮሐ. 5፡24-29 እና 11፡21-27)። እንዲሁም የእግዚአብሔር መገለጥ የክርስቶስን ትንሣኤ በሚያስተምረው ታሪካዊ ሐቅ ላይ የተመሠረተ ነው። አዳኛችን ሞትን ድል ስላደረገ፥ ሞትን ወይም ወደ ፊት የሚያጋጥመንን ነገር አንፈራም (1ኛ ቆሮ. 15፡12 ጀምሮ)። የእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን የሚያሻንን ዋስትናና መጽናናት ይሰጠናል።

## መመለስ፡- ክርስቶስ ዳግም ይመጣል (4፡14-15)

በተሰሎንቄ መልእክቶች ውስጥ በክርስቶስ መመለስ ላይ ያለውን አጽንኦት ተመልክተናል። ጳውሎስ የክርስቶስን መመለስ ከደኅንነት (1፡9-10)፥ ከአገልግሎት (2፡19-20)፥ እና ከጽናት (3፡11-13) ጋር ያዛምደዋል። በዚህ አንቀጽ ውስጥ ከኃዘን ጋር ያዛመደው ሲሆን፥ የክርስቶስን መምጣት የሚያሳየው ትምህርት እንዴት የተሰበረውን ልብ ሊጠግን እንደሚችል አስተምሮአል።

ጳውሎስ የሞቱትን አማኞች «ያንቀላፉት» በማለት ጠርቶአል። ኢየሱስም ይህንኑ አገላለጽ ተጠቅሞበታል (ዮሐ. 11፡11-13)። ጳውሎስ ኢየሱስ እንደ ሞተ በጥንቃቄ ገልጾአል፤ ለኢየሱስ ሞት «አንቀላፋ» የሚለው ቃል አላገለገለም። እርሱ ስለ እኛ ሞቷልና ሞትን መፍራት የለብንም።

ቢሆንም ጳውሎስ ነፍስ በሞት ጊዜ ያንቀላፋል አላለም። ይልቁኑ የአማኙ ነፍስ ከጌታ ጋር ለመሆን ወደዚያ እንደሚሄድ በግልጽ ተናግሮአል። «በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸውልና» (ቁ. 14)። ከእርሱ ጋር እስካልሆኑ ድረስ በሚመለስበት ጊዜ ሊያመጣቸው አይችልም። የሚያንቀላፋውም ሰውነት እንጂ፥ ነፍስ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ሞትን፥ «ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ ...» በማለት ይፈታዋል (ያዕ. 2፡26)። በምንሞትበት ጊዜ፥ መንፈስ ሰውነትን ለቆ ስለሚሄድ፥ ሰውነት አገልግሎቱን ትቶ ማንቀላፋት ይጀምራል። ሰውየው በኢየሱስ ክርስቶስ ካመነ ነፍሱና መንፈሱ ወደጌታ ይሄዳሉ። «ከሥጋ ተለይተን ... በጌታ ዘንድ ማደር ደስ ይለናል» (2ኛ ቆሮ. 5፡8)።

«በጌታ የሞቱትን» ይዞ እንደሚመለስ ስለምናውቅ፥ የጌታችን የመመለስ እውነታ ወዳጆቻችን በሞት ለተለዩብን ሰዎች መጽናኛችን ነው። አንድ ጊዜ ለአንድ ወዳጃችን፥ «ባለቤትህን እንዳጣህ ሰምቼአለሁ። በጣም አዝናለሁ» አልሁት። እርሱም፥ «የለም፥ አላጣኋትም። አንድ ነገር ያለበትን ስፍራ እስካወቅህ ድረስ አጥቻለሁ ለማለት አትችልም፤ እኔም ያለችበትን አውቃለሁ!» አለኝ። በእግዚአብሔር ቃል መሠረት፥ ወደ ፊት የሚሆነውንም እናውቃለን፤ አንድ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ ይመለስና ሕዝቡንም ከራሱ ጋር ያመጣቸዋል።

ይህ የሚሆነው መቼ ነው? ማንም ይህን ቀን ስለማያውቅ፥ «በዚህ ዕለት ነው» ማለቱ ስሕተት ነው። ጳውሎስ በቁጥር 15 እና 17 ላይ «እኛ» የሚለውን ተውላጠ-ስም መጠቀሙ፥ ጌታ ሲመጣ በሕይወት ለመቆየት ተስፋ ማድረጉን ያመለክታል። የሥነ-መለኮት ጠበብት ይህንን የክርስቶስን በቅርብ ጊዜ መመለስ አይቀሬነት የሚያስተምር ዶክትሪን ይሉታል። በቅርብ ጊዜ ሊሆን የሚችል የሚለው በማንኛውም ጊዜ ሊመለስ እንደሚችል ያሳያል። ክርስቲያኖች እንደመሆናችን፥ ምልክቶችን አንጠብቅም፤ ወይም ጌታችን ከመመለሱ በፊት ማንኛውም የተለየ ክስተት እንዲፈጸም አንሻም። እነዚህ ታላላቅ ክስተቶች የሚፈጸሙት «በድንገት፥ በቅጽበተ ዓይን» ነው (1ኛ ቆሮ. 15፡52)።

ኢየሱስ ክርስቶስ በአየር ላይ የሚመለስ ሲሆን፥ እኛ የምንቀበለው እዚያው አየር ላይ ነው (ቁ. 17)። ወዲያውኑ፥ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ከዓለም ላይ ይጠፋሉ። በአንድ የክረምት ወቅት የቤተ ክርስቲያናችን የሽርሽር ፕሮግራም አስተባባሪ የሆነው ሰው፥ ዋናው ኃላፊ በሌለበት ወቅት «ንጥቀት» እንደተፈጸመ በማስመሰል ሁኔታዎችን አቀነባብሮ ነበር። ኃላፊው በተመለሱ ጊዜ፥ ማንም ሰው አልነበረም፤ ልብሶች ሰዎች አውልቀው የጣሉአቸው ይመስል በየሜዳው ላይ ተበታትነዋል፤ የሞተሩ ጀልባ ያለነጂና ያለተሳፋሪዎች በሐይቅ ላይ ሲንሳፈፍ፥ በማዕድ ቤት ውስጥ ያለው መጥበሻና ብረትድስት ያለ አብሳይ ሲንቻቻ ተመለከቱ፤ ጥንቃቄ በተሞላበት የጊዜ ገደብ ከከተማ ያቃጨለው የስልክ ጥሪ፥ («ምንድን ነው የተፈጠረው? ምነው በዚህ አካባቢ ምንም ሰው አይታይም!» በማለት) በውጥረቱ ላይ ውጥረት ከመጨመር በቀር የረዳው ነገር አልነበረም። በመጨረሻም ኃላፊው፥ «ነገሩ እንደተፈጸመ መስሎኝ በእርግጥ ለጥቂት ጊዜ ደንግጬ ነበር» ብለዋል። እንግዲህ ይህ ክስተት ከደኅንነት ርቆ በጠፋው ዓለም ላይ ምን እንደሚያስከትል አስብ።

እኛ ክርስቲያኖች ብንሞትም በሕይወት ብንኖርም፥ አንድም ኢየሱስ ከእኛ ጋር ስለሚመለስ አለበለዚያም ለእኛ ስለሚመጣ፥ የምንፈራው ነገር የለንም። የመመለሱ እውነታ ለልባችን መጽናኛ ነው።

## በትንሣኤ የሞቱ ክርስቲያኖች ይነሣሉ (4፡ 15-16)

ጳውሎስ የትንሣኤውን መሠረታዊ ትምህርት ለአቴና ፈላስፋዎች በሚሰብክበት ጊዜ ብዙዎቹ አፌዙበት (የሐዋ. 17፡ 32)። ለግሪኮች ትልቁ ምኞታቸው ከሥጋቸው መላቀቅ ነበር። ታዲያ ሐቁ ይህ ሆኖ ሳለ ሰውነቱን በትንሣኤ ዳግመኛ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው ይኖር ይሆን? በተጨማሪ የሰውነቱ ክፍሎች ከበሰበሱና አፈር ትቢያ ከሆኑ ወዲያስ፥ ሰውነቱ ሊነሣ የሚችለው እንዴት ነው? በመሆኑም፥ በእነርሱ አመለካከት የትንሣኤው ትምህርት ሞኝነትና ጨርሶም ሊሆን የማይችል ነገር ነበር።

ኢየሱስ ክርስቶስ በአየር ላይ በደመና ሲመለስ፥ «በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ . . . በክርስቶስ የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ» (4፡ 16)። ይህም ማለት የሰውነትን ክፍሎች ዳግም ያገጣጥማል ማለት አይደለም፤ ትንሣኤ «ዳግም - ግንባታ» አይደለምና። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15 ከቁጥር 35 ጀምሮ ስለ ትንሣኤ የሙግት አሳብ ያቀርባል። የሰውነት ትንሣኤ አንድ ተክል ከዘሩ እንደሚበቅል ዓይነት ስለመሆኑ

ያስረዳል። አበባው የተዘራው ዘር አይደለም፤ ይሁንና ከዘር እስከ ተክሉ ማበብ ድረስ ተከታታይ ደረጃዎች አሉ። ክርስቲያኖች የከበረውን የክርስቶስን አካል የሚመስል ክቡር አካል ይለብሳሉ (ፊልጵ. 3፡20-21፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡47-58)። የሞተው አካል በመሬት ላይ የሚዘራው «ዘር» ሲሆን፥ የትንሣኤው አካል ከዚያ ዘር የሚመጣው አበባ ነው።

እንደ ዮሐንስ 5፡28-29 እና ራእይ 20፡1-6 የመሳሰሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ወደ ፊት ሁለት ትንሣኤዎች እንደሚኖሩ ያመለክታሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ በአየር ላይ በሚገለጽበት ጊዜ፥ በእርሱ አምነው የዳኑትን ብቻ ወደ ራሱ ይጠራቸዋል። ይህም «የመጀመሪያው ትንሣኤ» ወይም «የሕይወት ትንሣኤ» ይባላል። በዘመናት መጨረሻ፥ እግዚአብሔር አዲስ ሰማይና ምድር ከመፍጥሩ ጥቂት ቀደም ብሎ ሌላ ትንሣኤ ይኖራል። ይህም «ሁለተኛው ትንሣኤ» ወይም «የፍርድ ትንሣኤ» ይባላል። በበኩሌም በእነዚህ ሁለት ትንሣኤዎች መካከል፥ በምድር ላይ ታላቅ መከራና የሺህ ዓመቱ መንግሥት እንደሚፈጸም አምናለሁ።

በጳውሎስ ዘመን፥ ፈሪሳውያን በሙታን ትንሣኤ ሲያምኑ፥ ሰዱቃውያን ግን አያምኑም ነበር (የሐዋ. 23፡8)። ኢየሱስ የትንሣኤውን ዶክትሪን በማስተማር ሰዱቃውያንን አፋቸውን አስይዞአል (ማቴ. 22፡23-33)። የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ይህንኑ ዶክትሪን አስተምረዋል [ኢዮብ 14፡13-15፤ 19፡23-27፤ መዝ. [16]፡9-11፤ ዳን. 12፡2]። ኢየሱስ ከሙታን የመነሣቱ ሐቅ የትንሣኤን መኖር ያረጋግጣል።

በዚህ የትንሣኤ ክስተት ውስጥ ሦስት የተለዩ ድምፆች ያስተጋባሉ፡- የጌታ ድምፅ፥ የመለከት ድምፅ፥ እና የመላእክት አለቃ ድምፅ። ኢየሱስ ክርስቶስ ልክ በአልዓዛር መቃብር ደጃፍ ላይ እንዳደረገው፥ «የትእዛዝ ድምፅ» ያሰማል (ዮሐ. 11፡43)። «በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል» (ዮሐ. 5፡28)።

አንደኛ ቆሮንቶስ 15፡52ም መመለሱን ከመለከት ድምፅ ጋር ያዛምደዋል። በአይሁድ ባህል መለከቶች ጦርነት ለማወጅ፥ ልዩ ጊዜያትንና ወቅቶችን ለማስታወቅ ሕዝብን ለጉዞ ለመሰብሰብ ያገለግሉ ስለነበር (ዘኊ. 10)፥ የአይሁድ ሕዝብ ከመለከት ጋር የቀረበ ዝምድና ነበረው። በሮም መንግሥት ደግሞ፥ የአንድን ታላቅ ሰው መምጣት ለማስታወቅ መለከቶች ይነፉ ነበር። እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕግን ሲሰጥ፥ ከክስተቱ ቀደም ብሎ መለከት ተነፍቷል (ዘጸ. 19፡18-20)።

የሊቀ-መልአኩ ድምፅስ ለምን አስፈለገ? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው ብቸኛ ሊቀ-መልአክ ሚካኤል ሲሆን (ይሁዳ ቁ. 9)፥ ለእስራኤል ሕዝብ የተለየ አገልግሎት ያለው ይመስላል (ዳን. 10፡21፤ ራእይ 12፡7)። ዳንኤል 10፡13 ከአንድ የሚበዙ ሊቃነ-መላእክት እንዳሉ ስለሚጠቁም፥ ይህ ድምፅ የሚካኤል ነው ለማለት አንችልም። ምንም ይሁን ምን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ የመላእክት ሠራዊት የድሉ አብሣሪ ተካፋዮች ይሆናሉ።

ሞት የመጨረሻው ነገር እንዳልሆነ፥ ከክርስትና ዶክትሪን እንማራለን። መቃብር ፍጻሜ አይደለም። ሰውነት ወደ እንቅልፍ ሲገባ፥ ነፍስ ግን ከጌታዋ ጋር ለመሆን ወደዚያ ታቀናለች (ፊልጵ. 1፡20-24)። ጌታ በሚመለስበት ጊዜ ግን ነፍስን ከራሱ ዘንድ በማምጣትና ሰውነትን በክብር በማስነሣት፥ ለዘለዓለም የክብሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ነፍስንና ሥጋን አንድ አድርጐ ያቆማቸዋል። ይህም ሞትን በምንጋፈጥበት ጊዜ መጽናናትንና ዋስትናን ወደሚሰጠን ወደ አራተኛው ሐቅ ያመራናል።

## ንጥቀት፡- በሕይወት ያሉ አማኞች ይነጠቃሉ (4፡17)

«ንጥቀት» የሚለው ቃል «መያዝ፥ መውሰድ» ማለት ነው።

አንድ ጊዜ የግሪክ ሊቅ የሆኑት ዶክተር ኬነት ኤስ. ዊስት በዚህ ምንባብ ላይ ተመሥርተው በሚሰብኩበት ወቅት፥ በቁጥር 17 ላይ «መነጠቅ» ተብሎ የተተረጐመውን ቃል የተለያዩ የግሪክ ፍችዎች ሲያብራሩ ሰምቻለሁ። እነዚህም ትርጉሞች እያንዳንዳቸው የጌታችንን መመለስ በሚያመለክተው ትምህርት ላይ የተለየ እውነት ይጨምራሉ።

«በፍጥነት ነጥቆ መውሰድ»፡- ይህ ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ወደ ክርስቶስ ከመራው በኋላ፥ መንፈስ ቅዱስ «እንደነጠቀው» የሚያመለክት የሐዋርያት ሥራ 8፡39 ትርጉም ነው። ጌታ በአየር በሚመለስበት ጊዜ፥ በሕይወት የምንኖር አማኞች ከዓይን-ቅጽበት በበለጠ ፍጥነት እንነጠቃለን። ይህም ማለት ሲመለስ ከፈቃዱ ውጭ ሆነን ላለመገኘት እያንዳንዷን ደቂቃ የጌታችንን መመለስ በተስፋ እየተጠባበቅን መኖር አለብን ማለት ነው (1ኛ ዮሐ. 3፡1-3)።

«በጉልበት ነጥቆ መውሰድ» (ዮሐ. 6፡15 ተመልከት)፡- ይህስ ሰይጣንና ሠራዊቱ ምድሪቱን ለቀን እንዳንሄድ እንደሚጥሩ የሚቻላቸውን ሙከራ ሁሉ ያደርጋሉ ማለት ይሆን? በበኩሌ አንዳንድ ቅዱሳን ከዓለም ጋር

በጥብቅ በመቆራኘታቸው፥ የግድ ተጐትተው መወሰድ ይኖርባቸዋል የሚል አሳብ እንዳልሆነ አምናለሁ። ሎጥ ከሰዶም እንደወጣው፥ እነዚህም ቅዱሳን ከአበሳ ይድናሉ (ዘፍ. 19፡16)።

«ለራስ መውሰድ»፡- ይህ ጌታችን የራሱን ሙሽራ ለመውሰድ በሚመጣበት ጊዜ የሚሆነውን የንጥቀት ሁኔታ፥ ከጌታ ባለቤትነት አንጻር ያሳየናል።

«ወደ ሌላ ስፍራ መጓዝ»፡- ጳውሎስ ሰማያዊ ጉብኝቱን በሚገልጽበት ጊዜ በዚህ ቃል ተጠቅሟል (2ኛ ቆሮ. 12፡1-4)። ኢየሱስ ክርስቶስ የሄደው ስፍራ ሊያዘጋጅልን ሲሆን (ዮሐ. 14፡1-6)፥ በሚመለስበት ጊዜ ወደ ከበረው ስፍራ ይወስደናል። በዓለም መናኞችና እንግዶች ነን። እውነተኛው ዜግነታችን በሰማይ ነው (ፊልጵ. 3፡20-21)።

«ከአደጋ መዳን»፡- የሐዋርያት ሥራ 23፡10 ተመልከት። ይህም ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ዘንድ በዓለም ላይ ከሚመጣው ታላቅ የመከራ ጊዜ ቀደም ብላ እንደምትወሰድ ያመለክታል። አንደኛ ተሰሎንቄ 1፡10 እና 5፡9 ይህንኑ በግልጽ የሚናገሩ ይመስላል።

ለመሆኑ ደኅንነትን ያልተቀበለው ዓለም በንጥቀት ጊዜ ምን እንደተፈጸመ ያውቅ ይሆን? ያልዳኑትስ ሰዎች፥ ጩኸቱን፥ ድምፁንና መለከቱን ይሰሙ ይሆን? አንደኛ ቆሮንቶስ 15፡22፥ ይህ በድንገት ከመፈጸሙ የተነሣ በዓይን-ቅጽበት ውስጥ እንደሚከናወን ይናገራል። ጩኸቱ፥ ድምፁና መለከቱ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ስለሆነ፥ የማያምኑ ሰዎች ይሰሙታል ብሎ ለማመን የሚያበቃ ምክንያት የለም። ከሰሙም፥ ትርጉም የማይሰጥ ድምፅ ብቻ ይሰማሉ (ዮሐ. 12፡27-30 ተመልከት)። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ዓለምን ከመቅጽበት ለቀው ስለሚወጡ፥ ሥርዓት-አልበኝነትና ትልቅ ጭንቀት እንደሚፈጠር አይጠረጠርም። የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ከሚያውቁት በቀር፥ ዓለም በሆነው ነገር በአድናቆት ትሞላለች።

## ዳግም-ግንኙነት፡- የክርስቲያኖች ለዘላለም ከጌታ ጋሪ መሆን (4፡17-18)

ጌታ እኛን ለመውሰድ ሲመጣ፥ እኔና አንተ ጌታን በአየር ላይ በአካል እንቀበለዋለን። «እንቀበለዋለን» ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል፥ አንድን ንጉሥ ወይም በጣም ትልቅ ሰው የመቀበልን ወይም የመገናኘትን አሳብ ያሳያል። እዚህ በምድር ላይ ከክርስቶስ ጋር በእምነት

ተመላልሰናል፤በአየር ላይ ግን «እርሱን እንዳለ እናየዋለንና» እርሱን እንመስላለን (1ኛ ዮሐ. 3፡1-2)። ይህ ምንኛ የሰመረ ግንኙነት ይሆን!

የከበረ አካል ስለሚኖረን፥ ግንኙነቱም የከበረ ይሆናል። ኢየሱስ እዚህ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ፥ አንድ ቀን ክብሩን እድንመለከትና የክብሩ ተካፋዮች እንድንሆን ጸልዮአል (ዮሐ. 17፡22-24)። ዛሬ የምንቀበለው መከራ፥ እርሱ በሚመለስበት ጊዜ ወደ ክብር ይለወጣል (2ኛ ቆሮ. 4፡17-18፥ ሮሜ 8፡17-19)።

ከጌታ ጋር ለዘላለም ስለምንኖር፥ ዘላለማዊ ግንኙነት ይሆናል። የተስፋ ቃሉ፥ «እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ» የሚል ነበር (ዮሐ. 14፡3)። የመቤዠት ግቡ እኛን ከፍርድ ማዳን ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን እኛን ወደ ክርስቶስ ማድረስ ነው።

ከጌታ ጋር መገናኘታችን ፍርድ የመቀበያ ጊዜም ነው። ይህም «የክርስቶስ የፍርድ ወንበር» በመባል ይታወቃል (ሮሜ 14፡10 እና 2ኛ ቆሮ. 5፡10)። «የፍርድ ወንበር» ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል «ቤማ»፥ የኦሎምፒክ ዳኞች አክሊሎችን ለውድድሩ አሸናፊዎች የሚሸልሙበትን ስፍራ ያመለክታል። በሥራዎቻችን ላይ ፍርድ ይተላለፍና ሽልማቶችም ይሰጣሉ (1ኛ ቆሮ. 3፡8-15)።

የክርስቶስ የፍርድ ወንበር በራእይ 20፡11-15 ውስጥ ከተገለጸው የነጭ ዙፋን ፍርድ ጋር መምታታት የለበትም። እነዚህን ሁለት አስፈላጊ ክስተቶች እንደሚከተለው ማነጻጸር ይቻላል፡-

| የክርስቶስ የፍርድ ወንበር | የነጭ ዙፋን ፍርድ |
|---|---|
| - አማኞች ብቻ ይቀርባሉ | - የማያምኑ ሰዎች ብቻ ይቀርባሉ |
| - ወዲያው ከንጥቀት በኋላ ይፈጸማል | - ከሺህ ዓመቱ መንግሥት በኋላ ይፈጸማል |
| - ለአገልግሎት የሚሰጡ ሽልማቶችን ይወስናል | - የፍርድን መጠን ይወስናል |

በንጥቀት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር መገናኘት ብቻ ሳይሆን፥ አስቀድመው ከሞቱት አማኝ ወዳጆቻችንና ዘመዶቻችን ጋርም ደግሞ አብረን እንኖራለን። «ከእነርሱ ጋር» የሚለው ታላቅ የመጽናኛ ቃል ነው። ሞት ከፍተኛ የመለያያ ግድግዳ ሠሪ ቢሆንም፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ከሞት በኋላ ታላቁን የእርቅ ድልድይይዘረጋል።

መጽሐፍ ቅዱስ የዚህን ዳግም-ግንኙነት ዝርዝር ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ አይገልጽም። ኢየሱስ የመበለቲቱን ልጅ ከሞት ባስነሣው ጊዜ፥ በፍቅር «ለእናቱ ሰጣት» (ሉቃስ 7፡15)። ይህም ጌታ የፈራረሱትን የቤተሰብና የጓደኝነት ግንኙነቶች ዳግም ወደ አንድነት የማምጣት አስደሳች አገልግሎት እንደሚኖረው ይጠቁማል።

የጌታ መልክ ባንጸባረቀበት ተራራ ላይ፥ ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ኤልያስንና ሙሴን አውቀው ለይተዋል (ማቴ. 17፡1-5)። በመሆኑም ያለጥርጥር ቅዱሳን በክብር እርስ በርሳቸው ይተዋወቃሉ ማለት ነው፤ ከዚያን በፊት አይተናቸው የማናውቃቸውን አማኞች ሳይቀር እናውቃለን። «ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ» (1ኛ ቆሮ. 13፡12)።

በቀጣዩ ምዕራፍ ውስጥ ጳውሎስ ይህንን የዳግም ምጽአት ትምህርት ከማያምኑ ሰዎች ጋር እንዳዛመደው እንመለከታለን። ይሁንና አሁን እዚህ ላይ ቆም ብለን ጌታን ለመገናኘት መዘጋጀታችንን ለማወቅ ልባችንን ብንመረምር መልካም ነው። የጥሩ ክርስቲያን አንደኛው ምልክት ምጽአቱን በጉጉትና በናፍቆት መጠበቁ ነው (1ኛ ተሰ. 1፡10)። በጌታ እያደግን ስንሄድ የእርሱን መገለጥ መናፈቅና መጠባበቅ ብቻ ሳይሆን፥ ቶሎ መድረሱንም እንወዳለን (2ኛ ጢሞ. 4፡8)። በእርሱ ይህ ተስፋ ስላለን፥ በመገለጡ እንዳናፍር ሕይወታችንን በንጽሕና እንመራለን (1ኛ ዮሐ. 2፡28-3፡3)።

ፈሪሃ-እግዚአብሔር የነበራቸው የፕሬስቢተርያን ሰባኪ ሮበርት ሙሬይ ማክቼይን፥ አድማጮቻቸውን፥ «ክርስቶስ ዛሬ የሚመለስ ይመስላችኋልን?» ብለው ይጠይቁ ነበር። ብዙዎቹ፥ «አይ፥ ዛሬስ አይመጣም» ብለው ይመልሳሉ። ከዚያም ማክቼይን፥ «እንግዲህ ወዳጆቼ ሆይ፥ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፥ ክርስቶስ እናንተ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና» (ሉቃስ 12፡40) በማለት ይመልሳሉ።

ሞት የሕይወት እውነታ ነው። ከሞት የምናመልጥበት ብቸኛው መንገድ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ በሕይወት መቆየት ነው። ሞት የታወቀ ቀጠሮ እንጂ፥ ድንገተኛና ያልተለመደ ነገር አይደለም፤ «ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው» ይላል (ዕብ. 9፡27)። ዛሬ ብትሞት፥ ነፍስህ ወዴት ትሄዳለች?

አንድ ጊዜ በዊንድዘር ሕንፃ አቅራቢያ በሚገኘው አንድ የቆየ የእንግሊዞች መካነ መቃብር ውስጥ በቆመ ሐውልት ላይ መስህብነት ያለው ጽሑፍ ተቀርፆ አይቼ ነበር፤እንዲህም ይላል፡-

ወዳጄ፥

በዚህ ስታልፍ ቆም ብለህ አስብ
በአንድ ወቅት እኔም እንዳንተው ነበርሁ
አንተም አንድ ቀን እንደ እኔው ታልፋለህ
ተዘጋጅ ወዳጄ - እኔን ለመከተል!

ይህንን ያነበበ አንድ ጐብኚ ቀጣዮቹን ስንኞች እንዳከለበት ሰምቻለሁ፡-

የሄድህበትን መንገዱን ሳላውቀው፥
አንተን ለመከተል እንደምን ልከጅል!

ሆኖም እኛ ክርስቲያኖች ከኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤና ከመመለሱ ተስፋ የተነሣ፥ አስደናቂ ዋስትናና ተስፋ አለን።

አንተስ ዛሬ ይህ ተስፋ አለህ?
የትኛውንስ መንገድ ይዘህ እየሄድህ ነው?

## 1ኛ ተሰሎንቄ 5፡1-11

«ወንድሞች ሆይ፥ ስለ ዘመናትና ስለ ወራት ምንም እንዲጻፍላችሁ አያስፈልጋችሁም የጌታ ቀን፥ ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ፥ እንዲሁ ይመጣ ዘንድ ራሳችሁ አጥብቃችሁ አውቃችኋልና። ሰላምና ደኅንነት ነው ሲሉ፥ ያን ጊዜ ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል ከቶም አያመልጡም። እናንተ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ቀኑ እንደ ሌባ ይደርስባችሁ ዘንድ በጨለማ አይደላችሁም፥ ሁላችሁ የብርሃን ልጆች የቀንም ልጆች ናችሁና። እኛ ከሌሊት ወይም ከጨለማ አይደለንም እንግዲያስ እንንቃ በመጠንም እንኑር እንጂ እንደ ሌሎች አናንቀላፋ። የሚያንቀላፉ በሌሊት ያንቀላፋሉና፥ የሚሰክሩም በሌሊት ይሰክራሉና እኛ ግን ከቀን ስለ ሆንን፥ የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቁር እየለበስን በመጠን እንኑር እግዚአብሔር ለቁጣ አልመረጠንምና፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ። የምንነቃም ብንሆን፥ የምናንቀላፋም ብንሆን፥ ከእርሱ ጋር አብረን በሕይወት እንኖር ዘንድ ስለ እኛ ሞተ። ስለዚህ እናንተ ደግሞ እንደምታደርጉ፥ እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ አንዱም ሌላውን ያንጸው።»

# አታንቀላፉ!

ኢየሱስ ክርስቶስ የማስተባበሩንም ሆነ የመከፋፈሉንም ሚና ይጫወታል። እርሱን አዳኛቸው አድርገው የታመኑበት እንደ እግዚአብሔር ልጆች በክርስቶስ አንድ ሆነዋል። እና የአካሉ ክፍሎች ናቸው፤ «ሁላችን በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ አካል ነን» (ገላ. 3፡28)። ኢየሱስ ክርስቶስ በአየር ላይ ሲመለስ፥ «ከእርሱ ጋር እንነጠቃለን» (1ኛ ተሰ. 4፡17)፤ ዳግመኛም አንለያይም።

እንዲሁም ክርስቶስ የመከፋፈሉንም ሚና ይጫወታል። «በእርሱ የተነሣ በሕዝቡ መካከል መለያየት ሆነ» (ዮሐ. 7፡43፤ ደግሞ ዮሐ. 9፡16 እና 10፡19ን ተመልከት)። በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የሚኖረን እምነት ከሌሎች አማኞች ጋር ማስተባበር ብቻ ሳይሆን፥ ከተቀረውም ዓለም በመንፈሳዊ ሁኔታ ይለየናል። ኢየሱስ፥ «እኔ ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉም» ብሏል (ዮሐ. 17፡16)። የጌታን ምጽአት በሚጠባበቁ አማኞችና በዓለም ሕዝቦች መካከል ልዩነት አለ፤ ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ የሚያጕለብተውም ይህንን ዐቢይ አሳብ ነው።

ዓላማውም አማኞች ዙርያቸውን በከበቡአቸው አረማውያን መካከል የተቀደሰ ሕይወት ይመሩ ዘንድ ለማበረታታት ነበር። ይህንንም ያደረገው በሚያምኑና በማያምኑ ሰዎች መካከል የሚገኙትን ቅራኔ በመግለጽ ነበር።

## እውቀትና ድንቁርና (5፡1-2)

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ሦስት ሐረጐች ጥንቃቄ የተሞላበት ዕይታ እንዲደረግባቸው ያስፈልጋል።

1. «ዘመናትና ወራት»:- ይህ ሐረግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቻ ተጠቅሶ የሚገኝ ሲሆን፥ በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ያዘጋጀውን ዕቅድ ያመለክታል። ዳንኤል እግዚአብሔር የንጉሡን ሕልም እንዲያስተውል ባስቻለው ጊዜ፥ በዚሁ መንገድ ነበር የገለጸው (ዳን. 2፡21)። በሐዋርያት ሥራ 1፡7 ላይ ጌታችን ሐረጉን የተጠቀመበት ሁኔታ፥ ዘመናትና ወራት በመጀመሪያ ደረጃ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር እንደሚዛመዱ ያመለክታል።

እግዚአብሔር ለዓለም ሕዝብ ግልጽ የሆነ ዕቅድ አለው (የሐዋ. 17፡26)፤ እስራኤል ደግሞ ቁልፍ አገር ነች። ዶክተር ኤ.ቲ. ፒርሰን፥

«የዓለም ታሪክ የእግዚአብሔርን ሥራ የሚተርክ ነው» ይሉ ነበር። (ይህ አሳብ ከናፖሊዮን ፍቺ ጋር የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል። እርሱም እንዲህ አለ፡- « የዓለም ታሪክ ማለት ሰዎች የውሸት መዝገብ እንዲጠራቀም የተስማሙበት ውል ነው።») እግዚአብሔር ለዓለም ሕዝቦች፥ በተለይም ለእስራኤል ዘመናትንና ወራትን የወሰነ ሲሆን፥ ይህም ሁሉ «የጌታ ቀን» ተብሎ በሚጠራው አስጨናቂ ቀን ከፍጻሜ ይደርሳል።

2. «የጌታ ቀን»፡- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ቀን» አንድም የ24-ሰዓታትን የጊዜ ገደብ፥ አለበለዚያም እግዚአብሔር አንድ የተለየ ዓላማ የሚፈጽምበትን ረዘም ያለ ጊዜ ሊያመለክት ይችላል። በዘፍጥረት 2፡3 ላይ ይህ ቃል የሚያመለክተው 24- ሰዓታትን ሲሆን፥ ዳሩ ግን በቁጥር 4 ላይ ሙሉውን የፍጥረት ሳምንት ያሳያል።

የጌታ ቀን እግዚአብሔር በዓለም ላይ የሚፈርድበትና ሕዝቡን የሚቀጣበት ጊዜ ነው። በዚህም ጊዜ፥ እግዚአብሔር እስራኤልን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ መንግሥቱን ለመመሥረት ለሚመጣበት ሁኔታ ያዘጋጃታል። ስለዚህ ታላቅ ክፍለ-ጊዜ ሰፊ ገለጻ ለማግኘት፥ አሞጽ 5 ከቁጥር 18 ጀምሮ፥ ኢዩኤል 2 ከቁጥር 1 ጀምሮ፥ ሶፎንያስ 1፡14-18 እና ኢሳይያስ 2፡12-21 አንብብ።

ለዚህ ቃል ሌላው አገላለጽ «የያዕቆብ የመከራ ቀን» የሚለው ነው (ኤር. 30፡7)። በተጨማሪም በርካታ የትንቢት ተማሪዎች ታላቁ መከራ ብለው በመጥራት ራእይ 6-19ን፥ ክስተቱን የሚገልጽ ዋንኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በማድረግ ይጠቅሳሉ።

3. «በምሽት የሚመጣ ሌባ»፡- ጌታችን በዚህ መግለጫ ራሱ በሚያስተምርበት ወቅት ተጠቅሞአል (ማቴ. 24፡42-43፤ ሉቃ. 12፡35-40)። ይህም የጌታ ቀን ድንገተኛና አስገራሚ እንደሚሆን ያሳያል። በራእይ 3፡3 እና 16፡15 እንደምንመለከተው፥ አማኞች ሳይዘጋጁ ቀኑ እንዳይደርስባቸው ለማስጠንቀቅ ሲል ጌታ በዚሁ መግለጫ ተጠቅሞአል። ጌታ ለሕዝቡ የሚመለስበትን ጊዜ ስለማናውቅ፥ ለሥራና ለምስክርነት የምንተጋውን ያህል፥ መመለሱን በማያቋርጥ ንቃት ልንጠባበቅ ይገባል።

እንግዲህ እነዚህን ሦስት አሳቦች በአንድ ላይ በማጣመር፥ ጳውሎስ በተሰሎንቄ በመከራ ውስጥ የነበሩትን ወዳጆቹን ለማስተማር የፈለገውን ነገር ልንረዳ እንችላለን። አስቀድሞ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ስለመምጣቱ ገልጾ

ነበር፤ ይህም በ1ኛ ተሰሎንቄ 4፡13-18 የተጠቀሰው ነው። ከዚህ የቤተ ክርስቲያን ንጥቀት ቀጥሎም በምድር ላይ የጠነከረ የመከራና የሥቃይ ጊዜ እንደሚሆን ነግሮአቸዋል። እነዚህ ከእስራኤል ጋር የሚዛመዱ «ዘመናትና ወራት» ከቤተ ክርስቲያን ጋር ሊዛመዱ ወይም ጌታ ለቤተ ክርስቲያን የመምጣቱን እውነታ ሊያናጉ አይችሉም። በማንኛውም ጊዜ ሊመጣ የሚችል ሲሆን፥ ይህም የጌታ ቀን መጀመሪያ ይሆናል።

ጳውሎስ ስለ ጌታ ቀን በ2ኛ ተሰሎንቄ ውስጥ ሰፊ ማብራርያ ስለሚሰጥ፥ ይህንኑ ዝርዝር አሳብ ለኋለኛው ምዕራፍ እናቆየዋለን። በዚህ ስፍራ ትኩረት የሰጠው፥ የማያምኑ ሰዎች የእግዚአብሔርን ዕቅድ ሳያውቁ፥ አማኞች ግን ይህንኑ ያውቁ እንደነበር በመግለጹ ላይ ነበር። የእነዚህ ክስተቶች ድንገተኛነት፥ ዓለም ለመለኮታዊ እውቀት መሐይም መሆኗን ያሳያል።

## በተስፋ መጠባበቅና አድናቆት (5፡3-5)

እነዚህ እጅግ የከፋ ለውጥ የሚያስከትሉ ክስተቶች ከመፈጸማቸው ጥቂት ቀደም ብሎ፥ ከደኅንነት የራቀው ዓለም በውሸት ሰላምና ደኅንነት ሲደሰት ይቆያል። በዚህ ክፍል ውስጥ «እነርሱ» እና «እናንተ› (ወይም «እኛ») በሚሉ ቃላት መካከል የሚገኘውን ንጽጽር በጥንቃቄ አስተውል፤ «እነርሱ» የሚለው ያልዳኑትን ሰዎች ያመለክታል። እነርሱ «ሰላምና ደኅንነት!» ሲሉ፥ እኛ ግን «ኢየሱስ እየመጣ ነው፥ ፍርድም ደርሶአል!» እንላለን።

ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ስለማይሰሙ ወይም ለእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ ልባቸውን ስለማይሰጡ፥ ዓለም በመገረም ትዋጣለች። እግዚአብሔር የጥፋት ውኃ እየመጣ እንደሆነ በመግለጽ ቢያስጠነቅቅም፥ አምነው የዳኑት ስምንት ሰዎች ብቻ ነበሩ (1ኛ ጴጥ . 3፡20)። እንደዚሁም ሎጥ ከተማዪቱ ልትደመሰስ መሆኗን በመግለጽ ቤተሰቡን ቢያስጠነቅቅም፥ ሊሰሙት አልቻሉም (ዘፍ. 19፡12-14)። ኢየሱስ በዘመኑ የነበረውን ትውልድ ኢየሩሳሌም እንደምትደመሰስ በማስጠንቀቁ (ሉቃስ 21 ከቁጥር 19 ጀምሮ)፥ አማኞች ማስጠንቀቂያውን ሰምተው ሲያመልጡ፥ ሌሎች በርካታ ሰዎች ግን በወረራው ተደምስሰዋል።

እርግጥ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ የጥፋትን ውኃ፥ ብሎም የሰዶምና ገሞራን መደምሰስ የፍርድ ምሳሌ አድርጎ ተጠቅሞባቸአዋል (ማቴ. 24፡37-39 እና ሉቃስ 17፡26-30)። በዚያን ጊዜ የነበሩ ሰዎች እንደ

መብላት፥ መጠጣት፥ መጋባት የመሳሰሉትን ዕለታዊ ተግባሮች ያከናውኑ እንጂ፥ ፍርድ ከደጃቸው እንደቀረበ አልተረዱም ነበር።

አንዳንድ ሰዎች በቅን አስተሳሰብ ተነሣስተው ስለ ጌታችን የመምጫ ዕለት ቢወስኑም፥ ውድቀታቸው ለኃፍረት ዳረጋቸው እንጂ ከቶውንም አልረባላቸውም። በመሆኑም የሚመረጠው ትክክለኛውን ቀን ሳይወስኑ ምጽአቱን መጠባበቅ ነው። ለቤተ ክርስቲያኑ ከመመለሱ በፊት መፈጸም የሚገባቸው «ምልክቶች» የሉም።

የወደፊቱን ዕድል በተመለከተ፥ ክርስቲያኖች «የብርሃን ልጆች» እንጂ፥ «በጨለማ ውስጥ የሚኖሩ» አይደሉም። የማያምኑ ሰዎች በክርስቶስ የመመለስ ጉዳይ ላይ ይሳለቃሉ። «በመጨረሻው ዘመን...ዘባቾች በመዘበት እንዲመጡ ይህን በፊት እወቁ፤ እነርሱም፡- የመምጣቱ የተስፋ ቃል ወዴት ነው? ... ይላሉ» (2ኛ ጴጥ. 3፡3-4)።

ጌታችን ዳግም እንደሚመለስ የተስፋ ቃል ከሰጠበት ጊዜ አንሥቶ 20 ክፍለ-ዘመናት ያህል ተፈራርቀዋል፤እርሱ ግን ገና አልመጣም። ይህም እግዚአብሔር የእኛን የጊዜ ሰሌዳ አይከተልም ማለት እንጂ፥ ከቶውንም የተስፋ ቃሎቹን ያጥፋቸዋል ማለት አይደለም። «በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፥ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን ...» ነው (2ኛ ጴጥ. 3፡8)።

ጳውሎስ የሚመጣው ፍርድ «ምጥ እርጉዝን ሴት እንደሚይዛት» ዓይነት እንደሆነ ይናገራል (1ኛ ተሰ. 5፡3)። በዛሬው ዘመናዊ የሕክምና ጥበብ በተራቀቀበት ወቅት እንኳ፥ የምጥ ጣር ዓይነተኛና አሰቃቂ ነው። በምጥ ጣር ውስጥ፥ እናት ልጇን ከማኅፀን ወደ ውጭ የምታስወጣው በጅማት መኮማተርና መሳሳብ አማካኝነት ነው። ነቢዩ ኢሳይያስ የሚመጣውን «የጌታ ቀን» በሚገልጽበት ጊዜ፥ ይህንኑ መግለጫ ተጠቅሞአል (ኢሳ. 13፡6-13)። የዚህ የጌታ ቀን የመጀመሪያው ክፍል «የምጥ ጣር መጀመሪያ» ተብሏል (ማቴ. 24፡8)።

እንግዲህ ኢሳይያስ፥ ኢየሱስና ጳውሎስ የሚያስተምሩን እውነት ምንድን ነው? የሚያስተምሩን ከጌታ ቀን ውስጥ የመንግሥቱ ልደት እውነታ የሚወጣ መሆኑን ነው። የእግዚአብሔር ፍርዶች ከተፈጸሙ በኋላ፥ የእግዚአብሔርን ልጅ «በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል» (ማቴ. 24፡30)። ጳውሎስ ይህን ሁኔታ ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች በጻፈው ሁለተኛ መልእክት ውስጥ ገልጾአል።

ስለዚህ ምጽአቱን በመጠባበቅ ነቅተን እንኑር። ይህም ሲባል ደግሞ ነጭ ጨርቅ ለብሶ ከተራራ ጫፍ ላይ መቀመጥ ማለት አይደለም። ስለምን ይህ አድራጎት እግዚአብሔር የኮነነው ዓይነተኛ ባሕርይ በመሆኑ ነው! (የሐዋ. 1፡10-11)። ይልቁንም ምጽአቱን እያሰቡ መኖር ማለት፥ ሥራዎቻችን እንደሚፈረድባቸውና በምድር ላይ የማገልገል ዕድላችን እንደሚያበቃ በመረዳት፥ እግዚአብሔር ሕይወታችንን እንዳያት እናያታለን ማለት ነው።

ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመሄድ በመዘጋጀትና ጌታን ለመገናኘት በመዘጋጀት መካከል ልዩነት አለ። ለደኅንነቱ በእውነተኛ ልብ ክርስቶስን የታመነ ማንም ቢሆን ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመሄድ ዝግጁ ነው። በመስቀል ላይ ክርስቶስ የፈጸመው መሥዋዕት ለዚያ ዋስትና ይሰጠዋል። ይሁንና በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ጌታን ለመገናኘት መዘጋጀት ፍጹም የተለየ ነገር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ አማኞች ኢየሱስ ክርስቶስን ለማየት ደስተኞች እንደማይሆኑ ይጠቁማል። «አሁንም፥ ልጆች ሆይ፥ በሚገለጥበት ጊዜ እምነት እንዲሆንልን በመምጣቱም በእርሱ ፊት እንዳናፍር በእርሱ ኑሩ» (1ኛ ዮሐ. 2፡28)።

ለብዙ ዓመታት በመጋቢነት ሳገለግል፥ አማኞች ሆን ብለው ከእግዚአብሔር ቃል ሲወጡ የማየት አሳዛኝ ሁኔታ አጋጥሞኛል። ደኅንነትን ካላገኘው ሰው ጋር ጋብቻ ለመፈጸም በልበ-ደንዳናነት የወሰነችውን አንዲት ወጣት ሴት አስታውሳለሁ። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በመጠቀም ልረዳት ስሞክር፥ «አንተ ለምትለው ነገር ደንታ የለኝም። መጽሐፍ ቅዱስ ለሚለውም ነገር አልጨነቅበትም። ያንን ሰው አገባለሁ» አለችኝ። ታዲያ ይህቺ ሴት ከዕብራውያን 13፡17 አኳያ፥ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ስትቀርብ ደስተኛ ለመሆን ትችል ይሆን?

የጌታን ምጽአት በመጠባበቅ የሚኖሩ አማኞች፥ ያለጥርጥር ከዓለም ጋር ከሚስማሙ አማኞች የተሻለ ሕይወት ይጠብቃቸዋል። ጳውሎስ በዚህ መልእክት በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ የጌታን ምጽአት በመጠባበቅ የመኖርን ተግባራዊ ውጤቶች አስፍሯል። አሁን እነዚያን ቁጥሮች ለመከለስና ልብህን ለመመርመር ጊዜ ውሰድ።

## ንቃትና ስካር (5፡6-8)

መንቃት ማለት ሳያንቀላፉ ዓይንን ከፍቶ መቆየት፥ ጤናማና ባለማቋረጥ ተግባርን የማከናወን ሁኔታ ነው። ንጽጽሩን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ፥ ጳውሎስ ሰዎችን በሁለት ወገን በመመደብ አሳይቷል። አንደኛው ወገን

ሰካራምና እንቅልፋም ሲሆን፥ ሌላኛው ግን ንቁና ትጉ ነው። አደጋ እየቀረበ ቢመጣም ቅሉ ሰካራሞችና እንቅልፋሞች አያውቁትም ነበር። ንቁው ሕዝብ ግን ያለፍርሃት ተዘጋጅቶ ይጠባበቅ ነበር።

እኛ «የቀን ልጆች» ስለሆንን፥ እንደነዚያ የጨለማ ሕዝቦች ልንኖር አይገባም። «ሌሊቱ አልፎአል፥ ቀኑም ቀርቦአል። እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ። በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ፤ በዘፈንና በስካር አይሁን፥ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፥ በክርክርና በቅናት አይሁን» (ሮሜ 13፡12-13)።

በሌላ አባባል፥ «ቀኑ» እየቀረበ ስለመጣ፥ ለመንቃት፥ ለመጸዳዳትና ለመልበስ ጊዜው አሁን ነው ማለት ነው። ስንለብስም፥ «የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቍር እየለበስን በመጠን እንኑር» (1ኛ ተሰ. 5፡8)። ጌታችን ከመመለሱ በፊት በሚገኙ በእነዚህ የመጨረሻ ዘመናት ሊጠብቀን የሚችለው «የብርሃን ጋሻ» ብቻ ነው (ሮሜ 13፡12)።

ንቁ አእምሮ ያለው አማኝ በሕይወት ላይ ጭምትና ጤናማ አመለካከት አለው። በራስ የመርካትም ሆነ ተስፋ የመቁረጥ ሁኔታ አይታይበትም። የዘመኑን አሳዛኝ ዜናዎች ቢሰማም፥ ተስፋ አይቆርጥም። የሕይወትን አስቸጋሪ ገጽታዎች ቢጋፈጥም፥ «አበቃልኝ» አይልም። የወደፊት ተስፋው በእግዚአብሔር እጆች ውስጥ አስተማማኝ ፍጻሜ እንዳለው ስለሚያውቅ፥ እያንዳንዱን ዕለት በብልሃት፥ በጭምትነትና በመታዘዝ ያሳልፋል። አመለካከት የሕይወትን ስኬትና ውጤት ይወስናልና አመለካከትህ የቀና ከሆነ፥ ስኬታማነትህም የተረጋገጠ ነው።

ይሁንና ከደኅንነት የራቁት የዓለም ሕዝቦች ንቁ አይደሉም። በውሸት ገነት ውስጥ ተቀምጠው በውሸት ደኅንነት እንደሚደሰቱ ሰካራሞች ናቸው። በዕለተ በዓለ-ኀምሳ መንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያዎቹን ክርስቲያኖች ሲሞላ፥ ያልዳኑት ሰዎች ክርስቲያኖችን «ሰክራችኋል» በማለት ከሰሱአቸው (የሐዋ. 2፡13)። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ እንደ ሰካራም ሰው የሚኖሩት ያልዳኑ ሰዎች ናቸው። የእግዚአብሔር የቁጣው ሰይፍ በዓለም ላይ እያንዣበበ ቢሆንም፥ሰዎቹ ፈሪሃ-እግዚአብሔር የራቀው ሕይወት ከመምራት፥ ከንቱ ሕይወት ከመኖርና ለዘላለማዊ ጉዳዮች ቸልተኛ ከመሆን አልቦዘኑም።

ከዚህ በፊት እምነትን፥ ተስፋንና ፍቅርን የተመለከትን ሲሆን (1፡3)፥ አሁን ደግሞ ከዚች ዓለም ክፋት እንደሚከላከሉልን ጋሻ ሆነው ተገልጸዋል።

እምነትና ፍቅር ልብን እንደሚጋርድ ጋሻ ናቸው ማለት እምነት፥ በእግዚአብሔር ላይ፥ ፍቅር ለእግዚአብሔር ሕዝብ መሆን አለበት ማለት ነው። ተስፋ አእምሮን የሚጠብቅ ጠንካራ የራስ ቁር ነው። ራሳቸውን የሰጡ አማኞች በሰማያዊ ነገሮች ላይ ትኩረታቸውን ሲያደርጉ (ቈላ. 3፡1-3)፥ የማያምኑ ሰዎች ግን በዚህ ዓለም ነገሮች ላይ አእምሮአቸውን ያስቀምጣሉ።

የመዳን ተስፋ ማለት በመጨረሻው እንድናለን የማለት ተስፋ አይደለም። አንድ ሰው ዛሬውኑ እንደዳነና ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚሄድ ሊያውቅ ይችላል። ጳውሎስ የተሰሎንቄ አማኞች እንደዳኑና (1፡4) እርሱና እነርሱ ክርስቶስን በአየር ላይ እንደሚቀበሉት እርግጠኛ ነበር (4፡17)። «እንደዳንሁ አውቃለሁ!» የሚል ሰው በትዕቢት መናገሩ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያለውን እምነት እያሳየ ነው። አንደኛ ዮሐንስ የተጻፈው፥ መዳናችንን እንድናውቅ እንዲረዳን ታስቦ ነው (1ኛ ዮሐ. 5፡9-13)።

የመዳን ተስፋ ማለት «መዳን የሚሰጠን ተስፋ» ማለት ነው። በመሠረቱ ደኅንነትን በተመለከተ ሦስት ዓይነት የጊዜ ሰሌዳዎች አሉ። 1) የኃላፊ ጊዜ፡- ከኃጢአት ጥፋተኛነትና ቅጣት ድኜአለሁ፤ 2) የአሁን ጊዜ፡- ከኃጢአት ኃይልና ብክለት እየዳንሁ ነኝ፤ እና 3) የወደፊት ጊዜ፡- ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ኃጢአት ካለበት በመራቅ እድናለሁ። የጌታችን መመለስ የተባረከ ተስፋው «የደኅንነት ተስፋ» ነው፤ ያልዳኑ ሰዎች ተስፋ የላቸውም (ኤፌ. 2፡12)። ይህም «ነገ እንሞታለንና እንብላ፥ እንጠጣ፥ እንጋባ!» የሚለውን የሕይወት ስልት የሚከተሉበትን ምክንያት ይገልጽልናል።

ጳውሎስ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ከደኅንነት ርቆ የጠፋውን ዓለም ዝንባሌ ለመግለጽ፥ «እንቅልፍ» የሚለውን ቃል ደጋግሞ ጠቅሶታል። ባለፈው አንቀጽ ውስጥ (4፡13-18)፥ ጳውሎስ የአማኙን ሞት ለመግለጽ በዚሁ ቃል ተጠቅሞአል። ሰውነት ወደ እንቅልፍ ሲሄድ፥ መንፈስ ግን ከጌታ ጋር ወደ መሆን ይሄዳል። ይሁንና በዚህ ክፍል፥ እንቅልፍ ሞት ማለት ሳይሆን፥ ሥነ-ምግባራዊ ግዴለሽነትና ለመንፈሳዊ ነገሮች ደንታ-ቢስ መሆን ማለት ነው። ኢየሱስ ይህንኑ ቃል በዚሁ ትርጉሙ በማርቆስ 13፡32-37 ላይ ተጠቅሞበታል።

ሰዎች በማንቀላፋት ወይም ዕረፍት በመውሰድ ያላቸው ሁኔታ አንዱ ከሌላው በእጅጉ ይለያያል። አንዳንድ ሰዎች ዶሮ ሳይጮህ ከእንቅልፋቸው ተነስተው ሥራ መሥራት ይፈልጋሉ። ሌሎች ሰዎች ደግሞ የጠዋት ቡና እስኪፈላ ድረስ ከመኝታቸው መነሣት ያስቸግራቸዋል።

ከደኅንነት ርቀው፥ በስካር ለሚንገላቱት ግን፥ የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ማለት የብርሃን ፍጻሜና የዘላለም ጨለማ ጅማሬ ማለት ነው።

## ደኅንነትና ፍርድ (5፡9-11)

ወደ ፊት የሚመጣው ፍርድ እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀው ዕቅድ አካል ስላልሆነ፥ አማኞች ልንፈራው አይገባም። ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በዓለም ላይ በሚያወርደው አስፈሪ የፍርድ ጊዜ ውስጥ ማለትም በጌታ ቀን ውስጥ ያልፉ ይሆን? አይመስለኝም፤ እንደ 1ኛ ተሰሎንቄ 1፡10 እና 5፡9 የመሳሰሉ ጥቅሶችም ይህንኑ አሳብ የሚደግፉ ይመስላል። ክርስቲያኖች ሁልጊዜም በመከራ ማዕበል ሲንገላቱ ኖረዋል፤ ይህም አንድጊዜ የተሰጠ የክርስትና ሕይወት አካል ነው (ዮሐ. 15፡18-27 እና 16፡33)። ይሁንና ፈሪሃ-እግዚአብሔር ለራቀው ዓለም በተዘጋጀው ታላቅ መከራ ውስጥ አያልፉም።

መልካምና ፈሪሃ-እግዚአብሔራዊ ባሕርይ ያላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በዚህ ጉዳይ ላይ እንደማይስማሙ ስለማውቅ፥ ይህንን የኅብረት ወይም የመንፈሳዊነት መፈተኛ አድርጌ አልወስደውም። ይሁንና ቤተ ክርስቲያን የታላቁ መከራ ጊዜ ከመጀመሩ በፊት ወደ ሰማይ ትነጠቃለች ብዬ አምናለሁ። ለዚህም እምነት ያበቁኝን ምክንያቶች ቀጥዬ እጠቅሳለሁ፡-

1. የቤተ ክርስቲያን ባሕርይ፡- ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ስትሆን፥ እርሱ ደግሞ ራስዋ ነው (ቈላ. 2፡17-19)። በመስቀል ላይ በሞተልን ጊዜ፥ ለደኅንነታችን የሚያስፈልገውን መለኮታዊ ፍርድ ሁሉ ተሸክሞአል፤ ማንኛውንም የእግዚአብሔርን ቁጣ እንደማንቀምስ የተስፋ ቃል ገብቶልናል (ዮሐ. 5፡24)። ስለዚህ የጌታ ቀን የእግዚአብሔር የቁጣ ቀን ስለሆነ፥ የቤተ ክርስቲያን በዚህ መከራ ውስጥ ማለፍ ፍትሐዊነት የሌለውና አላስፈላጊም ይመስላል።

2. የመከራው ባሕርይ፡- ይህ እግዚአብሔር በአሕዛብ ሕዝቦች ላይ የሚፈርድበትና እስራኤልን ከተበተነችበት ሁሉ በማሰባሰብ ለመሢሑ ምጽአት የሚያዘጋጅበት ጊዜ ነው። የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚቀምሱት «የምድር ላይ ነዋሪዎች» እንጂ (ራእይ 3፡10)፥ ሰማያዊ ዜግነት ያላቸው ሰዎች አይደሉም (ፊልጵ. 3፡20)። እግዚአብሔር በምድር ነዋሪዎች ላይ ስለበደላቸው የሚፈርድባቸው ሲሆን (ኢሳ. 26፡20-21)፥ ዳኑ ግን በአማኞች ኃጢአቶች ላይ ቀደም ብሎ በመስቀል ላይ ፈርዷል።

3. የክርስቶስ ቶሎ የመመለስ ተስፋ፡- በቅርብ ጊዜ ማለት «ሊከሰት የተቃረበ» ማለት ነው። ለክርስቶስ መምጣት፥ የክርስቶስን አካል የሚያሟላውን የመጨረሻውን ሰው መዳን ከመጠበቅ በስተቀር፥ ሌላ መፈጸም ያለበት ምንም ነገር የለም። ጌታችን እስከታላቁ መከራ ዘመን መጨረሻ ድረስ የማይመጣ ቢሆን ኖሮ፥ መቼ እንደሚመጣ እርግጠኞች ሆነን ባወቅንም ነበር። ስለምን ቢባል የመከራው ዘመን ቅደም-ተከተሉ፥ ምልክቶቹና ጊዜያቱ ሁሉ በራእይ 6-19 ውስጥ በዝርዝር ተገልጸዋልና ነው። በተጨማሪም ከራእይ 4፡1-22፡13 ድረስ «ቤተ ክርስቲያን» የሚል ቃል እንዳልተጠቀሰ ልብ ማለቱ ተገቢ ነው። እንዲሁም ጳውሎስ ይህን መሠረታዊ ትምህርት በሚያብራራበት ወቅት «እኛ» እና «እናንተ» የሚሉትን ተውላጠ-ስሞች ስለተጠቀመ፥ ጳውሎስ የክርስቶስን መገለጥ ለማየት ተስፋ ያደርግ እንደነበር ልብ በል (1ኛ ተሰ. 4፡13-5፡11)። ሐዋርያው ዮሐንስም ይኸው ተመሳሳይ አመለካከት ስለነበረው፥ መጽሐፉን፥ «አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና» በሚል ጸሎት ደምድሞታል (ራእይ 22፡20)።

4. በራእይ 2-3 የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ሁኔታ፡- በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ጌታ እነዚህን ሰባት አብያተ ክርስቲያናት የመረጠው፥ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ መንፈሳዊ ትምህርት ለማብራራት እንደሆነ ያምናሉ። ኤፌሶን የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ስትሆን፥ ሰምርኔስ የመጀመሪያዎቹ የስደት ምዕተ-ዓመታት ተጠቂ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። የመጨረሻዪቱ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የመጨረሻውን ዘመን ከሃዲ ቤተ ክርስቲያን ትወክላለች።

ይህም የፊልድልፍያ ቤተ ክርስቲያን (ራእይ 3፡7-13) ደካማና ዳሩ ግን ታማኝ ሆና ልክ ክርስቶስ ከመመለሱ ጥቂት ቀደም ብላ የምትኖረውን ቤተ ክርስቲያን እንደምትገልጽ ያመለክታል። ይህች ቤተ ክርስቲያን በርካታ ዕድሎችና የተከፈቱ በሮች ያላት ወንጌል ሰባኪ ቤተ ክርስቲያን ነች። ይህች ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን በቅርብ ጊዜ መምጣት የምትሰብክ ስትሆን («የትዕግሥቴን ቃል ስለ ጠበቅህ» ራእይ 3፡10)፥ ከፍርድ ቀን እንደምትድን የተስፋ ቃል ገብቶላታል፡- «እኔ ደግሞ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ» (ራእይ 3፡10)። ይህም ከ1ኛ ተሰሎንቄ 5፡9ኙ የተስፋ ቃል ጋር ይዛመዳል።

5. በ2ኛ ተሰሎንቄ ውስጥ የሚገኘው የነገሮች ቅደም-ተከተል፡- ምንም እንኳን ይህንን ወደ በኋላ ላይ በዝርዝር የምንመለከተው ቢሆንም፥ ለጊዜው ጳውሎስ የተጠቀመው ቅደም-ተከተል በሌሎች የትንቢት መጻሕፍት ውስጥ ከተጠቀሰው ጋር እንደሚስማማ ልብ በል።

ጳውሎስ የክርስቶስን መመለስ፥ በመስቀል ላይ ከዋጀልን መቤዠት ጋር አያይዞታል፤ «በዋጋ ተገዝተናል።» እኛ የእርሱ ሙሽሪት ስለሆንን፥ በምድር ላይ ፍርድ ከመውረዱ በፊት፥ ወደራሱ ሊወስደን ይመጣል። ክርስቶስ የሞተልን በእርሱ (1ኛ ዮሐ. 4፡9)፥ ለእርሱ (2ኛ ቆሮ. 5፡15)፥ እና ከእርሱ ጋር (1ኛ ተሰ. 5፡10) እንኖር ዘንድ እንደ ሆነ ልብ በል። ብንኖር ወይም ብንሞት («የምንተኛ ወይም የምናንቀላፋም») የጌታ ነንና ከእርሱ ጋር እንኖራለን።

የትንቢት ጥናት ሙሉ ለሙሉ የምሁራን የመከራከሪያ ርእስ ወይም የሙግትና ያለመግባባት ምንጭ እንዲሆን ማድረግ የለብንም። ጳውሎስ ይህንን ክፍል ለነቢያት መጻሕፍት ተግባራዊ ተዛምዶ በመስጠት «ማጽናኛና ማጽኛ» ብሎ አጠቃሎታል። የምንወዳቸውን ሰዎች ዳግም የማግኘታችንና ከጌታ ጋር ለዘላለም የመኖራችን እውነታ የመጽናኛ ምንጭ ሲሆን (1ኛ ተሰ. 4፡18)፥ በጌታ ቀን የእግዚአብሔርን ቁጣ ያለመጋፈጣችን ደግሞ ሌላው የመጽናኛ ምንጭ ነው (1ኛ ተሰ. 5፡11)። የመጀመሪያው አዎንታዊ፥ ሁለተኛው አሉታዊ ሲሆን፥ ሁለቱም ግን የሚያጽናኑን ናቸው።

የጌታችን በቅርብ ጊዜ መመለስ በንጽሕና እንድንኖርና (1ኛ ዮሐ. 3፡1-3) የሰጠንን ማንኛውንም ሥራ በታማኝነት እንድናከናውን ያበረታታናል (ሉቃስ 12፡41-48)። እንዲሁም ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት እንድንካፈልና ወንድሞቻችንን እንድንወድም ያበረታታናል (ዕብ. 10፡25)። ከጌታ ጋር እንደምንሆን ማወቃችን በሕይወት አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ብርታት በመስጠት (2ኛ ቆሮ. 5፡1-8)፥ ከደኅንነት ርቀው የጠፉትን እንድንመልስ ያነሣሣናል (2ኛ ቆሮ. 5፡9-21)።

በዚህ ምድር ላይ ምቹ የአኗኗር ሁኔታ ያላቸው በርካታ አማኞች፥ ወደ መንግሥተ ሰማይ ስለመሄድና ከጌታ ጋር ስለመገናኘት እምብዛም አያስቡም። አንድ ቀን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንደሚቀርቡ ይዘነጋሉ። ኢየሱስ ዳግም እንደሚመለስ የማስታወሱ እውነታ፥ ወደ ላይ አቅንተን እንድንመለከትና እንድንታነፅ ይረዳናል።

እስከ ዛሬ በእርሱ ካልታመንህ፥ ወደ ፊት የሚጠብቅህ ፍርድ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እውነቱን ስለሚነግርህ፥ አላዋቂ መሆን የለብህም። ዛሬ በክርስቶስ ልትታመንና ዳግም ልትወለድ ስለምትችል፥ ሳትዘጋጅ ልትቆይ አይገባም። በክርስቶስ የደኅንነትን ብልጽግና በማግኘት ልትደሰት ስትችል፥ ዋጋ ቢስ ለሆነ እና ኃጢአት ለሞላበት የዓለም የአኗኗር ዘይቤ ለምን ራስህን ትሰጣለህ?

አምነህ ያልዳንህ ከሆነ፥ በፍርድ ፊት ለመቅረብ ቀጠሮ ይዘሃል ማለት ነው። «ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት፥ ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደተመደበባቸው» እሙን ነውና ከምትገምተው የጊዜ ገደብ ፈጥኖ ከተፍ ሊልብህ ይችላል (ዕብ. 9:27)። ለምን ከክርስቶስ ጋር «ቀጠሮ» ይዘህ፥ በግል አትገናኘውምና ለደኅንነትህም በእርሱ አትታመንም? «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና» (ሮሜ 10:13)።

# 1ኛ ተሰሎንቄ 5፡ 12-28

«ወንድሞች ሆይ፥ በመካከላችሁ የሚደክሙትን በጌታም የሚገዙአችሁን የሚገሥጹአችሁንም ታውቁ ዘንድ፥ ስለ ሥራቸውም በፍቅር ከመጠን ይልቅ ታከብሩአቸው ዘንድ እንለምናችኋለን፡፡እርስ በርሳችሁ በሰላም ሁኑ። ወንድሞች ሆይ፥ እንመክራችኋለን። ያለሥርዓት የሚሄዱትን ገሥጹአቸው፤ድፍረት የሌላቸውን አጽኑአቸው፤ ለደካሞች ትጉላቸው፤ ሰውን ሁሉ ታገሡ። ማንም ለሌላው በክፉ ፈንታ ክፉን እንዳይመልስ ተጠንቀቁ፤ ነገር ግን ሁልጊዜ እርስ በርሳችሁ ለሁሉም መልካሙን ለማድረግ ትጉ። ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና። መንፈስን አታጥፉ፤ ትንቢትን አትናቁ፤ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ፤ ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ።

«የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ። የሚጠራችሁ የታመነ ነው፥እርሱም ደግሞ ያደርገዋል።

«ወንድሞቼ ሆይ፥ ስለ እኛ ጸልዩ።

«ከወንድሞች ሁሉ ጋር በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ ተሰጣጡ።

«ይህ መልእክት ለቅዱሳን ወንድሞች ሁሉ እንዲነበብ በጌታ አምላችኋለሁ።

«የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን፤ አሜን።»

# ምእመናን ሁሉ እንደ አንድ ቤተሰብ አባላት

ጳውሎስ አማኞችን የሚጠራበት ተወዳጅ ስም «ወንድሞች» የሚለው ነው። ይህንን ስም በመልእክቶቹ ውስጥ ቢያንስ 60 ጊዜያት ያህል የተጠቀመበት ሲሆን፥ በሁለቱ የተሰሎንቄ መልእክቶች ውስጥ 27 ጊዜያት ያህል ጠቅሶታል። ጳውሎስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን እንደ አንድ ቤተሰብ ይመለከት ነበር። እያንዳንዱ ምእመን በእግዚአብሔር መንፈስ የተወለደ ሲሆን፥ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ተላብሶአል (1ኛ ጴጥ. 1፡22-25፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡3-4)። ሁላቸውም የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት ነበሩ።

አማኞች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ችላ ብለው ሲተዉ ወይም ሲያገሉ ማየት አሳዛኝ ነው። ማንኛውም ቤተሰብም ሆነ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ፍጹም አይደለም፤ ይሁንና ጠባቂና የሚያስፈልገውን የሚያሟላለት ቤተሰብ የሌለው ልጅ፥ በችጋር ከመሞት አያመልጥም። የእግዚአብሔር ልጁ እንዲያድግ፥ ተሰጥአውን እንዲያበለጽግና እግዚአብሔርን እንዲያገለግል ከተፈለገ፥ የቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ መሆን ያስፈልገዋል።

ለደስተኛና ጠንካራ የቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ የሚያስፈልጉ ነገሮች ምንድን ናቸው? አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናታችንን ለእግዚአብሔር ክብር የበለጠ መንፈሳዊ ልናደርግ የምንችለው እንዴት ነው? በዚህ የጽሑፉ የመዝጊያ ክፍል ውስጥ፥ ጳውሎስ እነዚህን ነገሮች ገልጾአል።

## የቤተሰብ መሪነት (5፡12-13)

መሪ የሌለው ቤተሰብ መፈራረሱ አይቀርም። በመሆኑም፥ አባት የቤቱን መሪነት ሲረከብ፥ እናትም በፍቅርና በመስማማት መንፈስ ከጐኑ ትቆማለች። ልጆች ደግም ወላጆቻቸውን መታዘዝ አለባቸው። ይህ እግዚአብሔር የመሠረተው ሥርዓት ስለሆነ፥ ይህንን የሥርዓት ደረጃ ማቀያየሩ የከፋ ችግር ሊያስከትል ይችላል።

ሚስተር ማርቲን ኤል. ግሮስ «ዘ ሳይኮሎጂካል ሶሳይቲ» በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ እንደገለጹት፥ በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካ የሕዝብ የትምህርት አወቃቀር ውስጥ ስልሳ ሺህ የተማሪ አማካሪዎችና ሰባት ሺህ የሥነ-ልቡና ጠበብት ተግባራቸውን ያከናውናሉ፤ ከእነዚህም መካከል ብዙዎቹ እንደ ተተኪ ወላጆች ሆነው ይሠራሉ። በርካታ ተማሪዎች የምክር

እርዳታ የሚያሻቸው ቢሆንም፥ ዳሩ ግን ይህ አገልግሎት የአፍቃሪና ታማኝ አባት ወይም እናትን ስፍራ የመተካት ብቃት የለውም።

ታላቁ ልጃችን ወደ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በገባ ጊዜ፥ የተመደበለትን አማካሪ አገኘ። አማካሪውም፥ «እንግዲህ፥ ማናቸውም ዓይነት ችግሮች ቢገጥሙህ፥ ወደ እኔ ከመምጣት አትቆጠብ» ብሎታል። ልጃችን ግን፥ «ማናቸውም ችግሮች ቢኖሩብኝ፥ ለአባቴ እናገራለሁ» በማለት መለሰለት። ይህን በማለቱ ለአማካሪው አክብሮት ወይም አድናቆት መንሳቱ ሳይሆን፥ የመሠረታዊውን መመሪያ መግለጫ መስጠቱ ነበር፤ ለልጆች ወላጆች ብቻ ሊሰጡት የሚችሉት ምሪት ያሻቸዋል።

እግዚአብሔር ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የመሪነትን ሹመት ሰጥቷል። «ሁላችንም በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ መሆናችን» እውነት ቢሆንም (ገላ. 3፡28)፥ ዳሩ ግን የቤተ ክርስቲያኒቱ ራስ ለሰዎች የተለያየ ስጦታ እንደሰጠና ከእነዚህም ሰዎች አንዳንዶቹ ፈቃዱን ይፈጽሙ ዘንድ ለአብያተ ክርስቲያናት መሪ ሆነው መመደባቸው እውነት ነው (ኤፌ. 4፡7-16)። ልክ ለአንድ መንጋ እረኛ እንደሚያስፈልግ ሁሉ (1ኛ ጴጥ. 5፡1-5)፥ ለቤተሰብም መሪ ያስፈልገዋል።

ወንድሞች ለመንፈሳዊ መሪዎቻቸው ያሉአቸው ኃላፊነቶች ምንድን ናቸው?

1. መቀበል፡- እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣቸው ስጦታዎች ስለሆኑና ከጌታም ዘንድ መንፈሳዊ ሥልጣን ስላላቸው፥ መሪዎችን ልንቀበላቸው ይገባል። እነርሱም አመራር ሰጪዎችና ምሳሌዎች እንጂ፥ አምባገነኖች አይደሉም፤ እነርሱም ጌታን እንደሚከተሉ፥ እኛም ልንከተላቸው ይገባል።

2. ማመስገን፡- ይህ «በመካከላችሁ የሚደክሙትን እወቁአቸው» ለሚለው ምክር ትርጉሙ ነው (1ኛ ተሰ. 5፡12)። እግዚአብሔር ክብሩን እስከወሰደ ድረስ፥ የእግዚአብሔርን ታማኝ አገልጋዮች ማክበሩ ስሕተት አይደለም። መንፈሳዊ መሪነት ታላቅ ኃላፊነትና አስቸጋሪ ሥራ ነው። እንደ መጋቢ፥ ሽማግሌ፥ ዲያቆን፥ ወይም ሌላ መንፈሳዊ መሪ ሆኖ ማገልገል ቀላል ነገር አይደለም። ጦርነቶችና ሸክሞች በርክተው ሳለ፥ አንዳንዴ ከምእመናኑ የሚለገሱት ማበረታቻዎች ከግምት በታች ይሆናሉ። የቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ መሪዎቻቸውን በዋዛ በመመልከት

ሳይጸልዩላቸው፥ አብረዋቸው ሳይሠሩና ሳያበረታቱአቸው ሲቀሩ አደገኛ ሁኔታ ይፈጠራል።

3. መውደድ፡- እነዚህ ሰዎች ወንድሞች እንደመሆናቸው «ከመካከላችን» የሚገኙ ሲሆን፥ መሪዎች እንደመሆናቸው «በጌታ ከእኛ በላይ» ናቸው። እውነተኛ ክርስቲያናዊ ፍቅር ከሌለ ይህ በጣም የሻከረ ግንኙነት ሊሆን ይችላል። ይኸውም ለመጋቢው በተመሳሳይ ጊዜ ከምእመናኑ «መሀል» እና «በላይ» ሆኖ ለመገኘት ጸጋንና የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ስለሚጠይቅ ነው። ሚዛኑን ካልጠበቀ፥ አገልግሎቱ ሊዳከምና ሊበላሽም ይችላል። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን መጋቢያቸው የቅርብ ወዳጃቸው እንዲሆን ይፈልጋሉ፤ ይኼ ግን አገልግሎቱን ያዳክመዋል። በሌላ በኩል በሥልጣኑ ላይ ብቻ የሚያተኩር ከሆነ፥ ራስ-ወዳድና አምባገነን ሊሆን ይችላል።

4. ማክበር፡- «ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ» (ዕብ. 13፡17)። የእግዚአብሔር አገልጋይ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ፥ የእግዚአብሔርን ቃል እንድንታዘዝ ሲጠይቀን፥ ትእዛዙን መፈጸም ይገባል፤ ይህም ማለት ሁሉም መንፈሳዊ መሪ በሁሉም ነገር ትክክል ነው ማለት አይደለም። አብርሃም፥ ዳዊትና ጴጥሮስ ሳይቀሩ በቃላቸውና በድርጊታቸው ስሕተት ፈጽመዋል። አስተዋይ መሪ ከሸክላ እንደ ተሠራ በማወቅ፥ በሚሳሳትበት ወይም የአዋቂዎች ምክር በሚያስፈልግበት ጊዜ በፈቃደኝነት ይቀበላል። በራሴ አገልግሎት ውስጥ፥ ከእኔ የተሻለ እውቀትና ልምድ ያላቸው የተራ ምእመናን ምክርና አገልግሎት በብዙ አቅጣጫዎች ጠቅሞኛል።

ይሁንና፥ ከውስንነታቸው ባሻገር፥ የእግዚአብሔር መንፈሳዊ መሪዎች ሊከበሩና ታዛዥነትንም ልናሳያቸው ይገባል፤ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ እስካልሆኑ ድረስ። የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መሪዎች በአንድነት ሲሰባሰቡ፥ ሲያለቅሱ፥ ሲጸልዩ፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሲሹና ሲከተሉ፥ እግዚአብሔር በሚያደርጉአቸው ውሳኔዎች ውስጥ እንደሚገባና በበላይነት እንደሚቆጣጠር እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን።

መንፈሳዊ መሪዎችን የሚከተል የቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ ውጤት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰላምንና አንድነትን ማግኘት ነው፤ «እርስ በርሳችሁ በሰላም ሁኑ» (5፡13)። በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከፋፈልና መለያየት የሚኖረው በመሪዎች፥ ወይም በምእመናን፥ ወይም በሁለቱም ወገን ራስ-ወዳድነትና ኃጢአት በመኖሩ ምክንያት ነው። ያዕቆብ

4፡ 1-3 በግልጽ እንደሚያስቀምጠው፥ ከውስጥ በኩል ራስ-ወዳድነት ካለ በውጭ በኩል አድመኛነትን ያስከትላል። በቤተሰቡ ውስጥ በረከትና ሰላም አግኝተን ልንደሰት የምንችለው፥ በጌታ ስም አንዳችን ለሌላችን ስንገዛ ብቻ ነው።

ይሁንና መሪዎች ብቻ የአገግሎቱን ሥራ ሁሉ ሊወጡ አይችሉም፤ በመሆኑም ጳውሎስ ሁለተኛውን አስፈላጊ ነገር አክሎ ይጠቅሳል፡-

## በቤተሰብ መካከል ያለ ኅብረት (5፡ 14-16)

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አብያተ ክርስቲያናት «የአካል ሕይወት» የሚባለውን ነገር ለዳግመኛ ጊዜ እየተለማመዱት መጥተዋል። ምንም እንኳ ይህ በቤተ ክርስቲያን መጠሪያነቱ የአንድን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ሙሉ በሙሉ ባያካትትም፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተገኘ ጽንሰ-አሳብ ነው። የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ጤንነትን ለመጠበቅና ሕይወትን ለማቆየት እርስ በርሳቸው እንደሚረዳዱ ሁሉ፥ የአካል ሕይወትም እያንዳንዱ ክርስቲያን ለሌላው የሚያበረክተውን አገልግሎት ያመለክታል።

የቤተሰቡ አባላት አንዱ ለሌላው ማገልገልን መማር አለባቸው። ታላላቆቹ አባላት ታናናሾቹን ከማስተማር ባሻገር (ቲቶ. 2፡3-5 ተመልከት)፥ በችግር ውስጥ በሚሆኑበትም ጊዜ ያበረታቱአቸዋል። በአንድ የክረምት የመጽሐፍ ቅዱስ ኮንፍራንስ ላይ እያስተማርን ሳለን፥ እኔና ባለቤቴ ዘጠኝ ልጆች ያሉአቸውን ግሩም ባለትዳሮች አገኘን። በዚህ ቤተሰብ ውስጥ ታላላቆቹ ልጆች ታናናሾቹን እንዴት እንደሚረዱዋቸውና ወላጆቻቸውም ኃላፊነታቸው በመቀነሱ የዕረፍት ጊዜያቸውን በደስታ እንደሚያሳልፉ መመልከቱ በጣም የሚያረካ ነበር።

በኤፌሶን 4፡ 12 ላይ እንደተመለከተው፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ መሪዎች ምእመናን የአገልግሎቱ ተካፋይ ይሆኑ ዘንድ እንዲሳተፉ የማስተባበርና የማስታጠቅ ኃላፊነት ይጠበቅባቸዋል። ሆኖም በብዙዎቹ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እንደሚታየው፥ ምእመናን መሪዎቹ የአገልግሎቱን ሥራ እንዲወጡ ደመወዝ ይከፍሉዋቸዋል። ይሁንና፥ መሪዎች ሁሉንም ሥራ ለማከናወን አይችሉም። ከዚህም የተነሣ፥ ሥራው መዳከምና መሞት ሲጀምር፥ ሁሉም ሰው በሰባኪው ላይ ወቀሳውን ይሰነዝራል።

ጳውሎስ የግል እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን አንዳንድ ልዩ የቤተሰብ አባላትን ጠቅሶአል።

1. ያለ ሥርዓት የሚሄዱ (5፡14)፡- ይህ ሐረግ «ግዴለሽ፥ ከመሥመር የወጣ» የሚል ፍች አለው። ይህ ቃል ደረጃውን ሳይጠብቅ በራሱ መንገድ የሚሰማራውን ወታደር ለመግለጽ ያገለገለ ቃል ነው። የቤተሰብ የፍቅር ድባብ የግል ዕድገትን የሚያበረታታ ሲሆን፥ ሁላችንም በተመሳሳይ መንገድ ልናከናውናቸው የሚገቡን አንዳንድ ነገሮችም አሉ። በቤተሰብ ውስጥ ደንቦችና መመዘኛዎች ከሌሉን፥ ሥርዓተ-አልበኝነት ይነግሣል። ጳውሎስ ሁለተኛውን የተሰሎንቄ መልእክት በጻፈም ጊዜ ይህንኑ ጉዳይ በድጋሚ በመጥቀሱ (3፡6፥ 11)፥ ይህ የመጀመሪያው ምክሩ ለውጥ ያላስገኘ መሆኑን ያመለክታል።

በቤተሰብ ውስጥ የግል ፈጠራ ችሎታ እንዳይዳብር የሚያደርጉ፥ ደንቦችና ወጐች ከቶውንም ከመጠን በላይ ሊጋነኑ አይገባም። ለአንድ ወላጅ፥ እያንዳንዱ ልጅ በራሱ ስብእና፥ ብቃትና ፍላጐት አኳያ ወደ ተሳካ መሥመር ሲያመራ መመልከቱ ትልቅ ደስታ ነው። ይሁንና ልጅ በደንቦች ላይ ሲያምፅ፥ ወጐችንና መመዘኛዎችን ሲያናንቅና የራሱን የሕይወት ዘይቤ፥ ነፃነትና ብስለት እንደሚያመለክት አድርጐ ሲያስብ መመልከቱ አሳዛኝ ነው። የዚህ ዓይነቱ አመለካከት በቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ሙግቶችንና መከፋፈልን ያስከትላል።

2. ድፍረት የሌላቸው (5፡14)፡- የዚህ ቃል ቀጥተኛ የግሪኩ ትርጉም «ልበ-ድንጉጥ፥ ሆደ-ባሻ» የሚል ነው። እነዚህ በቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ተስፋ ቆርጠው የሚመለሱ ሰዎች ናቸው። ሁልጊዜም የነገሮችን ሸካራ ገጽታ በመመልከት፥ ጉዞው አቀበት ሲሆንባቸው ማቋረጡን ይመርጣሉ። ሦስት ወይም አራት ልጆች ባሉበት ቤተሰብ ውስጥ፥ ባብዛኛው አንደኛው ተስፋ የሚቆርጥ ይሆናል። እያንዳንዱም የቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ ከመሀሉ የራሱ የሆነ ተስፋ ቆራጭ ሰው አለው።

እነዚህን ሰዎች ማበረታታት ያስፈልጋል። ይህ አሳብ ደግሞ በ1ኛ ተሰ. 2፡11 ላይ ይገኛል። የግሪኩ ቃል «ፓራ» ፥ ቅርብ እና «ሙተስ»፥ ንግግር ከሚሉ ሁለት ቃላት የተገነባ ነው። ድፍረት የሌላቸውን ሰዎች በሩቁ ከመቆጣት ቀረብ ብለን በፍቅር ልንናገራቸው ይገባል። «ሆደ-ባሻነት» ለሚያጠቃቸው ሰዎች በሕይወት ውስጥ የሚፈጸሙ መከራዎች እነርሱን ለማሳደግና በእምነት ለማጽናት እንደሚረዱ ልናስተምራቸው ይገባል።

3. ደካሞች (5፡14)፡- ይህ ቃል «ደካሞችን አጥብቃችሁ ያዙ» ተብሎ በቀጥታ ሊተረጐም ይችላል። «እንዳይወድቁ አጽኑአቸው!» ይሁንና

እነዚህ ደካማ አማኞች እነማናቸው? ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላለው የአገልግሎት ጉዳይ እየተናገረ ስለሆነ፥ በሥጋቸው ደካሞች የሆኑትን ማለቱ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። እርሱ የሚለው «በእምነት ደካሞች» የሆኑትንና በጌታ ያልበረቱትን ሰዎች ነው (ሮሜ 14፡1-15፡3)።

ባመዛኙ፥ ደካማ ክርስቲያኖች በክርስቶስ ያገኙትን ነፃነት ለመለማመድ የሚፈሩ ሰዎች ነበሩ። በደንቦችና ሥርዓቶች ይኖሩ ነበር። በሮም ግዛቶች የሚኖሩት ደካማ ክርስቲያኖች ሥጋ ካለመብላታቸውም በቀር፥ የአይሁድን የበዓል ቀናት ይጠብቁ ነበር። ሁሉንም ዓይነት ምግብ በሚበሉና በሁሉም ቀናት በሚሠሩ በሳል ቅዱሳን ላይ በሚሰነዝሩት የፍርድ ቃላትም ኃይለኞች ነበሩ።

በተወለድንበት ቤተሰብ ውስጥ ከሌሎች ይልቅ ፈጠን ብለው ወደ በሳልነት የሚደርሱ ልጆች እንዳሉ ሁሉ፥ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ቤተሰባችንም ውስጥ ጠንካራና ደካማ አባላት አሉ። እንግዲህ፥ እንዴት እንያዛቸው? ታጋሽና አስተማማኝ በሆነ ፍቅር ልንይዛቸው ይገባል። እያንዳንዱ በራሱ ጊዜና በራሱ መንገድ ወደ ብስለት ስለሚደርስ፥ አንዱን ልጅ ከሌላው ጋር ማወዳደሩ ተገቢ አይደለም። እነዚህን ደካማ አማኞች ልንንከባከብና በጌታ ቆመው እንዲመላለሱ ልንረዳቸው ይገባል።

እንዲህ ዓይነቱ የግል አገልግሎት ቀላል ባለመሆኑ፥ ጳውሎስ እኛን ለማበረታታት በማሰብ ጥቂት የጥበብ ምክሮችን ይሰጠናል፡-

ሀ. ትዕግሥተኛ ሁን (5፡14)፡- ቤተሰብን ለማስተዳደር ትዕግሥትን ይጠይቃል። ብዙ እገዛ የሚያስፈልገው ደካማው አባል አንድ ቀን ምርጥ መሪ ሊሆን ይችላልና ከቶውንም ተስፋ አትቁረጥ። በአንድ መጋቢ ወዳጄ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስብከት ካደረግሁ በኋላ፥ ቁጭ ብለን ስንነጋገር፥ አንድ 10 ዓመት ዕድሜ የሆነው ልጅ በአግዳሚ ወንበሮቹ መሀል አልፎ ሲሮጥ አየን። ወዳጄም፥ «በሰንበት ትምህርት ቤት በጣም በጥባጭ የነበሩ ልጆች ብዙውን ጊዜ መጋቢዎች ወይም ወንጌላውያን እንደሚሆኑ ልብ በልህ ታውቃለህ?» አለኝ። ስለዚህ በትዕግሥት መጠበቁ ውጤት ይኖረዋል!

ለ. አነሣሽ ምክንያቶችህን መርምር (5፡14) - ብዙውን ጊዜ ሌሎችን ስናገለግል፥ መልሰው ያጥላሉናል፥ብሎም ይቃወሙናል። ባመዛኙ አመስጋኞች አይደሉም። ይሁንና ሁልጊዜም በፍቅር ልናገለግልና ይቀር

ለማለትም መዘጋጀት አለብን። «ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ። ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ። ተወዳጆች ሆይ፥ ራሳችሁ አትበቀሉ፥ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፤ በቀል የእኔ ነው፥ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና። ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው፤ ቢጠማ አጠጣው፤ ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህና። ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ» (ሮሜ 12፡17-21)።

አነሳሽ ምክንያትህ (ዓላማህ) አድናቆትና ምስጋና ለማግኘት ከሆነ፥ በትካዜ ልትዋጥ ትችላለህ። ዳሩ ግን ዓላማህ፥ «ስለ ኢየሱስም ራሳችንን ለእናንተ ባሪያዎች እናደርጋለን» የሚል ከሆነ (2ኛ ቆሮ. 4፡5)፥ ከቶውንም ለኃዘን አትዳረግም።

ሐ. ደስተኛ ሁን (5፡16)፡- ደስታ ከአገልግሎት ውስጥ ሸክምን ያስወግዳል። «የእግዚአብሔርም ደስታ ኃይላችሁ ነውና» (ነህ. 8፡10)፤ እግዚአብሔር ደጉን አገልጋይና ለጋሱን ሰጪ ይወደዋል። እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ አጉል ተጠራጣሪ የሆነ ወይም በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጥ አባል አለው። ፊታቸውን መመልከትና ንግግራቸውን ማድመጥ፥ ልክ ሙት አካልን መርምሮ ሚቹን ለሕልፈት የዳረገውን ምክንያት ለመመስከር የሚያስቸግረውን ያህል የተወሳሰበ፥ ወይንም ደግሞ በክረምት ወደ ቀዝቃዛ ሐይቅ ውስጥ የመግባትን ያህል የከበደ ነው። እግዚአብሔር ቤተሰቡ ደስተኛ እንዲሆን ይፈልጋል፤ ይህም ማለት እያንዳንዱ የቤተሰቡ አባል ለደስታው መጕልበት አስተዋጽኦ ማበርከት አለበት ማለት ነው።

ጳውሎስ የጠቀሳቸው አራቱ መንፈሳዊ ባሕርያት፥ማለትም ፍቅር (ቁ. 13)፥ ደስታ (ቁ. 16)፥ ሰላም (ቁ. 13) እና ትዕግሥት (ቁ. 14)፥ በገላትያ 5፡22 ላይ የተጠቀሱ የመንፈስ ፍሬ አካላት ናቸው። እነዚህ መንፈሳዊ ብቃቶች እኛ የምናመርታቸው ሳይሆኑ፥ ለመንፈስ ቅዱስ ራሳችንን ስንሰጥና እንዲቆጣጠረንም ስንፈቅድለት የሚከሰቱ ነገሮች ናቸው።

የቤተሰብ ኅብረት ለቤተ ክርስቲያን ጤንነትና ዕድገት ወሳኝ ነው። ለመሆኑ አንተስ የራስህን የሸክም ድርሻ እየተወጣህ ነው? ወይስ ሌሎች ሥራውን እንዲያከናውኑ በታዛቢነት ትመለከታለህ?

## የቤተሰብ አምልኮ (5፡ 17-28)

አምልኮ እጅግ የላቀ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ ተግባር ነው። አገልግሎት ከአምልኮ መፍለቅ አለበት፤ ይህ ካልሆነ ግን ኃይልና የልብ መስጠት የሌለው የጥድፍያ ተግባር ይሆናል። «ውጤቶች» ሊኖሩት ቢችሉም፥ እግዚአብሔርን ሊያስከብሩ ወይም ዘለቄታነት ሊኖራቸው አይችልም። በርካታ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች በእውነተኛ አምልኮ ላይ አጽንኦት ስለማያደርጉ፥ ጉባኤው የሚፈልገውን ብቻ የሚያቀርቡ፥ ሃይማኖታዊ መዝናኛዎች በመሆን ላይ ይገኛሉ።

ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን የአምልኮ አገልግሎት የሚያስፈልጉትን ጠቃሚ ነጥቦች ዘርዝሯል፡-

1. ጸሎት (5፡ 17)፡- ጸሎት በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ዋጋ ይሰጠው የነበረው ከመሆኑም (1ኛ ቆሮ. 11፡ 1-6፤ የሐዋ. 1፡ 13-14፤ 4 ከቁጥር 23 ጀምሮ)፥ በምእምናኑም ዘንድ በጸሎት መተባበር ከፍተኛና የተቀደሰ ልምምድ ነበር። ዛሬ «አንድ ሰው በጸሎት እንዲመራን» እንጠይቃለን ማለቱን የተላመድነው ቢሆንም፥ ያ አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ይኑረው አይኑረው የምናውቀው ነገር የለም። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የጸሎት ስብሰባውን ሁልጊዜ በበላይነት የሚቆጣጠሩ ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች አሉ። በመንፈስ የምንመራ ከሆነ ግን (ይሁዳ 20)፥ ሁላችንም በጸሎታችን ውስጥ አንድነትንና ነፃነትን እንለማመዳለን፤ እግዚአብሔርም መልሱን ይሰጠናል።

«ሳታቋርጡ ጸልዩ» ማለት ሁልጊዜም ጸሎትን በማነብነብ ማሳለፍ እንዳለብን አያመለክትም። የቃሉ ትርጉም «አዘውትሮ በተከታታይ የሚፈጸም» ማለት እንጂ «ባለማቋረጥ የሚከናወን» ማለት አይደለም። ጸሎታችን የልባዊ ውይይት አካል እንዲሆን፥ በዙርያችን ሆነው የሚያውኩንን ድምፆች ሁሉ አስወግደን ከእግዚአብሔር ጋር መሆን አለብን። እግዚአብሔር የልብን መሻት ስለሚያውቅ (መዝ. [37]፡ 4)፥ ድምፃችን በማይሰማበት ጊዜ እንኳ ለእነዚያ መሻቶች ምላሽ ይሰጣል (መዝ. [10]፡ 17፤ [21]፡ 2)።

2. ምስጋና (5፡ 18)፡- ይህ ደግሞ ዋንኛ የአምልኮ አካል ነው። «በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ» በመጠቀም፥ ለጌታ ያለንን ፍቅርና ምስጋና እንገልጻለን (ኤፌ. 5፡ 19)። የእግዚአብሔርን ቃል

በመጠቀሙ ረገድ እያደግን ስንሄድ፥ በምስጋና አገላለጻችንም ማደግ አለብን፤ ሁለቱም አብረው የሚሄዱ ናቸውና (ቈላ. 3፡16)። አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን «በጸጋ እያደገች ከሆነ» ምእመኖችዋ ለእግዚአብሔር ምስጋና ለማቅረብ አዳዲስ መዝሙሮችን ለመማር ይሻሉ። አእምሮና ልብ እርስ በርሳቸው ካልተስማሙ፥ የክርስቲያን አምልኮ አንድም ያልበሰለ፥ አለበለዚያም ታማኝነት የጐደለው ይሆናል።

3. የእግዚአብሔር ቃል (5፡19-21)፡- ከእግዚአብሔር ቃል በስተቀር፥ ከጌታ የተሰጠን ሁነኛ መገለጥ የለንም። መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ዳር የሚገፋ አምልኮ መንፈሳዊ አይደለም። በስሜት መመሰጥና፥ብሎም በተለያዩ እንቅስቃሴዎች አምልኮን መግለጽ ሊኖር ይችላል፤ ይሁንና መንፈሳዊ እውነት እስከሌለ ድረስ፥ መንፈስ ቅዱስ ሥራውን ሊያከናውን አይችልም። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የሚገኙት ሦስቱ ምክሮች ጐን ለጐን የሚሄዱ ከመሆናቸውም፥ መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያን አምልኮ ውስጥ እንዴት እንደሚሠራ ለመረዳት ያስችሉናል።

የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን እንደእኛ ተጽፎ የተጠቃለለ መጽሐፍ ቅዱስ አልነበራትም። መንፈስ ቅዱስ ለተወሰኑ የቤተ ክርስቲያን አባሎች የትንቢትን ስጦታ በመስጠት፥ በእነርሱ በኩል መልእክቱን ያስተላልፍ ነበር። እኔ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በምሰብክበት ጊዜ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን እውነታ በመጥቀስ እሰብካለሁ። እነዚያ የቀድሞዎቹ ነቢያት ግን ልክ በመንፈስ ቅዱስ እንደተመሩ ወዲያውኑ እውነቱን በስብከት ያስተላልፉ ነበር። መንፈሳዊ እውቀታቸው በመንፈስ አማካኝነት የሚሰጣቸው ሲሆን፥ ባመዛኙ በልሳን ይናገሩ ነበር። ለዚህም ነው በ1ኛ ቆሮንቶስ 13 ውስጥ ሦስቱ ስጦታዎች ማለትም ትንቢት፥ ልሳናትና እውቀት በአንድ ላይ የተቀመጡት።

በመሠረቱ በዚህ ዓይነቱ አገልግሎት ውስጥ፥ ሰይጣን (ወይም ሥጋ) የእግዚአብሔርን መልእክት በማስመሰል፥ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ጥፋት ሊመራ ስለሚችል፥ አደገኛ ሁኔታዎች ያጋጥማሉ። ቤተ ክርስቲያን ተናጋሪዎቹን ብታግድ፥ መንፈስን የማጥፋት በደለኛ ልትሆን ትችላለች። የሚነገረውን ሁሉ ተቀብላ ብታምን ደግሞ፥ የሐሰት መናፍስትን መታዘዟ ሊሆን ይችላል። ለዚህ እንግዲህ መፍትሔው «ሁሉንም መመርመሩ» ነው። መናፍስትን የመለየት ስጦታ ሊኖር ይገባል (1ኛ ቆሮ. 12፡10፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡1-4)። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 14፡29-33 ውስጥ ዝርዝር ደንቦችን ሰጥቷል።

ዛሬ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ሙሉ መገለጥ ስላለን፥ የነቢያት ጉዳይ አስፈላጊ አይደለም። ነቢያትና ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያንን መሠረት ለመጣል ያገዙ ሲሆን (ኤፌ. 2፡20)፥ አሁን ግን ከዕይታ ርቀዋል። ያለን ብቸኛው «የትንቢት አገልግሎት» በእግዚአብሔር ቃል ስብከትና ትምህርት ውስጥ ብቻ ነው።

«ማጥፋት» የሚለውን ቃል በመጠቀም፥ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን መንፈስ እንደ እሳት አድርጎ ይገልጸዋል (ኢሳ. 4፡4፤ የሐዋ. 2፡3፤ ራእይ 4፡5 ተመልከት)። እሳት ንጽሕናን፥ ኃይልን፥ ብርሃንን፥ ሙቀትን፥ እና (ካስፈለገም) ጥፋትን ያመለክታል። መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችንና በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በሚሠራበት ጊዜ፥ ለልባችን የፍቅር ሙቀት፥ ለአእምሮአችን ብርሃን፥ ብሎም ለፈቃዳችን ኃይል ይኖረዋል። ሁላችንንም በአንድነት «ስለሚያቀልጠን፥» ኅብረትና መተባበር ይኖራል፤ ስለሚያነጻንም ኃጢአትን እናስወግዳለን።

የመንፈስ ቅዱስ እሳት ከልባችን መሠውያ ላይ ከቶውንም መጥፋት የለበትም፤ ሕይወታችንን የሚያነቃቃውንና የሚያጐለብተውን ለክርስቶስ ያለንን መሰጠት መጠበቅ አለብን።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ፥ «በአንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሣሣ አሳስብሃለሁ» ብሏል (2ኛ ጢሞ. 1፡6)። የዚህም አንቀጽ ፍች፥ «የተዳፈነውን እሳት አቀጣጥል» ማለት ነው። ይህን ለጢሞቴዎስ ማስታወስ ማስፈለጉ ምናልባትም ይህንን ስጦታ ችላ ይለው ስለነበር ሳይሆን አይቀርም (1ኛ ጢሞ. 4፡14)። አማኞችና አጥቢያ ጉባኤ አክራሪ ወገኖችን ማስወገድ አለባቸው፡- ስለምን ሕግ አጥባቂና ወግ ጠባቂው ሰው እሳቱን ሲያዳፍነው፥ በጭፍን አማኙ ደግሞ እሳቱ ሁሉንም ነገር እንዲያቃጥል ስለሚፈቅድ ነው።

ለአምልኮ በምንሰበሰብበት ጊዜ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያስተምረን ልንፈቅድለት ይገባል። ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ለሌሎች የምታጋራው ተዛማጅ ነገር ካለ «ማካፈሉ» መልካም ነው፤ በበኩሌ ግን በዚህ ዓይነቱ ስብሰባ ላይ ብዙውን ጊዜ ትክክለኛ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል የማልሰማበት ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል በመቃወም የሚነገርበት ሆኖ አግኝቼዋለሁ። «ለማስተማር መሻት» «ለመማር መሻት»ን ይጠይቃል። አንተንና ቤተ

ክርስቲያንህን ወደ ጥፋት ሊመራ ከሚችል የሐሰት መንፈስ ተጠበቅ። በመሆኑም የእግዚአብሔርን ቃል በመከተል ሁሉንም ፈትን።

4. ፈሪሃ-እግዚአብሔራዊ አኗኗር (5፡22-24)፡- የአምልኮ ዓላማ በባሕርያችንና በፀባያችን ይበልጥ ክርስቶስን እየመሰልን እንድንሄድ መርዳት ነው። ከሰማኋቸው የአምልኮ ድንጋጌዎች ሁሉ የሚልቀው የቀደሞው የካንተርቤሪ ሊቀ-ጳጳስ ዊልያም ተምፕል የሰጡት ነው፡- «ማምለክ ማለት ሕሊናን በእግዚአብሔር ቅድስና ማነቃቃት፥ አእምሮን በእግዚአብሔር እውነት መመገብ፥ አስተሳሰብን በእግዚአብሔር ውበት ማንጻት፥ ልብን ለእግዚአብሔር ፍቅር መክፈት፥ ፈቃድን ለእግዚአብሔር ዓላማ ማስገዛት ነው» ብለዋል።

ጳውሎስ በክርስትና አኗኗር የሚዛናዊነትን አስፈላጊነት በአጽንኦት ገልጾአል። ይህም፥ በአሉታዊ ጎኑ፡- «ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ» (ቁ. 22) የሚል ሲሆን፥ በአዎንታዊው ጎኑ ደግሞ፡- «የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ» (ቁ. 23) የሚል ነው። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በአሉታዊው ላይ ብቻ ስለሚያተኩሩ፥ ሚዛናዊነቱን ላልጠበቀ ሕይወትና አገልግሎት ይዳረጋሉ። «መቀደስ» ማለት «ለእግዚአብሔር ብቸኛ ዓላማ መለየት» ማለት ነው። የ«አቅጣጫ» ቅድስና አለ (ዕብ. 10፡10)፤ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለእግዚአብሔር ተለይተናል። በየዕለቱ ከኃጢአት እየራቅን፥ በቅድስና የምናድግበት «ተግባራዊ» ቅድስናም አለ (2ኛ ቆሮ. 7፡1)። ይህ ሁሉ ክርስቶስን በምንመለከትበት ጊዜ ለዘላለም እርሱን ስንመስል በ«ፍጹም» ቅድስና ይጠቃለላል (1ኛ ዮሐ. 3፡2)። ኢየሱስ ክርስቶስን ለማየት በተስፋ መጠባበቁ፥ ለተቀደሰ አኗኗር ትልቅ ማነቃቂያ ነው።

5. የክርስቲያን ኅብረት (5፡25-28)፡- የጋራ አምልኮው ካበቃ በኋላ፥ ቅዱሳን አንዱ ለሌላው አገልግሎት ያበረክታሉ። እርስ በርሳቸው ሰላምታ በመለዋወጥ የማበረታቻ ቃላት ይለዋወጣሉ። ልክ በመስመጥ ላይ ከሚገኝ መርከብ አይጦች እየተንጋጉ እንደሚሮጡ ሁሉ ጉባኤው በሸሸት የሚበተንባቸውን አብያተ ክርስቲያናት ሁኔታ ተመልክቻለሁ። ኅብረት የአምልኮ አካል ነው።

«የተቀደሰ አሳሳም» የሚለው የስሜት ጉዳይ አልነበረም። ባመዛኙ ወንዶች ወንዶችን፥ ሴቶች ደግሞ ሴቶችን ይስሙ ነበር (ሮሜ 16፡16፤ 1ኛ ቆሮ. 16፡20፤ 1ኛ ጴጥ. 5፡14 ተመልከት)። በአንዳንድ አገሮች በማገለግልበት ጊዜ፥ ቅዱሳን በዚህ መንገድ ሰላምታ ሲሰጡኝ አይቻለሁ፤

በዚህም አልተቀየምሁም ወይም አልተጠራጠርሁም። ጄ.ቢ. ፊልጽስ ይህን ክፍል፥ «ለወንድሞች ሁሉ የእጅ ሰላምታ ስጡ» በማለት ችግሩን ያቃልላሉ። ጳውሎስ የእግዚአብሔር ቃል በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስፈላጊ መሆኑን በሚገልጽ ሌላ ማስታወሻ መልእክቱን ያጠቃልላል። ቃሉ ባሕርያችንን ሊገራና ሕይወታችንን ሊመራ ይገባል። ቃሉን በግል ማንበብ ቢኖርብንም፥ አንደኛው ልምምድ ለሌላው ሚዛናዊነት ስለሚረዳ፥ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤም ውስጥ ቃሉን መስማት አለብን።

# 2ኛ ተሰሎንቄ 1፡1-12

«ጳውሎስና ስልዋኖስ ጢሞቴዎስም፥ በእግዚአብሔር በአባታችን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም ወደምትሆን ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን፤

«ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስም ጸጋ ሰላምም ለእናንተ ይሁን።

«ወንድሞች ሆይ፥ እምነታችሁ እጅግ ስለሚያድግ የሁላችሁም የእያንዳንዳችሁ ፍቅር እርስ በርሳችሁ ስለሚበዛ፥ ሁልጊዜ ስለእናንተ እግዚአብሔርን እንደሚገባ ልናመሰግን ግድ አለብን፤ ስለዚህ በምትታገሡበት በስደታችሁና በመከራችሁ ሁሉ ከመጽናታችሁና ከእምነታችሁ የተነሣ በእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ስለ እናንተ ራሳችን እንመካለን።

«ስለ እርሱ ደግሞ መከራ ለምትቀበሉለት ለእግዚአብሔር መንግሥት የምትበቁ ሆናችሁ ትቆጠሩ ዘንድ፥ ይህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ ምልክት ነው። ጌታ ኢየሱስ ከሥልጣኑ መላእክት ጋር ከሰማይ በእሳት ነበልባል ሲገለጥ፥ መከራን ለሚያሳዩአችሁ መከራን፥ መከራንም ለምትቀበሉ ከእኛ ጋር ዕረፍትን ብድራት አድርጎ እንዲመልስ በእግዚአብሔር ፊት በእርግጥ ጽድቅ ነውና። እግዚአብሔርን የማያውቁትን፥ ለጌታችንም ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል፤ በዚያም ቀን በቅዱሳኑ ሊከብር፥ ምስክርነታችንንም አምናችኋልና በሚያምኑት ሁሉ ዘንድ ሊገረም ሲመጣ፥ ከጌታ ፊት ከኃይሉም ክብር ርቀው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ። ስለዚህም ደግሞ እንደ አምላካችን እንደ ጌታም እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም በእናንተ ዘንድ ሊከብር እናንተም በእርሱ ዘንድ ልትከብሩ፥ አምላካችን ለመጥራቱ የምትበቁ አድርጎ ይቈጥራችሁ ዘንድ፥ የበጎነትንም ፈቃድ ሁሉ የእምነትንም ሥራ በኃይል ይፈጽም ዘንድ ስለ እናንተ ሁልጊዜ እንጸልያለን።»

# - 10 -

# ክፉዎች ዕረፍት የላቸውም

በተሰሎንቄ የነበሩ ክርስቲያኖች ስለ ጳውሎስ መልእክት እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር፤ ይሁንና መልእክቱ ችግሮቻቸውን ሁሉ ከመቅጽበት አልፈታላቸውም ነበር። እንዲያውም፥ ስደቱ እየከፋ በመሄዱ፥ አንዳንድ አማኞች በታላቁ የመከራ ዘመን ውስጥ የሚኖሩ መሰላቸው። ከዚያም በጳውሎስ ስም የተጻፈ በማስመሰል የተላከው መልእክት የጌታ ቀን በእርግጥ እንደደረሰ የሚገልጽ ይመስል ነበር። ማኅበረ-ምእመኑም በዚህ አመለካከት ግራ በመጋባት ተደናገጠ።

አንዳንድ አማኞች የጌታ ምጽአት እጅግ ስለተቃረበ፥ ሥራቸውን አቁመው እርሱን መጠባበቅ እንዳለባቸው አሰቡ። በመሆኑም ሌሎች ምእመናን ለእነዚህም ወገኖች የሚበቃ ቀለብ ለማዋጣት በመገደዳቸው፥ ተጨማሪ ሸክም ሆነውባቸው ነበር ማለት ነው። ሰይጣን በየዘመናቱ ስልቱን እየቀያየረ ይሠራል፤ እንደ አንበሳ ለመዋጥ (1ኛ ጴጥ. 5፡7-8)፥ እንደ እባብ ለማታለል ይሻል (2ኛ ቆሮ. 11፡3)።

ጳውሎስ ሁለተኛውን መልእክት የጻፈው ለእነዚህ ችግሮች ምላሽ ለመስጠት ነበር። (ለጥቅሶቹ አስተዋጽኦ ምዕራፍ አንድን ተመልከት።) በመሆኑም መልእክቱን እጅግ አሳሳቢ በሆነው ጉዳይ ይጀምራል፡- ይኸውም በእምነታቸው ምክንያት በሚቀበሉት ስደት ነው። በዚህ በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ፥ ጳውሎስ በመከራ ውስጥ ለነበሩ ወዳጆቹ ሦስት ነገሮችን አካፍሎአቸዋል።

## የምስጋና ማበረታቻ (1፡1-4)

ጳውሎስ ለወዳጆቹ ሰላምታ ከሰጠ በኋላ፥ እግዚአብሔርን በሕይወታቸው ውስጥ ሲያደርግ ስለነበረው ነገር ያመሰግናል። ጳውሎስ «በሁሉ አመስግኑ» የሚለውን የራሱን ምክር በሕይወቱ ይጠቀምበት ነበር (1ኛ ተሰ. 5፡18)። ጳውሎስ በእነዚህ ሁለት መልእክቶች ውስጥ የደጋገማቸውን ምስጋናዎች ተመልከት (1ኛ ተሰ. 1፡2፤ 2፡13፤ 3፡9፤ 2ኛ ተሰ. 1፡3፤ 2፡13)። ሰዎችንና ሁኔታዎችን የሚለውጠው ጸሎት ብቻ ሳይሆን፥ ምስጋናም ነው።

በአንድ ወቅት ሰይጣን ክርስቲያኖችን ለመጣል ስለሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተከታታይ ትምህርት አስተምር

ነበር። ከእነዚህም መሣሪያዎች መካከል አንዱ፥ በኢዮብ ሕይወት ላይ የደረሰው መከራ ነው። ሰይጣን በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሊያስቀምጠን ከቻለ፥ እምነታችንን ሊያደክም ይችል ይሆናል።

ታዲያ በጠዋቱ ፈረቃ ሳስተምር፥ «ሰይጣንን ለማሸነፍ እጅግ ከሚመረጡ መሣሪያዎች አንዱ ምስጋና ነው» ብዬ ነበር። «ከሕመሙ ባሻገር፥ ኢዮብ፥ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን!» ለማለት ችሎ ነበር። በመሆኑም፥ «አንተም ወደ ፊት ነገሮች ሲበላሹብህና ለመበሳጨት ስትፈተን፥ ወደ እግዚአብሔር ፊትህን መልስና አምስግነው» ማለቴ ይታወሰኛል።

በዚያን ዕለት የማምሻውን የትምህርት ክፍለ ጊዜ ከመጀመራችን በፊት፥ አንዲት ሴት ወደ እኔ ፈጥና መጣችና፥ «ያስተማርኸን ነገር ይሠራል፥ ይሠራል!» አለችኝ። ቀጥሎም ከሰዓት በኋላ ስላሳለፈችው ገጠመኝና ስለሆነው ሁሉ አጫወተችኝ። የነገረችኝ ታሪክ የማይታመን በመሆኑ፥ ባሕርይዋን ባላውቅ ኖሮ በተጠራጠርኋትም ነበር። እርሷ ግን በማከል፥ «ይሁንና በዚህ ሁሉ ምስጋና በማቅረቤ እግዚአብሔር የሚያስፈልገኝን ጸጋና ብርታት ሰጠኝ። ምስጋና ይሠራል፤ ይሠራል!» አለችኝ።

የተሰሎንቄ አማኞች መከራን ሲቀበሉ ራሳቸውን በጣም መንፈሳውያን አድርገው እንዳልቆጠሩ ጥርጥር የለውም፤ ይሁንና ጳውሎስ እግዚአብሔር በመካከላቸው ምን በመሥራት ላይ እንደነበረ ተረድቶ ነበር። እኔና አንተ ሕይወታችንን ለመገምገም ከሁሉም የዘገየን ነን። ብዙውን ጊዜ እኔና አንተ ሙሉ ለሙሉ ሳናውቀው ሌሎች በእኛ ውስጥ መንፈሳዊ ዕድገት እንዳለ ሊመለከቱ ይችላሉ። ጳውሎስ ምስጋና ያቀረበውና በዚያውም ወዳጆቹን ያበረታታው ምን ምን በረከቶች ስለ ተገኙ ነበር?

1. እምነታቸው እያደገ ነበር (1፡3)፡- ያልተፈተነ እምነት ሊታመን አይችልም። እግዚአብሔር የውሳኔአቸውን ጽናት የሚያረጋግጠው በዚህ መንገድ ስለሆነ፥ አዳዲስ አማኞች የእምነታቸውን መፈተን በተስፋ መጠባበቅ አለባቸው። እምነት እያደገ እንዲሄድ፥ እንደ ጡንቻ ልምምድ ማድረግ አስፈላጊ ነው። መከራና ስደት እግዚአብሔር እምነታችንን ለማጠናከር የሚጠቀምባቸው መንገዶች ናቸው።

ከምወዳቸው መጻሕፍት አንዱ የሃድሰን ቴይለር «መንፈሳዊ ምሥጢር» የሚለው ነው። በዚህ በሆዋርድ ቴይለር በተዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ፥

ቴይለር በእግዚአብሔር በማመን ብቻ ለመኖር ከወሰነበት ከመጀመሪያዋ ዕለት ጀምሮ እንዴት እምነቱ እየተጠናከረ እንደሄደ እንመለከታለን። የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥመውና በተለይም ሥራ የሚበዛበት አሠሪው ደመወዙን ለመክፈል በሚረሳበት ጊዜ ሁሉ፥ በእግዚአብሔር መተማመንን ተማረ። በመሆኑም ለዕለታዊ ነገሮች በእግዚአብሔር መተማመኑ በጨመረ መጠን በእምነት በማደጉ፥ ለጠቅላላው የሚሲዮን ድርጅቱ ስለሚያስፈልገው ነገር በእግዚአብሔር ሊተማመን ቻለ። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር የረሳው ይመስል ነበር፤ ይሁንና ቴይለር መጸለዩንና መተማመኑን ቀጠለ፤ እግዚአብሔርም ምላሽ ሰጠው።

ቀላል ሕይወት ወደ ከንቱ እምነት ሊያመራ ይችላል። በዕብራውያን 11 ውስጥ በምሳሌነት የተጠቀሱት ታላላቅ የእምነት ወንዶችና ሴቶች እምነታቸው ያድግ ዘንድ፥ በአንድ ወይም በሌላ በኩል ሁሉም መከራን የተቀበሉ ወይም በከፍተኛ መሰናከል ውስጥ ያለፉ ናቸው። ጳውሎስ እምነታቸው ፍጹም ይሆን ዘንድ ለተሰሎንቄ አማኞች ጸልዮአል (1ኛ ተሰ. 3፡10)፤ በመሆኑም፥ አሁን ለተመለሰው ጸሎት እግዚአብሔርን ያመሰግናል።

2. ፍቅራቸው የተትረፈረፈ ነበር (1፡3)፡- ይህም ደግሞ ለጳውሎስ የቀድሞ ጸሎት የተሰጠ ምላሽ ነበር (1ኛ ተሰ. 3፡12)። መከራ፥ ራስ-ወዳዶች ሊያደርገን ይችላል። ይሁንና መከራ ከጸጋና እምነት ጋር ከተቀላቀለ፥ ፍቅርን ያፈራል። «በፍቅር የሚሠራ እምነት» ነው (ገላ. 5፡6)። ክርስቲያኖች መከራ በሚቀበሉበት ጊዜ፥ እምነታቸው ወደ ላይ ወደ እግዚአብሔር ቤት ሲደርስ፥ ፍቅራቸው ደግሞ አብረው ወደሚያመልኩ አማኞች ሁሉ ይደርሳል።

ደራሲው ቶሮ በአንድ ወቅት «ከተማ ማለት ብዙ ሰዎች በብቸኝነት አብረው የሚኖሩበት» ስፍራ ነው በማለት ገልጾ ነበር። በአንደኛው አፓርታማ «መኖሪያ ቤት» ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች እጅግ እየተሠቃዩ በቀጣዩ አፓርታማ ውስጥ የሚኖሩት ግን ስለችግራቸው ምንም ላያውቁ ይችላሉ። ዘመናዊው ዓለማችን የሌሎችን ሥቃይ ተመልክተን በግዴለሽነት እስከናልፍ ድረስ፥ መንፈሳዊና ስሜታዊ መገንጠልንና መራራቅን ሊያስፋፉ ይችላል።

ለክርስቲያን ግን መከራ የተትረፈረፈ ፍቅር ለማፍራት ሊረዳ ይችላል። አረማዊው ዓለም የክርስትናን ኅብረት ተአምር ተመልክቶ የሰጠው ምስክርነት፥ «እቤት፥ እንዴት ይዋደዳሉ!» የሚል ነበር። የጥንቱ አማኞች

እርስ በርሳቸው ከመዋደድና ለጌታ ትእዛዝ ከመታዘዝ በቀር የሚያደርጉት አልነበራቸውም። የራሳቸው መከራ የሌሎችን መከራ ከመጋራት አላገዳቸውም ነበር።

3. ትዕግሥታቸው ያድግ ነበር (1፡4)፡- «መከራ ትዕግሥትን ያፈራል» (ሮሜ 5፡3 ቀጥተኛ ትርጉም)። መጽሐፍ በማንበብ (ይኼኛውንም ቢሆን) ወይም ትምህርት በመከታተል ታጋሽ ልትሆን አትችልም። ታጋሽ ለመሆን መከራ መቀበል አለብህ።

እነዚህ አማኞች የታገሡት ምን ነበር? ጳውሎስ ሁኔታቸውን ለመግለጽ በበርካታ ቃላት ተጠቅሞአል፥ «ስደት» ማለትም «ከውጭ የሚሰነዘር ጥቃት»፥ «መከራ» ቀጥተኛ ትርጉሙ «ውጥረት» ሲሆን፥ የተለያዩ ፈተናዎች የሚያስከትሉትን ጉዳቶች ያመለክታል (ቁ. 7)፤ እንዲሁም ደግሞ «ወደ ጠባብ ስፍራ መታጐር» ማለትም ሊሆን ይችላል። በየትኛውም መልኩ ብንመለከተውም፥ የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ቀላል ሕይወት እየገፉ አልነበሩም።

ይሁንና እግዚአብሔር ከቶውንም መከራችንን ለከንቱ አያደርገውም። መከራዎች ይጠቅሙናል እንጂ፥ አይጐዱንም (ያዕ. 1፡1-5፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡15-18)። በእግዚአብሔር ከታመንንና ራሳችንን ለእርሱ አሳልፈን ከሰጠን፥ መከራዎች በሕይወታችን ውስጥ ትዕግሥትና ብስለትን ያፈራሉ። ብናምፅና የደረሱብንን ሁኔታዎች ብንታገል ግን ያልበሰልንና ብስጩዎች ሆነን እንቀራለን። እግዚአብሔር መከራዎችን የሚያመጣው በሕይወታችን ውስጥ መልካሙን ባሕርይ ለማነፅ ነው። ምናልባትም እንጉዳይ በአንድ ሌሊት ሊበቅል ይችላል፤ ዳሩ ግን አንድን ትልቅ የዋርካ ዛፍ ለፍሬ ለማድረስ የበርካታ ዓመታትን ልፋትና የአውሎ ነፋስ ጥቃት ማሳለፍን ይጠይቃል።

4. ምስክርነታቸው ሌሎችን መርዳት ነበር (1፡4)፡- «ከመጽናታችሁና ከእምነታችሁ የተነሣ በእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ስለ እናንተ እራሳችን እንመካለን» (1፡4)። መከራ ለዕድገታችን ከመርዳቱ ባሻገር፥ ከተፈተንን በኋላ ሌሎችም እንዲያድጉ ልንረዳቸው እንችላለን። ሌሎችን እናጽናና ዘንድ እግዚአብሔር እኛን ያጽናናናል (2ኛ ቆሮ. 1፡4-5)። በመሆኑም የተለገሰንን ስጦታ ውጠን ጭጭ የምንል ኩሬዎች ሳንሆን፥ ተቀብለን የምናስተላልፍ አሸንዳዎች ልንሆን ይገባል።

በ1፡3 እና 4 ላይ «እምነት» ተብሎ የተተረጐመው ቃል «ታማኝነት» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። በእርግጥ ሁለቱም ጐን ለጐን የሚሄዱ ናቸው፤ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት በሕይወታችን ታማኝነት ልናሳይ እንችላለን። የተሰሎንቄ አማኞች ከታገሡዋቸው መከራዎች ባሻገር፥ ለጌታና እርስ በርሳቸውም ታማኞች ነበሩ። አንድ ሰው በችግር ውስጥ ሳለ ጌታንና ቤተ ክርስቲያንን በሚተዉበት ጊዜ፥ አንድም ዳግም እንዳልተወለደ ወይም ደግሞ በመንፈሳዊ ሕይወቱ በጣም ደካማ እንደሆነ ያስመሰክራል። እያደገ የሚሄድ እውነተኛ ክርስቲያን ምንም ቢመጣ ታማኝነቱን አያጓድልም።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት፥ የጠላት ሠራዊት ሰሜን አፍሪካን በከበበ ጊዜ፥ ሚሲዮናውያን ስፍራውን ለቀው መውጣት ነበረባቸውና ያለ አገልጋይ ስለሚቀሩት አብያተ ክርስቲያናት ትልቅ ሸክም ሆኖባቸው ነበር። ይሁንና ጦርነቱ አብቅቶ ሚሲዮናውያኑ በተመለሱ ጊዜ፥ ጠንካራና ንቁ አብያተ ክርስቲያናትን አገኙ። የጦርነቱ መከራዎች ቤተ ክርስቲያንን በማጽዳት፥ የእውነተኛ አማኞችን እምነት ለማጠናከር ረድቶአል። ይህ ነፃ በነበሩት አገሮች ውስጥ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ምንኛ ማበረታቻ ይሆን!

ጳውሎስ እግዚአብሔር በእነዚህ አዳዲስ ክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ይፈጽም ለነበረው ነገር ምስጋና የሚያቀርብበት በቂ ምክንያት ነበረው። ይሁንና «ተስፋ» እንደጐደላቸው አስተውለሃልን? «እምነት፥ ተስፋና ፍቅር» ከመጀመሪያው የእነዚህ አማኞች ባሕርያት ቢሆኑም (1ኛ ተሰ. 1፡3)፥ አሁን ጳውሎስ ምስጋናውን ያቀረበው ለእምነታቸውና ለፍቅራቸው ብቻ ነው። ምክንያቱ ምን ይሆን? ምናልባትም ስለተስፋቸው ግራ ተጋብተው ይሆናል። ይህም ወደ ሁለተኛው ማበረታቻ ይመራናል።

## የተስፋ ቃሉ ማበረታቻ (1፡5-10)

የጊዜው ሁኔታ የቱንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆንም፥ የተሰሎንቄ አማኞች አስተማማኝና የከበረ የወደፊት ተስፋ ነበራቸው። እንዲያውም፥ መከራዎቻቸው እግዚአብሔር ጻድቅ እንደሆነና ለእነርሱ ያለውን ታላቅ ዕቅድ ለመፈጸም እየሠራ እንዳለ የሚያረጋግጡ፥ «የቅን ፍርዱ መገለጥ ምልክቶች» ነበሩ። ምናልባትም መከራ የእግዚአብሔርን አለመሥራት (ዝምታ) ያመለክታል ወደ ማለቱ እናዘነብል ይሆናል፤ እውነቱ ግን የዚህ ተገላቢጦሽ ነው። በተጨማሪም፥ በመከራ ጊዜ የምናደርገው ተግባራዊ እንቅስቃሴ የእግዚአብሔርን በሥራ ላይ መሆን ለሌሎች ሰዎች ያረጋግጣል።

(ለዚህ መመሪያ ተጨማሪ ማረጋገጫ እንዲሆንህ ፊልጵስዩስ 1፡28-30 አንብብ)።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ በገባቸው የተስፋ ቃሎች ውስጥ ሦስት ልምምዶች ተካተዋል፡-

1. ሽልማት (1፡5)፡- «ስለ እርሱ ደግሞ መከራ ለምትቀበሉለት ለእግዚአብሔር መንግሥት የምትበቁ ሆናችሁ ትቆጠሩ ዘንድ ...» (1፡5)። እግዚአብሔር በሕይወታቸው ውስጥ መከራ እንዲያልፍ ካደረገባቸው ዓላማዎች አንዱ ሽልማት ነበር። ይሁንና መከራቸው ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገቡ ዘንድ እንዳስቻላቸው የሚጠቁም አሳብ አናገኝም። ስለ ምን ቢባል በክርስቶስ በማመን እንደዳኑ እናውቃለንና ነው (1ኛ ተሰ. 1)። «ደግሞ» የምትለዋ አናሳ ቃል ይህ ብቃት በጊዜው ከነበሩበት ሁኔታና ወደ ፊትም ከሚጠብቃቸው የእግዚአብሔር ክቡር መንግሥት ጋር የተያያዘ መሆኑን ታመለክታለች። በ1ኛ ጴጥሮስ 1፡3-9ም ተመሳሳይ አሳብ እናገኛለን።

አንድ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁኔታዎችን ይገለባብጥና አማኞች ሲሸለሙ ክፉዎችና ኃጢአተኞች መከራን ይቀበላሉ። ጌታችን በምድር ላይ የምቾት ሕይወት እንደምናሳልፍ የተስፋ ቃል አልገባልንም፤እንዲያውም ችግሮች እንደሚጋረጡብንና ጦርነትም እንደሚገጥመን አስተምሮናል። ይህም ሆኖ ለእርሱ ታማኞች ለነበሩት ሁሉ ወደ ፊት ሽልማት እንደሚሰጣቸው የተስፋ ቃል ገብቶአል (ማቴ. 5፡10-12)።

2. ካሳ (1፡6-10)፡- እግዚአብሔር ከደኅንነት ርቆ ለጠፋው ሕዝብ መከራን፥ ለዳኑት ደግሞ ዕረፍትን ካሳ አድርጎ ይሰጣል። «መካስ» ማለት «ብድራት መክፈል» ማለት ነው። በመሠረቱ፥ መንፈሳዊ ሰዎችን የሚያሳድዱ ኃጥአን ሁልጊዜም በዚህ ሕይወት ትክክለኛውን ክፍያ አይቀበሉም። እንዲያውም፥ የኃጥአን ወቅታዊ ብልጽግናና የመንፈሳውያን ችግር ምክንያት ለብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች ጥያቄ ሆኖባቸው ነበር [መዝ. (73)፤ ዕንባቆም 1፤ ኤር. 12፡1]። ብቸኛው ልምምዳችን መከራ ብቻ ከሆነ፥ ለምን ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያለበትን ሕይወት እንኖራለን? በማለት ራሳቸውን ይጠይቃሉ።

ክርስቲያኖች እንደመሆናችን፥ ለዘላለም እንጂ ለጊዜው ብቻ መኖር የለብንም። የክርስትና ሕይወታችንንም ዛሬ ትርጉም ያለው የሚያደርገው

«የዘላለም እሴቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት መኖራችን» ነው። በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስም።

ይህም የሁለት ገበሬዎችን ታሪክ ያስታውሰኛል፤ አንደኛው አማኝ፥ሌላኛው ደግሞ ከሃዲ ነበር። የመከር ጊዜ ሲደርስ፥ እግዚአብሔር የአማኙን የምርት ውጤት ያልባረከው ይመስል ነበርና ከሃዲው በአማኙ ጐረቤቱ ላይ ያፌዝ ጀመር። የከሃዲው ቤተሰብ አልታመም ነበር፤ እርሻው ብዙ አፍርቶለት ነበር፤ በመሆኑም፥ ብዙ ገንዘብ እንደሚያገኝ እርግጠኛ ነበር።

ከሃዲው «በእግዚአብሔር ማመንና ክርስቲያን መሆን ዋጋ አለው ያልኸኝ መስሎኝ ነበር!» አለ።

ክርስቲያኑም፥ «በእርግጥም ዋጋ አለው፤ ይሁንና እግዚአብሔር ሁልጊዜም የሚከፍለው በመከር ጊዜ ብቻ አይደለም» ሲል መለሰለት።

ያላመነ ሰው የሚጋፈጠው የወደፊት ሕይወት ምን ዓይነት ነው? ጳውሎስ ይህንኑ ለመግለጽ የተጠቀመባቸውን ሥዕላዊ ቃላት ተመልከት፡- መከራ፥ በቀል፥ የእሳት ነበልባል፥ ቅጣት፥ የዘላለም ጥፋት ነው። ክርስቶስን የማይቀበለው ዓለም በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ በዋለው ግፍ መጠን ፍዳውን ከእግዚአብሔር እጅ ይቀበላል! በሰብአዊ ታሪክ ውስጥ እንኳን የሚሠራ የካሳ ሕግ አለና፤ እንደዚያው ሁሉ፥ እግዚአብሔር ካሳ በሚከፍልበት ጊዜ፥ በዚሁ ዓይነት ይፈጽማል።

ፈረዖን ለአይሁድ ቤተሰብ የሚወለዱትን ወንዶች ልጆች ሁሉ በውኃ ውስጥ አስጥሞ ለማጥፋት ሞክሮ ነበርና የራሱም የጦር ሠራዊት በቀይ ባሕር ውስጥ ሰጠመ። ሐማን አይሁዶችን ከምድሪቱ ለማስወገድ ሤራ ቢወጥንም፥ ዳሩ ግን እርሱና የገዛ ልጆቹ ከምድሪቱ ተወገዱ። የንጉሥ ዳርዮስ አማካሪዎች ዳንኤልን አስሮ ወደ አንበሶች ጉድጓድ ውስጥ እንዲጥለው አስገደዱት፤ ይሁንና ብዙም ሳይቆይ እነርሱ ራሳቸው በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ ተጣሉ። ሕዝቡን ለማዳን ክርስቶስን የሠዉት የማያምኑ የአይሁድ መሪዎች (ዮሐ. 11፡49-53)፥ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ከተማቸው ስትደመሰስና ሕዝቡም ሲበታተን ተመልክተዋል።

ለእግዚአብሔር በኃጢአት ላይ መፍረድና ኃጢአተኞችን መኰነን ተገቢ ነው። ቅዱሱ እግዚአብሔር ኃጢአትን ሳይቀጣ ለመተው አይችልም። «አፍቃሪው አምላካችን እግዚአብሔር፥ በኃጢአተኞች ላይ እንደሚፈርድና ሰዎችን ወደ ሲኦል እንደሚያወርድ ለማመን አልችልም» የሚሉ ሰዎች፥

የእግዚአብሔርን ቅድስናም ሆነ የኃጢአትን አስከፊነት አልተረዱም ማለት ነው። «እግዚአብሔር ፍቅር» የመሆኑ እውነትነት አጠራጣሪ ባይሆንም (1ኛ ዮሐ. 4፡8)፥ «እግዚአብሔር ብርሃን» እንደሆነም ሊታወቅ ይገባል (1ኛ ዮሐ. 1፡5)፤ በቅድስናውም በኃጢአት ላይ መፍረድ አለበት።

አንድ ክርስቲያን ሐኪም የደኅንነትን አስፈላጊነትና የወደፊቱን የፍርድ እውነታ በሚከድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አባል ለሆነችና ሰናይ ምግባር ላላት አንዲት ሴት ለመመስከር ሞክሮ ነበር። በሽተኛዪቱ ሴት ግን፥ «እግዚአብሔር ከመጠን በላይ ስለሚወደኝ ሊኮንነኝ አይችልም። እግዚአብሔር የእሳት ባሕርን ዓይነት ስፍራ ያዘጋጃል ብዬ አላምንም» በማለት መለሰችለት።

የሴቲቱም በሽታ ሲመረመር ካንሰር ሆኖ ተገኘ። ቀዶ-ጥገና ማካሄድ የግድ አስፈላጊ ነበር። ሐኪሙም በሆስፒታል አልጋ ላይ ለተኛችው ሴት፥ «እጅግ በጣም ስለምወድሽ ሰውነትሽን በመቁረጥ የሕመም ስሜት ላሳድርብሽ አልሻም፤ እናም ቀዶ-ጥገናውን የማድረጉ ጉዳይ በጣም አሳስቦኛል» አላት።

በሽተኛዋም፥ «ዶክተር፥ በእርግጥ ብተወደኝ ኖሮ፥ እኔን ለማዳን የምትችለውን ጥረት ሁሉ ታደርግ ነበር። እንዴት ይህ አስቃቂ ነገር በሰውነቴ ውስጥ እንዲኖር ትፈልጋለህ?» በማለት መለሰችለት።

ካንሰር ለሰውነት ፀር እንደሆነ ሁሉ፥ ኃጢአትም ለዓለም አደገኛ ስለመሆኑና ሁለቱንም ሙሉ በሙሉ እስከናካቴው ማስወገድ እንደሚያስፈልግ ለዶክተር ለማብራራት የቀለለው ከዚያን በኋላ ነበር። አንድ የሕክምና ዶክተር በሽታን ሳይጠላና ሳያስወግደው ጤንነትን ሊወድ እንደማይችል ሁሉ፥ እግዚአብሔርም ኃጢአትን ሳይጠላና ሳይፈርድበት ጽድቅን ሊወድ አይችልም።

«ብቀላ» የሚለው ቃል፥ የእግዚአብሔርን ቅዱስ ሕግ ለማርካት የተጠቀሰ እንጂ፥ የግል ቂም መወጣትን ዓላማው ያደረገ አይደለም። እግዚአብሔር ከደኅንነት ርቀው በጠፉ ኃጢአተኞች ላይ ቂም አይይዝም። በአንጻሩ ግን፥ ልጁን ለእነርሱ እንዲሞት ከመላኩም በላይ፥ ወደ እርሱ ይመለሱ ዘንድ ይለምናቸዋል። ይሁንና ኃጢአተኞቹ «እግዚአብሔርን ላለማወቅና ወንጌሉን ላለመታዘዝ» (ቁ. 8) ከመረጡ፥ እግዚአብሔር ከመፍረድ በስተቀር ሌላ አማራጭ አይኖረውም።

ይህም ፍርድ የሚከናወነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያኑና ከመላእክቱ ጋር በሚመለስበት ጊዜ ነው (1:7)። ይህ ጳውሎስ በ1ኛ ተሰሎንቄ 4:13-18 ውስጥ ከገለጸው ክስተት ጋር አንድ ዓይነት አይደለም። እስኪ እነዚህን ሁለት ክስተቶች እነጻጽራቸው:-

| 1ኛ ተሰሎንቄ 4:13-18 | 2ኛ ተሰሎንቄ 1 |
| --- | --- |
| - ክርስቶስ በአየር ላይ ይገለጻል። | - ክርስቶስ ወደ ምድር ይመለሳል። |
| - በምሥጢር ለቤተ ክርስቲያኑ ይገለጻል። | - ከቤተ ክርስቲያን ጋር በግልጽ ይመጣል። |
| - አማኞች ከታላቁ መከራ ያመልጣሉ። | - የማያምኑ ሰዎች በታላቁ መከራ ይሠቃያሉ፤ ፍርድ ይወሰንባቸዋል። |
| - ባልታወቀ ጊዜ ይፈጸማል። | - በታላቁ መከራ ፍጻሜ ላይ፥ በጌታ ቀን ይፈጸማል። |

3. *ዕረፍት* (1:7 እና 10):- እግዚአብሔር ከደኅንነት ርቀው ለጠፉት መከራን፥ ለዳኑት ደግሞ ዕረፍትን ካሳ አድርጎ ይሰጣል። በቁጥር 7 ላይ የሚገኘው ሐረግ ተጨማሪ አስተያየት እንደሆነ አምናለሁ። ይኸውም «ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ፥ መከራን ለሚያሳዩአችሁ መከራን፥ (መከራን ለተቀበላችሁት ለናንተ ከእኛ ጋር ዕረፍትን) ብድራት አድርጎ እንዲመልስ» የሚለው ነው። ጌታ በአየር ላይ በሚገለጽበትና ከእርሱ ጋር እንድንሆን ወደ ላይ በምንነጠቅበት ጊዜ፥ ቅዱሳን ዕረፍታቸውን ይቀበላሉ።

«ዕረፍት» ማለት «እፎይታ፥ ከውጥረት ነፃ መሆን» ማለት ሲሆን፥ የ«መከራ» ተቃራኒ ነው። በምድራዊው ሕይወት፥ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በውጥረት ይመላለሳሉ:- «ያለ ልክ ከብዶብን ነበር» (2ኛ ቆሮ. 1:8)፤ በመከራና በስደት ሸክም ሥር ይኖራሉ። ይሁንና ክርስቶስን ስንመለከት፥ ያን ጊዜ እፎይታን እናገኛለን። እግዚአብሔር አስቀድሞ በኀልጎታ በኃጢአታችን ላይ ስለፈረደ፥ሌላ ኃይለኛ ቁጣም ሆነ ፍርድ ልንፈራ አይገባም (1ኛ ተሰ. 1:10 እና 5:9)።

ከደኅንነት ርቀው ለጠፉት ሰዎች ወደ ፊት ምን ዓይነት ሁኔታ ያጋጥማቸው ይሆን? የዳኑት በዕረፍትና በሰማይ ክብሮች ሲደሰቱ፥ የጠፉቱ ግን ቅጣትንና የዘላለምን ፍርድ ይጋፈጣሉ (1:9)። የዳኑት «ፊቱን ሲያዩ» (ራእይ 22:4)፥ የጠፉት ግን ከእግዚአብሔር ይለያሉ። አንዳንድ የኑፋቄ

እምነት አራማጆች አንድም ጊዜያዊ መከራ፥ አለበለዚያም ጠቅላላ ውድመት ነው በማለት «የዘላለምን ጥፋት» ትርጉም ለማላላት ሞክረዋል፤ ይሁንና ሁለቱም አሳቦች ትክክል አይደሉም። ሰዎች አሳቡን ለማጣመም ወይም ለማስወገድ ከሚያደርጉት ጥረት ባሻገር፥ የሐረጉ ትርጉም «የዘላለም ፍርድ» የሚለው ነው (ማቴ. 25፡41 ተመልከት)።

ጳውሎስ ወዳጆቹን በምስጋናና በተስፋ ቃል አበረታቷል፤ እንዲሁም ሦስተኛም የማበረታቻ ቃል ነበረው።

## የጸሎት ማበረታቻ (1፡11-12)

ጳውሎስ ለአዳዲስ አማኞች ሲጸልይ ነበር (1ኛ ተሰ. 1፡2፤ 3፡10)። በቁጥር 11 ላይ «ስለዚህ» የሚለው ቃል፥ «ከዚህ በላይ ካልኳቸው ነገሮች የተነሣ» የሚል ትርጉም አለው፤ ይኼም ክርስቶስ በቅዱሳኑ ሊከብርና በጠፉት ላይ ሊፈርድ ሲመለስ ነው። የወደፊቱ የክብር መገለጥ ሐዋርያው ለቅዱሳን እንዲጸልይ አነቃቃው። ከወደፊት ተስፋ የተነሣ ከቶውንም የአሁኑን ኃላፊነት ከመወጣት ልንሰንፍ አይገባም። በአንጻሩ፥ የወደፊቱ ተስፋ ዛሬ ታማኞች እንድንሆን ሊያበረታታን ይገባል።

በጳውሎስ ጸሎት ውስጥ ሦስት አሳሳቢ ሸክሞች ነበሩ።

1. ብቃታቸው (1፡11)፡- በቁጥር 5፥ ጳውሎስ ወደ ፊት ወደ ክብር ሲገቡ ለመንግሥቱ ብቁዎች እንዲሆኑ እንደሚፈልግ ገልጾ ነበር። በዚህ ስፍራ ላይ ግን በጊዜው ሁኔታቸው ላይ ያተኩራል። እግዚአብሔር የጠራቸው በጸጋውና በፍቅሩ ነበር፤ በመሆኑም፥ ጳውሎስ ለዚያ ጥሪ በተገቢው ሁኔታ ይመላለሱ ዘንድ ይሻል (2ኛ ተሰ. 2፡13-14)።

መከራ ብቻ በመቀበል መንፈሳዊ ብስለት አይመጣም፤ ነገር ግን የሰውዬውን ባሕርይ የጥንካሬ ደረጃ ያመጣል። እምነታችን በሚፈተንበት ጊዜ፥ ብቃታችንን እናሳያለን (1ኛ ጴጥ. 1፡6-9)። ከመፈተናችን በፊት እንኳ እግዚአብሔር ልባችንን ያውቃል፡- እኛ ግን የራሳችንን ልብ አናውቀውም። እንዲሁም ሌሎችም ቢሆኑ ብቃታችንን አያውቁም። ከታገሥናቸው መከራዎች የተነሣ እግዚአብሔር ብቃታችንን እንዲያንፅና የበለጠ ጠቃሚ ክርስቲያኖች እንዲያደርገን ልንጸልይ ይገባል።

2. እርምጃቸው (1፡11)፡- «የበጎነትንም ፈቃድ ሁሉ የእምነትንም ሥራ በኃይል ይፈጽም ዘንድ» ይላል። ባሕርይ ወደ ፀባይ ማምራቱ የግድ ነው። ጳውሎስ እግዚአብሔር እንዲያደርጉት የሚፈልገውን ነገር

ለማድረግ የሚያስችላቸው በእርሱ ኃይል የተሞላ፥ ጽኑ ፈቃድ እንዲኖራቸው ጸልዮአል። መታዘዝና አገልግሎት እርሱን በምንታመንበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ኃይል እንጂ፥ ከሰብአዊ ብቃቶችና ጥረቶች አይፈልቁም።

ጳውሎስ ቀደም ብሎ እምነትን ከፍቅር (1፡3) እና ከትዕግሥት ጋር አዛምዶ ነበር፤በዚህ ስፍራ ደግሞ ከኃይል ጋር ያዛምደዋል። በራሳችን ላይ ብቻ የምንታመን ከሆነ፥ በመከራ ድል ልንነሣ አንችልም፤ ዳሩ ግን እርሱን በመታመን ድል አድራጊዎች ልንሆን እንችላለን።

መንገድ በምሄድበት ጊዜ፥ ኃይልን አጠራቅሞ ቢበዛ ለሁለት ሰዓታት ያህል ያለውጫዊ የኃይል ምንጭ ሊሠራ የሚችል የኤሌክትሪክ ፂም መላጫ እይዛለሁ። ይህም በተለይ አንዳንድ አገሮችን በምጐበኝበት ጊዜ ይጠቅመኛል።

ለአንድ ሳምንት ያህል በክረምት ኮንፍራንስ ላይ እያስተማርሁ ሳለሁ፥ ምላጩ ኃይል እያጣ ሲሄድ አየሁ። እንዲያውም፥ በአንደኛው ጠዋት ፍጥነቱ በጣም በመቀነሱ፥ የተሰበረ መስሎኝ ነበር። ከዚያም ወደ ማታ ፍጥነቱን ጨምሮ ይሠራ ጀመር። የጥቂት ደቂቃዎች ምርመራ ሳደርግ ችግሩ ምን እንደሆነ ተረዳሁ፤ ለካስ ምላጬን ከግድግዳ ላይ በተሰካ ማብርያና ማጥፍያ ቁጥጥር ከሚሠራ «ሶኬት» ጋር አገናኝቼው ኖራል!በመሆኑም ባለቤቱ መብራቱን ክፍት ባደረገች ጊዜ ምላጩ ኃይል ሲያጠራቅም መብራቱን ስታጠፋው ደግሞ ምንም ኃይል አያገኝም ነበር።

ያም አጋጣሚ መንፈሳዊ ትምህርት አስተማረኝ። የማብርያና የማጥፍያውን ሁኔታ ሳይመለከቱ (በልማድ ጉልበት) የኃይሉን ምንጭ መተማመኑ ቀላል ነው። ጳውሎስ የወዳጆቹ «ማብርያ-ማጥፍያ ክፍቱን እንዲሆንና» መከራውን ታግሠው እግዚአብሔርን ለማስከበር የሚችሉበትን ኃይል በእምነታቸው እንዲቀበሉ ይጸልይ ነበር።

3. ምስክርነት (1፡12)፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱሳኑ ከእርሱ ጋር በሚመለሱበት ጊዜ በእነርሱ ይከበራል (1፡10)፤ ይሁንና ዛሬም በሕይወታችን ሊከብር ይገባዋል። የማያምኑ ሰዎች ስሙን ሲሳደቡ (1ኛ ጴጥ. 4 ከቁጥር 12 ጀምሮ)፥ አማኞች ግን ስሙን በመባረክ ሊያስከብሩት ይሻሉ። የሚያስደንቀው ታዲያ ክርስቶስን የሚያስከብረው አማኝ፥ በክርስቶስ መክበሩ ነው፡- «በእናንተ ዘንድ ሊከብር፥ እናንተም በእርሱ ዘንድ ልትከብሩ።»

ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? «እንደ ጌታም እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ» (1፡12)። ጸጋና ክብር አብረው ይሄዳሉ፤ መከራና ክብርም እንዲሁ [መዝ. (84)፡11፤ 1ኛ ጴጥ. 5፡10፤ መዝ. (45)፡2-3፤ ሮሜ. 5፡2፤ 2ኛ ቆሮ. 8፡19)። ጸጋውን ስንቀበል፥ ክብሩን እንገልጻለን።

«ለክፉዎች ሰላም የላቸውም ይላል እግዚአብሔር» (ኢሳ. 48፡22)። ለክፉዎች ዕረፍት የላቸውም! ይሁንና በክርስቶስ ለሚታመኑና ለክብሩ ለመኖር ለሚሹ ሰዎች ዕረፍት አላቸው። ለክርስቲያን ከሁሉም የሚልቀው ገና የሚመጣው ነው። «ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ» እናውቃለን (ሮሜ 8፡18)።

# 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 1-12

«ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለ መሰብሰባችን፥ በመንፈስ ወይም በቃል ከእኛ እንደሚመጣ በመልእክት፡- የጌታ ቀን ደርሶአል ብላችሁ፥ በአእምሮአችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡም እንለምናችኋለን። ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ፤ ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ፥ አይደርስምና። እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ፥ አምላክ ከተባለው ሁሉ፥ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው። ገና ከእናንተ ጋር ሳለሁ፥ ይህን እንዳልኋችሁ ትዝ አይላችሁምን? በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ፥ የሚከለክለውን አሁን ታውቃላችሁ። የዓመፅ ምሥጢር አሁን ይሠራልና፤ ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ። በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው፥ ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመፀኛ ይገለጣል፤ ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል።»

# - 11 -

# የእግዚአብሔር የጊዜ ሰሌዳ

የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ዓላማ ለእኛ የጊዜ ሰሌዳ እንድናዘጋጅ ለመርዳት ሳይሆን፥ ባሕርያችንን እንድንቀርጽ ለማድረግ ነው። ጳውሎስ ይህንን ሐቅ በሁለቱም የተሰሎንቄ መልእክቶቹ ውስጥ በአጽንኦት የጠቀሰ ሲሆን፥ ጌታችንም የመምጫውን ዕለት እንዳንቀርጥ አስጠንቅቆናል (ማቴ. 24:36፥ 42)። የጌታን መምጫ በሒሳብ ስሌት የሚወስኑ ሰዎች በአማኞች መካከል ጥርጣሬና ሁከትን ይፈጥራሉ፤ በተሰሎንቄ ላይ የደረሰው ይኸው ተመሳሳይ ነገር ነበር።

የሆነ ሰው አማኞቹ በጌታ ቀን ውስጥ እንደሚኖሩ በመናገር አታሎአቸው ነበር። ምናልባት ትምህርቱ በመጀመሪያ የመጣው ከስብሰባዎቻቸው በአንደኛው ላይ «በትንቢት ገለጻ» መልክ ሲሆን፥ ከዚያ በኋላ ከጳውሎስ መጣ በተባለው መልእክት አማካኝነት ይበልጥ እየተስፋፋ ሄደ። አማኞቹ በዚህ ትምህርት ፈጥነው በመደናገጣቸው፥ ከከባድ ሥጋት ላይ ወደቁ። እግዚአብሔር መርሐ-ግብሩን ቀይሮ ይሆን? ጳውሎስ ከመከራ እንደሚድኑ የሚያመለክት የተስፋ ቃል አልነገራቸውም ነበርን? (1ኛ ተሰ. 1:10 እና 5:9 ተመልከት)።

ልባቸውን ለማረጋጋትና እምነታቸውን ለማጽናት፥ ጳውሎስ በጌታ ቀን ውስጥ እንደማይኖሩ ገለጸላቸው። ለዚህም ምክንያቱ ቀላል ነበር። ይኸውም የተወሰኑ ሌሎች ክስተቶች እስኪፈጸሙ ድረስ የጌታ ቀን ሊመጣ አይችልም ነበር። ከዚያም በኋላ፥ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን የጊዜ ሰሌዳ የሚያመላክቱትን ትንቢታዊ ክስተቶች ይጠቅሳል።

## የቤተ ክርስቲያን ንጥቀት (2:1፥ 6-7)

ጳውሎስ በመጀመሪያው መልእክቱ ባስተማራቸው እውነት ላይ በመመሥረት ተረጋግተው እንዲኖሩ ይለምናቸዋል፤ ጌታ ተመልሶ ይመጣና የእርሱ የሆኑትን በአየር ላይ እንዲገናኙት ይነጥቃቸዋል (1ኛ ተሰ. 4:13-18)። ይህም የ«ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ መሰብሰባችን ...» ነው (ቁ. 1)። የሚኖሩት ሁለት የተለያዩ ክስተቶች ሳይሆኑ፥ በቅጽበትና ያለምንም ማስጠንቀቂያ የሚፈጸም አንድ ታላቅ ክስተት ነው።

ቤተ ክርስቲያን ከዓለም እንደተወሰደች፥ ሰይጣንና ኃይላቱ መርሐ-ግብራቸውን ይዘረጋሉ። የጌታ ቀን የቤተ ክርስቲያንን ንጥቀት ተከትሎ የሚመጣው ክፍለ-ጊዜ ነው። ይህም በምድር ላይ ለሚኖሩ ሰዎች ታላቅ የመከራ ጊዜ ይሆናል። ሰይጣንና ሠራዊቱ በምድር ላይ እየሠሩ ሳለ፥ እግዚአብሔር ከሰማይ የጽድቅ ፍርዱን ያወርዳል። ራእይ 6-19 ይህንኑ ክስተት ይገልጽልናል።

ሰይጣን አሁኑኑ «የዓመፁን ሰው» የማይገልጠው ለምንድን ነው? ምክንያቱም ዛሬ እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ የክፉውን ኃይላት እየተቋቋመ ስለሆነ ነው። በመሆኑም፥ ሰይጣን ደስ ባለው ጊዜ፥ ደስ ያሰኘውን ነገር ሊፈጽም አይችልም። ልዑሉ አምላካችን የሰውን ቁጣ እንኳ ወደ ምስጋናው ሊለውጥ ይችላል፤ «የሰዎች ቁጣ በበዛ መጠን ለአንተ ምስጋና ይበዛልሃል» (መዝ. [76]፡ 11 - አዲሱ ትርጉም)። በቁጥር 6 እና 7 ላይ፥ ጳውሎስ ዛሬም እንኳ የነገሮችን መርሐ-ግብር ለመጠበቅ የሚረዳውንና የሚከላከለውን ኃይል ማንነት ጠቅሶታል።

ይህ ከልካይ ማነው? ወይስ ምንድን ነው? ጳውሎስ ይህንን ለተሰሎንቄ ሰዎች በአካል ተገኝቶ ባስተማረበት ወቅት የገለጸላቸው ቢሆንም፥ በሁለቱም መልእክቶቹ ውስጥ አልጠቀሰውም። ይህ ከልካይ ዛሬ በዓለም ውስጥ እየሠራ ሲሆን፥ «ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ» (ቁ. 7) መሥራቱን ይቀጥላል።

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በግልጽ ባይታይም፥ ጳውሎስ በቁጥር 6 ላይ «የሚከለክለውን» ሲል የጾታ ልዩነት አያሳይም፤ በቁጥር 7 ላይ ግን፥ «የሚከለክል» የሚለው ተባዕታይ ጾታን የሚያንጸባርቅ ነው። በመሆኑም ከልካዩ፥ ዛሬ «[በዓለም] ውስጥ የሚኖር» እና አንድ ቀን ግን «[ከዓለም] ውስጥ የሚወሰድ» አካል ነው ማለት ነው።

በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ይህ ከልካይ መንፈስ ቅዱስ ነው ይላሉ። በእርግጥ፥ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ዓላማዎች ለመፈጸም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየሠራና የእግዚአብሔርን መርሐ-ግብር እያራመደ ይገኛል። ቤተ ክርስቲያን በምትነጠቅበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ከዓለም ሙሉ በሙሉ አይወሰድም (አሊያማ በታላቁ መከራ ወቅት ማንም ሊድን ባልቻለም ነበር)፤ ይሁንና ሰይጣንና ኃይላቱ ለሥራ ይሰማሩ ዘንድ ከመካከል ይወሰዳል። መንፈስ ቅዱስ በጌታ ቀን ያለጥርጥር በምድር ላይ ይኖራል፤ ይሁንና እንደዛሬው የክፋት ኃይሎችን አሠራር አይከለክልም።

ምንም እንኳን ቤተ ክርስቲያን መዳከሟና ወደ ውድቀት ማምራቷ የማያጠራጥር ቢሆንም፥ ከዚህ ሁሉ ባሻግር፥ በዓለም ውስጥ የሚኖሩትን ሚና ከቶውንም ልናሳንሰው አይገባም። በቤተ ክርስቲያን ላይ ትችት የሚሰነዝሩ ሰዎች፥ በዚህ ዓለም ውስጥ የእግዚአብሔር ሰዎች መኖር ላልዳኑ ሰዎች የመዳን በር እንደሚከፍት አያስተውሉም። የቤተ ክርስቲያን መኖር የፍርድን መምጣት እያዘገየው ነው። ሎጥ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሰው ባይሆንም፥ የእርሱ በሰዶም ከተማ ውስጥ መኖር የእግዚአብሔርን ቁጣ ወደ ኋላ ጐትቶአል (ዘፍ. 19፡12-29)።

ዛሬ በዓለም ውስጥ ሁለት መርሐ-ግብሮች አሉ፡- የእግዚአብሔር የማዳን መርሐ-ግብርና «የዓመፅ ማኅደር» የሆነው የሰይጣን የኃጢአት መርሐ-ግብር ነው። እግዚአብሔር ለመርሐ-ግብሩ የጊዜ ሰሌዳ የወሰነ ሲሆን፥ ሰይጣን የሚያደርገው ማንኛውም ነገር ይህንኑ ሰሌዳ ሊለውጠው አይችልም። ለክርስቶስ መምጣት «የዘመን ፍጻሜ» እንደነበረ ሁሉ (ገላ. 4፡4)፥ ለሐሳዊ-መሢሑም መገለጥ «የዘመን ፍጻሜ» አለው፤ ከዚህም መርሐ-ግብር ውጭ የሚሆን ምንም ነገር የለም። የእግዚአብሔር መንፈስ የመከልከል አገልግሎቱን እንዳበቃ፥ ቀጣዩ ክስተት ሊጀመር ይችላል።

## የሐሳዊ-መሢሕ መገለጥ (2፡3-5፥ 8)

ጳውሎስ ይህን ሐሳዊ-መሢሕ የሚለውን ቃል በመልእክቱ ውስጥ አልጠቀሰም። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህን ቃል የተጠቀመው ዮሐንስ ብቻ ነው (1ኛ ዮሐ. 2፡18፤ 22፤ 4፡3፤ 2ኛ ዮሐ. 7)። ይሁንና የመጨረሻውን ዘመን አምባገነን መሪ ለመግለጽ የምንጠቀምበት ቃል ጳውሎስ «የዓመፅ ሰው፥» «የጥፋት ልጅ» (ቁ. 3)፥ «ሥርዓት-አልባ» (ቁ. 8 - በቀጥታ ሲተረጐም) በማለት የተጠቀመበትን ስያሜ ነው።

ሰይጣን በሉሲፈርነቱ በእግዚአብሔር ላይ ካመፀበትና የእግዚአብሔርን ዙፋን ለመቆጣጠር ከሞከረበት ጊዜ አንሥቶ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ጦርነት በማድረግ ላይ ይገኛል (ኢሳ. 14፡12-5)። ሔዋንን በዔደን ገነት ውስጥ በመፈተን፥ በእርሷ አማካኝነት አዳምን ለውድቀት ዳርጓል (ዘፍ. 3)። በዘፍጥረት 3፡15 ላይ እግዚአብሔር በሰይጣንና በቤተሰቡ («ዘር») መካከል ጦርነት በማወጅ፥ ሰይጣንን በመጨረሻ ሙሉ ለሙሉ የሚያሸንፍ አዳኝ እንደሚመጣ የተስፋ ቃል ገብቶአል።

ሐሳዊ-መሢሕ የሚለው ፀረ-ክርስቶስ ማለት ሲሆን፥ በግሪክ ቋንቋ «ፀረ»ን የሚወክለው «አንታይ» የሚለው ቃል፥ ሁለት ትርጉሞች አሉት።

እነርሱም፥ ተቃዋሚ እና በእርሱ ምትክ የሚሉ ናቸው። በመሆኑም፥ ሰይጣን ክርስቶስን መቃወም ብቻ ሳይሆን፥ በክርስቶስ ምትክ አምልኮትንና ታዛዥነትን ሊቀበል ይሻል። ሰይጣን ምንጊዜም ቢሆን እንደ እግዚአብሔር አምልኮትና አገልግሎት ሊቀበል እንደተሯሯጠ ነው (ኢሳ. 14፡14፤ ሉቃስ 4፡5-8)። አንድ ቀን ከሁሉም የላቀ የጥበብ ሥራውን ማለትም ሐሳዊ-መሢሑን በማዘጋጀት፥ በዓለም ሊመለክና በውሸቶቹ ሊታመን ይጀምራል።

ጳውሎስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ወደነበሩት ቅዱሳት መጻሕፍት በማጣቀስ ይህን ሁሉ ለተሰሎንቄ አማኞች ገልጾላቸዋል። ለማጥናት የምንችልበት ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ በማግኘታችን እኛ የታደልን ነን፤ ከዚህም ውስጥ የሐሳዊ-መሢሑንና የሥራውን ጠቅላላ ሥዕል ልናገኝ እንችላለን። የትንቢት ተማሪዎች በሁሉም ዝርዝር ጉዳይ ላይ ላይስማሙ ቢችሉም፥ ዐበይት እውነቶቹን ስናዛምድ፥ በመጨረሻው ዘመን የሚሆነውን የሐሳዊ-መሢሕ መግለጫ እንደሚከተለው ሆኖ እናገኛለን፡-

1. ሰላም አድራጊው (ራእይ 6፡1-2)፡- በመሠረቱ፥ ይህ ሰው ከቤተ ክርስቲያን ንጥቀት በፊት መታየት ይጀምራል። አሥሩን የአውሮፓ መንግሥታት በማስተባበር ወደ ታላቅ ሥልጣን የሚያደርሳቸው ሰላማዊ የፖለቲካ መሪ ሆኖ ይቀርባል (ራእይ 17፡12-13 ተመልከት)። በነጭ ፈረስ ላይ የሚሄደው ሰው ክርስቶስን ይመስላል [ግን አይደለም] (ራእይ 19 ከቁጥር 11 ጀምሮ)። በሰላም ድል ለመንሣት ይወጣል፤ የቀስት መሳቢያ ደጋን አለው፤ ቀስቱ ግን የለውም። የጌታ ቀን አውሎ ነፋስ ከማጥለቅለቁ በፊት፥ ለዓለም አጭር የሰላም ጊዜ ያመጣል (1ኛ ተሰ. 5፡1-3)።

2. ጠባቂው (ዳን. 9፡24-27)፡- የዚህን ትንቢት አስገራሚ ዝርዝሮች ለመመርመር ባንችልም፥ አንዳንድ እውነቶችን መረዳቱ አስፈላጊ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ፥ ትንቢቱ የሚሠራው ለእስራኤል፥ ለኢየሩሳሌምና ለቤተ መቅደሱ እንጂ፥ ለቤተ ክርስቲያን አይደለም። ሁለተኛ፥ ትንቢቱ መሢሑ መቼ እንደሚመጣና የተወሰኑ ዓላማዎችን ለአይሁድ ሕዝብ እንደሚፈጽም ያውጃል። «ሱባዔ» የሰባት ዓመታት የጊዜ ገደብ የሚያመለክት ሲሆን፥ 70 ሱባዔ 490 ዓመታትን ያመለክታል። እነዚህ 490 ዓመታት በሦስት ክፍሎች መከፈላቸውን ልብ በል፤ ይኸውም ከተማዪቱ ዳግም የምትሠራባቸው 49 ዓመታት ወይም ሰባት ሱባዔዎች፥ በመጨረሻው ላይ መሢሑ መጥቶ የሚገደልባቸው 62 ሱባዔዎች ወይም

434 ዓመታት፥ «አለቃው» ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን የሚገባበት አንድ ሱባዔ ወይም 7 ዓመታት ነው።

በዚህ ትንቢት ውስጥ ሁለት አለቆች እንደሚገኙ ልብ በል፡- ክርስቶስ፥ መሢሑ አለቃ (ቁ. 25) እና ሐሳዊ-ክርስቶስ፥ «የሚመጣው አለቃ» (ቁ. 26)። በ70 ዓ.ም. ከተማዪቱንና ቤተ መቅደሱን ያፈረሱት ሮማውያን በመሆናቸው፥ «የሚመጣው አለቃ ሕዝብ» የተባሉት እነርሱ ናቸው። እንደዚሁም የሚመጣው ሐሳዊ-መሢሕ የቀድሞው የሮም መንግሥት አካል ከሆነ ሕዝብ ወገን የሚወለድ ይሆናል።

በመጨረሻውም፥ በ69ኛና በ70ኛ ሱባዔዎች መካከል የጊዜ ክፍተት እንዳለ ልብ በል። አሁን የምንኖረው በዚያ ክፍተት ውስጥ ነው። 69ኛ ሱባዔ በክርስቶስ አገልግሎት የተፈጸመ ሲሆን፥ 70ኛው ሱባዔ በሐሳዊ-መሢሕ መምጣት ይጀምራል። ሐሳዊ-መሢሑ እስራኤልን ለመጠበቅና ቤተ መቅደሱን ዳግም እንድትገነባ ለመፍቀድ ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን ይገባል። ይህም ለሰባት ዓመታት የሚደረግ ቃል ኪዳን ይሆናል። ለጊዜውም ቢሆን የመካከለኛውን ምሥራቅ ቀውስ ያረግባል። እስራኤልም በሰላማዊው ጊዜ ቤተ መቅደሷን ዳግም ትገነባለች። የጌታ ቀን በመባል የሚታወቀውን የሰባት ዓመታት የመከራ ጊዜ ማለትም የዳንኤልን 70ኛ ሱባዔ መጀመር የሚያመለክተው፥ የዚሁ ቃል ኪዳን መፈራረም እንጂ፥ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ አይደለም።

3. ሰላም አደፍራሽ (ዳን. 9፡27)፡- ከሦስት ዓመታት ተኩል በኋላ፥ ሐሳዊ-መሢሑ ከአይሁዶች ጋር የገባውን ቃል ኪዳን በማፍረስ፥ ቤተ መቅደሳቸውን ይወስዳል። ይህም ጳውሎስ፥ «ክህደቱ» በማለት የገለጸው ነው (2ኛ ተሰ. 2፡3)። ይህም ተራ ማታለል ወይም ክህደት ሳይሆን፥ «ዓመፁ» ነው። እስከዚህ ጊዜ ድረስ፥ ሐሳዊ-መሢሕ፥ እስራኤልን የመጠበቅ ግዴታ የነበረበት የአሥሩ አውሮፓ አገሮች ሰላማዊ መሪ ነበር። ይሁንና ከዚህ ጊዜ በኋላ፥ የአይሁድን ቤተ መቅደስ በመውሰድና የዓለም ሕዝብ እንዲያመልከው በመጠየቅ እውነተኛ ባሕርዩን ይገልጻል (ራእይ 13ን ተመልከት)።

ሐሳዊ-መሢሕ በሰይጣን ኃይል ስለሚሠራና ሰይጣንም ያለማቋርጥ የሕዝብን አምልኮት ስለሚፈልግ፥ «አምልኩኝ» ማለቱ አስገራሚ አይሆንም። የተለያዩ ቡድኖች ከእግዚአብሔር እውነት ያፈነገጡባቸውን በርካታ «ክህደቶች» የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይመሰክራል፤ ይሁንና ይህ የመጨረሻው ዓመፅ ከሁሉም የላቀ ይሆናል። የዓመፁ ሰው፥ እውነትም

ይሁን ሐሰት የሌላ የማንኛውንም ሃይማኖት ነገሮች ሁሉ ይቃወማል። እርሱን በማምለክ፥ ለሰይጣን የምትሰግደውንም የዓለም ቤተ ክርስቲያን ይመሠርታል።

ጌታችን ይህንን ክህደት፥ «የጥፋት ርኩሰት» በማለት የተነበየው ሲሆን (ማቴ. 24፡15)፥ ይህም በግልጽ ዳንኤል 9፡27ን የሚያመለክት ነው። ዓለም፥ በሰይጣን ኃይል ምልክቶችንና ድንቆችን በማድረግ ሕዝብን በሚያታልለው በዚህ ታላቅ መሪ ተደነቃለች።

4. አሳዳጁ (ራእይ 13፡15-17)፡- አብዛኛዎቹ የትንቢት ተማሪዎች የጥፋቱ ርኩሰት የሚፈጸመው ሐሳዊ-መሢሑ ከአይሁዶች ጋር ቃል ኪዳን ካደረገ ከሦስት ዓመታት ተኩል በኋላ እንደሚሆን ይስማማሉ (ዳን. 9፡27፥ «በሱባዔም እኩሌታ» ወይም ሦስት ዓመታት ተኩል ይላል)። ይህም የከፋ ስደትና መከራ የሚሆንበትን ጊዜ ያስከትላል። ኢየሱስ፥ «በዚያን ጊዜ ... ታላቅ መከራ ይሆናልና» ብሏል (ማቴ. 24፡21)። ሰይጣን በእስራኤል ላይ ቁጣውን ያወርዳል። የዓለምን የምጣኔ ሀብት ዘይቤ ስለሚቆጣጠርም፥ ዜጐች ለመግዛትና ለመሸጥ ይችሉ ዘንድ «የአውሬውን ምልክት» መቀበል ይኖርባቸዋል (ራእይ 13፡16-17)።

ሰዎች ብዙውን ጊዜ፥ «በሰባቱ ዓመታት የመከራ ጊዜ ውስጥ የሚድን ሰው ይገኝ ይሆን?» በማለት ይጠይቃሉ። መልሱ፥ «አዎን!» የሚል ነው። ራእይ 7፡1-8 ውስጥ እንደተገለጸው፥ (ምናልባትም ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቶስን በሚያስደንቅ ሁኔታ በራእይ በመመልከት እንደዳነው) 144 000 አይሁዶች ይድኑና ወንጌሉን ለሕዝብ ያዳርሳሉ። ሐዋርያው ዮሐንስ በታላቁ መከራ ውስጥ ደኅንነትን በማግኘት ስለሚወጡት እጅግ ብዙ አሕዛቦች ገልጾአል (ራእይ 7፡9-17)። ምንም እንኳ መንፈስ ቅዱስ የመከልከል ሚናውን በማቆም «ከመንገድ ቢወገድም» አሁንም በማዳን ኃይሉ መሥራቱን ይቀጥላል።

ይህም ሆኖ፥ በዚያን ጊዜ በክርስቶስ ለመታመንና ለእርሱ ለመኖር፥ ውድ ዋጋ መክፈልን ይጠይቃል። አማኞች ለአውሬው ምስል ለመስገድ ባለመፍቀዳቸው ይታረዳሉ። ምልክቱን ለመቀበል ባለመሻታቸው፥ ሥራ የማግኘት ወይም የመግዛት - የመሸጥ አቅም አይኖራቸውም። ዝናቸው ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ የናኘላቸው ሰዎች እንኳ ሳይቀሩ «ዳግም ተወልጃለሁ» ብለው ከሚናገሩበት ከዛሬው ዘመን እጅግ የሚቃረን ሁኔታ ይፈጠራል።

5. እስረኛው (ራእይ 19፡ 11-21)፡- እግዚአብሔር የጊዜ ሰሌዳ እንዳለው ልብ በል። ሰይጣን ዓለምን ለዘላለም እንዲገዛ አይፈቀድለትም። ኢየሱስ ክርስቶስ «በኃይልና በታላቅ ክብር» ይመለስና ሐሳዊ-መሲሑንና ተባባሪዎቹን ያስራቸዋል፤ ሰይጣንንም ጨምሮ ወደ ጥልቁ ይጥላቸዋል (ራእይ 20፡ 1-3)። ይህም የዓለም ሕዝቦች ኢየሱስ ክርስቶስን ለመውጋት ከሰይጣን ጋር የሚተባበሩበት የታላቁ ጦርነት አርማጌዶን ፍጻሜ ይሆናል (ራእይ 16፡ 16)። ይህም ወደ ቀጣዩ ክስተት ይወስደናል።

## የኢየሱስ ክርስቶስ መመለስ (2፡ 8-12)

ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ በክብርና በፍርድ ወደ ምድር የሚመለስበት ሲሆን፥ በ2ኛ ተሰሎንቄ 1፡5-10 እና ራእይ 19 ከቁጥር 11 ጀምሮ ተጠቅሶ ይገኛል። ይህም በሰባት ዓመቱ መከራ መጨረሻ ላይ «የዓመፅ ማኅደር» (የሰይጣን ክፉ መርሐ-ግብር) በአርማጌዶን ጦርነት ሲያከትም ይከናወናል። እዚህ ላይ የቤተ ክርስቲያንን ንጥቀት ከክርስቶስ ወደ ምድር መመለስ መለየት አስፈላጊ ነው። ይኸውም ቤተ ክርስቲያን ከእርሱ ጋር ለመገናኘት ወደ አየር የምትነጥቅበት የመጀመሪያው ክስተት ምሥጢራዊ ሲሆን፥ ቤተ ክርስቲያን ሰይጣንንና ኃይላቱን ለማሸነፍ ከክርስቶስ ጋር የምትመለስበት ሁለተኛው ክስተት ይፋዊ ነው።

1. በሐሳዊ-መሲሕ ላይ የሚሰጠው ፍርድ (2፡8-9)፡- ሐሳዊ መሲሑ ከሰይጣን ኃይልን ስለሚቀበል፥ ማንኛውም የምድር ላይ ዜጋ እርሱንና ኃይላቱን ለማሸነፍ አይችልም። «አውሬውን ማን ይመስለዋል፥ እርሱንስ ሊዋጋ ማን ይችላል?» (ራእይ 13፡ 4)። ሰይጣን የውሸት መሲሑ «በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም» ተግባሩን እንዲያከናውን ያስታጥቀዋል (2ኛ ተሰ. 2፡9)። በመሠረቱ፥ ይህ «ተአምራትን ምልክቶችንና ድንቆችን» የሠራውን ኢየሱስ ክርስቶስን ለመኮረጅ የሚደረግ ጥረት ነው (የሐዋ. 2፡22)።

ሰይጣን ሁልጊዜም ለማስመሰል ጌታ የሚሠራውን ሲቀዳ ኖሯል። በዓለም ውስጥ የዲያብሎስ ልጆች የሆኑ የውሸት ክርስቲያኖች አሉ (ማቴ. 13፡ 38፤ 2ኛ ቆሮ. 11፡26)። ሰይጣን፥ ሐሰተኛ ወንጌል የሚሰብኩ (ገላ. 1፡6-9) የውሸት አገልጋዮች አሉት (2ኛ ቆሮ. 11 ከቁጥር 13 ጀምሮ)። እንዲያውም «የሰይጣን ምኩራብ» (ራእይ 2፡9) ማለትም፥ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ እየመሰላቸው ዲያብሎስን የሚያገለግሉ ሰዎች የሚሰባሰቡበትም

ስፍራ አለ (1ኛ ቆሮ. 10፡19-21)። እነዚህ የውሸት ክርስቲያኖች ከሚያድን የክርስቶስ ጽድቅ የተለየ አስመሳይ ጽድቅ አላቸው (ሮሜ 10፡1-3፤ ፊልጵ. 3፡4-10)። ከፍርድ ፊት ሲቀርቡ ውሸትነቱ የሚረጋገጥ ሐሰተኛ የደኅንነት ዋስትና አላቸው (ማቴ. 7፡15-20)።

በሐዋርያት ዘመን፥ ተአምራት የመልእክቱን እውነትነት ለማረጋገጥ ይሰጡ ነበር (ዕብ. 2፡1-4)። የእግዚአብሔር ምርጥ ሐዋርያት ከእግዚአብሔር መላካቸውን ለማረጋገጥ፥ ተአምራትን የሹመት መግለጫ አድርገው ይጠቀሙበት ነበር (2ኛ ቆሮ. 12፡12)። ይሁንና፥ ተአምራት ብቻቸውን የሰውን ከእግዚአብሔር ዘንድ መላክ ሊያረጋግጡ አይችሉም፤ መልእክቱና ባሕርዩም ከግንዛቤ ውስጥ መግባት አለባቸው። መጥምቁ ዮሐንስ «ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ» ሲሆን (ዮሐ. 1፡6)፥ ዳሩ ግን «ምንም ተአምር አላደረገም» (ዮሐ. 10፡41)።

ሰይጣን ጌታ ካደረጋቸው ጋር ተመሳሳይ የሚመስሉትን ተአምራት ሊፈጽም ይችላል። በፈረዖን ቤተ መንግሥት ሙሴን የተቃወመው በእንዲህ ዓይነት መንገድ ነበር (ዘጸ. 7፡8-12፥ 20-22፤ 8፡5-7)። በመጨረሻው ፍርድ፥ በኢየሱስ ስም ተአምራት ያደረጉ አንዳንድ ሰዎች፥ ጭራሽ ያልዳኑ በመሆናቸው ምክንያት ከመንግሥተ ሰማይ ይወገዳሉ (ማቴ. 7፡21-23)። ይሁዳ ተአምራት ቢሠራም፥ ዳሩ ግን ዳግም አልተወለደም ነበር (ዮሐ. 6፡66-71፤ 13፡11፥ 18)።

የእግዚአብሔር ተአምራት ዓላማ ሕዝቡን ወደ እውነት መምራት ሲሆን፥ የሐሳዊ-መሢሕ ተአምራት ዓላማ ግን ሕዝቡ ውሸቱን እንዲያምን ማድረግ ይሆናል። ጳውሎስ «ውሸተኞች ድንቆች» (ቁ. 9) ያለው ተአምራቶቹ እውነት ባለመሆናቸው ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ሕዝቡ የሰይጣንን ውሸቶች እንዲያምን የሚገፋፉ በመሆናቸው ነው። ዓለም በርካሽ ማታለያዎች የሚጠቀመውን መሪ ለብዙ ጊዜ አይከተለውም (ራእይ 13፡13-14 ተመልከት)።

ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ፥ ሐሳዊ-መሢሑን «በአፉ መንፈስ ... በመገለጡ» ይፈርድበታል (ቁ. 8)። «ማጥፋት» እና «መሻር» የሚሉት አንቀጾች ሰይጣን ተደምስሶ እንደሚጠፋ አያመለክቱም፤ ራእይ 20፡10 እንደሚያመለክተው ሰይጣንና ጭፍራዎቹ በእሳት ባሕር ውስጥ ለዘላለም ይሠቃያሉ። ይህንኑ ዐረፍተ ነገር፥ «ጌታ ኢየሱስ በአፉ እስትንፋስ የሚያስወግደውና በመገኘቱ ነጸብራቅ ሥራዎቹን ወደ ፍጻሜ የሚያመጣበት» ብሎ መተርጐም ይቻላል።

ጌታችን ለቤተ ክርስቲያኑ የሚመጣበት ጊዜ እየቀረበ ሲመጣ፥ በዚህ ዓለም ውስጥ የሰይጣን አሠራሮች እየተጠናከሩ ይሄዳሉ (1ኛ ጢሞ. 4 እና 2ኛ ጢሞ. 3 አንብብ)። ሰይጣን ሐሰተኛ ስለሆነ፥ በእግዚአብሔር ቃል እውነት ልንቃወመው ይገባል (ኤፌ. 6፡17)። ጌታችን ሰይጣንን በበረሃ ውስጥ ድል ባደረገበት ጊዜ የተጠቀመው በዚሁ መሣሪያ ነበር (ማቴ. 4፡1-11)። ሰይጣን ውሸተኛና ነፍሰ-ገዳይ ነው (ዮሐ. 8፡44)። እግዚአብሔር በእውነቱ አማካኝነት ሕይወት ሲሰጥ፥ ሰይጣን ግን በውሸቱ አማካኝነት ሰዎችን ያርዳል። አንድ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰይጣንንና ዘዴዎቹን እንደሚያጠፋ በማወቃችን እንጽናናለን።

2) ላልዳኑት የሚሰጠው ፍርድ (2፡10-12)፡- በሰባት ዓመቱ የመከራ ወቅት በርካታ አይሁዶችና አሕዛብ እንደሚድኑ ተመልክተናል። ይሁንና እጅግ በርካታ የዓለም ሕዝቦችም ይጠፋሉ። እግዚአብሔር በዓለም ላይ ከሚያወርዳቸው አስጨናቂ ፍርዶች የተነሣ ብዙ ሰዎች ይሞታሉ (ራእይ 6፡7-8፤ 8፡11፤ 9፡18፤ 11፡13 ተመልከት)። ሌሎች ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመለስና የዳኑትን ካልዳኑት ሲለይ ይጠፋሉ (ማቴ. 25፡31-46)።

እነዚህ ሰዎች አምነው የሚድኑበት ዕድል እንደነበራቸው ልብ ማለት ያሻል። እግዚአብሔር ከደኅንነት ርቀው በጠፉት ላይ ፍርድ በማስተላለፍ አይደሰትም (ሕዝ. 33፡11)። እግዚአብሔር «ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል» (2ኛ ጴጥ. 3፡9)። እነዚህ ሰዎች እውነቱን ተቀብለው ለማመን ባለመፈለጋቸው፥ ይፈርድባቸውና ለዘላለም ይሠቃያሉ። እንዲያውም፥ ልባቸው እጅግ ስለሚጠጥር፥ ለእውነት ምንም ዓይነት ፍቅር አይኖራቸውም። ውሸተኞችና የውሸት አፍቃሪዎች ከሰማያዊቷ ከተማ ተለይተው (ራእይ 22፡15) ወደ እሳት ባሕር ይጣላሉ።

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ጳውሎስ አንድ ቀጥተኛ እውነት ተናግሯል። ይኸውም አንድ ሰው በመጨረሻው ላይ ተታሎ ውሸትን ከማመን ደረጃ ከመድረሱም፥ እውነትን ሊቃወም ይችላል። በምንም ዓይነት ገለልተኛ ወይም መሃል ሰፋሪ መሆን አይቻልም፤ አንድም እውነቱን እናምናለን አለዚያም ውሸቱን እናምናለን። በመሆኑም እውነቱን አለመቀበል ማለት ውሸትን መቀበል ማለት ነው።

ይህ ማለት አንድ ሰው ክርስቶስን ላለመቀበሉ እግዚአብሔር መወቀስ አለበት ማለት ነው? ይኼማ ሙሴ መቅሰፍቶችን በግብፅ ላይ በሚያወርድበት ጊዜ ስለነበረው የፈረዖን መንፈሳዊ ሁኔታ እግዚአብሔርን እንደመውቀስ ማለት ነው። ፈረዖን የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶና የእግዚአብሔርን ድንቆች ተመልክቶ ሲያበቃ፥ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለመስገድ አልፈለገም ነበር። ፈረዖን አንዳንድ ጊዜ ለአፍ ያህል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ተቀብያለሁ ቢልም፥ በመጨረሻው ላይ ግን ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ አልፈለገም ነበር። ልቡን በማደንደኑ እውነቱን ለማመን አልቻለም ነበር፤ ይህም እግዚአብሔር በግብፅ ምድር ላይ የመጨረሻ ፍርዱን እንዲያወርድ ገፋፋው።

ቁጥር 11 «ሐሰትን ያምኑ ዘንድ» ይላል። «ሐሰቱ» ምንድን ነው? ሰይጣን ሐሰተኛ በመሆኑ፥ በሰው ዘር ላይ በበርካታ ማታለያዎች ይጠቀማል። ይሁንና ከመጀመሪያው ሰውን ወደ ጥፋት የመራ አንድ «ሐሰት» አለ። ይህም ሐሰት ሰይጣን በመጀመሪያ ላይ ለሔዋን፥ «እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ» በማለት የተናገራት ነው። ሐሰተኛነቱም ሰው የራሱ አምላክ ስለሆነ ደስ ያሰኘውን ሊያደርግና በራሱ ሰብአዊ ጥረቶች ራሱን ሊያሻሽል ይችላል የሚል አሳብ በማቀፉ ነው። ይህም ሂደት በሮሜ 1፡ ከቁጥር 18 ጀምሮ ተጠቅሶ ይገኛል። በተለይ ቁጥር 25ን ተመልከት፡- «ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው።»

በሌላ አነጋገር ሰይጣን በሰው የትዕቢት መንፈስ ይጠቀማል ማለት ነው። ሉሲፈርን ወደ ሰይጣን የለወጠው ይኸው ትዕቢት ነበር (ኢሳ. 14፡12-15፤ ሕዝ. 28፡11-18)። በዚህ ዓለም ውስጥ ሰውን የሰይጣንን ፈቃድ ወደመከተሉ ወጥመድ የሚያመራው ትዕቢት ነው (2ኛ ጢሞ. 2፡24-26)።

አንድ ወዳጄ የሆነ የአንድ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ፥ በወንጌል ተግባር ላይ ተሰማርቶ ሳለ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላጋጠመው አንድ ሁኔታ አጫውቶኝ ነበር። ይኸውም ታላላቅ ችግሮችን ስለሚያመጣው አንድ የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣን ታሪክ ነው። ወንጌላዊው በሰፈሩ እስካለ፥ ባለሥልጣኑ መንፈሳዊ ኑሮ ይኖራል፤ ዳሩ ግን ወንጌላዊው በአካባቢው ከሌለ ሰውየው በሰይጣን ቁጥጥር ሥር የዋለ ይመስል አግባብነት የጐደላቸውን ተግባራት ይፈጽማል። በመጨረሻም ወንጌላዊውና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰውየውን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በማናዘዝ እውነቱን ደረሱበት፤ ሰይጣን

የባለሥልጣኑን ሕይወት ለመቆጣጠር ትዕቢትን መሣሪያ አድርጐ ይጠቀምበት ነበር።

ሰውየውም ሲያብራራ፥ «የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ሆኜ ሰሾም፥ ‹ከእንግዲህ አንተ አንድ ታዋቂና ዝነኛ ሰው ነህ› የሚል ድምፅ ሰማሁ። ለዚያም ድምፅ ራሴን በመስጠቴ፥ ሰይጣን በሕይወቴ ውስጥ በመግባት አየለ» ብሏል። ኃጢአቱን በመናዘዙ ቤተ ክርስቲያን ጸሎት አደረገችለትና እግዚአብሔር ነፃ አወጣው።

«አሁንማ አንተ አንድ ታዋቂና ዝነኛ ሰው ሆንሃል፤ ስለዚህ በፈጣሪ ፈንታ ፍጡሩን አምልክ!» የሚለው የሰይጣን ሐሰተኛ ምክር ሲሆን፥ ዛሬም ዓለምን የሚገዛው ይኸው ሐሰት ነው ብዬ እፈራለሁ። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አምሳል ፈጥሮታል፤ ዛሬ ደግሞ ሰው እግዚአብሔርን በራሱ አምሳል እየፈጠረ ነው።

ክርስቶስ የሚፈርድባቸው ሰዎች እውነትን ባለመውደዳቸው ብቻ ሳይሆን፥ «በዓመፃም ደስ ይላቸው» የነበሩ በመሆናቸው ነው (ቁ. 12)። እንዲህ ዓይነት ለመሰለው ሰው ማብራሪያ ለማግኘት በመዝሙር [50] ቁ. 16-21 ያለውን አንብብ። በተጨማሪም መዝሙር (52)ን አንብብ። የአይሁድ ካህናት ይሁዳ ክርስቶስን አሳልፎ ለመስጠት በመስማማቱ ያለጥርጥር «ተደስተው» ነበር (ማር. 14፡10-11)። አስቀድሜ እንደጠቀስሁት፥ ይህ ሐሰትን የማመን ሂደት በሮሜ 1 ውስጥ ተገልጾ ይገኛል። የዚሁ ጥቅስ የመደምደሚያ ቁጥር ይህንኑ እውነት በግልጽ ያስቀምጣል - «እንደነዚህ ለሚያደርጉት ሞት ይገባቸዋል የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ እያወቁ እነዚህን ከሚያደርጉ ጋር ይስማማሉ እንጂ አድራጊዎች ብቻ አይደሉም» (1፡32)።

ዳሩ ግን ይህን ማለት ከንጥቀት በፊት የወንጌሉን መልእክት የሰሙ ሰዎች ከንጥቀት በኋላ ሊድኑ አይችሉም ማለት ይሆን? የግድ እንደዚህ ማለት አይሆንም። ያ እውነት ቢሆንማ ኖሮ፥ ለጠፉት ሰዎች የምናቀርበው ምስክርነት፥ ክርስቶስ ሲመለስ ለኩነኔ በሆነባቸውም ነበር። ይሁንና፥ ማንኛውም ከደኅንነት ርቆ የጠፋ ኃጢአተኛ የእግዚአብሔርን እውነት በግዴለሽነት የማስተናገድ ወይም በተደጋጋሚ የእግዚአብሔርን ልጅ የማግለል አጋጣሚ አይኖረውም ማለት ነው። ኃጢአተኛው የእግዚአብሔርን እውነት ባገለለ መጠን፥ ሰብአዊው ልቡ እየጠጠረ ይመጣና የሰይጣንን ሐሰት ለመቀበል ይቀለዋል።

የእግዚአብሔርን ቃል «በእውነት እንዳለ . . . እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል» አድርገው ያልተቀበሉትን የተሰሎንቄ አማኞች ምሳሌነት መከተሉ ምንኛ የተሻለ ነው! (1ኛ ተሰ. 2፡13)። እውነቱን ተቀብለው ዳኑ።

አንተስ እውነቱን ተቀብለሃል?

# 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡13-3፡5

«እኛ ግን፥ በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥ ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አለብን፥ እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኩራት መርጦአችኋልና፤ ለዚህም የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለማግኘት በወንጌላችን ጠራችሁ። እንግዲያስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ጸንታችሁ ቁሙ፥ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ።

«ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና የወደደን በጸጋም የዘላለምን መጽናናት በጎንም ተስፋ የሰጠን እግዚአብሔር አባታችን ልባችሁን ያጽናኑት በበጎም ሥራና በቃል ሁሉ ያጽኑአችሁ።

«በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ የጌታ ቃል እንዲሮጥ በእናንተም ዘንድ ደግሞ እንደሚሆን እንዲከበር፥ እምነትም ለሁሉ ስለማይሆን ከዓመፀኞችና ከክፉዎች ሰዎች እንድንድን ስለ እኛ ጸልዩ። ነገር ግን የሚያጸናችሁ ከክፉውም የሚጠብቃችሁ ጌታ የታመነ ነው። የምናዛችሁንም አሁን እንድታደርጉ ወደ ፊትም ደግሞ እንድታደርጉ ስለ እናንተ በጌታ ታምነናል። ጌታም ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ወደ ክርስቶስም ትዕግሥት ልባችንን ያቅናው።»

# - 12 -

# እውነት ብቻ

ጳውሎስ ሚዛናዊነትን የጠበቀ አገልግሎት የሚሰጥ ሚዛናዊ ክርስቲያን ነበር፤ ለዚህም በመልእክቱ መደምደሚያ ላይ መረጃ እናገኛለን። ከትንቢት ወደ ተግባራዊ የክርስቲያን አኗኗር ተጉዞአል። ከአሉታዊ (የሰይጣን ሐሰት) ወደ አዎንታዊ (የእግዚአብሔር እውነት)፥ ከማስጠንቀቂያ ወደ ምስጋናና ጸሎት ተመልሷል።

ዛሬ ሚዛኑን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት እጅግ በጣም ያስፈልገናል። በአንድ ወቅት ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊያደርግ የሚፈልገውን ነገር ሙሉ ለሙሉ ከዕይታ በማራቅ፥ በምትኩ በአይሁዶች ሕይወት ውስጥ ወደ ፊት በሚፈጸምው ጉዳይ ላይ ብቻ ያተኰረ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮንፍራንስ (ጉባኤ) ተከታትዩ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ የትንቢትን ጥናት ከቶውንም ከኃላፊነት የምናመልጥበት ቀዳዳ አድርገን መጠቀም የለብንም።

ቀደም ብለን ከተመለከትነው የሰይጣን ታላቅ ሐሰት በተቃራኒ፥ የጳውሎስ አጽንኦት በእግዚአብሔር ቃል እውነት ላይ ነበር። እያንዳንዱ አማኝ ለእግዚአብሔር እውነት አራት ኃላፊነቶች አሉበት።

## እውነቱን ማመን (2፡13-14)

ጳውሎስ በዚህ መልእክት ውስጥ ለዚህች ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርባቸውን ተደጋጋሚ ምስጋናዎች ተመልክተናል (1ኛ ተሰ. 1፡2፤ 2፡13፤ 3፡9፤ 2ኛ ተሰ. 1፡3፤ 2፡13)። በሕይወታቸው ለእግዚአብሔር ሥራ ምላሽ ስለሰጡበት ሁኔታ ምስጋና ያቀርባል። በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች፥ ጳውሎስ በደኅንነት ልምምዳቸው ውስጥ የነበሩትን ደረጃዎች ከልሶአል።

1. እግዚአብሔር ወድዶአቸዋል (2፡13)፡- እግዚአብሔር ከደኅንነት ርቆ ለጠፋው ዓለም የሚያደርገው ነገር ሁሉ የሚመነጨው ከዘላለማዊ ፍቅሩ ነው። ታላቁን የደኅንነት ዕቅዱን የግብር ይውጣ ያህል አድርገን መውሰድ የለብንም። የእርሱ ደኅንነት መሠረት የጣለው በፍቅሩ ላይ ሲሆን (ዮሐ. 3፡16)፥ እግዚአብሔር የዚህን ፍቅር እውነትነት ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም ኃጢአት በሞተበት መስቀል ላይ አረጋግጦአል (ሮሜ 5፡8)።
2. እግዚአብሔር መርጦአቸዋል (2፡13)፡- እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ ስለወደደና ዳሩ ግን ዓለሙ ሁሉ ስላልዳነ፥ የሚያድነን ፍቅር ብቻ አይደለም። ፍቅር በጸጋና በምሕረት ራሱን ይገልጻል። እግዚአብሔር

በክርስቶስ አማካኝነት የማይገባንን ነገር ይሰጠናል፤ በምሕረቱ ደግሞ የሚገባንን ቅጣት አልሰጠንም፤ ያንኑ ቅጣት ለክርስቶስ ሰጠው እንጂ! እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን እንደሚመርጥ ግልጽ ነው። (1ኛ ተሰ. 1፡4፤ ኤፌ. 1፡4፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡2)።

3. እግዚአብሔር ለይቶአቸዋል (2፡13)፡- «መቀደስ» ማለት «መለየት» ማለት ነው። ይበልጥ ኢየሱስ ክርስቶስን እየመሰልን እንድንሄድ የሚያደርግ፥ እያደገ የሚሄድ ቅድስና አለ (1ኛ ተሰ. 5፡23)። ይሁንና ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የሚናገረው ቅድስና መንፈስ ቅዱስ የማያምነውን ሰው በክርስቶስ ወደማመን የሚመራበትን ሁኔታ ያመለክታል። «እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው በመንፈስም እንደሚቀደሱ ... ለተመረጡት» (1ኛ ጴጥ. 1፡2)። አማኙን ወደ መረዳት የሚያመጣው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው (ዮሐ. 16፡7-11)። እኔም ብሆን በጊዜው ባላስተውለውም፥ የኋላ ኋላ ግን መለስ ብዬ ሳሰላስለው፥ መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ወዳለው እምነት እንዴት እንደመራኝ ወለል ብሎ ይታየኛል። ይህም በሁሉም አማኝ ዘንድ የደረሰ ነው።

4. እግዚአብሔር ጠራቸው (2፡14)፡- ፍጻሜውን (ደኅንነት) የወሰነው ይኸው እግዚአብሔር ወደ ፍጻሜው የሚያደርሰውንም መንገድ («እውነትን በማመን») ወስኖአል። «እግዚአብሔር አስቀድሞ የወደዳቸውን ስለመረጠ፥ መጸለይ፥ መመስከርና ወንጌላውያንን መላክ አያስፈልገንም» የሚሉ ሰዎች መለኮታዊውን ምርጫ አልተረዱም ማለት ነው። ለወንጌል አገልግሎት ከሁሉም የሚልቀው ማበረታቻ እግዚአብሔር ለቃሉ ምላሽ በመስጠት ወደ እርሱ ሊመለሱ የሚገባቸው ሰዎች እንዳሉት ማወቁ ነው (የሐዋ. 18፡1-11 አንብብ)።

እግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅዱን ለመፈጸም፥ ጳውሎስ፥ ሲላስና ጢሞቴዎስን ቃሉን እንዲሰብኩ ወደ ተሰሎንቄ ልኮአቸዋል። «በዘላለም ዕቅድ» የተወሰነው «በወቅቱ» ተፈጽሞአል። እግዚአብሔር ወንጌሉን ከደኅንነት ርቀው ለጠፉት ለማድረስ ሰዎችን መሣሪያ አድርጎ ተጠቅሞአል፤ እነዚህም ሰዎች በክርስቶስ በማመን «የእግዚአብሔር ምርጦች» መሆናቸውን አረጋገጡ (1ኛ ተሰ. 1፡4)። የእግዚአብሔር ጥሪ ወደ ከተማዪቱ ሁሉ ደረሰ፤ ይሁንና ስኬታማ የሆነው እውነቱን በማመን ክርስቶስን በተቀበሉት ሰዎች ዘንድ ብቻ ነው።

የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነትና የሰውን ኃላፊነት አስመልክቶ አላስፈላጊ ከሆነ ምርምር ውስጥ መግባት አደገኛ ነው። ሁለቱም አሳቦች በመጽሐፍ

ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ። «ደኅንነት ከእግዚአብሔር ዘንድ» እንደሆነና (ዮናስ 2፡10) ከደኅንነት ርቀው የጠፉት ኃጢአተኞች ራሳቸውን ሊያድኑ እንደማይችሉ እናውቃለን። ለደኅንነታችን «ምሥጢራዊ» የሆኑ ነገሮች እንዳሉ በመቀበል ልንተማመንባቸው በምንችላቸው «ማረጋገጫዎች» ልንደሰት ይገባል። ስለዚህ የምርጫን ዶክትሪን፥ ቤተ ክርስቲያንን ለመከፋፈል ወይም ደካማውን ለማወክ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ጌታን ለማስከበር ልንጠቀምበት ይገባል።

5. እግዚአብሔር ክብርን ሰጣቸው (2፡14)፡- በኃላፊው ዘላለማዊ የጊዜ ሰሌዳ የተጀመረው ነገር በወደፊቱ የዘላለም ጊዜ ውስጥ ፍጻሜውን ያገኛል፤ እኛም የእግዚአብሔር የክብሩ ተካፋዮች እንሆናለን (ሮሜ 8፡29-30፤ ዮሐ. 17፡24)። በጸጋ የሚጀምረው ነገር ወደ ክብር ይመራል። ይህ ግን ለጠፉ ኃጢአተኞች ከተወሰነው የወደፊት ዕጣ ጋር የሚቃረን ነው (2ኛ ተሰ. 1፡8-10)። ለአማኞች አሁኑኑ የእግዚአብሔር ክብር በውስጣቸው ይገኝናል (ዮሐ. 17፡22፤ በሮሜ 8፡30 ላይ ደግሞ «አከበራቸው» የሚለውን የኃላፊ ጊዜ አምልካች ልብ ብለህ አጢን)። እንደዚሁም አሁን የክርስቶስን መመለስ እየተጠባበቅን ሲሆን፥ በዚያን ጊዜ ደግሞ ክብሩ በይፋ ይገለጻል (2ኛ ተሰ. 1፡10፤ ሮሜ 8፡17-19)።

ኃጢአተኞች በእግዚአብሔር እውነት ሲያምኑ እግዚአብሔር ያድናቸዋል። የሰይጣንን ሐሰት ሲያምኑና እውነተኛ ፍቅርን ሲያገልሉ ግን ሊድኑ አይችሉም (2ኛ ተሰ. 2፡10-12)። ስለ እግዚአብሔር እውነት ገለልተኛ አቋም መያዝ አደገኛ ነው። አሳዛኝ ዘላለማዊ ውጤቶችንም ያስከትላል።

## እውነቱን መጠበቅ (2፡15)

ጳውሎስ በእውነት ላይ ስለሚነሣው የወደፊት ዓመፅ ነግሮአቸዋል (2ኛ ተሰ. 2፡3)፤ ይህም በሐሳዊ-መሲሕ የሚመራው ታላቅ ክህደት ነው። ይሁንና በጊዜውም የሚታይ አደጋ እንደነበር በመግለጽ፥ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን እውነት እንድትጠብቅና ከዚያም ፊቷን እንዳትመልስ አስጠንቅቋል። ስለዚህ ጉዳይ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያዎች አሉ (1ኛ ዮሐ. 2፡18-24፤ 4፡1-3፤ 2ኛ ጴጥ. 2፤ 1ኛ ጢሞ. 4፤ 2ኛ ጢሞ. 3 ጥቂቶቹ ናቸው)።

እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ውስጥ በቃሉ እውነት አማካኝነት ሲሠራ፥ ሰይጣን ውሸቶቹን በመተካት ይህንኑ እውነት ይቃወማል። የሰው ባሕርይ ደግሞ ውሸትን በቀላሉ በመቀበል እውነትን ወደ መቃወሙ ያዘነብላል። ሰይጣንም ከሁሉም የላቀ ሥራውን የሚያከናውነው የእግዚአብሔርን እውነት በማያምኑና ለስሙ የክርስቲያን ተቋሞች (አብያተ ክርስቲያናት፥ ትምህርት ቤቶች፥ ወዘተ.) ተብለው በሚጠሩ ድርጅቶች አማካኝነት ነው። እነዚህ ድርጅቶች «የመንፈሳዊነት ቅርፅ» ቢኖራቸውም፥ የእግዚአብሔርን የማዳን ኃይል እውነታ ከቶውንም አያውቁም።

ጳውሎስ «ወግ» ሲል፥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረቱትን ሃይማኖታዊ አስተሳሰቦች ማለቱ አይደለም። ጌታችንም ቢሆን የተቃወመው ሰው ሠራሽ የሆኑትን ሃይማኖታዊ ወጐች ሲሆን (ማር. 7፡1-3)፥ ጳውሎስም ከእነዚህ ወጐች እንድንርቅ አስጠንቅቆናል (ቈላ. 2፡8)። የሃይማኖት ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ግልጽ እውነት እያገለሉ በሰው ወጐች ላይ ሲሟገቱ መመልከቱ በጣም አሳዛኝ ነው።

«ወግ» ማለት «ከአንድ ሰው ወደ ሌላው የተላለፈ ነገር» ማለት ነው። የወንጌሉ እውነት እንደ ቃል መልእክት በክርስቶስና በሐዋርያት ተጀመረ። በኋላም፥ ይኸው እውነት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ተጽፎ የመጽሐፍ ቅዱስ አካል ሊሆን በቃ (2ኛ ጢሞ. 3፡12-17፤ 2ኛ ጴጥ. 2፡16-21 ተመልከት)። የእግዚአብሔር እውነት ሰው የፈለሰፈው ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር ለሰው የተሰጠ ሲሆን (ገላ. 1፡11-12፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡1-6)፥ የእያንዳንዱ ትውልድ አማኞች ይህንኑ እውነት ጠብቀው ለሌሎች አስተላልፈዋል (2ኛ ጢሞ. 2፡2)።

ጳውሎስ እውነትን በመጠበቅ ረገድ ከአማኞች የሚጠበቁትን ሁለት ኃላፊነቶች በግልጽ አስቀምጦአል፤ «ጸንታችሁ ቁሙ ... ወግ ያዙ» (2ኛ ተሰ. 2፡15)። «ጸንታችሁ ቁሙ» ማለት «ከወንጌሉ እውነት ፈቀቅ አትበሉ» ማለት ነው (1ኛ ቆሮ. 16፡13 እና ቈላ. 1፡23 ተመልከት)። እኔና ባለቤቴ የለንደንን ሕንፃዎች በጐበኘንበትና የነገሥታቱን ጌጣጌጦች በተመለከትንበት ጊዜ፥ ሕዝቡ ወዲያና ወዲህ ቢተረማመስም ዘበኞቹ ግን በአንድ ቦታ ጸንተው እንደቆሙ አስተውለናል። መላው ትኩረታቸው በጐብኚዎቹ ላይ በመሆኑ፥ ከተመደቡበት ስፍራ ሊያንቀሳቅሳቸው የሚችል ምንም ነገር አልነበረም። እኔና አንተም «ውዱን እምነት» በመጠበቅ ላይ ስለምንገኝ፥ በሰይጣን ማታለያ ወይም በሰዎች ውዳሴ ስፍራችንን ልንለቅ አይገባም።

ከቆምን፥ የጸና አቋም ልንይዝ እንችላለን። ይህም ማለት «አጽንቶና አጥብቆ መያዝ» ማለት ነው። ይህ ቃል «ጥንካሬ፥ ችሎታ፥ ኃይል» ከሚለው የግሪክ ቃል ጋር የተያያዘ ነው። የእግዚአብሔርን እውነት በግዴለሽነት ሳይሆን፥ ከእጃችን እንዳያፈተልክ በኃይል አጥብቀን መያዝ አለብን። በእያንዳንዱ ትውልድ ውስጥ የሚኖሩ ክርስቲያኖች እውነቱን ከሌሎች በመቀበል፥ መጠበቅና ለቀጣዩ ትውልድ ያለምንም ጉድለት መተላለፉን ማረጋገጥ አለባቸው።

እርግጥ በዙርያችን የሚገኙ ኃይላት ከአቋማችን ሊያዋዥቁንና ሊያፈናቅሉን ስለሚፈልጉ፥ ጠንክረን መቆምና እውነትን መያዝ ቀላል ነገር አይደለም። ሰይጣን የእግዚአብሔርን እውነት ለመቃወም በውሸቶች እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ስለሚያውቅ፥ ይህንኑ ተግባር በወገኖች ኅብረት ውስጥ ሊያከናውን ይሻል (የሐዋ. 20፡28-32)። ስለዚህም ነው አንዳንድ ጊዜ ታማኝ አማኞች ከእምነት ከራቁ ወገኖች ሊርቁ ይገባል የተባለው (ሮሜ 16፡17-20፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡14-7፡1፤ 2ኛ ዮሐ. 7-10፤ 1ኛ ጢሞ. 6፡3-5)።

ይህንን አሳብ እስኪ በሁለት የማስጠንቀቂያ ቃላት ላጠቃልል። በመጀመሪያ፥ ለእኛ የተሰጠን «እምነት» ከሰው ትርጓሜዎችና አሳቦች ጋር መደናገር የለበትም። ፈሪሳውያን የራሳቸውን ትርጓሜ እንደ እግዚአብሔር ቃል ያህል የተቀደሰ አድርገው በመቁጠር ይመለከቱት ነበር (ማር. 7፡7-9)። የወንጌል አማኞች ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል መሠረታዊ ትምህርቶች ቢቀበሉም፥ ዳሩ ግን ሁሉም አማኞች በአናሳ የአተረጓጎም ጉዳዮች ላይ (በተለይም ትንቢቶችን በተመለከተ)፥ ወይም በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ላይ አይስማሙም። ስለዚህ የሰውን አሳቦች የኅብረት ወይም የመንፈሳዊነት መለኪያ ማድረጉ አደገኛ ነው።

ሁለተኛ፥ እውነት፥ ሕይወቱንና ኃይሉን እንዳያጣ፥ አሽገን ወይም ሸሽገን ልናስቀምጠው አይገባም። ከእግዚአብሔር የእውነት መዝገብ ውስጥ «አዲሱንና አሮጌውን» እንደሚያወጡ ታማኝ ሠራተኞች ልንሆን ይገባል (ማቴ. 13፡52)። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ገና በርካታ እውነት ስላለ፥ ሁሉንም እንዳወቅን አድርገን ማሰብ የለብንም። ቃሉ እንደ ዘር ስለሆነ (ሉቃስ 8፡11)፥ ዘሩ በሚዘራበት ጊዜ፥ ተክሎችን፥ ፍሬንና ተጨማሪ ዘርን ያስገኛል። ከጥንት የቆዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን መናገሩ መልካም ቢሆንም፥ መንፈስ ቅዱስ ከቃሉ ውስጥ አዳዲስ እውነቶችን

እንዲያስተምረንና የቆዩትን እውነቶች በአዲስ ሁኔታ ከሕይወታችን ጋር እንዲያዛምድ ፈቃደኞች ልንሆን ይገባል።

## በእውነት መኖር (2፡ 16-17)

እውነቱን ማመንና መጠበቁ ብቻ በቂ አይደለም፤ በእውነት መኖር አለብን። ቃሉን ብንሰማና ዳሩ ግን ባንታዘዘው፥ ራሳችንን እናታልላለን (ያዕ. 1፡22-25)።

እነዚህ ሁለት ቁጥሮች ጳውሎስ ለወዳጆቹ የነበረውን መሻትና ጸሎት ይገልጻሉ፤ እግዚአብሔር እንዲያጽናናቸው («ልባችሁን አጽናኑት») እና እንዲያጸናቸው («በበጎም ሥራና በቃል ሁሉ የጸናችሁ ሁኑ») ይፈልግ ነበር። በመሆኑም ሁለቱም ቃላት በተሰሎንቄ መልእክቶች ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ አላቸው።

ጳውሎስ ከእነርሱ ጋር በነበረ ጊዜ፥ አባት ለልጆቹ እንደሚያደርግ በግል ደረጃ አጽናንቶአቸዋል (1ኛ ተሰ. 2፡11)። እንደዚሁም ጢሞቴዎስን እንዲያጽናናቸው የላከው ሲሆን (3፡2)፥ ጢሞቴዎስ ስለታማኝነታቸው በነገረው ጊዜ ጳውሎስ ራሱ በጣም ተጽናንቶ ነበር (3፡7)።

ጳውሎስ እግዚአብሔርን ለማስደሰት እንዲኖሩና (4፡1) ለሌሎች ባላቸው ፍቅር እንዲያድጉ አበራቶአቸዋል (4፡10)። እርስ በርሳቸው ይበረታቱም ዘንድ ስለ ቤተ ክርስቲያን ንጥቀት አስተምሮአቸዋል (4፡18)። ፍርሃታቸውንም ለማርገብ፥ ስለ ጌታ ቀን አብራርቶላቸዋል (5፡11)። ከትምህርቱ በተጨማሪ፥ እርስ በርሳቸው አገልግሎት እንዲለዋወጡ ገፋፍቶአቸዋል (5፡18)።

በጌታ መጽናትም ዐቢይና እጅግ ወሳኙ አሳብ ነው። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ወደ ተሰሎንቄ መልሶ የላከው በእምነታቸው እንዲያጸናቸው ሲሆን (1ኛ ተሰ. 3፡2)፥ በሌላም በኩል እግዚአብሔር እንዲያጸናቸው ይጸልይ ነበር (3፡13)። አንድ ልጅ ለመራመድ ወይም ለመሮጥ ከመማሩ በፊት፥ እንዴት እንደሚቆም ማስተማር አስፈላጊ ነው።

የሚያጸናው እግዚአብሔር ሲሆን፥ ዳሩ ግን ሥራውን ለማከናወን በሰዎች ይጠቀማል። በአብያተ ክርስቲያናቱ ውስጥ እጅግ አስፈላጊው ነገር፥ አዳዲስ አማኞችን ለማጽናት ጊዜ የሚወስዱ ክርስቲያኖችን ማግኘት ነው። እንደ ቤተ ክርስቲያን ይፋዊ ጉባኤዎች ሁሉ፥ የቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ

ጥናቶችም ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው ናቸው። ይህም ሆኖ አንድን ሰው በግል ደቀ መዝሙር ማድረጉም አስፈላጊ ነው። ጳውሎስ የተሰሎንቄን አማኞች በግል ደረጃ አንድ-ለአንድ አጽናንቶአቸዋል፤ እኛም ምሳሌነቱን ልንከተል ይገባል።

ጳውሎስ የክርስትና ሕይወታቸውን በተመለከተ ስለ ሁለት ነገሮች ያስብ ነበር፤ ይኸውም ስለ ቃላቸውና ስለ አረማመዳቸው ነው። አረማመዳችን ከቃላችን ጋር የሚጻረር ከሆነ፥ ምስክርነታችንን እናጣለን። «ቃላችን» እና «አረማመዳችን» መስማማት አለባቸው፤ ለጌታ ከተሰጠው ልባችን ውስጥ መልካም ተግባራትና መልካም ቃላት ሊፈልቁ ይገባል።

በመልካም ሥራችን አማካኝነት ባንድንም (ቲቶ 3፡3-7፤ ኤፌ. 2፡8-10)፥ ዳሩ ግን መልካም ሥራዎች የደኅንነት መረጃዎች ናቸው (ቲቶ 2፡11-15)። በመልካም ቃላት ላይ መደገፉ ብቻ አይበቃም፤ ቃላት በተግባራት ሊደገፉ ይገባል (1ኛ ዮሐ. 3፡18)፤ ይህም ወቅታዊ ሳይሆን፥ ተከታታይነት ያለው ልምምድ መሆን አለበት። በመሆኑም በቃላችንና በተግባራችን ልንጸና ይገባል።

ይህ እንዴት ይቻላል? ይህንን በጸጋው ሊያደርገው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ ጳውሎስም ለወዳጆቹ የፈለገው ይህንኑ ለማሳወቅ ነው። እግዚአብሔር በጸጋው ዘላለማዊ መጽናኛና መልካም ተስፋ ሰጥቶናል። የጳውሎስ ቃላት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስንና እግዚአብሔር አብን በማስተባበር፥ የክርስቶስን አምላክነት እንደሚገልጹ ልብ በል። በቁጥር 16 ላይ ለእግዚአብሔር የተሰጡ ሁለት መጠሪያዎች በብዙ ሳይሆን በነጠላ ግሥ መቅረባቸው እኩልነታቸውን ያመለክታል። በ1ኛ ተሰሎንቄ 3፡11 ላይም ተመሳሳይ አወቃቀር በመጠቀም፥ የአብንና የወልድን እኩልነት ያጠናክራል።

ዛሬ በርካታ ክርስቲያኖች እውነትን በመጠበቅ ላይ እያተኮሩ፥ በእውነት ከመኖር ግን ይታቀባሉ። ሆኖም እውነትን ለመጠበቅ ከሚረዱ እጅግ ጠቃሚ መንገዶች አንዱ እውነትን በተግባር መተርጐም ነው። እምነትን መጠበቁ አስፈላጊ ቢሆንም፥ እምነትን በተግባር ከማሳየት ወደ ኋላ ልንል አይገባም። አልዓዛር የሙታንን ትንሣኤ በተመለከተ ገለጻ ማቅረብ አያስፈልገውም ነበር፤ ሰዎች እርሱን በሕይወት በማየት ብቻ አይተው አምነዋል (ዮሐ. 12፡9-11)።

## እውነትን ማካፈል (3፡1-5)

የኃላፊነቶች ቅደም-ተከተል አስፈላጊ ነው። መማርና መኖር ጐን ለጐን መሄድ አለባቸው። እውነትን ብናምን፥ ይኸው እምነት ሕይወታችንን ይለውጠዋል። ይህንንም እውነት ለሌሎች ለማካፈል እንድንችል እንጠብቀዋለን፥ እንለማመደዋለን። ግብዞች ለመሆን እስካልፈለግን ድረስ የማናምነውን ነገር ለሌሎች ልናካፍል አንችልም፤ ዳሩ ግን ራሳችን በተግባር ላይ ያዋልነውን ነገር፥ ከሁሉም በተሻለ ሁኔታ ለሌሎች ልናካፍል እንችላለን።

የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ስለ ሆነ (ዕብ. 4፡12)፥ በነፃ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ አለብን። ጳውሎስ በዚህ ስፍራ መዝሙር [147]፡15ን ይጠቅሳል፤ «ነገሩን ወደ ምድር ይሰድዳል፥ ቃሉም እጅግ ፈጥኖ ይሮጣል።» የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሊታሰሩ ቢችሉም፥ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ቃል ሊታሰር አይችልም (2ኛ ጢሞ. 2፡9)። እውነትን ከሕይወታችን ጋር ስናዛምደውና ለእውነት አገልግሎት ስንጸልይ፥ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ልብ ለመሰራጨትና የእግዚአብሔርን ዓላማዎች በዓለም ውስጥ ለመፈጸም ነፃነት ይኖረዋል።

የእግዚአብሔር ቃል በሚያካፍሉትና በሚቀበሉት ሰዎች ሕይወት ውስጥ ይከብራል። በጲስድያ በምትገኘው አንጾኪያ ውስጥ ጳውሎስም የተመለከተው ይህንኑ ነበር፤ «አሕዛብም [መዳን እንደሚችሉ] ሰምተው ደስ አላቸው፥ የእግዚአብሔርንም ቃል አከበሩ፥ ለዘላለም ሕይወትም የተዘጋጁ ሁሉ አመኑ፤ የጌታም ቃል በአገሩ ሁሉ ተስፋፋ» (የሐዋ. 13፡48-49)።

በአሁኑ ጊዜ ግን እጅግ ብዙው የክርስትና ሥራ የሚከናወነው በሰዎች ዕቅዶችና ቅስቀሳዎች እንጂ፥ በእግዚአብሔር ቃል አይደለም። በመርሐ-ግብሮቻችን እየታመንን፥ የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ ለመከተል ችላ እንላለን። መርሐ-ግብሮቻችንን ብናውጅም፥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ሳንታመን እንቀራለን። አጽናፈ-ዓለሙ የተፈጠረውና የተጋጠመው በእግዚአብሔር ቃል ነው (ዕብ. 11፡3)። ያለጥርጥር ቃሉ በዚህች ዓለም ውስጥ ሥራውን ሊፈጽም ይችላል። ይሁንና የመድረኮች ስብከት አገልግሎት ባመዛኙ በዓለማዊ የመዝናኛ ፕሮግራሞች ተተክቷል። ዶክተር ዶናልድ ኮገን የሚባሉ የካንተርቤሪ ሊቀ-ጳጳስ ክርስቲያን መጋቢዎችን በማስመልከት፥ «ሥራቸው በጐችን መመገብ እንጂ ፍየሎችን ማዝናናት አይደለም» ብለዋል።

በሦስት ስፍራዎች በመጋቢነት ሳገለግል የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚፈጽም አይቼአለሁ። በጐች በሚገባ በሚመገቡበት ጊዜ፥ በፍቅር ሊሰማሩ፥ ሊዋለዱ፥ እረኛውን ሊከተሉና ለመሥዋዕትነት ሊሰጡ ይችላሉ፤ በዚህም ደስ ይላቸዋል። በጐች እርስ በርሳቸው የሚጣሉት፥ የሚታመሙትና የሚባዝኑት፥ በሚራቡና በሚጥገሙበት ጊዜ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ሥራውን በሚፈጽምበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር ክብሩን ይቀበላል። መልካሙ ወዳጄ ዶክተር ቦብ ኩክ፥ «እየተፈጸመ ያለውን ነገር ለማብራራት ከቻላችሁ፥ አድራጊው እግዚአብሔር አይደለም ማለት ነው!» ይሉ ነበር።

በመሠረቱ፥ ምንጊዜም ቢሆን በእግዚአብሔር ቃልና ሥራ ላይ ተቃውሞ ይነሣል። ጳውሎስ ክፉና ኃጢአተኛ ከሆኑ፥ ከማያምኑ ሰዎች ጋር ከመወዳጀት ይድን ዘንድ የሚያውቁት ሁሉ እንዲጸልዩለት ለምኗል። መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ለማካፈል ለጌታ በተሰጡ ሰዎች እንደሚጠቀም ሁሉ፥ ሰይጣንም ቃሉን ለመቃወም በኃጢአተኞች ይጠቀማል። ክፉው ሰው፥ ክርስቲያን አማኞች ቃሉን እንዲቃወሙ በማድረግ ይደሰታል። ሰይጣን በጴጥሮስ በኩል ለመናገር የሞከረውን ያህል (ማቴ. 16፡21-23)፥ በሐናንያና በሰጲራ አማካኝነትም ሥራውን ሠርቷል (የሐዋ. 5፡1-11)።

ጳውሎስ አንባቢዎቹ ራሳቸውን ለሰይጣን እንደማይሰጡ፥ ዳሩ ግን ታማኙ ጌታ እንዲያንጻቸውና ከክፉው እንዲጠብቃቸው እራሳቸውን እንደሚያዘጋጁ ይተማመን ነበር (3፡3)። በራሳችን ልንታመን ባንችልም፥ ዳሩ ግን ስለራሳችንም ሆነ ስለሌሎችም በእግዚአብሔር ልንታመን እንችላለን።

መጋቢው ወይም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ብቻ ቃሉን ማካፈላቸው በቂ አይደለም፤ እያንዳንዱ ክርስቲያን የዚሁ ዋንኛ አገልግሎት አካል መሆን አለበት። ጳውሎስ በ3፡4 ላይ የተጠቀመበት «ማዘዝ» የሚለው ቃል «ከበላይ አለቃ የተላለፈ የውትድርና ትእዛዝ» ማለት ነው። ይህንንም ቃል በ1ኛ ተሰሎንቄ 4፡2 ላይ የጠቀሰው ሲሆን፥ በዚሁ ምዕራፍ በቁጥር 4፥ 6፥ 10 ና 12 ላይም ደግሞ ጠቅሶታል። ክርስቶስ የደኅንነታችን መሪ ሲሆን፥ እኛ ደግሞ ወታደሮቹ ነን (2ኛ ጢሞ. 2፡3-4)። በጦርነት ውስጥ፥ የአለቆች ብቻ መዋጋት በቂ አይደለም፤ እያንዳንዱ ሰው ኃላፊነቱን መወጣት አለበት። ይኸው አሳብ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም እውነት ነው።

በአሁኑ ጊዜ ባብዛኛው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደምንመለከተው ሁሉ፥ በተመሳሳይ ሁኔታ በጦር ኃይሉም ውስጥ ጭምር ያለመታዘዝ፥ ሥነ -ሥርዓትን የመጋፋትና የዲሲፕሊን ጉድለት የሚታይበት ከሆነ ውጤቱ ምን ይሆናል? ከቶውንም ጦርነቱን ሊያሸንፍ አይችልም። ወታደሮች ሥልጠናውን የሚወስዱት ደስ ባለኛቸው ጊዜ ከሆነ፥ ጠላትን ለመጋፈጥ በሚያስችል ሁኔታ ሊታጠቁ አይችሉም። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን የእግዚአብሔርን ቃል ላለመቀበል እንደሚያምፁ ሁሉ የጦር ሠራዊቱም የአለቆቻቸውን ትእዛዛት ላለማክበር አሻፈረኝ ቢሉ፥ በወታደራዊ ፍርድ ቤት ይዳኛሉ።

አንድ ወታደር በመጀመሪያ ደረጃ ከታማኝነትና ከፍርሃት የተነሣ ይታዘዛል። ይሁንና ክርስቲያን ለመታዘዝ እጅግ የላቀ ዓላማ አለው፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ፍቅርና የክርስቶስ መመለስ ግድ ይለዋልና ነው (ቁ. 5)። «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» (ዮሐ. 14፡15)። አዛዥ ባለሥልጣን ከጭፍሮቹ ፍቅርን አይጠይቅም፤ ከወደዱት ግን በበለጠ አክብሮት ይታዘዙታል። የጦርነት ታሪክ እንደሚዘግበው፥ የጀግንነት ተግባራት የተፈጸሙት መሪዎቻቸውን በወደዱና ለእነርሱም ሲሉ በፈቃዳቸው በተሠው ሰዎች ነው። አዳኛችን እኛን በመውደድ፥ በፋንታችን ሞቶአል። እኛስ ልንታዘዘው አንችልም ይሆን?

ለእኛ ሲል ተመልሶ ይመጣል። ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፋቸው መልእክቶች ዐቢይ አሳብ ይኸው ሲሆን፥ ይህንኑ እውነት ከዕለታዊ ተግባራዊ ሕይወት ጋር ያዛምደዋል። አንድ ቀን ተመልሶ ስለ ሕይወታችን ዘገባ እንድናቀርብ ስለሚጠይቀን፥ እንደ እግዚአብሔር ወታደሮች ቃሉን ለሌሎች ማካፈል አለብን። «መገለጡን እንወዳለን?» (2ኛ ጢሞ. 4፡8)፤ «በመምጣቱስ በፊቱ እናፍር ይሆን?» (1ኛ ዮሐ. 2፡28)።

እንግዲህ፥ በዚህ ስፍራ ልንፈጽማቸው የሚገቡን አራት ኃላፊነቶች አሉ፡- እውነቱን ማመን፥ እውነቱን መጠበቅ፥ በእውነቱ መኖርና እውነቱን ማካፈል። እነዚህን ኃላፊነቶች ብንፈጽም፥በሕይወታችን ደስታንና ኃይልን፥ በአብያተ ክርስቲያናታችን ደግሞ ዕድገትንና በረከትን እናገኛለን።

# 2ኛ ተሰሎንቄ 3፡6-18

«ወንድሞች ሆይ፥ ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛችኋለን። እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁና፤ በእናንተ ዘንድ ያለ ሥርዓት አልሄድንምና፤ ከእናንተ ዘንድ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት፥ ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ፥ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም። ይህም እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር እንጂ፥ ያለ ሥልጣን ስለሆንን አይደለም። ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን፡- ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና። ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፥ በሰው ነገር እየገቡ፥ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና። እንደነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዝዛቸዋለን እንመክራቸውማለን። እናንተ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ።

«በዚህ መልእክት ለተላከ ቃላችን የማይታዘዝ ማንም ቢኖር፥ ይህን ተመልከቱት፥ ያፍርም ዘንድ ከእርሱ ጋር አትተባበሩ። ነገር ግን እንደ ወንድም ገሥጹት እንጂ እንደ ጠላት አትቍጠሩት።

«የሰላምም ጌታ ራሱ በሁሉም መንገድ ዘወትር ሰላምን ይስጣችሁ። ጌታ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

«በገዛ እጄ የተጻፈ የእኔ የጳውሎስ ሰላምታ ይህ ነው፤ የመልእክቴ ሁሉ ማስረጃ ይህ ነው፤ እንዲህ እጽፋለሁ። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።»

# - 13 -

## በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ሥርዓት

ችግሮች እልባት ሳያገኙ ሲቀሩ፥ ሥር እየሰደዱ በመሄድ ከከፋ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ። በሰው ጥፍር ውስጥ ዘልቃ የገባች ስንጥር ውሎ ሲያድር መርዛማነትን ልትፈጥርና ለቀዶ-ጥገና ሕክምናም ልታደርስ ትችላለች። የዛገ ምስማር እንደወጋህ ለሐኪምህ ብትነግረው፥ ምንም እንኳ ለአንተ ቁስሉ በጣም አነስተኛ ቢመስልህም፥ ዳሩ ግን ሐኪሙ በፍጥነት የመንጋጋ ቆልፍ (ቲታነስ) መርፌ እንድትወጋ ያደርግሃል።

የቤተ ክርስቲያን ችግሮች ልክ እንደ ሥጋዊ ችግሮች ናቸው፤ እልባት ካልተገኘላቸው፥ ሥር እየሰደዱ በመሄድ ከከፋ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ልክ እንደ ሰው አካል ነች፤ ጥቃቅን ተሐዋስያን (ጀርምስ) ሥጋዊውን አካል እንደሚጐዱ ሁሉ፥ ኃጢአትም መንፈሳዊውን አካል ይመርዘዋል። ጳውሎስ የመጀመሪያ መልእክቱን ለተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍ፥ ለሥራ-ፈት ጣልቃ-ገቦችም ወደ ሥራ እንዲሰማሩ አስጠንቅቆአቸዋል (1ኛ ተሰ. 4፡11)። ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችም «ከሥርዓት ውጪ የሚሄዱትን ገሥጹአቸው» በማለት መክሮአቸዋል (5፡14)። «ከሥርዓት ውጪ» ማለት «ከመስመር የወጣ ወታደር» ማለት ነው። ጳውሎስ የሁለተኛውን መልእክት ቀሪ ክፍሎች ለዚህ ጉዳይ ማዋሉ፥ እነዚህ ችግር ፈጣሪዎች ንስሐ ገብተው ከጥፋታቸው ባለመመለሳቸው ይመስላል።

ችግሩ ምን ነበር? አንዳንድ የማኅበረ ምዕመናን አባላት ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ መመለስ የሰጠውን ትምህርት በተሳሳተ መልኩ በመረዳት፥ ሥራቸውን ለቀው የቤተ ክርስቲያን ጥገኞች ሆነው ነበር። ሌሎች ሲሠሩ እነርሱ ቁጭ ብለው የቤተ ክርስቲያንን ድጋፍ ይጠብቁ ነበር። ይህ ሰነፍ ቅዱሳን የሚገኙበት ቡድን፥ ጳውሎስ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡2 ላይ ለጠቀሰው የሐሰት ትምህርት ምንጭ ሳይሆን አይቀርም። እንዲሁም ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚገኙ ሰዎች ሐሜት ያስፋፉ ነበር። ለሐሜት በቂ ጊዜ ስለነበራቸውና እንደበታቸውም የሰላ በመሆኑ፥ ለምን አትሠሩም ተብለው በተጠየቁ ቁጥር የሚሰጡት መልስ «ጌታ በቅርብ ጊዜ ይመጣል!» የሚለውን ማመካኛ ነበር።

የእግዚአብሔርን ቃል እውነት አዛብቶ መተርጐምና አዛብቶ ማገናዘብ፥ ማለቂያ የሌለውን መከራ ሊጋብዝ ይችላል። ታሪክ የጌታችንን የመምጫ

ዕለት የወሰኑትን፥ ንብረታቸውን የሸጡትንና በተራራ ጫፍ ላይ ተቀምጠው መምጫውን የተጠባበቁትን ሰዎች ያለማስተዋል ዘገባ ያቀርብልናል። ማናቸውንም መለኮታዊ ትምህርት እንድንተላለፍ የሚያበረታታ ማንኛውም ትምህርት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አይደለም።

ለምሳሌ ፈሪሳውያን አምስተኛውን ትእዛዝ እንደሚያከብሩ ቢለፍፉም፥ ዳሩ ግን ወላጆችን ለመቀማት የሚያመች መንገድ ያዘጋጁ ነበር። «እርሱ (ኢየሱስ) ግን እንዲህ አላቸው፡- ኢሳይያስ ስለ እናንተ ስለ ግብዞች፡-

‹ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል› ተብሎ እንደ ተጻፈ በእውነት ትንቢት ተናገረ። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትታችሁ ጽዋን ማድጋንም እንደማጠብ የሰውን ወግ ትጠብቃላችሁ፥ ይህንም የመሰል ብዙ ሌላ ነገር ታደርጋላችሁ።

«እንዲህም አላቸው፡- ወጋችሁን ትጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እጅግ ንቃችኋል። ሙሴ፡- አባትህንና እናትህን አክብር ደግሞ፡- አባቱን ወይም እናቱን የሰደበ ፈጽሞ ይሙት ብሎአልና። እናንተ ግን ትላላችሁ፡- ሰው አባቱን ወይም እናቱን፡- ከእኔ የምትጠቀምበት ነገር ሁሉ ቁርባን (ለእግዚአብሔር የተሰጠ) ማለት መባ ነው ቢል፥ ለአባቱና ለእናቱ ምንም እንኳ ሊያደርግ ወደ ፊት አትፈቅዱለትም፤ ባስተላለፋችሁትም ወግ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ እንደዚሁም ይህን የሚመስል ብዙ ነገር ታደርጋላችሁ» (ማር. 7፡6-13)።»

ጳውሎስ ችግሩን ለመቅረፍ ጠቅላላው ቤተ ክርስቲያን በኅብረት እንደሚሠራ ተስፋ ያደርግ ነበር። በፍቅር የምትመላለስ ቤተ ክርስቲያን የራስዋን አባላት ሕይወት በማቃናት፥ እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔርን እንዲታዘዝ ለመርዳት መሻት አለባት። ጳውሎስ በዚህ በኩል ለመርዳት ሲል፥ ግዴለሽ አማኞች ከኃጢአታቸው ተመልሰው የራሳቸውን የመተዳደሪያ ተግባር ያከናውኑ ዘንድ፥ አራት ዓላማዎችን አስፍሮላቸዋል።

## የቃሉ ምክር (3፡6)

ጳውሎስ ይህን «ማዘዝ» የሚለውን ኃይለኛ ቃል በመጀመሪያው የተሰሎንቄ መልእክቱ ውስጥ የጠቀሰ ሲሆን (4፡2፥ 11)፥ በዚህም ምዕራፍ ውስጥ ቀደም ብለን ተመልክተነዋል (ቁ. 4)። በድጋሚ በቁጥር 10 እና 12 ላይም ጠቅሶታል። አስቀድሞ እንደተገለጸው፥ የቃሉ ትርጉም «ከበላይ ባለሥልጣን የተላለፈ ወታደራዊ ትእዛዝ» ማለት ነው። ጳውሎስ ቤተ

ክርስቲያንን እንደሠራዊት የተመለከተ ሲሆን፥ ሠራዊቱ ሥርዓቶችን የማያከብር ከሆነ፥ ሥርዓተ-አልበኝነት ይሰፍናል። የሚያሳዝነው፥ አንዳንዶቹ ቅዱሳን «ያለ ሥርዓት» ይመላለሱ ነበር (1ኛ ተሰ. 5፡14፤ 2ኛ ተሰ. 3፡6፥ 7፥ 11)።

ጳውሎስ፥ «ሊሠራ የማይወድ ቢኖር አይብላ» ብሎ ለማዘዝ የሚያስችል ምን ሥልጣን ነበረው? (ቁ. 10)። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የማዘዝ ሥልጣን ነበረው። በተሰሎንቄ መልእክቶቹ ውስጥ፥ ጳውሎስ ቢያንስ 20 ጊዜ የአዳኙን ሙሉ ማዕረግ ጠቅሶአል፤ «ኢየሱስ» ማለት «አዳኝ» ማለት ሲሆን፥ ይህም ሰብአዊ ስሙ ነው (ማቴ. 1፡21)። «ክርስቶስ» «መሚሕ-የተቀባ» ማለት ሲሆን፥ መለኮታዊ ማዕረጉ ነው። ሌሎች ሰዎች (በዕብራዊ ቅርፁ «ኢያሱ» የሚለውን) የኢየሱስን ስም ሊጠቀሙበት ይችላሉ፤ የተቀቡት ደግሞ ስለመቀባታቸው ሊናገሩ ይችላሉ፤ ይህም እንደ ነቢያት፥ ካህናትና ነገሥታት ያሉት ናቸው። ይሁንና ሁለቱን አጠቃሎ የሚይዘው ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለው ስም «ጌታ» ማለት «ያህዌ እግዚአብሔር» በሚለው ስያሜው በይበልጥ የተብራራ ይሆናል።

በአራቱ ወንጌላትና በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ጌታችን ብዙውን ጊዜ ኢየሱስ ተብሎ ተጠርቷል፤ ይህም ቢሆን፥ ይህ ስም ብቻውን በተቀሩት የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ውስጥ የተጠቀሰው በጣም በመጠኑ ነው። በመሆኑም፥ በተወሰኑ አጋጣሚዎች ብቻ መጠቀሱ አዳኛቸውን «ኢየሱስ» ብለው በሚጠሩት ሰዎች ላይ ከመፍረድ ሊገታን የሚገባ ከመሆኑም፥ በዚህ ስም የተጠራው በይበልጥ በምድር ላይ በሚያገለግልበት ወቅት የመሆኑ እውነታ፥ በክብር ስሙ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብለን እንድንጠራው ሊያደፋፍረን ይገባል (ፊልጵ. 2፡11)። ከእንግዲህ «ክርስቶስን» ከፍ ከፍ እንደ ተደረገ የእግዚአብሔር ልጅና «ለቤተ ክርስቲያን በነገር ሁሉ ራስ» እንደ ሆነ እንጂ፥ «በሥጋ እንደሚሆን አናውቅም» (2ኛ ቆሮ. 5፡16)። ጌትነቱም በሥራችንንና በመዋዕለ-ንዋይ አስተዳደራችንንም ሁሉ ላይ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለጉልበት (ወይም የአእምሮ) ሥራ ምን ያስተምራል? መረዳት ያለብን፥ ኃጢአት ከመምጣቱ በፊት «ሥራ» የሰው ሕይወት አካል መሆኑን ነው። እግዚአብሔር ለአዳም የገነትን የአትክልት ስፍራ የመጠበቅና የመንከባከብ ሥራ ሰጠው (ዘፍ. 2፡15)። ምንም እንኳ ኃጢአት ሥራን እጅግ አድካሚ ወደ ሆነ ጥረት ቢለውጠውም (ዘፍ. 3፡17-19)፥ የሥራ አስፈላጊነት የኃጢአት ውጤት ነው ተብሎ መታሰብ የለበትም። ሰው

ለሰብአዊ ድርሻው ማሟያ መሥራት አለበት፤ እግዚአብሔር የፈጠረው እንዲሠራ ነው።

ለመሆኑ እግዚአብሔር ሥራ የሚበዛባቸውን ሰዎች እንደጠራ ልብ ብለህ ይሆን? ሙሴ የበጐች እረኛ ሲሆን (ዘጸ. 3)፥ ኢያሱ የሙሴን ኃላፊነት ከመሸከሙ በፊት የሙሴ አገልጋይ ነበር (ዘጸ. 33፡11)። ጌዴዎን እግዚአብሔር በሚጠራው ጊዜ ስንዴ ይወቃ ነበር (መሳ. 6 ከቁጥር 11 ጀምሮ)፤ ዳዊትም የአባቱን በጐች ይጠብቅ ነበር (1ኛ ሳሙ. 16 ከቁጥር 11 ጀምሮ)። ጌታችን በደቀ መዛሙርትነት ያገለግሉት ዘንድ አራት ዓሣ አጥማጆችን የጠራ ሲሆን፥ እርሱ ራሱም በአናፂነት ሠርቷል። ጳውሎስ ድንኳን ሠሪ ሲሆን (የሐዋ. 18፡1-3)፥ በዚህም አገልግሎቱን ለመደገፍ በቅቷል።

አይሁዶች ሥራን የሚያከብሩና የሃይማኖት አስተማሪዎቻቸውም እንዲሠሩ የሚፈልጉ ነበሩ። ግሪኮች ግን የጉልበት ሥራን በመናቅ በባሪያዎቻቸው ትከሻ ላይ ይጭኑ ነበር። በመሆኑም በዚህ የግሪክ ተጽዕኖ ላይ ስለ ጌታ መመለስ የነበራቸው የተሳሳተ አሳብ ስለታከለበት አልፎ አልፎ አማኞችን ክርስቲያናዊ ባልሆነ መንገድ እንዲኖሩ አደረጋቸው።

እርግጥ አንዳንድ ሰዎች ምናልባት ከአካል ጉድለት ወይም ከቤተሰብ ኃላፊነቶች የተነሣ ላይሠሩ እንደሚችሉ ጳውሎስ ተገንዝቦ ነበር። «ሊሠራ የማይወድ ቢኖር» ማለቱም ለዚሁ ነው። እንግዲህ ጥያቄው የፈቃደኝነት እንጂ የችሎታ ጉዳይ አይደለም። አንድ አማኝ ሊሠራ ባለመቻሉ በችግር ውስጥ ቢገባ፥ ይህንኑ አማኝ መርዳት ለቤተ ክርስቲያን መልካም አጋጣሚ፥ ዕድልና ግዴታ ነው (ያዕ. 2፡14-17፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡16-18)።

በመሠረቱ እነዚህን ሰነፍ አማኞች የቃሉ ምክርና ተግሣጽ ለሥራ ሊያነሣሣቸው ይገባ ነበር፤ ይሁንና ጳውሎስ ሁለተኛ ማበረታቻ ምክርም ይለግሣቸዋል።

## የሐዋርያው ምሳሌነት (3፡7-10)

ሐዋርያ እንደመሆኑ፥ ጳውሎስ የመዋለ-ንዋይ ድጋፍ የማግኘት መብት ቢኖረውም፥ ዳሩ ግን ለአዳዲሶቹ አማኞች መልካም ምሳሌነትን ያሳይ ዘንድ፥ ሆን ብሎ መብቱን ወደ ዳር ይገፋዋል (1ኛ ቆሮ. 9፡6-14 ተመልከት)። በዚህም አመለካከቱ፥ ጳውሎስ በሳል ክርስቲያን መሪ መሆኑን አረጋግጦአል። ራስ-ወዳድነት የሚያጠቃቸው መሪዎች የደጋፊዎቻቸውን ቁጥር ለማሳደግ በሰዎች የሚጠቀሙ ሲሆን፥ ሁልጊዜም በመብታቸው ላይ

ያተኩራሉ። በእውነት የተሰጠ መሪ ግን መብቶቹን የሚጠቀምባቸው ሰዎችን ለማነፅ ሲሆን፥ ለሌሎች በጐነት ሲል መብቶቹንና መልካም ዕድሎቹን ሁሉ መሥዋዕት እስከማድረግ ይደርሳል።

ጳውሎስ የሥራ ምሳሌነቱን ባለፈው መልእክቱ ውስጥ ጠቅሶአል (1ኛ ተሰ. 2፡9)። አንባቢዎቹም ጳውሎስና ተባባሪዎቹ ከታዳጊዋ ቤተ ክርስቲያን ምንም ዓይነት ድጋፍ እንዳላገኙ ያውቁ ነበር። ይልቁንም፥ በግል ጥረታቸው የራሳቸውን አስፈላጊ ነገሮች በማሟላትና የሌሎችን ጉዳዮች በማርካት በአርአያነት የሚጠቀሱ ነበሩ። አንባቢዎቹን፥ «እኛን ምሰሉ» በማለት መክሮአቸዋል።

ይህም ከሁሉም ይበልጥ ያበረከተው አስተዋጽኦ ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያደረበትንና ለመሥዋዕትነት ዝግጁ የሆነን ሕይወት ጠቀሜታ በማሳየት ረገድ ነው። አንድ ክርስቲያን መሪ የቃሉን ሥልጣን ሊያመለክት ቢችልም፥ የራሱንም የታዛዥነት ምሳሌ ሊያሳይ እስካልቻለ ምእመናን ሊሰሙት አይፈልጉም። በአምባገነንነትና በምስክርነት መካከል ያለው ልዩነት ይህ ነው። አንድ መሪ መልካም ምስክርነት የሚያገኘው ለቃሉ ሲታዘዝና ሕዝቡን በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ሆኖ ሲያገለግል ነው። በመሆኑም፥ ምስክርነት የሚመጣው ከዕለታዊ ኑሮና ምሳሌነት ሲሆን፥ ሥልጣን የሚመጣው ከሹመት ነው። ምስክርነት መሪው ሥልጣኑን ከተግባር ላይ የሚያውልበትን መንገድ ያመቻቻል።

እያንዳንዱ ክርስቲያን አገልጋይ፥ ጌታን በሚያገለግልበት ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ድጋፍ የማግኘት መብት አለው (ሉቃስ 10፡7፤ ገላ. 6፡6፤ 1 ጢሞ. 5፡17-18)። በመሆኑም፥ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን አገልጋዮች ላለመደገፍ የጳውሎስን ምሳሌነት እንደ ማመካኛ አድርጋ ልትጠቀምበት አይገባም። ይሁንና ማንኛውም የእግዚአብሔር አገልጋይ መብቱን ለእግዚአብሔር ክብር ወደ ጐን የመተው ምርጫ አለው። ጳውሎስ ይህንን ያደረገው በተሰሎንቄ ለነበሩ አዳዲስ አማኞች ምሳሌነቱን ለማሳየት ነበር።

የጳውሎስ የሕይወት መመሪያ አዳዲስ አማኞችን ማበረታታት ብቻ ሳይሆን፥ የከሳሾቹንም አፍ አስይዞአል። በየከተማዎች በመዘዋወር ገንዘብ ለማግኘት «ሸቀጣቸውን የሚቸበችቡ» አታላይ አስተማሪዎች ነበሩ። ጳውሎስ ከእነርሱ ጋር ሊመደብ አልፈለገም ነበር። ማንም ያልዳነ ሰው፥ «ጳውሎስ የሚሰብከው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ነው» እንዲለው አልፈለገም ነበር። በ1ኛ ቆሮንቶስ 9 ውስጥ እንደጠቀሰው፥ ጳውሎስ ወንጌልን «በነፃ»

ለመስበክ እንጂ፥ ከደኅንነት ርቀው የጠፉትን ሰዎች የመመለሱን ተግባር በገንዘብ የተነሣ ለማስተጓጐል አልፈለገም ነበር።

ዳሩ ግን አሁንም ቢሆን የእነዚህ አማኞች ግዴለሽ አመለካከት ቤተ ክርስቲያኒቱን እየጐዳ ነበርና፥ ጳውሎስ ለታዛዥነታቸው ሦስተኛውን ዓላማ (አነሣሽ ምክንያት) ይጨምራል፡-

## የቤተ ክርስቲያን ማበረታቻ (3፡11-15)

«እናንተ ግን፥ወንድሞች ሆይ፥መልካሙን ሥራ ለመሥራት አትታክቱ» የሚለው የቁጥር 13 ቁልፍ አሳብ ነው። ታማኝ ክርስቲያኖች ለመሥራት በማይፈልጉ ግዴለሽ ባልደረቦቻቸው ሁኔታ ተስፋ ቆርጠው ነበር። ሙግታቸውም፥ «እነርሱ የማይሠሩ ከሆነ፥ እኛስ ለምን እንሠራለን?» የሚል ነበርና፥ ጳውሎስ ይህንኑ እንቅስቃሴ በእንጭጩ ይቀጨዋል።

ሁልጊዜም በአንድ አማኝ ሕይወት ውስጥ ያለው ኃጢአት፥ በቀሪዎቹ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ላይ ተጽዕኖ ያስከትላል። የአካሉ ክፍሎች እንደመሆናችን፥ አንዳችን ሌላውን እንጠቅማለን፤ እንጐዳለንም። የጥቂት ቅዱሳን መጥፎ ምሳሌነት፥ የቀሪዎቹን የቤተ ክርስቲያን ምእመናን የተሰጠ ሕይወት ሊያወድምና አገልግሎታቸውንም ሊያከስም ይችላል።

ጳውሎስ የእነዚህን ሰዎች ኃጢአት በዝርዝር አስቀምጦአል። በመጀመሪያ ደረጃ፥ «ያለ ሥርዓት፥» ወይም ፈር በለቀቀ ሁኔታ ይመላለሱ ነበር። ትእዛዛትን ይተላለፉ ነበርና፥ ይህም በማኅበረ-ምእመናኑ መካከል ግራ መጋባትንና ክፍፍልን አመጣ። በተጨማሪም «ጣልቃ-ገቦች» እንጂ፥ ብርቱ ሠራተኞች አልነበሩም። «ጣልቃ-ገብ» ተብሎ የተተረጐመውን የግሪክ ቃል፥ ቃል በቃል ስንፈታው፥ «ግርግር መፍጠር» ማለት ነው፤ ይህም ምንም ዓይነት ፍሬ ነገር ሳይፈጽሙ፥ ወዲያ ወዲህ መራወጥ ማለት ነው። አንደኛ ጢሞቴዎስ 5፡13 እንደሚያመለክተው «ጣልቃ-ገቦች» በማያገባቸው ጉዳይ ውስጥ ይገባሉ።

ከሞላ-ጐደል ሁሉም ባህል ስለ ሥራ ፈትነት የራሱ የሆነ አገላለጽ አለው። የሮም ሰዎች፥ «ምንም ነገር ባለመሥራት፥ ሰዎች ክፉ ነገር መሥራትን ይማራሉ» ይላሉ። አይዛክ ዋት የተባለው ፈላስፋ ደግሞ፥ «ሰይጣን ለሥራ-ፈቶች ያከናውኑት ዘንድ አንድ የተንኰል ሥራ ያገኝላቸዋል» በማለት ጽፎአል። የአይሁድ የሃይማኖት መምህራን፥ «ልጁን ሥራ ያላስተማረ ወላጅ፥ ሌብነትን ያስተምረዋል» ይላሉ።

አካባቢውን እያወኩ ወዲያና ወዲህ ከማለት ይልቅ፥ እነዚህ ሰዎች «በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን» መብላት ነበረባቸው። ስለ ክርስቶስ መመለስ የነበራቸው የተሳሳተ አመለካከት ወደ ልቅ የስሜት ደረጃ አደረሳቸው። በመሆኑም ጳውሎስ፥ «የመጠቀ የስሜት አመለካከታችሁ ስሕተት ነው፤ ተረጋግታችሁ ሥሩ» በማለት ያስጠነቅቃቸዋል። አንድ ሰው በሥራ ከተያዘ ሚዛናዊነት ለጐደለው አስተሳሰብና ማስተዋል ለራቀው ተግባር ሁሉ ጊዜ የለውም።

ይሁንና እነዚህ ቅዱሳን ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ምትክ በሥራ ላይ ብቻ ቢሰማሩ፥ ቤተ ክርስቲያን ምን ማድረግ አለባት? ጳውሎስ ቀደም ባለው በመጀመሪያ መልእክቱ በመከራቸውና (1ኛ ተሰ. 5:14) እንደተሳሳቱ በመግለጽ ባስጠነቀቃቸው ጊዜ፥ ወቅታዊ እርምጃ ወስዶአል። ይህም ሆኖ እነርሱ ሥርዓት በጐደለው ባሕርያቸው መኳዛቸውን ቀጥለዋል። አሁንም በሁለተኛ መልእክቱ ዳግም በማስጠንቀቅ፥ ተጨማሪ እርምጃ ይወስዳል፤ እነዚህ አማኞች የማይታዘዙ ከሆነ፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ ምእመናን በግል ደረጃ ሥርዓት ሊያስይዙአቸው ይገባል።

በአሁኑ ወቅት የቤተ ክርስቲያን የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ብዙም ሲያነጋግር አንመለከትም። በብዙዎቹ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እንደሚታየው፥ አንድ ጊዜ ሰውየው ከተጠመቀና የቤተ ክርስቲያን አባል ከሆነ በኋላ፥ ባመዛኙ የራሱን ሕይወት እንዲመራ ይተዋል። ከበድ የሚል ይፋዊ ኃጢአት ቢፈጽም እንኳን መጋቢው ወይም ቦርዱ ለጉዳዩ እልባት ይሰጣል እንጂ፥ ጠቅላላው የቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ በጥፋቱ ላይ ተወያይቶ ምክር ሲለግሰው ወይም የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ሲወስድበት አንመለከትም።

የቤተ ክርስቲያን የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ምንድን ነው? በመጀመሪያ ደረጃ፥ የቤተ ክርስቲያን የሥነ-ሥርዓት እርምጃ፥ መጋቢውና እውቅና የተሰጠው ቦርድ፥ እንደ ወንጌላዊ የፖሊስ ሠራዊት ኃጢአት የሚሠራውን አማኝ አድነው በመያዝ፥ ከቤተ ክርስቲያን የሚያስወግዱበት አሠራር አይደለም። እንዲህ ዓይነት አምባገነን መሪዎች ያሉባቸው አብያተ ክርስቲያናት መኖራቸው ባይጠረጠርም፥በጳውሎስ አእምሮ ውስጥ የነበረው አሳብ ይህ አልነበረም። ለልጅ የቤተሰብ የሥነ-ሥርዓት እርምጃ እንደሚያስፈልግ ሁሉ፥ ለምእመንም የቤተ ክርስቲያን የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ያስፈልጋል፤ይህም የሚያርም ፍቅር የሚያገኝበትና አካሄዱንም የሚያዳብርበት ዕድል ነው። ወላጅ ልጁን በሚቀጣበት ጊዜ፥ ቀውጢ ልጁ

የተሻለ ሰው እንዲሆንለት የሚጥር አባት ሆኖ እንጂ፥ በወንጀለኛ ላይ እንደሚፈርድ ዳኛ በመሆን አይደለም።

በትክክል ልንረዳቸው የሚገቡ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ደረጃዎች አሉ፡-

1. በክርስቲያኖች መካከል የሚገኙ የግል ልዩነቶች (ማቴ. 18፡15-18፤ ፊልጵ. 4፡1-3)፡- አንድ ወንድም ወይም እህት (አውቀውም ሆነ ሳያውቁ) በደል ቢፈጽሙብኝ፥ በግል ወደዚያ ሰው መሄድና ለጉዳዩ እልባት ማግኘት ይኖርብኛል። ሌላ ሰው በጉዳዩ ውስጥ ማስገባት የሚያስፈልገኝ ከሆነ ሰውዬው ጉዳዩን ለማስተካከል ካልፈለገ ብቻ ሲሆን፥ ሌላው አማራጭ ሁሉ እስኪሞከር ድረስ ግን ወደ ቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ ማስተላለፉ ተገቢ አይደለም።

በመጋቢነት አገልግሎቴ ውስጥ፥ እንዲህ ዓይነት በርካታ ችግሮች ተመልክቻለሁ። ሌላው አማኝ በሚበድላቸው ጊዜ ክርስቲያኖች የሚፈጽሙት ትልቁ ስሕተት፥ ወደ በደላቸው ሰው በቀጥታ ከመሄድ ይልቅ፥ ለመጋቢው ወይም ለሌላ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን መናገር ነው። ሌላው ስሕተት ደግሞ በኃጢአት የወደቀውን ወንድም ከመመለስ ይልቅ፥ የክርክሩ አሸናፊ ለመሆን ጥረት ማድረግ ነው።

2. የዶክትሪን ስሕተት፡- ከሁሉም በፊት ሰውየው ለምን የተሳሳተ ዶክትሪን እንደሚያስተምር ምክንያቱን ልትደርስበት ሞክር። ምናልባትም ባለማወቅ ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ጉድለት ሊሆን ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፥ በትዕግሥት እውነቱን ማስተማር ይገባል (2ኛ ጢሞ. 2፡23-26)። በዚያው መንገድ ከቀጠለ ገሥጸው (ቲቶ 1፡10-14)። ጳውሎስ ጴጥሮስን መገሠጽ ነበረበት (ገላ. 2 ከቁጥር 11 ጀምሮ)። ያ ሰው ግን አሁንም በስሕተቱ ከቀጠለ፥ ፊቀቅ ማለትና (ሮሜ 16፡17-18) ከዚያ ሰው መለየት ያስፈልጋል (2ኛ ጢሞ. 2 ከቁጥር 18 ጀምሮ፤ 2ኛ ዮሐ. ከቁጥር 9 ጀምሮ)።

3. በኃጢአት የወደቀ አማኝ (ገላ. 6፡1-3)፡- ታላቁ ሐዋርያ ጴጥሮስ እንኳ ጌታችንን ክዷል። ዳዊትም በምኞት ተረቶ ዝሙት ፈጽሞአል። አንድ ክርስቲያን የታወቀ ኃጢአት ሲፈጽም ቢገኝ፥ መንፈሳዊ የቤተ ክርስቲያን አባላት በገርነትና በፍቅር ማቅናት አለባቸው። በዚህ ስፍራ «ማቅናት» ማለት «የተሰበረን አጥንት በጥንቃቄ መጠገን» ማለት ነው፤ ለዚህም ፍቅርና ትዕግሥት ያሻል። ብዙውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን

ኃጢአት በፈጸመው አማኝ ላይ በፍጥነት ፍርድ ትበይናለች፤ በዚህም ውስጥ የተፈጸመው አደጋ ለዓመታት ችግሮችን ሲፈጥር ይቆያል።

4. ተደጋጋሚ ጥፋት የሚፈጽም አማኝ (ቲቶ 3፡10)፡- በዚህ ስፍራ «መለያየት» የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዶክትሪንን ስሕተት ሳይሆን፥ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለየ አቋም እንዲይዙ የሚያደርገውን የትዕቢት አመለካከት ነው። የግሪኩ ቃል፥ «ምርጫ ማድረግ» የሚል ትርጉም አለው። ይህም በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወደ መከፋፈልና ወገናዊነት ይመራል (ከገላ. 5፡20 ላይ «መለያየት» የሚለውን ተመልከት)። ለማንኛውም ነገር ደጋፊ ወይም ተቃዋሚ ቡድኖች የማይገኙባት ቤተ ክርስቲያን አትገኝም። በመጋቢያን፥ በሕንፃው ሥራ መርሐ-ግብር ላይ፥ በማዕድ ቤት ግድግዳ ቀለሞች ምርጫ እንኳ ሳይቀር፥ የአሳብ መለያየት ሊያጋጥም ይችላል። ብዙውን ጊዜ እነዚህ «መለያየትን» የሚወዱ ሰዎች፥ ተፈላጊነትን ወይም ታዋቂነትን የሚሹ ሰዎች ናቸው፤ ተከታይ እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ ችግሮችን ይፈጥሩ ዘንድ፥ ሰይጣን ጣልቃ በመግባት ሊጠቀምበት የሚችል ከባድ የስሜት ችግር አለባቸው። ምናልባት በቤት፥ ወይም በሥራ ቦታ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር አጋጥሞአቸው ይሆናል፤ ምናልባት፥ ከዚህ ቀደም አንድ መጋቢ ወይም ቤተ ክርስቲያን ስሜታቸውን ጐድቶት ይሆናል።

ለእነዚህ «መለያየትን ለሚወዱ» ሰዎች ሁለት ይፋዊ ማስጠንቀቂያዎችን መስጠት አስፈላጊ ነው። ይህን ቤተ ክርስቲያንን የመከፋፈል ኃጢአታቸውን ከቀጠሉበት ግን፥ ሦስተኛ ማስጠንቀቂያ ሊሰጣቸውና ከጉባኤው ሊገለሉ ይገባል። «መለያየትን የሚያነሣ ሰው ጠማማ እንዲሆን በራሱም ላይ ፈርዶ ኃጢአት እንዲያደርግ አውቀህ፥ አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜም ከገሠጽኸው በኋላ እንዲህ ከሚመስል ሰው ራቅ» (ቲቶ 3፡10-11)።

እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥልጣን ባይሰጣቸው ምርጫዩ ነው። እንዲሁም ደግሞ፥ «ተበሳጭተው» ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከለቀቁ በኋላ፥ ሁለት ጊዜ ብቻ ወደ ኅብረቱ እንዲመለሱ ሊደረግ ይገባል። ለሦስተኛ ጊዜ ከወጡ-ወጡ!

5. ግልጽ የወሲብ ግድፈት (1ኛ ቆሮ. 5)፡- ቤተ ክርስቲያን በኃጢአተኛው ምክንያት ልታነባና (ለሞተ ሰው ለሚደረገውም ለቅሶ ይኸው ቃል ያገለግላል) ወደ ንስሐ ለማምጣት ልትሻ ይገባል። በንስሐ

ለመመለስ ካልፈለገ፥ ማኅበረ-ምእመናኑ በኅብረት ሊያስወግዱት ይገባል (በቁ. 13 ላይ የግሪኩ ቃል «አውጡት» የሚል ነው)። ንስሐ ከገባ ግን፥ ይቅርታ ተደርጐለት ከቤተ ክርስቲያን ኅብረት ጋር እንዲቀላቀል ሊደረግ ይገባል (2ኛ ቆሮ. 2፡6-11)።

«ሰነፍ አማኞችን» በተመለከተ፥ ጳውሎስ ማኅበረ-ምእመናኑ እንዲመክራቸው፥ እንዲያስጠነቅቃቸውና ንስሐ ገብተው ካልተመለሱም፥ ከነርሱ ጋር የቀረበ ግንኙነት ከማድረግ እንዲታቀቡ ተናግሯል። ምናልባት ይህ ማለት እነዚህን አማኞች ከጌታ እራት ማግለልና ወደ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ቤትም እንዳይጋበዙ ማቀብ ሳይሆን አይቀርም። 2ኛ ተሰሎንቄ 3፡14 የሚዛመደው ለሁሉም የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ሳይሆን፥ ለኑሮ መተዳደሪያቸው ለማይሠሩ ቅዱሳን ነው።

«ከእነርሱ ጋር አትተባበሩ» የሚለው በቀጥታ ሲተረጐም «ኅብረት አታድርጉ» ማለት ነው፤ ይኸው ቃል በ1ኛ ቆሮንቶስ 5፡9 ላይ ተጠቅሶአል። በትውውቅ፥ በጓደኝነትና ኅብረት ውስጥ ልዩነት አለ፤ ኅብረት ማለት «ጋርዮሽ» ማለት ነውና። ለታዛዥ ቅዱሳን የማይታዘዙትን ክርስቲያኖች፥ እንደተሰጡ ቅዱሳን ቆጥሮ ማስተናገዱ፥ ለኃጢአታቸው ድጋፍ መስጠት ነው።

ይህም ሆኖ፥ ጳውሎስ (የሰውን የአክራሪነት ባሕርይ ስለሚያውቅ፥) በደለኞቹን እንደ ጠላት እንዳይመለከቱ አስጠንቅቆአል። «አሁንም በክርስቶስ ወንድሞቻችሁ ናቸው» በማለት በተጨማሪ አሳስቧል። ሎጥ በሰዶም ውስጥ ከመኖሩ የተነሣ፥ ከእግዚአብሔርም ሆነ ከአብርሃም ጋር ኅብረት ባይኖረውም፥ አብርሃም ግን ወንድሙ ስለሆነ፥ ሎጥን ከጠላት እጅ አድኖታል (ዘፍጥረት 14 በተለይም ቁጥር 14ን ተመልከት)። በስሕተት ውስጥ የሚመላለሰውን ወንድም ለመርዳት ብዙ ትዕግሥት፥ ፍቅርና ጸጋን ይጠይቃል፤ ለዚህም ነው ጳውሎስ የመተዳደሪያ ሥራን ስለማከናወን የመጨረሻውን አነሳሽ-ምክንያት (ዓላማ) ያከለው!

## የጌታ ማስቻል (3፡16-18)

እግዚአብሔር እንታዘዘው ዘንድ የሚያስፍልገውን ሁሉ ስላሟላ፥ ማንኛውም አማኝ፥ «የእግዚአብሔርን ቃል ልታዘዝና ወደ አገልግሎት ልሰማራ አልችልም» ብሎ ሊናገር አይችልም። እርሱ የሰላም ጌታ ነው። በመሆኑም፥ እርሱ የሕይወታችን ጌታ እስከሆነ፥ እኛም በልባችን ውስጥ

ሰላም ሊኖረን፥ በቤተ ክርስቲያን ኅብረታችን ውስጥ የሰላምን አስፈላጊነት ለማበረታታት እገዛ ልናደርግ እንችላለን።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር ካለ፥ በአንድ በሆነ አማኝ ልብ ውስጥ ችግር አለ ማለት ነው። ክርስቶስ የጌትነቱን ስፍራ ከያዘ፥ በልብ ውስጥ ሰላም አለ ማለት ነው። በልብ ውስጥ ጦርነት ካለ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወታችን ጌታ አይደለም ማለት ነው (ያዕ. 4፡1-10 ተመልከት)።

በማያቋርጥ ውዥንብርና ውድድር ውስጥ የነበረ አንድ የሰንበት ትምህርት ቤት ትዝ ይለኛል። ነገሮችን አስተካክለን ለጥቂት ሳምንታት ያህል እፎይ ከማለታችን እሳተ-ገሞራው እንደገና ተመልሶ ይፈነዳል። ከብዙ ጸሎትና ምርመራ በኋላ አንዲት የክፍሉ ተማሪ መምህርት ለመሆን እንደፈለገች ተረዳን። እርሷም በመንፈሳዊ ግኝቶችዋ በመኩራራት፥ እስካሁን ከምታስተምረው የተሰጠች ሴት የበለጠ ሥራ እንደምታከናውን ተሰምቷት ነበር።

ምንም እንኳ ይህች የክፍሉ ተማሪ ከቶውንም በመምህርቷ ላይ ይፋዊ ተቃውሞ ወይም ትችት ባትሰነዝርም፥ አመለካከቷና ያደረገቻቸው ነገሮች በኅብረቱ ውስጥ የመከፋፈልን ስሜት ዘርተው ነበር። ይህ ችግር ከተቃለለ በኋላ፥ በክፍሉ ውስጥ የሰላም ጌታ ነገሠና እግዚአብሔርም በረከቱን ያወርድ ጀመር።

እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የሚያስችለን ሰላሙ ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን የእርሱ መገኘትም ጭምር ነው፡- «ጌታ ከሁላችሁ ጋር ይሁን!» እርሱ በፍጹም አይተወንም ወይም አይጥለንም፤ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእኛ ጋር ነው (ዕብ. 13፡5፤ ማቴ. 28፡20)።

በመጨረሻም፥ ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር ጸጋ አስታውሶአቸዋል። «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን» (ቁ. 18) የሚለው ጳውሎስ ከመልእክቶቹ ማብቂያ ላይ የሚያስቀምጠው ይፋዊ ፊርማ ነበር። ይህንንም ያለው በእርሱ ስም በማስመሰል በስሙ ተጽፎ ከቀረበላቸው የማታለያ መልእክት የተነሣ ነው (2ኛ ተሰ. 2፡2)። በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ከተደገፍን፥ ለእግዚአብሔር ክብር ፈቃዱን ልንፈጽም እንችላለን። «ጸጋዬ ይበቃሀል» (2ኛ ቆሮ. 12፡9)።

ከመሥመር ውጭ የሆነና የጌታን ትእዛዝ የማያከብር ወታደር፥ ለጌታ አለመገዛቱን እራሱ ያረጋግጣል። የቤተ ክርስቲያን ችግሮች የግል ችግሮች ስለሆኑ፥ በግል ልናቃልላቸው ይገባል። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን

ውስጥ ሥርዓት እንዲኖር ይፈልጋል። «ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን» (1ኛ ቆሮ. 14፡40)

አንተስ ለቤተ ክርስቲያን ሰላም ከሚታገሉት ወገን ነህ ወይስ ጦርነት ከሚያጭሩት?

እስኪ ድሉን እንዲያቀዳጀንና (ኢያሱ 5፡13-15) ለሕዝቡ ያለውንም ዓላማ ከግቡ እንዲያደርስ፥ ኢያሱ እንዳደረገው ሁሉ፥ እኛም በእግዚአብሔር ሠራዊት አዝማችና መሪ እግር ሥር እንውደቅ።

ጌታ በቅርብ ጊዜ ይመጣል፥ አንተም ለምጽአቱ ተዘጋጅ!